ማውጫ ገጽ


1. የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር /የኬኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር እና የኬኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ/.................................... 1
2. በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ /ጳውሎስ ሩምቾ እና ጫልቱ መርዳሳ/.......................................................................................... 9
3. በስነ-ሥርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ (ጋዲሴ ኢረጌ እና ወርቅ አንጥፉ በቀለ) 12
4. ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈጸም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት (ዋዜማ የልብስና ሸራ ምርቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት አክስዮን ማህበር)........................................................................... 17
5. በመንጓዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች በጉዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ (የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት) ............................................................... 24
6. በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቱ የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ /የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና በሮኒ አቲክፖ/.................................................. 31
7. አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ (ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ መንግሥቱ ኃብቴ) ...................................... 41
8. ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት (ውርጌሣ ታደሰ እና እነ መለሰ ተካ) ................................................ 47
9. በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቱ በህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ /ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን/ ...................................................... 55
10. ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሣሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት (ሼህ ኢትዮጵያ አ/ማ እና አስቴር ብርሃነስላሴ) .................................. 60
11. በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈጸም ስለማያስከትለው ውጤት /የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሶስና አስፋው/ ......................................................................................................66
12. በአንዳንድ ውሎች የተመለከተ የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍርድ ቤት ስላለው ስልጣን /አስቴር አርአያ እና ግርማ ወዳጆ/ ............................... 75

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**
**ሰበር ሰሚ ችሎት**

**የመ/ቁ. 18180**

**ዳኞች፡-** **አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ**
**አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ**
**አቶ አብዱልቃድር መሐመድ**
**ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ**
**አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ**

**አመልካች፡-** የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ የሰራተኞች ማህበር
**መልስ ሰጪ፡-** የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ

*ስለ ስራ ክርክር- የስራ ክርክር ችሎቶች ሰልጣን - የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን /የሰራተኞች ቅነሳ ጉዳይ በሚመለከት የሚነሳ የስራ ክርክር ለማየት/ -የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 138/1/፣ 147*

አመልካች በሰራተኛ ማህበራችን አማካኝነት የተወሰደብን የቅነሳ እርምጃ ህገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብን ክፍያ ተሰጥቶን ወደ ስራችን እንመለስ በማለት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ጥያቄ ቦርዱ በመቀበል የተደረገው ቅነሳ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 28 እና 29 ድንጋጌዎችን የሚጥስ በመሆኑ አመልካቾች ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ከስልጣኑ ውጭ የሰጠው ነው በሚል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሻረው የቀረበ አቤቱታ



**ው ሣ ኔ ፡-** የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የመዳኘት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ክርክሮችን ሲሆን የስራ ክርክር ችሎቶች ደግሞ የግል የስራ ክርክሮችን እንዲዳኙ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡
2. ህጉ የስራ ክርክር ጉዳዮችን የወል ወይም የግል ብሎ ለመለየት የተከራካሪ ሰራተኞችን ቁጥር እንደ መስፈርት መውሰድ እንዳለበት አያመላክትም፡፡
3. ከአጠቃላይ የህጉ መንፈስ እና ድንጋጌዎች በመነሳት አንድ የስራ ክርክር ጉዳይ የወል ነው የሚባለው ጉዳዩ በጋራ የሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሲሆን አንድን የስራ ክርክር ጉዳይ የግል የሥራ ክርክር ጉዳይ የሚያደርገው ደግሞ ጉዳዩ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የሌለ እንደሆነ ነው፡፡
4. የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው በመሆኑ የወል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩን የማየት ስልጣንም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡
5. የአሰሪና ሰራተኛ ፍ/ቤት ቦርዱ የህግ ስህተት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ከመመሪያ ጋር ወደ ቦርዱ ከመመለስ አልፎ የቦርዱ ውሳኔ መሻር አይችልም፡፡

የመ/ቁ.18180

ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኬኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መ/ሰ/ማ /56/ ሰዎች ወኪል ሰይድ ሀሚድ ቀረበ

ተጠሪ፡- የኬኬ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገቡ የተያዘው ክርክር ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ጉዳዩ አሠሪ የሆነው የአሁን ተጠሪ ሠራተኛ በሆኑት በአሁን አመልካቾች ላይ የወሰደውን የቅነሣ እርምጃ የሚመለከት ነው፡፡

አመልካቾች በሠራተኛ ማኀበራቸው አማካኝነት የተወሰደብን የቅነሣ እርምጃ ሕገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብን ክፍያ ተሰጥቶን ወደ ሥራችን እንመለስ ሲሉ በተጠሪው ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የቅነሣውን ተገቢነት ይገልጻል የሚለውን መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ቦርድ ደግሞ የተደረገው ቅነሣ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 28 እና 29ን የሚጥስ በመሆኑ አመልካቾቹ በአንቀጽ 42/2/ መሠረት ወደ ሥራቸው ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ ውሣኔ ላይ በተጠሪ አማካኝነት በመ/ቁ.30769 ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ቦርዱ ይህን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የቦርዱን ውሣኔ ጥቅምት 25/1997 ዓ.ም ሽሮታል፡፡

በመቀጠል አመልካቾች ይህ የፍ/ቤቱ ውሣኔ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 147/2ን እና 154/2ን የሚጥስ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነውና ይሻርልን በማለት አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚልበትን ምክንያት የሚዘረዝር መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት ክርክሩን ሊያስነሣ በቻለው አወዛጋቢ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዋነኛነት ሊፈቱ የሚገባቸው የነገሩ ጭብጦችም፡-

1ኛ. የሠራተኛ ቅነሣን አስመልክቶ የቀረበውን የህን ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የማነው? የፍርድ ቤት ነው? ወይስ የቦርድ?

2ኛ. ፍ/ቤት በቦርድ የተሰጠን ውሣኔ ለመሻር ሥልጣን አለው? የሚሉት መሆናቸውን ተገንዝቧል፡፡

ለመጀመሪያው ነጥብ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ሠራተኛ ቅነሣ፣ ስለ ቦርድ እና ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል፡፡ ቦርድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጉዳዮች ፍ/ቤት ሊቀርቡ ከሚገባቸው የሚለዩበትን ምክንያት መረዳትን ይፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ ግንዛቤ እንድናገኝ የሚያደርገን ደግሞ ስለ ቦርድ ሥልጣን የሚደነግገው የአዋጅ ቁ.147/1/ እና ስለ ፍ/ቤት ስልጣን የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ይሆናል፡፡

ስለ ቦርድ ሥልጣን ከተደነገገበት የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 147/1/ ውስጥ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሚኖረው በንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ ላይ ቦርዱ በአንቀጽ 142/1/ ላይ የተመለከቱትን የሥራ ክርክሮች የመዳኘት እና ተከራካሪዎቹን የማስታረቅ ሥልጣን አለው በሚል የተመለከተው የሕጉ ክፍል ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲነበቡ ቦርዱ በአንቀጽ 142/1/ ስር በተዘረዘሩትና በሌሎች የወል የሥራ ክርክሮች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንደተሰጠው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአዋ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የሥራ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን ለፍ/ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

የወል የሥራ ክርክሮች ለቦርድ፤ የግል የሥራ ክርክሮች ደግሞ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ናቸው ማለት ብቻውን ግን ሁለቱ ተቋማት በዚህ ረገድ ያላቸውን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል በግልጽ እንድንለየው የሚያደርገን አይደለም፡፡ ይልቁንም የወል የሥራ ክርክር ማለት ምን ማለት ነው? የግል የሥራ ክርክር ማለትስ ምን ሊሆን ይገባል? የሥራ ክርክሮችን በምንና እንዴት የወል ወይም የግል የሥራ ክርክር ብለን ልንመድባቸው እንችላለን? የሚሉና ሌሎቹንም መሰል ጥያቄዎችን እንድናነሣ የሚያደርገን ነው፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታችን ደግሞ የሚቀርቡ የሥራ

ክርክሮችን ከየትኛው እንደምንፈርጃቸው የሚያመለክተንና በዚህ ተጨባጭ ጉዳይ ለተያዘውም የመጀመሪያ ጭብጥ መፍቻ እንድናገኝለት የሚረዳን ነው፡፡

## ስለ የወል እና የግል የሥራ ክርክር አይነቶች

የአዋጅ ቁ.42/85 ለወልም ሆነ የግል የሥራ ክርክር የሰጠው ትርጓሜ የለም፡፡ የሥራ ክርክር በዚህ አዋጅ የተተረጎመ ቢሆንም ትርጓሜው የወልና የግል የሥራ ክርክርን እንድንለይ የሚያስችለን አይደለም፡፡ ስለሆነም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት በግርድፉ ለማስቀመጥ ሌላ መለኪያ እንድናበጅ የሚጠይቀን ነው፡፡

እንደሚታወቀው ከአሠሪ ጋር የሚደረግ የሥራ ክርክር በሠራተኞች ማኅበር ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሠራተኞች ወይም በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚካሄድ ነው፡፡ የወል የሚለው ቃል አገላለጽ የጋራ የሆነ ጉዳይ መኖሩን ለማመልከት ያህል የሚበቃ መሆኑም እርግጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የወሉን ከግል ለመለየት የተከራካሪዎቹን ሠራተኞች ቁጥር እንደመለያ መስፈርት መውሰድ እንደምንችል የሚጠቁመን የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይህ ደግሞ ሕጉ ሁለቱን ክርክሮች ለመለየት የፈለገበትን ሌላ መንገድ እንድንፈትሽ ያደርገናል፡፡ ለዚህም ሁለቱ የክርክር አይነቶች በምሣሌነት በተናጥል የተዘረዘሩበትን የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/ን እና 138/1/ን መሠረት ማድረጉ አግባብነት ያለው መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ ይጠቅመናል፡፡

አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/

ሀ. ስለደመወዝና ሌሎች ጥቅሞች አወሳሰን፣

ለ. አዲስ የሥራ ሁኔታዎችን ስለመመስረት፤

ሐ. የሕብረት ስምምነት ስለመዋዋል፣ ስለማሻሻል፣ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ስለሚፈርስበት፣

መ. አዋጁን፣ የሕብረት ስምምነት ወይም የሥራ ደንብ ድንጋጌዎችን በሚመለከት የሚነሣ የትርጉም ክርክር፣

ሠ. ስለሠራተኛ አቀጣጠርና እድገት አሰጣጥ ሥርዓት፣

ረ. አጠቃላይ ሠራተኞችንና የድርጅቱን ሕልውና የሚነኩ ጉዳዮች፣

ሰ. ዕድገት ዝውውር እና ሥልጠናን በሚመለከት አሠሪው በሚወስዳቸው እርምጃዎች ምክንያት የሚቀርቡ ክሶች፣

ሸ. የሠራተኞች ቅነሣ እና የመሳሰሉት የሥራ ክርክሮች የወል የሥራ ክርክሮች መሆናቸውን ደንግጓል፡፡



እንደዚሁም አብዛኛዎቹ የድንጋጌው ክፍሎች በውጤታቸው የሁሉንም ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮችን ያቀፉ መሆናቸውን በግልጽ አመላክተውናል፡፡ ለምሣሌነት በንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/፣ /ለ/፣ /ሐ/፣ /ሠ/፣ /ረ/ እና /ሸ/ የተጠቀሱትን የሥራ ክርክር አይነቶች መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህ የድንጋጌው አብዛኛው ንዑስ አንቀጾች ክርክሩ የወል ለመባል የጋራ የሆነን የሠራተኞቹን መብትና ጥቅም የሚመለከት ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ ካሣዩን ደግሞ በቀሪዎቹ ንዑስ አንቀጾች ላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም በድንጋጌው ያልተካተቱትን ተመሳሳይ የሥራ ክርክሮችን የወልነት ፀባይ ከሠራተኞቹ የጋራ መብትና ጥቅም ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ ልንመዝነው የሚገባን ይሆናል፡፡ ስለሆነም ጥያቄው የደመወዝም ሆነ የሥልጠና፣ የሕግ ትርጉም ነክም ሆነ ወይም ሌላ የወል የሚሰኘው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 138/1/

ሀ. ከሥራ ማስወጣትን ጨምሮ ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የሚመለከቱ ክሶች፣

ለ. የሥራ ውል መቋረጥ ወይም መሰረዝን የሚመለከቱ ክሶች፣

ሐ. የሥራ ሰዓትን፤ የተከፋይ ሂሳብን፤ ፈቃድንና እረፍትን የሚመለከቱ ክሶች፣

መ. የቅጥር ማስረጃ ሠርቲፊኬት መስጠትን የሚመለከቱ ክሶች፣

ሠ. የጉዳት ካሣን የሚመለከቱ ክሶች እና

ረ. በአዋጁ መሠረት የሚቀርብ ማንኛውም የወንጀልና ደንብ መተላፍ እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የግል የሥራ ክርክሮች መሆናቸው ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ድንጋጌ የጋራ የሆነን የሠራተኞች ጉዳይ እንደሚያጠቃልል የሚገልጽ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሥራ ክርክሩ በእነዚህ በተዘረዘሩትም ሆነ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ ሲቀርብ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ያለመኖሩ ጉዳይ ክርክሩን የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

እንግዲህ አንድ የሥራ ክርክር በአንድ ወይም በብዙ ሠራተኞች መቅረቡ ጉዳዩ የወል ወይም የግል የሥራ ክርክር መሆኑን የሚያረጋግጥልን አይደለም፡፡ ይልቁንም ክርክሩ የወል መሆኑን የሚያሳየን ውጤቱ ከግል አልፎ የሠራተኞቹን የጋራ መብትና

ጥቅም የሚነካ የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የግል ነው የምንለው ደግሞ ውጤቱ በተከራካሪው ሠራተኛ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ስናገኘው ነው፡፡

ወደ ጭብጣችን ስንመለስ አመልካቾች ተጠሪው የቅነሣ እርምጃ ለመወሰድ የሚያስችል ምክንያት የለውም፤ ቅነሣውም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 29 የተመለከተውን ቅደም ተከተል ያከበረ አይደለም በሚል አይነት መሟገታቸውን ያሳየናል፡፡ እንደሚታወቀው የሠራተኞች ቅነሣ መላውን የድርጅቱን ሠራተኞች ከግምት በማስገባት በሕግ አግባብ ሊከናወን የሚገባ ተግባር ነው፡፡ ቅነሣው ህግን ተመስርቶ አለመደረጉን አሳያለሁ በሚል ሁኔታ የሚቀርብ አቤቱታም በውጤቱ ሁሉንም ሠራተኞች የሚመለከት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ የአመልካቾች ክርክር ደግሞ በዚህ መልኩ የቀረበ መሆኑ ከፍ ሲል ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ጉዳይ የወል እንጂ የግል የሥራ ክርክር የሚሰኝበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ክርክሩን የመዳኘቱ ሥልጣንም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/ /ሸ/ መሠረት የቦርድ እንጂ የፍ/ቤት አይሆንም፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠ መሆኑን ምክንያት በማድረግ የቅነሣውን ህጋዊነት የመመርመር ሥልጣን የፍ/ቤት ነው ሲል ወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ ከፍ ሲል እንደተገለፀው አንድ የሥራ ክርክር በቦርድ ወይም የግል የሥራ ክርክር መሆኑ እንጂ የሥራ ውሉ የመቋረጥ ወይም ያለመቋረጡ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ምክንያትም ከሕጉ ጋር የሚጣጣም አልሆነም፡፡

በሁለተኛው ደረጃ የተያዘው ጭብጥም አግባብነት ካለው የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 154/2/ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የቦርድ ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበትና የሕግ ስህተቱም የውሣኔውን ውጤት አዛብቶት የተገኘ እንደሆነ ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ከዝርዝርና ከአጠቃላይ መመሪያ ጋር ለመጨረሻ ውሣኔ ወደ ቦርድ እንደሚመልሰው፤ ነገር ግን የቦርዱን ውሣኔ ለመሻርም ሆነ ለማሻሻል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡

በእርግጥ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ እራሱ መሻሩ የውሣኔ አሰጣጡ ከተጠቀሰው ሕግ ጋር አለመጣጣሙን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ የቦርዱን ውሣኔ የሕግ ስህተት ለማረም እንዲችል በዚሁ ሕግ ሰፊ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ውሣኔውን በይግባኝ ሊሽረውም ሆነ ሊያሻሽለው ባይችልም የሕግ



ስህተቱ ታርሞ በጉዳዩ እንደገና ውሣኔ ይስጥበት ዘንድ ክርክሩን ወደ ቦርድ እንዲመልሰው ሕጉ በግልጽ ፈቅዶለታል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ እራሱ ለመሻር ሥልጣን የሌለው በመሆኑ የፍርድ አሰጣጡ ከተጠቀሰው ህግ አግባብ ሊቃና የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ. ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የሠራተኛ ቅነሣ የወል የሥራ ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የቦርድ እንጂ የፍርድ ቤት ሊሆን አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

2ኛ. ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ተገንዝቦ ወደ ክርክሩ በመግባትና በቦርዱ የተሰጠው ፍርድ ከሕግ አኳያ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን በመመርመር ጉዳዩ ከመመሪያ ጋር ወደ ቦርድ ሊመለስ የሚገባው መሆን አለመሆኑ ረገድ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለትም ተወስኗል፡፡

3ኛ. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ማየት እንዲቀጥል ያስችለው ዘንድም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343/1/ መሠረት ተመልሶለታል፡፡

## *የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*

## *ሰበር ሰሚ ችሎት*

የመ/ቁ. 15493

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ጳውሎስ ሩምቾ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ

**የውል ግደታዎች መቅረት - ስለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ- ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህሊና ግምቶች - የፍትሐብሔር ህግ ቁጥሮች 1845፣ 2024**

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው የጥብቅና አበል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 /ለ/ መሠረት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር የሥር ተከሣሾች በአመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሌሎች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. የሐሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡
2. በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 በተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያልሆነ ወገን /ተከሣሽ/ ክፍያውን በከፊል መክፈሉ ግምቱን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 /1/ መሠረት ቀሪ አያደርግም፡፡



ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም

የመ/ቁ.15493

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ጳውሎስ ሩምቾ

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ

### <u>ፍርድ</u>

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው የጥብቅና አበል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ለ/ መሠረት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር የሥር ተከሣሾች በአመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሌሎች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻሩ ነው፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ መልስ ሰጪም በጉዳዩ ላይ ያላትን የጽሁፍ መልስ አቅርባለች፡፡

አመልካች የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚለው /1/ ከጥብቅና አበሉ ውስጥ የመጨረሻ ክፍያ የተፈፀመው ሰኔ 1990 ዓ.መ በመሆኑ ክስ እስከቀረበበት ታህሣሥ 18 ቀን 1992 ዓ.ም በፍትሐብሄር ሕግ ቁ.2024 /ለ/ የተጠቀሰው የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ አላለፈም /2/ መልስ ሰጪዎች ከፊል ዕዳውን በመፈፀማቸው ዕዳውን እንዳመኑ ስለሚቆጠር በ2024 የተቀመጠው የህግ ግምት በ2025/1/ መሠረት ቀሪ ሆኖአል፡፡ /3/ የጥብቅና ውሉ በጽሁፍ የተደረገ በመሆኑ የይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት በ10 ዓመት እንጂ በ2024 መሠረት በሁለት ዓመት አይደለም የሚሉትንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ክርክሮች በማቅረብ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀናላት ጠይቃለች፡፡

አመልካች በመልስ ሰጪ ላይ ጥር 1 ቀን 1992 ዓ.ም ክስ የመሰረተው ጥቅምት 7 ቀን 1988 ዓ.ም በአመልካችና በመልስ ሰጪ መካከል የተመሰረተውን የጥብቅና አገልገሎት ውል መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር

ችሎት ተዋዋዮቹ በውላቸው ላይ ለጥብቅና ውሉ ምክንያት የሆነው ቤት መልስ ሰጪ እጅ በገባ በሁለት ወር የጥብቅና ክፍያ መጠናቀቅ እንዳለበት ስለሚገልጽና ቤቱ ሕዳር 1988 መልስ ሰጪ እጅ የገባ በመሆኑ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ክስ በቀረበበት ጊዜ ከሁለት ዓመት በላይ ስለሆነው በ2024 መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ብሏል፡፡

ለዚህ ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ ምክንያት የሆነው ዕዳ መክፈል ከነበረበት ሁለት ዓመት በላይ እንደሆነው በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦአል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት በሁለት ዓመት ውስጥ ያልተከፈለ ዕዳ እንደተከፈለ እንደሚቆጠር በዚህ ሰበር ችሎት በመ.ቁ.17068 ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ የጥብቅና አበል ክፍያን የሚመለከተው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ለ/ም አንዱ የድንጋጌው አካል በመሆኑ በተጠቀሰው ትርጓሜ መሠረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ የፈፀመው የህግ ስህተት የለም፡፡ አመልካች የሕግ ግምትና የይርጋ ህግን በማመሳሰል ጉዳዩ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1845 እንዲታይለት ቢጠይቅም የተያዘው ጉዳይ የክፍያ ግምት እንጂ የይርጋ ጉዳይ ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም፡፡ የክፍያ ግምት ውሉ በጽሁፍ የተደረገ ሲሆን ተፈጻሚ አይሆንም የሚል ህግ ባለመኖሩ አመልካች ውላችን በጽሁፍ ስለሰፈረ 2024/ለ/ ተፈጻሚ ሊሆንብኝ አይገባም ያለው ተቀባይነት የለውም፡፡ መልሰ ሰጪ በከፊል የጥብቅና አበል መክፈላቸውም ቢሆን አሁን ክስ የቀረበበትን ቀሪውን የጥብቅና አበል ማመናቸውን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የሕጉን ግምት ተፈጻሚነት በ2025/1/ መሠረት ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበት ብር 71,000 /ሰባ አንድ ሺህ/ ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ የተጠየቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024/ለ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ መሻሩ ሕጉን በትክክል ተፈፃሚ ማድረጉን እንጂ የህግ ስህተት መፈፀሙን አያመለክትም፡፡

**ውሣኔ**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ.00253 በ20/7/96 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡



## *የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*

## *ሰበር ሰሚ ችሎት*

የመ/ቁ. 17361

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ
መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ

***በከሣሽነት ወይም ተከሣሽነት በሙግት ተካፋይ ስለመሆን - ስለተከራካሪ ወገን መምትና ስለክሱ ያለመቋረጥ - ስለ ጊዜ አወሳሰንና አቆጣጠር- የፍትሐበሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 49 - ስለ ግዴታዎች መቅረት - ስለ ይርጋ - የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1856***

አመልካች ከስር ከሳሽ የነበረችውን ወ/ሮ ብሪቱ ብሩን ተክታ ለመከራከር ያቀረበችው ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 49 የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ጥያቄዋን ውድቅ በማድረጉ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ባለመቀበሉ መልስ ሰጭ ባነሳችው ክርክር ፍርድ ቤቶቹ ክሱን ውድቅ በማድረጋቸው የቀረበ አቤቱታ

**ው ሳ ኔ፡-** የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. በሥረ ነገር /Substantive/ ህጎች የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች በሥነ ሥርዓት ሕጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ ናቸው፡፡
2. በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረን ጊዜ ሳይጠብቅ የሚቀርብን ጥያቄ ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

የመ/ቁ. 17361

ሐምሌ 25 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ወርቅአነጥፉ በቀለ

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተመለከቱ የሥነሥርዓት ደንቦች አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ ሲቀርብ የበቃው አመልካች ከስር ከሣሽ የነበረችውን ወ/ሮ ብሪቱ ብሩን ተክታ ለመከራከር ያቀረበችው ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤት በፍትሀብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 49 የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ መሆኑን በመግለጽ ጥያቄዋን ውድቅ በማድረጉ ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ ዋነኛ የቅሬታ ነጥብም ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 49(2) የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ ማንም ተከራካሪ ወገን ሳያነሳው ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ተፈጻሚ ማድረጉ ሕጉ ይርጋን በማስመልከት ያስቀመጠውን ሥርዓት የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ ይሻልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ በመወሰኑ መልስ ሰጪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ የመልሱ መሠረታዋ ይዘት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ምንም የሕግ ስህተት ሰለሌለበት ሊፀና ይገባዋል የሚል ነው፡፡ አመልካቿ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡ ይዘቱ ከሰበር ማመልከቻው የተለየ አይደለም፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱተ በሥረ ነገር ሕጎች /Substantive Laws/ የተደነገጉ የይርጋ ደነቦች በሥነሥርዓት ሐጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ወይስ አይደሉም? በሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ የሚገኙትን የጊዜ ገደቦች ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ተፈጻሚነታቸውን ሊከታተሉ ይችላሉ



ወይስ እንደሥረነገር የይርጋ ህግ በተከራካሪ ወገን ካልተነሱ እንደተተው ይቆጠራል የሚሉትን የሕግ ነጥቦች የማያስነሳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ መረዳት እንደቻልነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ቀደም ብላ ክስ መስርታ የነበረችውን ወ/ሮ ብሪቱ ብሩን ተክታ የፍትሐብሄር ክሱን በወራሽነት እንድትቀጥል ያቀረበችውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ጥያቄው የቀረበው የፍትሀብሄር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 49 እንደሚያዘው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በማለት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 49(1) ከሣሽ ሲሞቱ የክሱ መብት ለሌላ የሚተላለፍ የሆነ እንደሆነ የሟቹ ንብረት አስተዳዳሪ ተተክቶ ክሱን ሊቀጥል እንደሚችል የሚፈቅድ ሲሆን የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት #ክሱን ለመቀጠል መብት አለን የሚሉት ወገኖች ዋናው ከሣሽ ወይም ከሣሾች በሞቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድላቸው ሳያመለክቱ የቀሩ እንደሆነ የተጀመረው ክርክር ውድቅ ይሆናል; በማለት ይደነግጋል፡፡

የፍትሀብሔር ሥነሥርዓት ሕግ የሙግትን ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ የተለያዩ የጊዜ ገደቦችን አስቀምጧል፡፡ ይኸው ሕግ ያስቀመጣቸውን የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም በሚመለከትም በሥነሥርዓት ሕጉ ምዕራፍ ሰባት በርካታ ድንጋጌዎችን አስፍሮአል፡፡ የሕጉ ቁጥር 192 #በአንድ ክርክር ላይ መፈፀም ወይም መደረግ የሚገባው ነገር ሲኖርና ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ በሕግ ያልተወሰነ ሲሆን የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የሚተየውን ጊዜ ይወስናል; በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሙግት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በሕግ በተቀመጠው አሊያም ፍርድ ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ቁጥር 195 #በዚህ ሕግ በቁጥር 196 የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ነገር እንዲፈፀም ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ቢፈፀምም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል; በማለት በተወሰነ የጊዜ ገደብ መፈፀም ያለባቸው ተግባሪት ሕጉ ወይም ፍ/ቤቱ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ከተከናወኑ ብቻ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጎች ዋነኛ ዓላማ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሰ ወጪ በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ህጎች የሰፈሩ የጊዜ ገደባች አፈጻጸም በአንድ ጉዳይ ካሉት ተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ተከራካሪዎች ጥቅም፣ በፍርድ ቤት መኖር

ያለበትን የሙግት አመራርና አጠቃላይ የሀብትና የጊዜ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የጊዜ ገደቦች አለመከበር ለመዘግየት፣ ለጉዳዮች መከማቸትና መጨናነቅ ምክንያትም ስለሚሆን የሚጎዳው በአንድ ሙግት የሚሳተፉትን ብቻ ሳይሆን የሌሎች የፍርድ ቤት ተጠቃሚዎች መብትና ጥቅምም ይነካል፡፡ ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር የሙግት ሂደት ሥርዓት እንዲይዝ ማድረግ ደግሞ ከተከራካሪዎችም የሚጠበቅ ቢሆንም በዋናነት ግን የፍርድ ቤቱ ሃላፊነት ነው፡፡ ይህን ሃላፊነት እንዲወጣ ከሚያደርጉት መንገዶች አንዱ ደግሞ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የሰፈሩት የጊዜ ገደቦች በአግባቡ መፈፀማቸውን መከታተልና ያልተፈፀሙ ሆነው ሲገኙ ደግሞ ህጉ እንደሚያዘው ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ መውሰድ ነው፡፡

በሥነሥርዓት ሕጉ የሰፈሩ ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ይርጋን አስመልክቶ በፈትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1856/2/ ከሰፈረውና የይርጋ ጉዳይ በተከራካሪዎች ካልተነሣ በፍርድ ቤት አይነሳም ከሚለው ሕግ የተለየ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ የሰፈረው የይግርጋ ሕግ ዋነኛ ዓላማ የተዋዋዮችን ጥቅም መጠበቅ ነው፡፡ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆነ ተከሣሽ ይርጋውን ካላነሣም የሚጎዳው እሱ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገን የተወውን መብት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት እንዲያነሣው አይፈቀድም፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች መከበር አለመከበራቸውን ግን ፍርድ ቤቱ የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡ በተከራካሪ ወገን ባይነሣ እንኳን በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 195 እንደተደነገገው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከናወነው ነገር ሁሉ እንዳልተፈፀመ ሆኖ ስለሚቆጠር የሥነሥርዓት የጊዜ ገደቦች ተሟጋቾችን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱንም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ሕጉ በግልጽ የሰፈረው የጊዜ ገደብ ካለኝ በኋላ የሚቀርብን ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረጉ ትክክለኛው አካሄድ ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ጥያቄዋን ለፍርድ ቤቱ ያቀረበችው የቀድሞዋ ተከራካሪ የወ/ሮ ብሪቱ ብሩ ወራሽ መሆንዋን ካረጋገጠች ከ3 ዓመት በኋላ ነው፡፡ ከመዝገቡ ለመረዳት እንደተቻለው የወራሽነት ውሣኔ ያገኘችው ሐምሌ 15/91 ሲሆን ለፍርድ በቱ ጥያቄዋን ያቀረበችው ደግሞ ጥር 20/1994 ነው፡፡ ይህም የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 49 ያስቀመጠው የአንድ አመት የጊዜ ገደብ ማለፉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሕግ የሰፈረውን ጊዜ ገደብ ያልጠበቀ ነገር የተሟጋችን



ተቃውሞ ሳየጠብቅ ፍርድ ቤቱ ራሱ ውድቅ ማድረጉ ደግሞ ትክክለኛ የጉዳይ አመራር እንጂ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 20576 ግንቦት 1 ቀን 1975 የሰጠው ውሣኔ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 22451 ሐምሌ 21 ቀን 1996 የሰጠው ውሣኔ ፀንተዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## *የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*

## *ሰበር ሰሚ ችሎት*

የመ/ቁ. 17352

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አበዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መልስ ሰጭ፡- የነገው ሰው ትምህርት አ/ማ

*ለዳኝነት ስለሚከፈል ገንዘብ - ከስነ ስርዓት ውጭ ስለሚቀርብ ክስ /የግባኝ/ - የፍትሐበሔር ሥነሥርዓት ህግ ቁጥሮች 215፣ 320/2/፣ 207፣ 211/2/*

አመልካች ከስር ፍ/ቤት በመ/ሰጭ እንዲከፍለው የጠየቀው ወለድ በመ/ሰጭ ሊከፈለው የማገባ ቢሆንም አመልካች ክሱን ሲያቀርብ ለወለድ ጥያቄው የዳኝነት ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ ወለድን በሚመለከት ያቀረበው ጠያቂ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመወሰኑና ከዚህ አንፃር የቀረበውን መስቀለኛ ይገባኝ የፌዴሪል ጠቅላይ ፍ/ቤተ ውድቅ ስላደረገው የቀረበው አቤቱታ

*ው ሳ ኔ፡-* የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ የወለድ ከፍያን በሚመለከት የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

1. አንድ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የስነ ስርዓት ስህተት የፈጸመ እነደሆነ ከተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ስህተቱን ማረም አለበት፡፡
2. የስነ ስርዓት ስህተት ፈጽሞ እንደሆነ ጥያቄው ለፍ/ቤቱ ሳየቀርብ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡





ሐምሌ 28 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አበዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግል ማኅበር

መልስ ሰጭ፡- የነገው ሰው ትምህርት አ/ማ

### <u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር ችሎቱ በዚህ መዝገብ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮአል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው ወለድ በስር ተከማሽ ሊከፍል የሚገባው ቢሆንም ከሣሹ ክሱን ሲያቀርብ ከነሐሴ 16/91 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጥቅምት 27 ቀን 1994 ድረስ ያለውን ወለድ አስቦ ዳኝነት ስላልከፈለበት በዚህ ጊዜ ውስጥ የቀረበውን የወለድ ሂሣብ ፈ/ቤቱ አልተቀበለውም በማለት በመወሰኑ ነው፡፡ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መስቀለኛ ይግባኝ ቢያቀርብም ተቀባይነት ባለማግኙቱ ጉዳዩ ለሰበር ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር በመቅረቡ መልስ ሰጪ መልሱን፣ አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር ማመልከቻ በተከሣሽ እንዲከፈል የተጠየቀው ብር 562,966.74 /ምስት መቶ ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሣ ስድስት ከሰባ አራት ሣንቲም/ የወለድ ሂማብ ዳኝነት አልተከፈለበትም ተብሎ መታለፉ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል የሚል ሲሆን መልስ ሰጪ በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ሰህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠየቀው ወለድ ዳኝነት ያልተከፈለበት መሆኑ፣ በሌላው ጉዳይ የተከፈለ የዳኝነት ያልተከፈለበት መሆኑ፣ በሌላው ጉዳይ የተከፈለ የዳኝነተ ሂሣብ ለወለድ ጥያቄው ይያዝልኝ ማለት የማይቻል መሆኑ፣ በሰበር በቀረበው ጥያቄ የመጨረሻ ውሜኔ የሰጠው ጥቅምት 5 ቀን 97 ሲሆን በዚህም ላይ የቀረበ የሰበር አቤቱታ አለመኖሩ፣ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በመስቀለኛ ይግባኝነት

ቀርቦ ውድቅ የተደረገው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቦ ዘመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የሰበር ችሎቱ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አንድ ተሟጋች መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ሂሣብ ገቢ ሳያደርግ ክርክሩ እንደቀጠለ ፍ/ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ መፈፀም ያለበት ሕጋዊ ሥርዓት ምንድነው? የሚለውን ጭብጥ የማያስነሣ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የሕግ ትርጉም ወደሚያስፈልገው ዋናው ጉዳይ ከመሄዱ በፊት ፍርድ ቤቱ መልስ ሰጪ በመልሱ ላይ ያቀረባቸውን ነጥቦች ተመልክቷል፡፡

መልስ ሰጪው በስር ፍርድ ቤት የሂሣብ ይቀናነስልኝ ጥያቄ ስላልተነሣ ለሌላ ጉዳይ የተከፈለው ዳኝነት ለወለዱ ይጣጣልኝ የሚለው ጠያቄ በሰበር ሊታይ አይገባውም ብሏል፡፡ ለፍርድ ቤት የሚከፈል ዳኝነት በአጠቃላይ ከሣሽ በሚጠይቀው ዳኝነት የሚታሰብ እንጂ ለእያንዳንዷ ርዕስ እየተለየ የሚጠየቅ ባለመሆኑ ክርክሩ የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ገቢ መሆን ያለበትን ሂሣብ የሚመለከት እንጂ በሁለቱ መካከል ያለውን ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከት ባለመሆኑ በአንዱ ወገን መነሣት አለመነሣቱ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡

ከዚህ ሌላ በአመልካች የቀረበው የሰበር ማመልከቻ የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት መሆኑን በመጥቀስ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ ሆኖም ለሰበር ችሎት የቀረበው ጥያቄ በመስቀለኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን ከፍርድ ቤቱ ማኅደር ለመገንዘብ ተለናል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም ሊባል አይችልም፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጪ ይግባኝ ጠይቄ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ አግኝቻለሁ የሚለውም አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበበትና ከክስ በፊት ያለውን የወለድ ሂሣብ የሚመለከት ሳይሆን ከውሣኔ በኋላ ያለውን ሂሣብ የሚመለከት መሆኑ #ተገቢው ዳኝነት ተከፍሎበት ሣይጠየቅ ወይም ወደፊት ይከፈልበት ሳይባል ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ዋናው ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ወለድ ታስቦ ይከፈልበት በሚል መወሰኑ ትክክል ነው የምንለው አይደለም; ከሚለው መልስ ሰጪው ራሱ በመልሱ ካካተተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ ክፍል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎችንና ውሣኔዎችን በማምታታት ይኸው አሁን ለሰበር የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም በማለት የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም በማለት የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ ይህ ችሎት የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ብሎ የያዘው የሕግ ነጥብ የዳኝነት መክፈል የነበረበት ባለጉዳይ ሂሣቡን እንዳልከፈለ ፍ/ቤቱ ሲረጋገጥ ሊሰጥ የሚገባው ውሣኔ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ



የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የጠየቀው የወለድ ሂሣብ ለአመልካች መከፈል ያለበት ስለመሆኑ በፍርዱ ተቀብዘለአል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከነሐሴ 16/91 እስከ ጥቅምት 27/1994 ድረስ ያለውን የወለድ ሂሣብ ብር 562,966.74 ውድቅ ያደረገው ከሣሹ ወለድ አስበው ዳኝነት አልከፈሉበትም በማለት ነው፡፡

ማንኛውም ለፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብ ሰው በሕጉ በተተመነው መሠረት የዳኝነት መከፈል እንዳለበት በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 215/1/ የተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ጉዳይ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ከመቀጠሉ በፊት የሚመለከተው የፍርድ ቤቱ ክፍል ይህ አስተዳደራዊ የሆነ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ በኩል በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በሕጉ መሠረት የዳኘነት መከፈል የነበረበት ተከራካሪ ወገን ይህን ተግባር ሳይፈጽም ቢቀር ሕጉ ያስቀመጠው መፍትሄ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሙግት ሂደት የሚፈፀሙ ጉድለቶችን ለማረም የተለያዩ መፍትሄዎችን አስቀምጧል፡፡ በዋናነትና በተለምዶ በብዛት ሥራ ላይ የሚውለው ጉዳዮችን ለይግባኝ ፍ/ቤት እያቀረቡ ስህተቶች እንዲታረሙ መጠየቅ ነው፡፡ ይህ የመፍትሄ አቅጣጫ አንድ በሙግት ሂደት የተፈፀመን ስህተት ስህተቱን ፈፀመ ለተባለው ፍርድ ቤት ሳይሆን በእርከን የበላዩ ለሆነው ሌላ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሚከናወን ሲሆን በሥነሥርዓት ሕግ ቁ. 320 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መሠረት የሚሰተናገድ ነው፡፡

በሙግት ሂደት የሚከሰቱ ስህተቶችን ለማረም ግን ይግባኝ አንዱ ምናልባትም የመጨረሻው አማራጭ እንጂ ብቸኛው አማራጭ አለመሆኑን ከሕጉ አደረጃጀት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የሥነሥርዓት ሕግ ስህተቶችን ወደ የግባኝ ፍርድ ቤት መውሰድ ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን ስህተቱን ፈፀመ ለተባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚቻልበትን ሥርዓት አስቀምጧል፡፡ ከፍትሀብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.320/2/ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ፍርድ ቤት የገዛ ትዕዛዙን ለማሻሻል፣ ለማረም ወይም እንደገና ለማጣራት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው ይኸው ቅድመ ሁኔታ ከተሟላ ብቻ መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ አግባብነት ያለው የሕጉ ክፍል እንዲህ ይላል በተሰጠው ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚቻል ቢሆንም እንኳ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት በዚህ ህግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ፍርዱን ለማረም ለማሻሻል ወይም እንደገና ለማጣራት የማችል ከሆነ ይኸው ሥርዓት አስቀድሞ ሳይፈፀም ይገባኙን ማቅረብ አይፈቀድም፡፡

ይህ ድንጋጌ አንድ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ራሱ መልሶ የሚያይበት ሥርዓት መኖሩንና ቀዳሚው የመፍትሄ አቅጣጫ ማንኛውንም ጉዳይ ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መውሰድ ሳይሆን ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ለራሱ በማቅረብ

ተሠራ የተባለው ስህተት እንዲታረም መጠየቅ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ አሠራር የይግባኝ ፍርድ ቤቶችን መጨናነቅ የሚቀንስ ከመሆኑ ባሻገር ተከራካሪ ወገኖች በአቅራቢያቸው ላለውና ጉዳዩን ለሚያውቀው ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን አቅርበው የተቀላጠፈ መፍትሄ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች፣ ጉዳዮች ባነሳ ጊዜና ወጪ እንዲስተናገዱ ዕድል የሚሰጥ አሠራር ነው፡፡

በሥነሥርዓት ሕጉ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት በዚህ ሁኔታ መልሶ ቀድሞ ያያቸውን ጉዳዮች የሚያስተናግድባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም /ለምሣሌ አንቀጽ 6፣ 74፣ 78፣ 358/ አሁን ከቀረበልን ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነትና ተፈጻሚነት ያለው ግን በሥነሥርዓት ህጉ አንቀጽ 207 ላይ የሠፈረው መሠረተ ሃሣብ ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ሙሉ ከፍል የሚከተለው ነው፡፡

በህግ ተለይቶ ካልተደነገገ ወይም ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም ልዩ ተዕዛዝ ካልሰጠ በቀር በዚህ ሕግ የተመለከቱትን ውሣኔዎች ወይም በውሣኔዎቹ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ባለመፈፀም ከሥነሥርዓት ውጭ የሆነ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ደንብ ውጭ የሆኑ ተግባር ሲፈፀም፣ ከተከራካሪዎቹ ወገኖች አንዱ ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ይህ ከሥነሥርዓት ውጪ የቀረበው ክስ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሠረዝ ወይም ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በዚህም ምክንያት ስለሚደርሰው ኪሣራና ስለሌላውም ወጭ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡

የዚሁ ሕግ የእንግሊዝኛ ቅጂ እንዲህ ይነበባል፡፡

207 <u>Principle</u>

Unless otherwise expressly provided by law of directed by the court, where irregularities arise from noncompliance with any provision of this code or regulation made there under the court, many of its own motion or on the application of either party, set aside such proceedings either party, set aside such proceedings either wholly or in part as irregular, or amend them or make, on such term as it thinks fit, such other order as may be appropriate.

ከዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ መንደርደሪያ መርህ መረዳት እንደሚቻለው በማንኛውም ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ሥነሥርዓቱን ያልተከተለ ክስ የቀረበ እንደሆነ ወይም በክሱ ሂደት ሕጉ ያስቀመጣቸው የሥነሥርዓት ደንቦች በአግባቡ ያልተፈፀሙ እንደሆነ ፍርድ ቤት ሥርዓቱ ከሚያዘው ውጪ የተሠራውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ ይህም የሚከሃወነው በተከራካሪዎች አመልካችነት ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መርህና



ደንብ መሠረት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች በሚያካሂዱት የዳኝነት ሥራ የሥነሥርዓቱን ደንብ ያልተከተለ ክንውን በራሳቸውም ሆነ በአስተዳደር ክፍሉ መፈፀሙን ሲያውቁ ወይም ሲደርሱበት ስህተቱን እንዲያርሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚታየው የተለመደው አሠራር ዳኛ የሰጠውን ትዕዛዝ መቀየር አይችልም፣ መቀየር የሚችለው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ብቻ ነው የሚል ቢሆንም ይህ በተለምዶ የዳበረው አሠራር የሥነሥርዓቱ ሕጉ ያስፈረደውን ከላይ የተጠቀሰውን መሠረታዊ መርህ የሚጻረር ነው፡፡ ሥነ ሠርዓት ነክ የሆነን ጉዳይ የሚመለከት እስከሆነ ድረስ ባለጉዳዮች ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው ስህተቱን ለፈፀመው ፍርድ ቤት ማመልከት ይፈቀድላቸዋል፣ ዳኞችም እርግጥም ሰህተት መሠራቱን ካመኑበት ስህተቱን የማረም ሥልጣንም አላቸው፡፡ /የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁ.209/

ወደያዝነው ዋናው ጭብጥ ስንመለስ የከፍተኛ ፍ/ቤት ወለድን አስመልክቶ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ወለድ ሊከፈለው አይገባም በሚል ምክንያት ሳየሆን ለፍርድ ቤት ገቢ መሆን የነበረበትን የዳኝነት ሂሣብ አልከፈለም በማለት ነው፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 215/1/ እንደተደነገገው ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ ዳኝነት ካልተከፈለባቸው በቀር ተቀባይነት አያገኙም፡፡ ስለዚህ የዳኝነት ሂማብ ለፍርድ ቤት ገቢ ማድረግ በክስ ሂደት መከናወን ያለበት ተግባር ነው፡፡ የዳኝነት ክፍያ መጠናቀቅ ያለበት ክሱ ሲቀርብ እንደሆነ ከድነጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህን ሥራ እንዲያከናውኑ የተመደቡ የሚመለከታቸው የፍርድ ቤቱ ክፍሎች ይህ ህጉ የሚጠይቀውን ሥርዓት መከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ማከናወን ያለበት ይህ ተግባር ሳይከናወን ቀርቶ ክሱ ለፍርድ ቤት /ለዳኛ/ ቢቀርብ ክሱ ከሥነ ሥርዓት ውጪ የቀረበ /procedurally irregular/ ይሆናል፡፡ በፍትሐብሄር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 207 እንደተደነገገው የሥነሥርዓት ሕጉን ወይም በሱ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በመጣስ የቀረበን ከሥነሥርዓት ውጪ የተፈፀመን ተግባር የማቃናት ሃላፊነት ለፍ/ቤቱ የተሰጠ በመሆኑ የሥነሥርዓት ግድፈት የተፈፀመ መሆኑ ሲታወቅ በዚህ መሠረት መከናወን ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት ያልተከፈለ የዳኝነት ክፍያ ካለ የክሱን ሂደት አስመልከቶ የተፈፀመ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መኖሩን ስለሚያመለከት ዳኞች በተጠቀሰው ሕግ መሠረት ግድፈቱን በማስተካከል ያልተከፈለ ሂሣብ ካለ ተሰልቶ እንዲከፈል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በያዝነውም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማድረግ የነበረበት ይህንን ነው፡፡ አመልካች ወለድ እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ ይኸው የአመልካች ጥያቄ በሕግ ተቀባይነት ያለው መሆኑንም ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል፡፡ በመሆኑም ያልተከፈለ ሂሣብ ካለ በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 207 መሠረት ማስከፈል ሲገባው ይህን አልፎ የቀረበውን

ክስ በዚህ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ ሕጉ ያስቀመጠውን የሙግት አመራር የተከተለ አይደለም። በመሆኑም ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም።

የፍተሀብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 211/2/ #ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በተባለበት ጉዳይ ላይ የተፈፀመውን ማንኛውንም የሥነ ሥርዓት ጉድለት በራሱ አስተያየት ሊያርም ይችላል; በማለት ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የሰበር ችሎት የዳኝነትን አከፋፈል አስመልክቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፈፀመውን የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማቃናት እንዳለበት አምኖአል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከ16/12/91 እስከ ጥቅምት 27/1994 ዓ.ም ያለውን የወለድ ክፍያ በሚመለከት በመዝገብ ቁ.11641 የሰጠውን ውሣኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15574 የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል።
2. መልስ ሰጪ ከ16/12/91 እስከ 27/2/94 ላለው ጊዜ በዋናው ገንዘብ ላይ 9% ወለድ ይከፈል።
3. በዚሁ በተፈረደው የወለድ መጠን ያልተከፈለ የዳኝነት ገንዘብ አመልካቹ ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ገቢ ያድርግ። የውሣኔው ገልባጭ የሚሰጠው የዳኝነቱን ገንዘብ ገቢ ማድረጉ ከተረጋገጠ በኋላ ነው ተብሏል።
4. መልስ ሰጪ በዚህ ፍርድ ቤት ውሣኔ አመልካች ለዚህ ፍርድ ቤት ገቢ ያደረገውን የዳኝነት ሂሣብ ይተካለት፣ ሌላው በዚህ ፍርድ ቤት ያለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
5. ውሣኔያቸው ላይ ለውጥ መደረጉን እንዲያውቁት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ለጠቅላይ ፍ/ቤት የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይላክ።



## *የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*
## *ሰበር ሰሚ ችሎት*

የመ/ቁ. 14605

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት

መልስ ሰጪዎች፡- 1. ኮሜት ትራንስዓርት ድርጅት
2. ሸበሌ ትራንስፖርት ድርጅት
3. በከልቻ ትራንስፖርት ድርጅት
4. ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት
5. አዲስ ሜካኒካል ድርጅት
6. አቶ ዮሐንስ ተሰፋ

*ስለ ማጓጓዝ ስራ - የአጓዥ ኃላፊነት - የተመዘገቡ ጓዞች ወይም ዕቃዎች የጠፉ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን - በተለያዩ ምክንያቶች ከኃላፊነት መዳን የንግድ ህግ ቁጥሮች 590፣ 591፣ ውል - ውልን ስላለመፈጸም- ከዐቅም በላይ የሆነ ኀይል - የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1792*

አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ከ1ኛ-5ኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች መኪና አቅራቢነት ነጭ ጋዝ ናፍታ አሰጭኖ ከአሰብ ወደ ባህር ዳር በሚጓጓዝበት ወቅት መኪናው ተገልብጦ ዋጋው ብር 51,089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሰምንት ሳንቲም/ የሆነ ነዳጅ ስለፈሰሰ ይህንኑ ዋጋ ብር 51,089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሰምንት ሳንቲም/ ከ1-5 ያሉት ተጠሪዎ እንዲሁም የመኪናው ባለንብረት 6ኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ነዳጁ

የፈሰሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ ዕቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ወይም ጉዳት ሲያገኛቸዉ ወይም የማስረከቢያ ጊዜው ቢዘገይ በኃላፊነት የሚጠቅ ሲሆን ከዚህ ኃላፊነት የሚነው ዕቃው የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰው ወይም የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በተቀባዩ ጥፋት ሲሆን ነው፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል የሚባለው ባለእዳው /አጓዡ/ በቅድሚያ በምንም መልኩ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይቻል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡
3. ወደ መኪና ሮጦ የገባን ሰው ለማዳን በተወሰደ ርምጃ ምክንያት በመጓጓዝ ላይ የነበረ ዕቃ ላይ የደረሰ ጉዳት ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ተከስቷል የሚባል አይደለም፡፡



የመ/ቁ. 14605

ቀን ሐምሌ 29/1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አበዱልቃድር መሐመድ

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት

ተጠሪዎች፡- 1. ኮሜት ትራንስዓርት ድርጅት

2. ሸበሌ ትራንስፖርት ድርጅት

3. በከልቻ ትራንስፖርት ድርጅት

4. ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት

5. አዲስ ሜካኒካል ድርጅት

6. አቶ ዮሐንስ ተሰፋ

## ፍርድ

ለአሁን አቤቱታ መነሻ የሆነው ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጳጉሜ 3/1992 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በዚያ ፍ/ቤት ከ1ኛ-5ኛ ድረስ ባሉት ተጠሪዎች መኪና አቅራቢነት አመልካች 34993 ሊትር ነጭ ጋዝ ናፍታ አስጭኖ ከአሰብ ወደ ባህርዳር በሚጓጓዝበት ወቅት መኪናው በመገልበጡ የተጫነው ነዳጅ በሙሉ ስለፈሰሰ የፈሰሰውን ነዳጅ ዋጋ ብር 51089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ስምንት ሳንቲም/ ከነወለዱ አምስቱም ተጠሪዎች እንዲከፍሉ፡፡ 6ኛውም ተጠሪ የመኪናው ባለንብረት ስለሆነ በአንድነት እና በነጠላ በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አቀራክሮ ነዳጁ የፈሰሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሃይል ስለሆነ ተጠሪዎቹ በሙሉ ለክሱ ሃላፊ አይደሉም በማለተ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የስር ፍርድ ቤቱን ውሳፀነ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ላይ ሲሆን የአመልካተ ቅሬታ በአጭሩ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች #ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታን; ሲተረጉሙ የህግ ስህተት ፈጽመዋል የሚል ነው ተጠሪዎችም ለቀረበው አቤቱታ መልስ አቅርበዋል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በአንድነት በ17/10/96 በተጻፈ መልስ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ በክሱ ይተካልን፣ ይህ ቢታለፍ ነዳጁ የፈሰሰው ከተባለም የቀድሞ የኢትዮጲያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ከአመልካች ጋር የማጓጓዣ ውል ስላልፈጸመ ለጥፋቱ ሃላፊ አንሆንም፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ሃላፊነት እንደሌለበት በመ/ቁ/9678 እና በመ/ቁ 6979 በሰበር ችሎት ውሳኔ ተሰጥቷል የሚል ነው፡፡

6ኛ ተጠሪ በበኩሉ በ9/6/97 በተጻፈ መልስ ነደጁ የፈሰሰው ከፈቅም በላይ በሆነ መክንያት ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንዲጸናለት ጥቅቋል፡፡

አመልካችም በመልስ መልሱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ከፍ ሲል የተገለጸው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገው አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም፣

1. አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይስ አይደለም?
2. ካልሆነ ተጠሪዎች ለክሱ ሃላፊ ሊሆኑ ይገባልን? የሚሉት ነጥቦች መታየት አለባቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>

አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በሃላፊነት እንደሚጠየቅ የግን ህጉ ቁጥር 590 ሲያመለክት አጓዡ ከዚህ ሀላፊነት የሚድነው ደግሞ የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰው ወይም የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በእቃው ውሳጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ የን/ህ/ቁ 591 ያመለከታል፡፡

በመሆኑም አንድ አጓዥ የሚያጓጉዘው እቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት ከሆነ ከሃላፊነት ለመዳን እቃው የጠፋው ወይም የተጎዳው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን ወይም ከራሱ ከእቃው ጉድለት መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ሲሆን



ከምክንያቶቹ ውስጥም ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ የሚለው በመሆኑ ችሎቱም ይህ ሁኔታ ተከስቷል የሚባለው መቼ ነው የሚባለውን ከህጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በንግድ ህጉ ውስጥ “ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ወደ ፍ/ብ/ህጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ወደሚመለከቱት ድንጋጌዎች ማምራቱ የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረትም የፍ/ህ/ቁ 1792ን ስንመለከት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ወይም የለም የሚባለው መቼ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ሀይል ደርሷል የሚባለው ባለእዳ ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍጹም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ከንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለእዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈጻጸም ከባድ የሆነ ወጪ በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት መመልከት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለእዳው በቅድሚያ በምንም መልኩ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለእዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብ እና ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት ማየት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል የሚችለው ፈጽሞውኑ ሊቋቋሙት ወይም ሊቆጣጠሩት የማይቻል ወይም ማንኛውም ጠንቃቃ ሰው ሊገምተው እና ሊያስበው የማይቻለው ሁኔታ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1793 የተዘረዘሩት ምክንያቶችም ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይም ስናመራ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ነጻ ያደረጓቸው ነዳጁ የፈሰሰው ወደ መኪናው ሮጦ የገባን ሰው ለማዳን በተወሰደ እርምጃ ስለሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ድንገተኛ ደራሽ አደጋ ነው በማለት ነው፡፡ ነገር ግን አንድ

የመኪና አሽከርካሪ መኪያ በሚያሽከረክርበት ወቅት በመንገዱ ድንገት ሰው ሊገባበት እንደሚችል፣ የተለያዩ የመጋጨት ወይም የመገልበጥ አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል ቀደም ብሎ ሊገምት ወይም ሊያስብ የሚችለው ነገር ነው፡፡ የመኪና አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ጊዜ በመንገዱ ላይ ድንገት ሰው ሊገባ ወይም ድንገተኛ አደጋ ሊያጋጥም ይችላል ብሎ ፈጽሞ አያስብም ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም 6ኛ ተጠሪ መኪናውን ሲያሽከረክር ድንገት ሰው ሮጦ ወደ መንገዱ መግባቱ ብቻ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ መኖሩን አያሳይም፡፡ ስለዚህም የስር ፍ/ቤቶች ለነዳጁ መፍሰስ ምክንያት የሆነውን አደጋ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለጸው አንድ አንቨር በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ዓዦች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡ ከኃላፊነቱ ነጻ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንደኛው ደግሞ አደጋው ወይም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 6ኛ ተጠሪ አንቨር መሆኑ ክርክር አልተነሳበትም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ደግሞ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንየት አይደለም፡፡ ስለዚህም 6ኛ ተጠሪ ለጉዳቱ በን/ህ/ቁ 590 መሠረት ኃላፊ ነው፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉትን ተጠሪዎችን ኃላፊነት ስንመለከት ተጠሪዎቹ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው የማይባል ከሆነ የፈረሰው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን እቃውን ለማጓጓዝ ከአመልካች ጋር ያደረገው ውል ስለሌለ ኃላፊነት የለብንም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን አንጂ በስር ፍ/ቤት የፈረሰው ድርጅት የእቃ ላኪ ኮሚሲዮን እቃ አጓዡ ያለበት መብት እና ግዴታ ያለበት በመሆኑ (የፍ/ህ/ቁ. 2252 (3)) ተጠሪዎቹ ለደረሰው ጉዳት በአንድነት አና በነጠላ ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በተጨማሪ ያነሱት ክርክር በተመሳሳይ ጉዳት ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ኃላፊነት እንደሌለበት ቀደም ሲል ተወስኗል የሚል ሲሆን እንደዚህ አይነት ውሳኔ ተሰጥቶ እንኳን ቢሆን በተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ይሆንም፡፡

በመጨረሻም እነዚሁ ተጠሪዎች ወደ አክስዮንነት የተቀየርን ስለሆነ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ተተክቶ ይከራከር ሲሉ የጠየቁ



ቢሆንም ቦርዱ በኃላፊነታቸው መጠን እዳቸውን የመክፈል ግዴታ ካለበት በአፈጻጸም ጊዜ እንዲተካ ሊጠይቁ የሚችሉ በመሆኑ ጥያቄያቸው በዚሁ ታልፏል፡፡

## ውሣኔ

- ተጠሪዎች በአንድነት እና በነጠላ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈሉ፡፡
- አመልካች በክርክሩ ወቅት ለደረሰበት ወጪ እና ኪሣራ ዝርዝሩን በስር ፍ/ቤት አቅርቦ ያስወስን፡፡
- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 349/87 በ3/13/92 ዓ.ም. እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2317/93 በ14/3/96 ዓ.ም. የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 17068

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት
መልስ ሰጪ፡- ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ

*ውል የግዴታዎች መቅረት - ስለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ - ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህሊና ግምቶች- የፍትሐብሔር ህግ ቁጥሮች 1856፣ 2024፡- ስለ አቤቱታ -ህጋዊ ስለሆኑ ግምቶች - የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 89*

አመልካች በስር ፍ/ቤት መ/ሰጪ ያልከፈለው የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍለው በመጠየቅ ባቀረበው ክስ መ/ሰጪ ሳይቀርብና ኪራዩ ተከፍሏል የሚል ክርክር ሳይነስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 መሰረት ከሁለት አመት በላይ የሆነው የኪራይ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል የአመልካችን ክስ በከፊል ውድቅ ስላደረገውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን ስላጸናው የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ፡-</u> የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ጸንቷል።

1. የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው።
2. የቀረበላቸው ፍሬ ነገር በህግ ግምት ከተሸፈነ ተከሳሽ ፍሬ ነገሩን ካደም አልካደ ፍ/ቤቶች የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው።



የመ/ቁ. 17068
ሐምሌ 19 ቀን 1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ
አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት
መልስ ሰጪ፡- ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ (ባለቤት)

### <u>ፍርድ</u>

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ክስ ካቀረበበት ገንዘብ መካከል ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው ሂሣብ ተከሣሽ በፍ.ብ.ሕግ ቁጥር 2024 መሠረት እንደከፈለ ስለሚቆጠር ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን ሂሣብ በሚመለከት ከሣሽ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት በመወሰናቸው እና ሌሎችንም ክስ የቀተበባቸው ሂሣቦች ውድቅ በማድረጋቸው ነው።

የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም የቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት በማጣቱ የሰበር ማመልከቻ አቅርቧል። የሰበር ማመልከቻው ይዘት በርካታ ነጥቦችን ያካተተ ሲሆን ዋና ዋና ነጥቦቹ የቤቱ ኪራይ በአሜሪካን ዶላር ሊከፈለን ሲገባ ታልፎብናል፣ የውሃ ፍጆታና የአገልግሎት ሂሣብ ውድቅ ተደርጎብናል፣ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን ሂሣብ አስመልክቶ ክሱ ውድቅ መሆኑ አግባብ አይደለም፣ የተወሰነልን ወጪና ኪሣራም ካወጣነው ወጪ በታች በመሆኑ ትክክለ አይደለም የሚል ነው።

አመልካች ካቀረባቸው ነጥቦች መካከል በሰበር ሊታይ ይገባል የተባለው የሕግ ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች ተከሣሽ ክሱን ለመከላከል ባልቀረበበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 ላይ በሰፈረው የሕሊና ግምት መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው የኪራይ ክፍያ እንደፈከፈለ ይቆጠራል በማለት የአመልካቹን ክስ በከፊል ውድቅ ማድረጋቸው አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ነው። በመሆኑም አመልካች ያቀረባቸው ሌሎች የቅሬታ ነጥቦች መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩን የሚያመለክቱ ስላልሆኑ ይህ ችሎት በነዚህ ቅሬታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት አላስፈለገውም።

የሕሊና ግምቱን በሚመለከት አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚለው፡-

ሀ. "በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1856(2) ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋ ደንብን መከላከያ በራሳቸው አነሳሽነት ክሱ በይርጋ ውድቅ ነው በማለታቸው፣

ለ. ተከሣሹ ለቀረበበት ክስ መልስ ለመስጠት ካለመፈለጉም በላይ እዳውን አልካደም፣

ሐ. የሕሊና ግምት ይወሰድልኝ ማስረጃ ማቅረብ አልችልም ጠፍቶብኛል ስለዚህ የሕግ ግምት ይወሰድልኝ በማለት ተከሣሹ ሳይከራከር፣

መ. የይርጋ ክርክር የሚያነሳው ወገን ግዴታውን አለመውጣቱን ሳይክድ የተጣለበት ግዴታ ግን በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን ከኃላፊነት ነፃ ነኝ አልጠየቅም የሚል ክርክር ሲያቀርብ ነው" የሚሉ የክርክር ነጥቦችን በማቅረብ ነው፡፡

መልስ ሰጭ መልስ ካለው ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ቢሰጥም ለዚሁ በተያዘው ቀጠሮ አልቀረበም፣ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሰበር እንዲታይ በተያዘው የሕግ ነጥብ ላይ የቀረበ የመልስ ሰጭ መልስ የለም፡፡

ይኸው ችሎት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰፈረው የሕግ ግምት ተከሣሹ ቀርቦ ዕዳውን ባልካደበት ወይም ጭራሽ ባልቀረበበት ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል አይሆንም በሚለው የሕግ ጉዳይ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ወደ ዋናው ነጥጥ ከመግባቱ በፊት አመልካች ያቀረባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች የህሊና ግምትን ከማመለከተው የሕግ ነጥብ ጋር ያላቸውን አግባብነት መርምሯል፡፡

አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰፈረው የሕግ ግምት ይርጋን ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር አንድ እንደሆኑ በመቁጠር ፍርድ ቤት የሕሊናውን ግምት በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው አይገባም የሚል የሕግ ክርክር አቅርቧል፡፡ ሆኖም በፍትሐብሔር ሕጉ የሰፈረው የህሊና ግምት በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 1845 (ወይም በሌሎች በርካታ አንቀጾች) ከሰፈረው የይርጋ ደንብ የተለየ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ይህን መከራከሪያ የሚቀበለው አይደለም፡፡ የይርጋ ደንብ አንድ ክስ በፍርድ ቤቱ ቀርቦ በስረ ነገር እንዳይታይ የሚከለክል ሲሆን የሕሊና ግምት (በ2024 የሰፈረው የመክፈል ግምትን ጨምሮ) በሌላ በኩል የማስረዳት ሸክምን ከአንድ ወገን ወደ ሌላው የማስተላለፍ ውጤት ብቻ ያለው በመሆኑ ከሣሽ ያቀረበውን ክስ ይዘት መርምሮ ውሣኔ መስጠትን የሚከለክል አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የሰፈረውን ይርጋ ተከሣሹ ወገን ካላነሳው ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳ እንደማይችል በፍትሐብሔር



ሕግ ቁ.1856 የተጠቀሰ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ለይርጋ ድንጋጌዎች እንጂ በሕግ ግምት የማስረዳት ሸክም ከአንድ ተሟጋች ወደ ሌላው በሚዘዋወርባቸው ሁኔታዎች አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ድርጅት ይርጋን (Period of limitation) ከሕግ ግምት (Presumptions) ጋር በማመሳሰል ለይርጋ ተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ ለህግ ግምትም ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የህጉን መንፈስ፣ ዓላማና ግልጽ ይዘት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበትና በዚህ መዝገብ የህግ ትርጉም የሚሰጠው ዋነኛው ነጥብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰፈረው የሕግ ግምት ተፈፃሚ የሚሆነው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? የሚል ሲሆን ተከሣሽ ቀርቦ የቀረበበትን ክስ ባልካደበት ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚለው ነጥብም ከዚሁ ተያይዞ የሚነሳ ነው፡፡

የሕግ ግምት አፈፃፀም የስረነገር (Substantive) ሕግ እና የስነ ሥርዓት (Procedural) ህግ ገጽታዎች ያሉት ሲሆን ከላይ የተነሱትን ነጥቦች በአግባቡ ለመመለስ የኢትዮጵያ ሕግ በሁለቱም ረገድ ያለውን ዝርዝር ድንጋጌ መመልከትና መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በኢትዮጵያ የስረነገር ሕጎች በርካታ የሕግ ግምቶች ያሉ ሲሆን አሁን ከቀረበልን ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2024 የሰፈረው ግምት ነው፡፡ ይህ የግህ ግምት ስለ ውሎች ማስረጃ በሚመለከተው ክፍል የሚገኝ ሲሆን በውል የሚጠየቅ ገንዘብ እንደተከፈለ ከሚያስቆጥሩ የሕሊና ግምቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ዕዳው እንዲከፈል ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈሉ የቀሩ በአንቀጹ ተዘርዝረው የተቀመጡትን ዕዳዎች እንደተከፈሉ ይቆጠራል፡፡ በዚህ ግምት ከሚሸፈኑ ዕዳዎች መካከል ለቤት ኪራል የሚከፈል ዕዳ አንዱ ነው፡፡ (ቁ.2024/መ)

የሕግ ግምቶች መሠረታዊ ውጤት የማስረዳት ሸክምን ከአንዱ ወገን ወደሌላው እንዲሻገር ማድረግ ቢሆንም የማስረዳት ሸክሙ የዞረበት ወገን የሕግ ግምቱን ማፍረስ የሚችልበት የሕግ ሁኔታ ይለያያል፡፡ አንዳንድ የህግ ግምቶች የግምቱ ተጠቃሚ ያልሆነው ወገን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ የሚያፈርሳቸው ሲሆኑ (Reputable Presumption) ሌሎች የሕግ ግምቶች ደግሞ ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ

በማቅረብማፍረስን የማይፈቅዱ (Irrefutable Presumption) ናቸው፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ከ2020 — 2024 ያሰፈራቸውን የህግ ግምቶች ለማፍረስ ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ ከሕጉ አንቀጽ 2026(1) ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸው ድንጋጌ "ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ ለተገለጠው የሕሊና ግምት መቃወሚያ የሚሆን ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ለመቀበል አይቻል" በማለት በሕጉ የሰፈሩትን ግምቶች ለማፍረስ አንደኛው ወገን ማንኛውንም ዓይነት ማስርጃ ማቅረብ እንደማይፈቅሉለት በመርህ ደረጃ በግልጽ አስፍሯል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ ቢኖርም አንዱ ወገን ይህን አስገዳጅ የህግ ግምት ማፍረስ የሚችለው ሌላው ወገን መሀላ እንዲፈጽምለት በመጠየቅ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መልክ ሌላው ወገን መሃላ እንዲወርድለት በመጠየቅ የማስረዳት ሸክሙን በመወጣት የሚሻ ወገን የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 83 በሚያዘው መሠረት ይህን ማስረጃውን ክሱን በሚያቀርብበት ወቅት እንዲጠቅስ ይጠበቅበታል፡፡

በውል ሕግ የሰፈሩት እነዚህ ድንጋጌዎች የስረ ነገር ሕግ ክፍሎች በመሆናቸው ፍርድ ቤቶች ሊከተሉዋቸው የሚገባ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የማስረጃን አቅራረብ የሚመለከቱ ከመሆናቸው በስተቀር እንደማንኛውም ሌላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች በባለጉዳዮች ቢጠቀሱም ባይጠቀሱም ፍርድ ቤቱ አግባብነት ባለበት ሁኔታ ሁሉ ተፈፃሚ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ በመሠረቱ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ባለጉዳዮች ለጉዳያቸው አግባብነት ያለውን ፍሬነገርና የሚጠይቁትን ዳኝነት ከመግለጽ አልፈው በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን ወይም የማይሆነውን ድንጋጌ እንዲጠቅሱ አይጠበቅባቸውም፡፡ በመሆኑም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የተጠቀሰውን የሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያበቃ ፍሬ ነገር የቀረበለት መሆኑን የተረዳ ፍ/ቤት በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የሚሸፈነውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ የመቁጠር ግዴታ አለበት፡፡

የሕግ ግምቶችን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕጉ የሰፈረው ይህ መሠረተ ሃሣብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉም በተመሣሣይ መንገድ ተደንግጎ የምናገኘው ነው፡፡ በዚሁ ሕግ መሠረት ማንኛውም ተከሣሽ በመርህ ደረጃ ለፍርድ ቤቱ በሚያቀርበው መልስ ክስ የቀረበበትን ነገር በግልጽና በዝርዝር ማስተባበል ይጠበቅበታል፡፡ በክስ አቤቱታ ላይ የቀረበ ማንኛውም ነገር በግልጽ ካልተካደ



እንደታመነ ሊቆጠር እንደሚችልም ይደነግጋል፡፡ ይህ አባባል አጠቃላይ የፍትሐብሔር መደበኛ ሙግት አካሄድን የሚመለከት ቢሆንም ተከሣሹ የሕግ ግምት ተጠቃሚ ሲሆን በግምቱ የሚሸፈነውን ፍሬ ነገር በሚመለከት ይህ ግዴታ እንደሚወርድለት የሕጉ አንቀጽ 89 በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ ድንጋጌ "አስቀድሞ በአንደኛው ወገን አቤቱታ ወይም ሙግት በግልጽ የተካደ ጉዳይ ካልሆነ በቀር አንዱ ወገን ተከራካሪ ህጋዊ በሆነ ግምት የሚደገፍበትን ነገር ወይም ሌላው ወገን ማስረጃ እንዲያቀርብ ተገቢ የሆነበትን ጉዳይ ሌላው ወገን በአቤቱታው ውስጥ መጥቀስ አይገባውም" በማለት የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሆነ ተሟጋች በሚያቀርበው መልስ በህግ ግምት የተሸፈነውን ፍሬ ነገር በግልጽ የመካድ ግዴታ እንደሌለበት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አንድ ተከሣሽ በሕግ ግምት የተሸፈነውን ፍሬ ነገር በማስመልከት በመልኩ በግልጽና በዝርዝር መካድ አይጠበቅበትም፡፡ በመሆኑም በህግ ግምት የተሸፈነን ጉዳይ በማስመልከት ማንኛውም ፍርድ ቤት ቢሆን ተከሣሹ በግልጽ ስላልካደ እንዳመነ ይቆጠራል በማለት ፍርድ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ይህ መሰረተ ሃሣብ በፍትሐብሔር ሕጉ ካለው መሠረተ ሃሣብ ጋር ተመሳሳይ እና የሚጣጣም ነው፡፡

የሕግ ግምትን አስመልክቶ ያለው የሕግ ማዕቀፍ ይህ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ውሣኔ ይህንኑ መሠረት ያደረገ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ተከሣሹ የሕግ ግምት ተጠቃሚ በሚሆንበት ወቅት የሚከተሉት ሂደትና የሚሰጡት ውሣኔም በሌሎች በመደበኛ የሙግት ሂደት ከሚተከሉዋቸው የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ደንቦች የተለዩ መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡

በመሆኑም የቀረበላቸው ፍሬ ነገር በህግ ግምት እስከተሸፈነ ድረስ ፍርድ ቤቶች ተከሣሽ ካደም አልካደ የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተከሣሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲቀጥል መደረጉም አስገዳጅ በሆኑት የሕግ አንቀጾች አፈጻጸም ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ ተከሳሹ ፍርድ ቤት ቢቀርብም በግልጽ እንዲክድ የማይገደደውን ፍሬ ነገር ጉዳዩ እርሱ በሌለበት በመቀጠሉ እንዳመነ የሚቆጠርበት በቂ ሕግ ምክንያት የለም፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ክስ በቀረበበት የኪራይ ክፍያ በከፊል መጠየቅ ከነበረበት ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው ስለመሆኑ ከከሣሽ ክስ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተከሣሽ ባያነሳውም ወይም በሌለበት ቢታይም በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2024 ስር ያለውን የሕግ ግምት ተፈፃሚ በማድረግ ዕዳው እንደተከፈለ መቁጠር ተገቢ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶችም ያደረጉት ይህንኑ ነው፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቶቹ ህጉን በትክክል ተፈፃሚ ያደረጉ ስለሆነ ውሣኔው የሚነቀፍ አይደለም፡፡

**ውሣኔ**

1. የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ፀንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ

**የሀሣብ ልዩነት**

በአብዛኛው ድምጽ በተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 የተመለከተውም ሆነ ሌሎች የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ የተለዩ መሆናቸው የተገለፀ ሲሆን እኛም ይህን የምንቀበለው ነው፡፡ የሕግ ግምት የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የማስረዳት ሸክምን በግምቱ ተጠቃሚ ከሆነው ወገን ወደ አልሆነው ተከራካሪ ማሸገር ብቻ መሆኑንም የምናምንበት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት አንድን ሕግ ተመስርቶ ፍርድ ለማስፈር የቀረበለት ወይም የያዘው የፍሬ ነገር ክርክር ከተጠቃሹ ሕግ ጋር ግንኙነት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ፍ/ቤቱ ሕጉን መሠረት አድርጎ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊትም ሕጉ ለክርክሩ አግባብነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

እኛም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 የተመለከተው የሕሊና ግምት ከተያዘው ክርክር ጋር ያለውን አግባብነት መርምረናል፡፡ አብዛኛው ድምጽ እዳ እንዲከፍል የተጠየቀው ተከሣሽ ቀርቦ እዳውን ባይክድም ወይም ጭራሹን ባይቀርብም ፍ/ቤት ይህን ድንጋጌ ተመስርቶ በሕሊና ግምቱ ተጠቃሚ ሊያደርገውና እዳው እንደተከፈለ ሊቆጠርለት ይገባል ሲል ለድንጋጌው በሰጠው ትርጓሜ እና በደረሰበት መደምደሚያ ግን ባለመስማማት እንደሚከተለው በሐሳብ ተለይተናል፡፡

እንደሚታወቀው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እዳ እንደተከፈለ ይቆጠር ዘንድ ሕግ ግምት የወሰደበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 ማስረጃ ስለማቅረብ ግዴታና ስለአቀባበሉ በተዘረዘረበት የፍ/ብ/ሕግ ምዕራፍ ሰባት ክፍል አንድ ስር የሚገኝ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር ያለ የሕሊና ግምት ልክ እንደ ጽሑፍ፣ ምስክር፣ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ሁሉ አንድ የማስረጃ አይነት ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2002 ላይ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እዳው እንደተከፈለ መቆጠሩን ቀሪ ማድረግ እንደሚቻል የሚደነግገው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 ደግሞ እነዚህ የሕሊና ግምቶች እራሣቸው ማስረጃዎች



መሆናቸውን ግልጽ የሚያደርግልን ነው፡፡ ስለሆነም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024ን ጨምሮ በዚህ ምዕራፍ ክፍል ሶስት ውስጥ የተደነገጉት ተጠያቂው ገንዘብ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የሕሊና ግምቶች በሙሉ እንደ አንድ የክርክር ማስረጃ የሚወሰዱ እንጂ ሕግ በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የሕሊና ግምት የወሰደባቸው ናቸው ሊሰኙ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ለአንድ ውሣኔ መሠረት የመሆናቸውም ጉዳይ ከዚህ የሕጉ መንፈስና አላማ ጋር እየተዛመደ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ይህንንም ግልጽ ለማድረግ ጉዳዩን የፍትሐብሔር ሙግት ከሚመራበት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች አኳያ ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ ክስ የቀረበበት ተከሣሽ የተከሰሰበትን ነገር በግልጽ መካድ እንደሚገባውና ይህን ካላደረገ ደግሞ ክሱን እንደአመነ ሊቆጠር እንደሚገባው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.83፣ 334/1/መ/ እና 235 ላይ ተመልክቷል፡፡ እንበልና የሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈው የኪራይ ሂሣብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ቀርቦ አለመክፈሉን /እዳውን/ ቢያምን ወይም በግልጽ ባይክድ ፍ/ቤቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242ን ተመስርቶ በእምነቱ መሰረት ፍርድ ሊሰጥ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ወደ ተጠቀሰው የሕሊና ግምት ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ አየታይም፡፡ የያዘውም ፍሬ ነገር የዚህን ስረ ነገር ሕግ ተፈፃሚነት የሚጠይቀው አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይኸን የኪራይ ሂሣብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ከፍያለሁ ቢልና የቀረበበትን ክስ ቢክድ ፍ/ቤቱ 1ኛ/ ተከሣሹ እዳውን ሊከፍል የሚገባው ስለመሆን፣ አለመሆኑ ጭብጥ ሊይዝ 2ኛ/ በተሹ ቢጠቀስም ባየጠቀስም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024ን ሊመሠረትና ተከሣሹን በሐሊና ግምት ማስረጀው ተጠቃሚ እንዲሆን ሊያደርገው ይገባዋል፡፡ በሕሊና ግምት ተጠቃሚው ተከሣሽ ሌላ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ ከማቅረብ ግዴታ ነፃ የሚወጣ ሲሆን ከማሹ ግን ይህ የሕሊና ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2026/2/ መሠረት በመሐላ ብቻ እንዲፈርስለት ለመጠየቅ ይችላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ሁለት ዓመት ያለፈው የኪራይ ሒሣብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ቀርቦ መልስ የሰጠ ወይም መከራከሪያውን ያሰማ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ አግባብነት ካላቸው የፍ/ብ/ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ሲታይ ተከሣሹ እዳውን አለመክፈሉን ወይም ክሱን ማመኑን የሚያሳየን እንጂ በምንም መለኪያ ክሱን ክዷል ወደሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርሰን የሚችል አይሆንም፡፡ ፍ/ቤቱም በፍሬ ነገርም ሆነ በሕጉ ረገድ ልዩነት የተፈጠረበት ክርክር ቀርቦለታል የሚያሰኝ ባለመሆኑም ውሣኔ

ሊያሳርፍበት የሚገባ ጭብጥ ለመያዝ አይችልም፡፡ ይልቁንም ተከሣሹ የመከላከያ መልስ አላቀረበምና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.246 መሠረት በጉዳዩ ጭብጥ እንዲይዝበት የሚገደድበት አይሆንም፡፡ ይህ ደግሞ ተከሣሹ ክሱን እንዳመነ ተቆጥሮ በእምነቱ መሠረት ፍርድ ሊሰጥበት እንደሚገባ የሚያመለክተን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የእምነት መነሻ ተደርጐ ፍርድ ሲሰጥ ደግሞ ወደ ሕሊና ግምት ማስረጃው መሄዱ አላስፈላጊ ነው፡፡ በውጤቱም ተከሣሹ በሐሊና ግምት ማስረጃው ተጠቃሚ መሆን እንደማይገባውና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024ም እዳው ባልተካደ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ተከሣሹ ቀርባ መልሰ /መለላከያ/ ባቀረበ ጊዜም በፍ/ቤት አነሳሽነት ለውሣኔ መሠረት ሊሆን እንደማይችል የሚያረጋግጥልን ነው፡፡

በተጨማሪም አብዛኛው ድምጽ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.89ን በመጥቀስና ይህ ድንጋጌ የሕሊና ግምቱ ተጠቃሚ የሆነው ወገን የፍሬ ነገር ክርክር የማቅረብ ግዴታውን የሚያስቀርለት ነው በማለት ድንጋጌው ከስረ ነገር ሕጉ ጋር ይጣጣማል የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረሱን ተረድተናል፡፡ እኛም ምንም እንኳን የዚህ ድንጋጌ የአማርኛ ቅጅ በጣም ግልጽ ሆኖ ባናገኘውም ከእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር በአንድነት ሲታይ አንደኛ ድንጋጌው በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የተደረገ የሕግ ግምትን እሳቤ አድርጐ የተደነገገ መሆኑን፤ ሁለተኛ የግራ ቀኙን ተሟጋቾች በክርክር ውስጥ መኖር የማጠይቅ መሆኑን፤ እንዲሁም ሶስተኛ አንደኛውን ወገን ተከራካሪ ባይከራከርበትም በሕግ ግምቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ጉዳዩ በሌላው ወገን ያልተካደ ይሆን ዘንድ የሚፈልግ መሆኑን ለመረዳት ያህል ግን የሚበቃ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ሕጉ የሚፈልጋቸው መስፈርቶች ደግሞ እንደ ማስማረጃ ከሚቆጠረው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ጋርም ሆነ በጉዳዩ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር የተያያዙ አይደሉም፡፡ ስለሆነም በእኛ እምነት ይህ ድንጋጌ ከመሠረቱም ከዚህ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024ን ጭምር በስረ ነገር ሕጉ ምዕራፍ 7 ክፍል 3 ስር እንደተከፈሉ ይቆጠሩ ዘንድ የሕሊና ግምት የተወሰደባቸውን እዳዎች አስመልክቶ ክስ ሲቀርብ ሙግቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተመለከተውን መደበኛ የሙግት ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን እንጂ የተለየ ደንብ ሊከተል የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተከሣሹ ቀርቦ እዳውን /ክሱን/ በመካድ እስከአልተከራከረም በሕሊና ግምቱ ተጠቃሚ ሊደረግና ከእዳው ነፃ ሊሆን አይገባውም፡፡ ይልቁንም የሕሊና ግምቱ ለፍርድ መሠረት ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለምና ክሱን በማስረጃ አስደግፎ ያቀረበው ከሣሽ (አመልካች) ክሱን በመሰረትክበት ጊዜ ያልተከፈለህ ስለመሆኑ በመሐላ እንዲረጋገጥልህ አልጠየቅክም በሚል ምክንያት እዳው አይከፈልህም ሲባል የሚገባው ሆኖ አላገኘውም፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች ስማችን በ2ኛ እና በ4ኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኞች የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድ ተሽሮ አመልካቹ የጠየቀው የቤት ኪራይ እንዲከፈለው ሊወሰን ሲገባ መጽናቱ ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው ፍርድ ሊሻር ይገባው ነበር ስንል በሐሣብ ተለይተናል፡፡

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

**ሰበር ሰሚ ችሎት**

የመ/ቁ. 14974

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ

መልስ ሰጪ፡- 1. አቶ መንግሥቱ ኃብ
2. አቶ ዮሴፍ ገ/ሥላሴ

*ስለ እንደራሴነት - ከገዛ ራስ ጋር ስለሚደረግ ውል ፍጹም ስለሆነ እንደራሴነት - ጥብቅ የሆነ ቅን ልቡና- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 2188፣2189፣2209፡- በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን - ስለ ወኪሎች - ስለ ባለጉዳዩ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ መቅረት- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ህግ ቁጥሮች 57፣78*

2ኛ መ/ሰጭ የአመልካች ወኪል ሆኖ ከ1ኛ መ/ሰጭ ጋር በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ በአመልካች ወኪልነቱ 2ኛ መ/ሰጭ መልስ ሰጥቶ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲነሳ ያቀረበችውን ጥያቄ የም/ሸ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ወኪልሽ መልስ ሰጥቷል በሚል ውድቅ በማድረጉና ጉዳዩን በይግባኝ ያለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸው የቀረበ አቤቱታ



<u>ው ሳ ኔ፡-</u> የም/ሸ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ሰበር ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

1. አንድ ተወካይ ፍጹም ታማኝ መሆን ያለበት ሲሆን በወካዩ ጥቅምና በራሱ ጥቅም መካከል ግጭት ባለበት ጊዜ ለወካዩ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር አይችልም፡፡

የመ/ቁ. 14974

ሃምሌ 28 ቀን 1997 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ
ተጠሪ፡- 1. አቶ መንግሥቱ ኃብ
2. አቶ ዮሴፍ ገ/ሥላሴ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ብይን የተሰጠው በም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በአሁኑ ተጠሪዎች የአሁኗን አመልካች ጨምሮ ሶስት ሰዎች ላይ ክስ መስርተው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁኗ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 78 መሠረት ታመለክታለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካች አቤቱታ ለአሁኖቹ ተጠሪዎች እንዲደርሳቸው አድርጎ ተጠሪዎቹም በክርክሩ ወቅት ለአመልካቿ ወኪል መጥሪያ ደርሶ መልስ የሰጠች ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተቃውመዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ህዳር 17/1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 78 መሠረት አንድ ሰው ክርክሩ ውስጥ ገብቶ መከራከር የሚችለው በሌለበት እና ሳይከራከር ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ወይም ብይን ሲሰጥ ነው፡፡ አመልካች ግን በተወካይዋ በኩል መጥሪያ ደርሷት መልስ ሰጥታ የተከራከረች በመሆኑና ውክልናው የተነሳ ለመሆኑም የቀረበ ነገር ስለሌለ አቤቱታዋ ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ውሳኔ ስህተት የሌውም በማለት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት የዘጋው ሲሆን የዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡



የአሁኑ አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ብይን ላይ ሲሆን የአመልካችዋ ዋና ቅሬታም፣ 2ኛ ተጠሪ ራሱ ክስ አቅራቢ እራሱ መልስ ሰጪ ሆኖ ያቀረበው ክርክር ከህጉ መንፈስ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ለቀረበው አቤቱታ መልስ እንዲሰጡ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ከመዝገቡ የስር 2ኛ ከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ) የአመለካች (የስር 3ኛ ተከሳሽ) ወኪል በመሠረተው ክስም በአመልካች ስም መከላከያ መልስ መስጠቱን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አንድ ተወካይ በወካይ ላይ በመሠረተው ክስ በወካዩ ስም መልስ ሊያቀርብ ይችላል ወይ? አቅርቦስ ከሆነ ክርክሩ ወካዩ እንዳቀረበው ሊቆጠር ይችላል ወይ? የሚሉ ነጥቦች የህግ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

አንድ ባለጉዳይ ፍ/ቤት መቅረብ የማይፈቅድ ከሆነ ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ ለሚጠይቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ-ፈጅነት፣ በወኪልነት፣ በጠበቃነት ሊከራከር እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 57 ስር ተገልጿል፡፡ በመሆኑም አንድ ባለጉዳይ በሚከሰስበት ሆነ በሚከስበት ጉዳይ ፍ/ቤት መቅረብ ካልፈለገ ወይም ካልቻለ እሱን በመወከል እንዲከራከር ለሌላ ሰው ውክልና መስጠት የሚችል ሲሆን ይህም ውክልና የሚሰጠው ስለውክልና የሚመለከቱትን የፍ/ብ ሔር ህጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ወኪል የውክልናውን ስራ የሚፈጽምበት ጊዜ እነዚህን የህጉን ድንጋጌዎች በመከተል ይሆናል፡፡ ወኪሉም ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ክልል ሳይወጣ በህጉ መሠረት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ወካዩ ራሱ እንደሚፈጽማቸው ተደርገው ይቆጠራሉ (የፍ/ህ/ቁ 2189 (1))፡፡ በመሆኑም አንድ ወኪል ስለሌላው ሰው ሆኖ በፍ/ቤት ክርክር እንዲቀርብ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት የሚያቀርበው ክርክር ባለጉዳዩ እንዳቀረበው ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ ሲሆን አንድ ሰው ስለሌላ ሰው ሆኖ ክርክር እንዲያቀርብ የውክልና ስልጣን ተሰጥቶት እንኳን ቢሆን ወኪሉ ራሱ ወካዩን በከሰሰበት ጉዳይ ግን በወካዩ ስም ክርክር ሊያቀርብ ይችላል ወይ? የሚለው ነጥብ ውክልናን ከሚመለከቱት አጠቃላይ የህጉ ድንጋጌዎች እና ከህጉ አላማ ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ነው፡

ውክልና ማለት ተወካይ የሆነ ሰው ወካዩ ለሆነው ሌላ ሰው እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎች በወካዩ ስም ለማከናወን የሚገባበት ውል ነው፡፡ (ፍ/ህ/ቁ 2198)፡፡ በመሆኑም አንድ ተወካይ የውክልና ስራ በሚፈጽምበት ጊዜ የወካዩን ህጋዊ ሁኔታዎችን የመለወጥ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይሕም በመሆኑ ተወካዩ ለወካዩ ፍጹም ታማኝ የመሆን እና የወካዩን ጥቅም ሙሉ ለሙሉ የማስጠበቅ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ስለሆነም ተወካዩ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባው የወካዩን ጥቅም ብቻ በመሆኑ የጥቅም ግጭት ባለበት ሁኔታ ተወካዩ በስራው አፈጻጸም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የጥቅም ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ አንድ ተወካይ ከራሱ ጥቅም ይልቅ የወካዩን ጥቅም ሊያስቀድም ይችላል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህም ተወካዩ የራሱን ጥቅም የሚመለከት ጉዳይ ሲያጋጥመው ሁኔታውን ለወካዩ ሳያሳውቅና ወካዩ ሳይስማማ ስራውን እንዳይፈጽም ይከላከላል፡፡ ስለወኪልነት የተደነገጉትን የፍ/ብሔር ድንጋጌዎች ስንመለከትም ተወካዩ ከወካዩ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ጥብቅ የሆነ ቅን ልቦና ሊኖረው እንደሚገባ እና የውክልና ስልጣኑን የሚያስቀሩ ምክንያቶች እንዳለበት (የፍ/ብ/ህ/ቁ 2208)፣ ተወካዩ ስራውን የሚፈጽመው በተለይ ለወካዩ ጥቅም ሊሰጥ የሚችል መንገድ ብቻ መሆን እንዳለበት (ፍ/ብ/ህ/ቁ 2209(1))፣ እንዲሁም ተወካዩ በራሱ ስም ከወካዩ ጋር የሚያደርገው ውል ወካዩ ካላጸደቀው በቀር ሊፈርስ እንደሚችል (የፍ/ህ/ቁ 2188) መደንገጋቸው ተወካዩ ለወካዩ ፍጹም ታማኝ መሆን እንዳለበት እና ለወካዩ ጥቅም ብቻ መስራት እንዳለበት፣ የጥቅም ግጭት ባለበት ጊዜ ሁሉ ሁኔታውን ለወካዩ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ተወካይ የጥቅም ግጭት ባለበት ጊዜ ለወካዩ ሳያሳውቅ የሚየከናውነውን ስራ ወካዩ ሊቃወመው የሚችል መሆኑን እና በዚህ ሁኔታ የተከናወነው ስራም ወካዩ ካላፀደቀው በቀር ወካዩ ራሱ እንደፈጸመው ሊቆጠር እንደማይገባ ከውክልና ግንኙነት አጠቃላይ ዓላማ እና ከፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በአመልካች (በስር 3ኛ ተከሳሽ) ላይ የመሰረተው ክስ በወኪሉ እና በተወካዩ መሃከል ግልጽ የጥቅም ግጭት ፈጥሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ራሱ ከሳሽ ሆኖ የቀረበበትን ጉዳይ ለአመልካች የገለፀላት መሆኑ እና አመልካቿም ተጠሪው የቀረበውን መልስ የተስማማችበት



ለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ አመልካቿ እንዲያውም ወኪሏ የሰጠውን መልስ ተቃውማዋለች፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ራሱ በመሠረተው ክስ ለአመልካች ሳያሳውቅ ያቀረበው መከላከያ መልስ ስለወኪልነት የተመለከቱትን መርሆች እና የህጉን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ አመልካች በወኪሏ በኩል ክርክር አቅርባለች ማለት አይቻልም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች በወኪሏ በኩል መልስ ሰጥታ የተከራከረች በመሆኑ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ልትጠይቅ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ብይን የህግ ስህተት አለበት፡፡

**ውሳኔ**

- አመልካች በሌለችበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ገብታ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የመሰለውን ይወስን፡፡
- የም/ሸ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ-13/95 በ17/3/95 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 464/95 በ20/6/95 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ፍ/ቤት በመ/ቁ 532/95 በ3/5/96 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 14184

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ውርጌሳ ታደሰ

መልስ ሰጪ፡- አቶ መለሰ ተካ — አቶ ፍሬሰንበት አዝማች
አቶ በቀለ ዴልኬራ — አቶ አለሙ ደልሊቦ
አቶ ከተማ ኢብሣ — አቶ ወ/ሰማያት ዲማ
አቶ ፍቃዱ ራህመቶ — አቶ አማረ ተሰማ
አቶ ኤፌሶን መጋቢ

*በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት በሙግት ተወካይ ለመሆን ስለ ባለጉዳዩ /ከሳሽ/ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ መቅረብ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር ቁጥሮች 73*

አመልካች ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ዕለት በችሎቱ ባለመገኘታቸው ምክንያት ያቀረቡትን ክስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትሐብሐር ሥነ/ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሠረት በመዝጋቱ እና ይህንኑ ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በአብላጫ ድምጽ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጣቸው ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡

1. ክስ ያቀረበ ሰው ክሱ የሚዘጋበት ክርክሩን እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. ከተከሣሹ መልስ ለመቀበል የሚያዝ ቀጠሮ ተከሣሹ እንጂ ሕጉ እንደሚያዘው ጉዳዮ የሚሰማበት ቀጠሮ አይደለም
3. መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሳሽ ባይቀርብ ፍ/ቤቱ የተከሳሹን መልስ ተቀብሎ ጉዳዮን ለተከታዩ ክንውን ማዘጋጀት እንጅ ክሱን መዝጋት የለበትም፡፡



ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም
የመ/ቁ. 14184

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ውርጌሳ ታደሰ ጠበቃ ህይሉ አግዘው

መልስ ሰጪ፡- አቶ መለሰ ተካ — አቶ ፍሬሰንበት አዝማች
አቶ በቀለ ዴልኬራ — አቶ አለሙ ደልሊቦ
አቶ ከተማ ኢብሣ — አቶ ወ/ሰማያት ዲማ
አቶ ፍቃዱ ራህመቶ — አቶ አማረ ተሰማ
አቶ ኤፌሶን መጋቢ
} ሁሉም አልቀረቡም

### ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የህግ ነጥብ አንድ ጉዳይ በይግባኝ ፍ/ቤት በሚታይበት ወቅት ከተከራካሪዎቹ የአንዱ መቅረት የሚያስከትለው በሕጉ የተደነገገ ውጤት ምንድነው? የሚል ነው፡፡ ለዚሁ የሕግ ነጥብ መነሣት ምክንያት የሆነው ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ዕለት በችሎት ባለመገኘታቸው ምክንያት አመልካቾችን በሚመለከት ቀርቦ የነበረውን ይግባኝ በፍትሀብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.73 መሠረት በመዝጋቱ ነው፡፡ አመልካች መዝገቡ ተመልሶ እንዲከፈት ጥያቄ ቢያቀርብም ለባለጉዳዩ መቅረትም ሆነ ለጠበቃው መቅረት የቀረበው ምክንያት በቂ ስላልሆነ የተዘጋው ይግባኝ አይከፈትም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፣ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበ ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡

አመልካች ጠበቃ የሰበር አቤቱታ በመቅረቡና ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ መልስ ሰጪ እንዲቀርቡ ታዞ በጉዳዩ መልስ ቀርቦአል፡፡ የመልስ መልስም እንደዚሁ ቀርቦ ከማኅደሩ ጋር ተያይዞአል፡፡

የሰበር ችሎት በዚሁ የቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻነት መታየት ያለበት ትልቁ የሕግ ትርጉም አንድ ፍርድ ቤት በይግባኝ ደረጃ ይግባኝ ባይ አልቀረበም በማለት የይግባኝ መዝገቡን ለመዝጋት የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፍትሐብሔር የሙግት ሂደት የሚመራው በፍትሀብሔር ሥነ

ሥርዓት ሕግ ጥያቄ መመለስ የሚኖርበት ሕጉ የሚያስቀምጠው ሥርዓት መሠረት ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ የአንዱ ወይም የሌላው ተከራካሪ ፍርድ ቤት በያዘው ቀነ ቀጠሮ አለመገኘት የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብም መሠረታዊ ከሆነ ከመክሰስ መብትና ክስ ከመከላከል መብት ጋር እጅጉን የተያያዘ በመሆኑ መስተናገድ የሚኖረበት ሕጉ የሚያስቀምጠው መስፈርት መሠረት ብቻ መሆን የኖረበታል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በከፊል ውድቅ የደረገው የፍትሀብሔር ሥነ ሥርሀት ሕጉን ቁጥር 73 በመጥቀስ ስለሆነ የትዕዛዙን ትክክል መሆን አለመሆ ለመመርመር በዚህ ቁጥር የሰፈረው ድንጋጌ ስለተከራካሪዎች መቅረብና አለመቅረብ የሚደነግጉትን ተዛማጅ ቁጥሮች መመልከት ያስፈልጋል፣ በቁጥር 73 የሰፈረው ድንጋጌ

> ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንሲማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሣሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበት ቢሆን የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ ከሣሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል፡፡

በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው ክስ ያቀረበ ሰው ክሱ የሚዘጋበት የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ሳይሆን ክርክሩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረቡ እንደሆነ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በመሠረቱ ማንም ሰው ክስ ሊያጣ ወይም በከፊል ሊቀርበት የሚገባው ሕግ በግልጽ ለይቶ ባሰፈረው ምክንያት ብቻ ነው፡፡ አንድን ጉዳይ ለማየት የተሰየመ ፍ/ቤት የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለመፈፀም በርካታ ቀጠሮዎች እንደሚሰጥ የታወቀ ነው፡፡ ክስ ያቀረበ ሰው በሁሉም ቀጠሮዎች እንዲገኝ የሚጠበቅበት ቢሆንም በተያዘው ቀጠሮ ባለመገኘቱ ምክንያት ያቀረበው ክስ ሊዘጋበት የሚችለው ግን ሕጉ ለይቶና ዘርዝሮ ባስቀመጣቸው ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ብቻ ነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች በቅጡ ለመንዘብ የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን የከሣሽና/ወይም የተከሣሽ አለመቅረብ (non appearance of parties) አስመልክቶ ያስቀመጠውን ሥርዓት ከአጠቃላይ የሙግት ሂደት ጋር አገናዝቦ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡



ከላይ እንደተጠቀሰው በዚህ መዝገብ የሕግ ትርጉም የሚሻው ትልቁ ጥያቄ አንድ ከሣሽ ወይም ይግባኝ ባይ በቀነ ቀጠሮ አልቀረብክም ተብሎ ክሱ /ይግባኙ/ የሚዘጋበት መቼ ነው? የሚለው ነው፡፡ ከሕጉ ቁጥሮች 69፣70፣73 ለመገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ በተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ ምክንያት አንድ መዝገብ እንዲዘጋ ወይም ተከሣሹ በሌለበት የነገሩ መሰማት እንዲቀጥል ትዕዛዝ የሚሰጠው ከሣሽ ወይም ተከሣሹ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረው ቀን ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ነው፡፡ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የሚሉትን በቅደም ተከተል እንመልከት፡፡

69(1) ነገሩን ለማየት ፍርድ ቤቱ በወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ተከሣሾች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡ የተከራካሪ ወገኖች መቅረብ እንደተረጋገጠም ክርክሩ መሰማት ይጀምራል፡፡

70 የተከሣሽ ያለመቅረብ
<u>ክርክሩ እንዲሰማ</u> በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ቀርቦ ተከሣሹ ያልቀረበ እንደሆነ ለጉዳዩ ውሣኔ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሥርዓት ነው፡፡

73 ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሣሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበትም ቢሆን ፍርድ ቤቱ ተከሣሹ በሙሉ ወይም በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ ተከሣሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል፡፡

አንድን ጉዳይ አይቶ ውሣኔ ለመወሰን በርካታ ቀጠሮዎችን ፍርድ ቤት እንደሚሰጥ የሚታወቅ ሲሆን ከነዚህ በርካታ ቀጠሮዎች መካከል በአንዱ ወይም በሌላኛው ወይም በሁለቱም አለመቅረብ ምክንያት ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የባለጉዳዮቹ መቅረት የተከሰተው ጉዳይ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ለመስማት ቀጠሮ የተያዘበት ቀን ከሌሎች ቀጠሮዎች በተለየ ሁኔታ እንዲታይ ሕግ አውጪው መፈለጉ ግልጽ ነው፡፡ በተለምዶ ብዙ ፍርድ ቤቶች መልስ ለመቀበል ከሣሽ ወይም ተከሣሽ ወምይ ሁለቱም ያልቀረቡ እንደሆነ ፍርድ ቤቶቹ እነዚህን ድንጋጌዎች

በመጥቀስ ጉዳዩ እንዲዘጋ ወይም ተከሣሹ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የሚሰጡ ቢሆንም የድንጋጌዎቹ ይዘት ይህን አሠራር የሚደግፍ አይደለም፡፡ መልስ ለመቀበል የሚያዝ ቀጠሮ ተከሣሹ የጽሁፍ መልሱን ለማቅረብ እንዲችል የሚያዝ ቀጠሮ እንጂ ሕጉ እንደሚያዘው ጉዳዩ የሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ሳይቀርብ ቢቀር ጉዳዩ ለማሰማት በተቀጠረበት ቀን ሳይቀርብ ቀረ ተብሎ መዝገቡ ሊዘጋበት የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ በመሠረቱ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ የሚያዘው በአንድ ጉዳይ ክስ የተመሠረተበት ሰው በጉዳዩ ላይ የቀረበበትን ክስ ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ ሃሣቡን በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማስረጃም ካለው የማሰረጃውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከከሣሹ የሚጠበቅ ክንዋኔ የለም፡፡ ከሣሹ ሳይቀርብ ቀረ እንኳን ቢባል በፍርድ ቤቱ የሥራ ሂደት ላይ የሚያስከትለው መስተጓጐል ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ባይቀርብ የተከሣሹን መልስ ተቀብሎ ለተከታዩ ክንውን ጉዳዩን ከማዘጋጀት አልፎ መዝገቡን ለመርዝጋት በቂ ምክንያት የለም፣ የመዝገብ መዘጋትን ያህል ትልቅ እርምጃ በአንድ ተከሣሽ ላይ ለመውሰድ ቢያንስ በከሣሹ በኩል መፈፀም የነበረበት ነገር ግን ሳይፈፀም የቀረ በህግ የተደገፈ በቂ ምክንያት መኖር አለበት፡፡ የተከሣሽን የጽሁፍ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ መዝገቡ እንደሚዘጋ የሚገልጽ ድንጋጌ በሥነ ሥርዓት ህጋችን የትኛውም ክፍል አይገኝም፡፡ የህግ ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ የአንድን ተከሣሽ ክስ መዘጋት ደግሞ አግባብ አይሆንም ተከሣሹ ባለመቅረቡ ምክንያት ክሱ እንዲዘጋ ህጉ የሚያዘው ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ከሣሹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኑው፡፡ ከሕጉ አደረጃጀትም መገንዘበ እንደሚቻለው ክሱ የሚሰማው የክስና የመከላከያ ጽሁፎች (ከቁጥር 222-240 የፍትብሔር ሥነሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት) ልውውጥ ከተከናወነ በኋላ ነው፡፡ የጽሁፉን ልውውጥ የሚመለከተው የሕጉ ክፍል "ስለክስና ስለመከላከያ ጽሁፍ" በሚል ርዕስ ራሱን የቻለ አንድ ክፍል ሲሆን በዚህ የጽሁፍ ልውውጥ በኋላ የሚከተለው ክንውን ደግሞ "ክስን ስለመስማት" በሚል ርዕስ ራሱን በቻለ ሌላ ምዕራፍ የምናገኘው ነው፡፡ (241-273) ከዚህ የህጉ አደረጃጀት የጽሁፍ መልስ የሚቀርብበት ቀነ ቀጠሮ በመርህ ደረጃ የክሱ



መሰማት ከሚከናወንበት ቀነ ቀጠሮ የተለየ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ከህጉ አደረጃጀት ባሻገር የክስ መሰማትን የሚመለከተው የሙግት ሂደት በሁለት የተከፈለ ሲሆን ሁለቱም የከሣሽና የተከሣሽን መገኘት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ የከሣሽና የተከሣሽን መገኘት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ ሊከፈት የሚፈፀመውን ሥነ ሥርዓት (First hearing) ለአብነት መመልከት ይቻላል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 24(1) መሠረት ክሱ መሰማት በሚጀምርበት ቀን ፍርድ ቤቱ የባለጉዳዮቹን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ ክሱንና መልሱን እንደሚያነብና ተከሣሹ መልሱ ላይ የካደውን ነገር ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ በቃል እንደሚጠይቀው ይገልጻል፡፡ የዚሁ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ወይም ስለሱ ሆኖ የቀረበውን ሰው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ጉዳዮች ወይም ሌሎች ነገሮች አብራርቶ ለማስረዳት ጠቃሚና ተገቢ መስሎ በገመተው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ፍርድ ቤቱ ሊመረምራቸው እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከሣሽ ወይም ተከሣሹ እንዲብራራለት የሚፈልገው ጉዳይ ካለ በፍርድ ቤቱ በኩል እንዲጠየቅለት ማድረግ እንደሚችልም በዚሁ ድንጋጌ ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

ይህ የሚያስገነዝበው የመሰማት ሂደት የከሣሽና የተከሣሽ መገኘት የግድ የሚል ተሟጋቾቹም ጭምር የሚሣተፉበት ሂደት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሂደት ፍርድ ቤቱ ባለጉዳዩችንም ጭምር በማነጋገር ጉዳዩን ለዋናው የሙግት ደረጃ የሚያዘጋጅበት በመሆኑ በከሣሹና የተከሣሹ (ወይም የወኪሎቻቸው) መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከሁለቱ የአንዱ አለመገኘት ለሂደቱ መስተጓጐል የሚኖረው ተጽእኖም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ከሌሎች ቀጠሮዎች ይበልጥ ባለጉዳዩች ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ባይቀርቡ የሚከተለው ውጤት ከሌላው የበለጠ ጠንካራ መሆኑ አስፈለጊ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ 2 (ከቁጥር 241 - 273) ያሉት ሁሉም ድንጋጌዎች የተሟጋቾች አለመገኘት የሚያስከትለውን ውጤት ከመሰማት ሂደት ጋር አያይዘው የሚያቀርቡትም በከፊል በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ለማንኛውም የመሰማት ቀነ ቀጠሮ የተከሣሽን የጽሁፍ መልስ ለመቀበል የሚሰጠው ቀነ ቀጠሮ የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም ክርክሩ የሚሰማበት ወቅት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የተደነገጉትን ደንቦች የተለየ ባህርይና ዓላማ ባለው መልስ የመቀበል ቀነ ቀጠሮ ተፈጻሚ ማድረግ አግባብነት የለውም፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ

ቁጥሮች 69፣70 እና 73 ሥር ያሉት ድንጋጌዎች ለመልስ በተቀጠረበት ቀን ተፈጻሚ ካልሆኑ ከሣሹ ወይም ተከሣሹ ወይም ሁለቱም ሳይቀርቡ የቀረ እንደሆነ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የትኞቹ ናቸው የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 67፣70፣73 እና ሌሎች ተዛማጅ ድንጋጌዎች ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ ለመሰማት (hearing) በተቀጠረበት ቀን ያልቀረቡ እንደሆነ ብቻ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ (እንደነገሩ ሁኔታ ይግባኝ ባይ) ወይም ተከሣሹ (የይግባኝ መልስ ሰጪ) ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሚሆን ሌላ የህግ ድጋፍ መኖር ይኖርበታል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ከ192 እስከ 199 ባሉት ቁጥሮች ፍርድ ቤት እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ሳይፈፀሙ ሲቀሩ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች የተለያዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በቁጥር 199 ሥር ያለው ድንጋጌ አሁን ለያዝነው ጉዳይ በተለይ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ቁጥር 199(1) ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በዚያው ቀን ቀጠሮ የመሰለውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር (2) ደግሞ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ወገኖች ጉድለት ያልሆነ እንደሆነ ግን ፍርድ ቤቱ ሌላ ቀጠሮ ይሰጣል ይላል፡፡

አንድ ጉዳይ የተከሣሽን መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ያልቀረቡ እንደሆነ (እንደነገሩ ሁነታ ይግባኝ ባይ ወይም መልስ ሰጪ) ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የሚገባቸው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ ከድንጋጌው ንኡስ አንቀጽ አንድ ለማየት እንደሚቻለው ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም በቀረ ቁጥር መዝገብ የሚዘጋበት ሁኔታ እንደሌለ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ትዕዛዝ የሚሰጠው አንድ ጉዳይ እንዲፈጽም የታዘዘው ወገን ያን የታዘዘውን ጉዳይ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ ይህን ክንውን ሳይፈጽም ቢቀር ፍርድ ቤቱ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመሰለውን ይወስናል፡፡ ከሣሹ ከመልስ በተቀጠረበት ቀን ባይቀርብ ግን ከሣሹ እንዲፈጽመው የታነዘዘው ነገር ስለሌለ ቀጣዩን ክንውን አስመልክቶ ትዕዛዝ ከመስጠት ውጪ የከሣሹን መዝገብ መዝጋት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የተከሣሹን የጽሁፍ መልስ ከማህደሩ ጋር አያይዞ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን ቀጠሮ ወስኖ ለዚሁ አስፈላጊ ትዕዛዞችን መስጠት አለበት እንጂ መዝገቡን መዝጋት የለበትም፡፡ ከላይ ተደጋግሞ እንደተገለፀው መዝገብ የሚዘጋው ከሣሹ ጉዳዩን ለመስማት በፍርድ ቤት ቀጠሮ በተያዘበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡

የተከራካሪዎች መቅረብን አስመልክቶ በሰፊው ማየት የስፈለግን በያዝነው ጉዳይ ከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ባይን መዝገብ የዘጋው መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ይግባኝ ባዩ አልቀረበም በማለት የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.73ን በመጥቀሱ ነው፡፡ ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የአሁኑ አመልካች ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የቀረውን ጉዳዩን ለማሰማት በተያዘ ቀጠሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ለመዝጋት ምክንያት አድርጐ የጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የሰጠውን ትዕዛዝ ፈጽሞ የሚደግፍ አይደለም፡፡ መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ከይግባኝ ባይ የሚጠበቅ ክንውን ስላልነበረም ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን መልስ ተቀብሎ ቀጣዩን ቀጠሮ (ክንውን) በማስመልከት ትዕዛዝ ከሚሰጥ በስተቀር በተከሣሹ ላይ የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 199ን መሠረት በማድረግ የሚሰጠው ትዕዛዝ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ የዘጋው እንዲፈጽም ትዕዛዝ ተሰጥቶት ሳይፈጽመው የቀረ ክንውን ሳይኖርና መዝገብ እንዲዘጋ ሕግ ያስቀመጠውን ሥርዓት ሳይከተል በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡ መዝገቡን መልሶ ላለመክፈት የሰጠው ምክንያት ስህተት ባይሆንም ፍርድ ቤት የሠራውንና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስተካከል ሲገባው ያለፈውን ግድፈት በሥ.ሥ.ሕ.ቁ 207 እና 211(2) መሠረት ማቀናት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቷል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

(1) ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ.04000 ጥር 21 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.11523 ጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
(2) ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ እንዲከፈት አድርጐ ካቆመበት እንዲቀጥል ታዟል፡፡
(3) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 14047

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡-- ዶ/ር ዳንኤል አለሙ

መልስ ሰጪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሮማነወርቅ የማነብርሃን

2. ወ/ሮ በቀለች ወረደ

3. ወ/ሮ ምስለአበባ ውቤ

*ውል - የግዴታ ዎች መቅረት - ሰለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ-ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህልና ግምቶች - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1856፣2024*

አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 1981 ዓ.ም ከመ/ሰጭዎች ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውል መሠረት ለሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ብር 46000(አርባ ስድስት ሺ.ህ) እንዲከፈላቸው በ1988 ዓ.ም ያቀረቡትን ክስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱ ክፍያው መጠየቅ ከነበረበት ጊዜ ሁለት ዓመት በኂላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024(ለ) መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ ስላደረውና ውሣኔውን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስላጸና የቀረበ አቤቱታ፣

ውሣኔ፡- የሰበር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ጸንቷል፡፡

1. በፍብ/ሕ/ቁ 2024 በተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያልሆነ ወገን (ከሣሽ) ክፍያው እንዳልተፈጸመ የማስረዳት ሽክም ያለበት ሲሆን ይኸን ሽክሙን መወጣት የሚችለው መሃላ በማውረድ ብቻ ነው፡፡
2. የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡





ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፣- ዶ/ር ዳንኤል አለሙ

መልስ ሰሰጪዎች፡-1ኛ. ወ/ሮ ሮማነወርቅ የማነብርሃን በክርክሩ አልቀረቡም
2ኛ. ወ/ሮ በቀለች ወረደ
3ኛ. ወ/ሮ ምስለአበባ ውቤ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሣኔ

አመልካች ለሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የሰጠው አመልካች መልስ ሰጭዎች በፍርድ ቤት ያላቸውን የተለያዩ ጉዳዮች በተለየዩ መዝገቦች እነሱን ወክዬ እንድከራከር ወክለውኛል፣ የጥብቅና ውሉም ታህሳስ 1 ቀን 1981 ተፈርሟል፣ በውሉ መሠረት ለፈፀምኩት የጥብቅና አገልግሎት በአጠቃላይ ብር 46.000 (አርባ ስድስት ሺ.ህ) ይከፈለኝ በማለት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ መልስ ሰጭዎች ለክሱ በሰጡት መልስ ውሉ የተፈፀመው በ1981 ሲሆን ክሱ ግን የቀረበው በ1988 ነው፣ ይሄውም የተጠቀሰውን ክፍያ ሳንጠየቅ ሁለት ዓመት ያለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024(ለ) መሠረት ክፍያው እንደተፈፀመ ይቆጠራል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ሌሎች ክርክሮችንም አንስተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም መልስ ሰጭዎች ክፍያውን በጽሁፍ አላመኑም፣ ክሱ ከሁለት አመት ገደቡ በኂላ በመቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) መሠረት የህሊና ግምት እንዳይወሰድ መልስ ሰጭዎች የመሃላ ቃል እንዲሰጡ አልጠየቁም በመሆኑም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) መሠረት ክፍያው መፈፀሙን የህሊና ግምት ወስዷል፡፡ በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል አመልካች የጥብቅና አገልግሎት የሰጠሁት በተለያዩ መዝገቦች ሲሆን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄውም እንደየችሎቱ የክርክር ሂደት ጉዳዮች ተጠቃለለው ውሣኔ ሲያገኙ መቅረብ የሚገባው በመሆኑ ጥያቄው በዚሁ መሠረት ቀርቧል፡፡ መልስ ሰጭዎች የጥብቅና ውሉ መፈፀሙን አልካዱም፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ሊፈርስ የሚችል የህሊና ግምት የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2025 እና ተከታታዮቹ የሕሊና ግምቱ እንዳይወሰድ (ለማፍረስ) ያቀረብኩትን ክርክር ፍ/ቤቱ ሊመለከትልኝ ይገባ ነበር፣ ስለሆነም የሰበር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለፈፀመበት እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ባለመቅረባቸው ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል የቀረበውን ማመልከቻ ብቻ መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡፡

በቀረበው ጉዳይ በሰበር መታየት ያለበት ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2024 የሰፈረውን የሕሊና ግምት አመልካች በመሠረተው ክስ ተፈፃሚ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ1981 ዓ.ም ከመልስ ሰጪዎች ጋር በመሰረትነው የጥብቅና ውል መነሻነት ላበረከትኩት አገልግሎብ ብር 46.000 (አርባ ስድስት ሺህ) ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡ ከክሱ ይዘት ለመመልከት እንደሚቻለው አመልካች ከመልስ ሰሊዎች የሚፈልጉት ክፍያ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት መልስ ሰጪዎች ከውሉ የሚመነጨውን የክፍያ ግዴታቸውን አልተወጡም በሚል ነው፡፡ የጥብቅና አበል መከፈል አለመከፈሉ አከራካሪ በሆነ ጊዜ የማስረዳት ሸክሙ የማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 (ለ) ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን የጥብቅና ክፍያ በሚመለከት የሕሊና ግምት በማስቀመጥ በውል የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን እንደከፈለ ይቆጠራል በማለት የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩልም በሕጉ 2026(1) ይህን የሕሊና ግምት ማፍረስ እንደማይቻልና የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ አልተከፈለኝም የሚል ወገን ያለው ብቸኛ ግምቱን የማፍረሻ አማራጭ መሃላ እንዲወርድለት መጠየቅ ብቻ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡

በዚህ መሠረት መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ወይም ክፍያውን ያልጠየቀ ተዋዋይ በውሉ መሠረት የሚገባውን ክፍያ እንዳገኘ የሚገመትበት ብቻ ሳይሆን ክፍያው እንዳልተከፈለው የሚያስረዳው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትም ሌላ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ከሚከተለው ሥርዓት የተለየ ይሆናል፡፡ በመደበኛ የሙግት ሂደት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን እንዲያስረዳ የሚጠበቅበትን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ብዙም የሕግ ገደብ የለበትም፡፡ ፍሬ ነገሩን ያስረዳልኛል የሚለውን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ ይችላል፡፡ የጽሁፍ፣ የሰው ወይም የአካባቢ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክሙን ሊወጣ ይችላል፡፡ በፍትሐብሄር ሕጉ 2024 የሚሸፈን ፍሬ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ ግን የማስረዳት ሸክሙ ከአንዱ ወገን (ከተከሣሽ) ወደ ሌላው (ወደከሣሽ) ከመዛወሩ በተጨማሪ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት የሚቻልበት የማስረጃ አይነትም ውሱን ነው፡፡ በ2026 መሠረት



የማስረዳት ሸክም የተሸጋገረበት ከሣሽ ይህን የማሰረዳት ሸክሙን መወጣት የሚችለው መሃላ በማውረድ ብቻ ነው፡፡ ሌላ የትኛውም ዓይነት ማስረጃ ቢሆን የሕሊናውን ግምት ሊያፈርሰው አይችልም፡፡

በዚህ ህግ የሰፈረው የህሊና ግምት ከይርጋ ሕግ ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ በ2024 የሰፈረው የሕሊና ግምት የማስረዳት ሸክም ከተከሣሽ ወደከሣሽ ያዞራል፣ የማስረዳት ሸክም የዞረበት ከሣሽ የሚያስረዳበትን መንገድ ይደነግጋል፡፡ በሆኑም በጊዜ ማለፍ ምክንያት ክሱ እንዲቋረጥ አያደርግም፡፡ የይርጋ ሕግ በሌላ በኩል በጊዜ ማለፍ ምክንያት የመከሰስ መብትን ስለሚያስቀር ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን ማነው? የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል አልተወጣም? ወዘተ- -ጥያቄዎችን በማንሣት ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር ሊገባ አይችልም፡፡ በመሆኑም የይርጋው ጊዜ በፍ.ብ.ሕ ቁ.1845 መሠረት 10 ዓመት የሆነ ጉዳይ በዚሁ ሕግ 2024 በተደነገገው የሕሊና ግምት መሠረት ሊስተናገድ ይችላል፡፡ የይርጋ ጊዜው ያላለፈን ጉዳይ በሕጉ ቁጥር 2024 መሠረት እንደተከፈለ መቁጠር እርስ በርሱ የሚጋጭ ነገር ማከናወን አይደለም፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላቀረበው ክስ ምክንያት የሆነው ውል የተመሠረተው በ1981 ዓ.ም መሆኑን ግራ ቀኙ ተስማምተውበታል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሣሾች የሕጉ ግምት ተጠቃሚዎች ናቸው ያለው የተጠየቀው ክፍያ በ1981 ዓ.ም መከፈል የነበረበት ነው በማለት ነው፡፡ ለዚሁ መነሻ ያደረገው ተጨማሪ ፍሬ ነገር አመልካች ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ መከፈል ነበረበት በተባለው መጠን ላይ ወለድ መጠየቁ ነው፡፡ አመልካች በሌላ በኩል ክፍያው መከፈል የነበረበት ጊዜ ውሉ የተፈፀመበት 1981 ዓ.ም ሳይሆን ጉዳዩ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የሚታይ በመሆኑ ውሣኔ የተሰጠበት ጊዜ መሆን ነበረበት ብሏል፡፡ ሆኖም ውሣኔ የተሰጠው መቼ እንደሆነ ለሰበር አቤቱታ ባቀረበው ማመልከቻ ላይ አልገለፀም፡፡ ሕጉ ከሚያዘው ከ2 ዓመት በታች መሆኑን ለማሣየት ክሱ ከቀረበበት ከ1988 ዓ.ም በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተወሰነ መሆኑን ማስረዳት ሲኖርበት በዚህ ረገድ የቀረበ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ውሉ የተፈረመበትና በከሣሽ መከፈል ከነበረበት ተብሎ ለወለድ ስሌት መሠረት የሆነውን 1981 ዓ.ም መነሻ መደረጉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ክሱ በ1988 ዓ.ም የቀረበ እንደመሆኑ ተከሣሾቹ የፍ.ብ.ሕ.ቁ 2024(ለ) “ለጠበቆች፣ ለውል አዋዋዮች ለሌሎችም የሕግ አማካሪዎች በሙያ ሥራቸው ወይም በሹመት ሥራቸው ላደረጉት

አገልግሎት የሚከፈል ዕዳ" ዕዳው መከፈል ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ናቸው መባሉ በአግባቡ ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሕግን ግምት ተፈጻሚ ከማድረግ አልፎ አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚል ውሣኔ ባለመስጠቱ እንደአመልካች አባባል በፍ.ብ.ሕ.ቁ 1845 የሰፈረውን የይርጋ ሕግ አለቦታው ተጠቅሞበታል ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ በፍ.ብ.ሕ. 2024(ለ)ን መሠረት አድርጐ ውድቅ ማድረጉም ሆነ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 337 መሠረት ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስሀተት መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡

መልስ ሰጪዎች የሕግ ግምት ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ፣ የውሉን መኖሩን አለመካዳቸው፣ በውሉ መሠረት ለመክፈል መስማማታቸውና ማመናቸው፣ ውሉ ፈርሷል ብለው አለመከራከራቸው ወዘተ… የሙግቱን ውጤት የሚቀይረው አይደለም፡፡ ውሉ አለ እንኳን ቢባል ዞሮ ዞሮ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን እንደተከፈለ መቆጠሩ የሚቀር አይደለም፡፡ ይህ ሊቀር የሚችለው መሃላ እንዲወርድ ተጠይቆ እንደሆነና መሃላው የከሣሽን ክስ ያረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑ ከሰበር ማመልከቻውም ሆነ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገቡ የተገነዘብነው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

## ውሣኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመቁ.5095 የካቲት 11 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡



## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 15835

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካቶች፡- ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ
መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ

በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን

- ስለ ባለ ጉደዩ ፍ/ቤት ሣይቀርብ መቅረት - የተከሣሽ ያለመቅረብ- ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረ ዕለት የተከሣሽ መልስ አለማቅረብ- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥሮች 70፣233

የአሁኑ መልስ ሰጪ በከፍተኛው ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሠረቱት ክስ የአሁን አመልካችን መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ቀርቦ መልስ ባለማቅረቡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ከሰጠ በኂላ መ/ሰጭ ክሱን በማሻሻላቸው የተሻሻለው ክስ እንደ አዲስ ክስ መቆር ስላለበት መልስ ልስጥበት በማለት አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ ስላደረገውና ይህንኑ ትእዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ስላጸናው የቀረበ አቤቱታ፣

<u>ው ሣ ኔ ፡-</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጧቸው ትእዛዞች ተሽረዋል፡፡

1. ተከሣሽ ከክሱ አስወጥቶ /Ex-parte/ ጉዳዩ መታየቱ የሚቀጥለው ተከሣሹ ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ችሎት ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. ጉዳዩ የተከሣሽን መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ተከሣሽ ያልቀረበ እንደሆነ መልሱን በጽሁፍ ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀረቡታል እንጂ በቀጣዩ ሂደት ከመሳተፍ አይከለከልም፡፡



ሐምሌ 29 ቀን 1997

የመ/ቁ 15835

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካቶች፡- ሼል ኢትዮጵያ አክስዮን ማህበር

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መሠረት ለቀረበው ክርክር መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የጠቅላይ ፍ/ቤት የተቀበለው ትዕዛዝ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩ በሰበር መታየት ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ መልስ ሰጪም ቀርቦ በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ ክርክሩን አቅርቦአል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሣሽ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠቱን አውቆ ለተሻሻለው ክስ መልስ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 73 መሠረት ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የተወሰነ መሆኑን በመግለጽ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረጉ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የጣሰ አሠራር ነው በማለት በሰበር እንዲስተካከልለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች ዋና ክርክር የተሻሻለው ክስ እንደ አዲስ ክስ መቆጠር ስላለበት ቀደም ብሎ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ የተወሰነ ቢሆንም ለተሻሻለው ክስ መልስ የመስጠት መብቱ ሊቀርበት አይገባም የሚል ነው፡፡ መልስ ሰጪ በዚህ ጉዳይ ላይ መልሱን በጽሁፍ በማቅረብ የክሱ መሻሻል ቀደም ሲል የተሰጡትን ትእዛዞች የሚሽር ባለመሆኑ አመልካች ለተሻሻለው ክስ መልስ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ በሁለቱም ፍቤቶች ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት መኖሩን አያሳይም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካች መልስ ለማቅረብ በተቀጠረበት ቀን መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ መታዘዙን

ተገንዝቧል፣ በተሻሻለው ክስ መልስ ሊያቀርብ አይገባም የሚል ትእዛዝ የተሰጠውም ቀደም ብሎ የተሰጠውን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ተረድቷል፡፡ በዚህም መሠት ጉዳዩን በአግባቡ ለማስተናገድ የአሁኑ አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ዕለት መለሱን ይዞ ባለመቅረቡ የሚከተለው ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለውንና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ነጥቦች መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

አንድ ተከሣሽ ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረበት ዕለት መልሱን ይዞ ካልቀረበ ክርክሩ በሌለበት የሚሰማ መሆኑ ፍርድ ቤቱ በሚልክለት መጥሪያ ላይ እንደሚገልጽለት በፍሥ.ሥ.ሕ.ቁ 233 ላይ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቀ 70 ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ቀርቦ ተከሣሽ ያልቀረበ እንደሆነ ተከሣሹ ያልቀረበው የተላከለት መጥሪያ ደርሶት ከሆነ ተከሣሹ በሌለበት የነገሩ መሰማት እንደሚቀጥል ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ሁለት በተለያዩ ጊዜ የሚከናወኑ የሙግት ደረጃዎችን የሚመለከቱ ቢሆኑም የተከሣሽን መቅረት አስመልክቶ የሚያስከትሉት ውጤት ተመሳሳይ ይመስላል፡፡ የጽሁፍ መልሱን ሳያቀርብ የቀረ ተከሣሽ በ233 መሠረት በሌለበት ጉዳዩ እንደሚሰማ ጉዳዩ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ ተከሣሽም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚሰማ በቁጥር 70(ሀ) መሠረት ትእዛዝ የሚሰጥበት ይመስላል፡፡ የሁለቱም ድንጋጌዎች የአማርኛ ቅጂ ለመልስ በተቀጠረበት ቀን መቅረትና ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን መቅረት አንድ አይነት ውጤት ያላቸው እንደሆነ የሚገልጹ ቢሆኑም የሁለቱም የእንግሊዝኛ ቅጂዎች ግን የተለየ ጽንሰ ሃሳብ የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡

የእንግሊዝኛ የ70(ሀ) የእንግሊዝኛ ድንጋጌ ስለ Ex-part ሲናገር የ233 ግን የሚደነግገው ስለ default proceeding ነው፡፡ሁለቱም የተለያየ ይዘት የተለያየ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡

የ70(ሀ) የእንግሊዝኛ ቅጂ

> 70 where the plaintiff appears and defendant does not appear when the suit is called on for hearing (a) if it is proved that the summons was duly served, the suit shall be heard ex-parte

በማለት ሲደነግግ አግባብነት ያለው የ233 ክፈል ደግሞ

> …. The court shall cause… requiring him to appear with his statement of defense to be fixed in the summons and informing him that the case wile be proceeded withnotwithstanding that he does not appear or that he appears without his statement of defense. በማለት ይደገግጋል፡፡



ሁለቱን የእንግሊዝኛ ቅጂዎች በማነጻጸር ለመገንዘብ እንደሚቻለው ለመልስ በተቀጠረ ቀን ተከሣሽ መልሱን ይዞ ባይቀርብ የሚከተለው ውጤት ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ባይገኝ ከሚከተለው ውጤት ጋር አንድ አይነት አይደለም፡፡ የ233 ድንጋጌ መለሱን ባያቀርብም የጉዳዩ መሰማት እንደሚቀጥል (default proceeding) ከሚይሳይ በቀር ተከሣሽ ከክርክር እንዲወጣ የሚያደርግበት ሥርዓት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በ70(ሀ) ስር ያለው ድንጋጌ ጉዳዩ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን የቀረ ተከሣሽ ጉዳዩ እሱ በሌለበት መቀጠል(default proceeding) ብቻ ሳይሆን ከክርክሩ እንዲወጣ (ex-part) እንደሚደረግ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህም በአማርኛ ቅጂ ላይ ያለው አገላለጽ በእንግሊዝኛው ላይ ያለውን ሃሳብ በትክክል አለማስተላለፉን ያመለክታል፡፡

የትርጉም ልዩነት ሲኖር የአማርኛውን ቅጂ በመውሰድ ዕልባት መስጠት ይቻላል በማለት ጉዳዩ ማጠቃለል አንዱ አማራጭ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አማራጭ አሁን በያዝነው ጉዳይ በግልጽ የሚታየውን የትርጉም ስህተት እንዲቀጥል የሚያደርግ በመሆኑ ትክክለኛ አማራጭ ነው አንልም፡፡ ይልቁም የተከሰተውን የትርጉም ልዩነት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማ እንዲሁም ተከሣሽ በቀረበበት ክስ የመደመጥ መብትን ይበልጥ ሊያስከብር በሚችል ሁኔታ መተርጐም በበለጠ የፍትህ አስተዳደርን ዓላማ በበለጠ ስለሚያሳካ የእንግሊዝኛው ቅጂ መከተሉን መርጠናል፡፡

በዚህም መሠረት አንድ ተከሣሽ ከክስ እንዲወጣ መደረግ ያለበት ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እንጂ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ካልቀረበ መሆን የለበትም፡፡ ይህ አተረጓጐም ተከሣሹ መልስ ለመቀበል በተያዘ ቀጠሮ ሳይቀርብ ቢቀር ፍርድ ቤቱ ምን ያደርጋል የሚል ጥያቄ ማስከተሉ የሚቀር አይደለም፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ፍርድ ቤት የሰጠው ቀጠሮ ሳይከበር ቢቀር ፍርድ ቤቱ ምን ያደርጋል ከሚል ሌላ ጥያቄ ጋር ተያይዞ መመለስ ያለበት ነው፡፡

በሙግት ሂደት ፍርድ ቤት የተለያዩ ጉዳዮች መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ቀጠሮዎችን ይሰጣል ሆኖም ፍ/ቤቱ የሰጠው ቀጠሮ በአንዱ ወይም በሌላው ተሟጋች በተሰተጓጎለ ቁጥር ለመስተጓጎሉ ምክንያት የሆነው ወገን ከክርክ እንዲወጣ (Ex-parte) አይደረግም፡፡ የቀጠሮው አለመከበር ቀጠሮ ከተሰጠሰት ምክንያት ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ በየጉዳዩ የተለያየ ትዕዛዝ የሚሰ ቢሆንም መሠረታዊው የጉዳዩ ሂደት የሚስተናገደው በሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ 7 በሚገኙት መርሆዎችና ድንጋጌዎች መሠረት መሆን አለበት፡፡ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 194 እንደተገለፀው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን ያለበት ድርጊት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልተከናወነ ዋጋ እንደሌለው የገልጻል፡፡ በዚህም መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ መልሱን ከማቅረብ ጋር ተያየዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀሩበታል፡፡ በቀጣዩ ሂደት ከመሳተፍ አይከለከልም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አሁን አመልካች በተሻሻለው ክስ ላይ መልስ መስጠት አትችልም የተባለው ቀደም ብሎ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን መለሱን ይዞ አለመቅረቡን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረ ቀን ተከሣሹ መልሱን ሳያቀርብ ቢቀር የጽሁፍ መልስና የማስረጃ ዝርዝር የማቅረብ ዕድሉን ከሚያጣ በቀር ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን መታዘዝ አልነበረበትም፡፡ በዚህም ምክንያት አንድን ተከሣሽ ሕጉ ከሚፈቅደው ሁኔታ ውጪ ከክርክር ውጪ ማድረግ በጉዳዩ ላይ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ ክሱ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሲሰጥ ተከሣሽ መልስ ማቅረብ አትችልም የተባለው ከዚህ ሥነ ሥርዓት ግድፈት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው፡፡ አመልካቹ ከክርክሩ መውጣት ሳይኖርበት አውጥቶ ለተሻሻለው ክስ መለስ አታቀርብም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን በማመን ይህን ግድፈት ማስተካከል ሲገባው አልፎታል፡፡ በመሆኑም የሰበር ችሎት የተፈፀመውን የሥነ ሥርዓት ግድፈት በፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 211 ስር በተደነገገው መሠረት ማሰተካከል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ውሣኔ

1. የአሁን አመልካች በከፈተኛ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ከክርክር ውጪ የተደረገው በአግባሱ ስላልሆነ ወደ ክርክሩ ይግባ፡፡
2. ለተሻሻለው ክስ መልስ ማቅረብ እንዲችል በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሻሻለው ክስ ግልባጭ ይሰጠው፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡



## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 15992

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት
መልስ ሰጪ፡- ወ/ት ሶስና አስፋው

*ውል- ስለውል አፃፃፍ/ ፎርም/- ስለ ውል አፃፃፍ ነፃነት- ስለ ውል አጻጻፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈጸም የሚያስከትለው ውጤት - የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች፣- የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች በስምምነት ስለሚሆን ያጻጻፍ አይነት - የግዴታዎች ቀሪ መሆን - ስለ ይርጋ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1719፣1720/1/ 1723፣ 1726 ፣1727፣ 1845*

በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተደረገው የኪራይ ውል በሁለት ምክንያት ያልተረጋገጠ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1726/1/ እና 1727/1/ መሠረት የውል ረቂቅ እንጅ አስገደጅነት የለውም፣ አመልካች ከጠየቀው ኪራይ ውስጥ እስከ 8/2/89 ያለው መጠየቅ ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት አመት ያለፈው በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፣

ው ሳ ኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. በኢትዮጵያ የውል ህግ ውል አመሰራረት ደንቦች መሰረት በህግ ወይም በተዋዋዮች በራሳቸው የተለየ ፎርም ካልተፈለገ በቀር ለውል መመስረት በሁለት ተዋዋዮች መካከል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ ነው፡፡
2. የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚደረግ ውል ባለቤትነትን /ownership/፣ የአላባ ጥቅምን /usufruct/፣ መያዣን /mortgage/ ወይም ሌላ አገልግሎትን /servitude/ ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የተደረገ ካልሆነ በቀር የግል በህግ በተመለከተው አጻጻፍ /ፎርም/ መከናወን የለበትም፡፡ የኪራይ ውል ከነዚህ ውሎች ውጭ በመሆኑ ከተዋዋዮች ስምምነት ካልሆነ በቀር በህጉ የተለየ አጻጻፍ /ፎርም/ የሚጠይቁት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑበትም፡፡
3. የህግ ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡



የመ/ቁ. 15992
ሐምሌ 19 ቀን 1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብድልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

መልስ ሰጪ፡- ወ/ት ሶስና አስፋው

በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ መርምሮ ችሎቱ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ውሣኔ የተሰጠው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የውሣኔውም ይዘት የቤት ኪራይ ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1727/2/ እና 1726/1/ መሠረት የውል ረቂቅ እንጂ አስገዳጅነት አይኖረውም፣ በመሆኑም ከሣሽ ማስረጃዬ ነው ብሎ ያቀረበው ሰነድ ይህንን ስለማያሟላና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የኪራይ ውል አለ ሊባል ስለማይችል ከሣሹ የኪራይ ቤቶች አስተደደር ድርጅት የአሁን መልስ ሰጭ ከ23/5/70 ዓ.ም እስከ 30/1/91 ዓ.ም ያልተከፈለ የኪራይ ሂሣብ ብር 65,790.67 እና ወለድ ብር 168,785.90 በድምሩ ብር 234,576.57 እንድትከፍል ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም የሚል ነው፡፡ ይኸው ፍ/ቤት ተከሣሽ ያቀረበችውን ይርጋን የሚመለከት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ከሣሽ ከጠየቀው ክፍያ ውስጥ እስከ 8/2/89 ዓ.ም ድረስ ያለው በይርጋ ይታገዳል በማለት ቀደም ሲል በ23/10/92 ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡

ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ይህን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለሰበር ችሎቱ የሰበር ማመልከቻ አቅርቧል፡፡

የሰበር ችሎት በዚህ የክርክር ሂደት

1ኛ. ይርጋን አስመልክቶ በሰጠው ትዕዛዝ

2ኛ. የኪራይ ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተደረገ አይፀናም በማለት የሰጠው ውሣኔ የህግ ትርጉም የሚያስነሱ በመሆናቸው ጉዳዩ በሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፤ በዚህም መሠረት መልስ ሰጪ መልሱን፣ አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡

የሰበር ችሎቱ በቀረበለት ጉዳይ የህግ ትርጉም የሚሹትን ነጥቦች ከፍሬ ነገር ጉዳዮች በመለየት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት፣

1ኛ. የሚፀና የኪራይ ውል ለመመስረት መሟላት ያለበት የህግ መስፈርት ምንድን ነው?

2ኛ. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የተመለከተውን የሕግ ግምት ክስን በይርጋ ከሚያግደው ድንጋጌ /1845/ ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? የሚሉትን የሕግ ነጥቦች መርምሮአል፡፡

<u>የሚፀና የኪራይ ውል ለመመስረት ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት በተመለተ፤</u>

ከላይ እንደተገለፀው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ያቀረበውን ክስ ውድቅ ያደረገው በከሣሽ በኩል የቀረበው ሰነድ በሁለት ምስክሮች አልተፈረመም በማለት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1719/1/ በጠቅላላው ሥርዓት በሁለቱ ወገን ተዋዋዮች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በሁለት ተዋዋዮች መካከል በህግ የሚፀና ሕጋዊ ውጤት ያለው ውል ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ነው፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ የውል ሕግ የውል አመሰራረት መሠረታዊ መርህ በህግ ወይም በተዋዋዮች በራሳቸው የተለየ ፎርም ካልተፈለገ በስተቀር ለውል መመስረት በሁለቱ ተዋዋዮች መካከል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ ነው የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ውል ህጉ ያስቀመጠውን የፎርም መስፈርት አያሟላም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ይህን ውል የሚመለከት በግልጽ የተቀመጠና የተለየ የአጻጻፍ ሥርዓት /ፎርም/ መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ህጉ የተለየ ጽሁፍ የሚጠይቅ በሆነ ጊዜ ይኸው ሥርዓት እስካልተሟላ ድረስ ውሉ እንደረቂቅ ከሚቆጠር በቀር በተዋዋዮች መካከል የሚፀናና አስገዳጅነት ያለው ህጋዊ ግንኙነት ሊመሰረት አይችልም (1720(1))፡፡ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት የሆነው ይኸው የሕግ ድንጋጌ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም ይህ



ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕጉ የተለየ ፎርም የግድ የሚልባቸው ውሎች ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም መጀመሪያ መታየት ያለበት ነጥብ የኢትዮጵያ ህግ ቤትን አስመልክቶ የሚደረግ የኪራይ ውል በተለየ ፎርም እንዲከናወን ይጠይቃል ወይስ አይጠይቅም የሚለው ነው?

ስለ ውል አጻጻፍ /ፎርም/ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕግ ክፍል /አንቀጽ 1719-1730/ የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ ድንጋጌ የለውም፡፡ በፍርድ ቤቱ በቀጥታ ባይጠቀስም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ድንጋጌ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች የሚደነግገው አንቀጽ 1723 ነው፡፡ ሆኖም ይህም አንቀጽ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረጉ ውሎች የተለየ ፎርም እንዲኖራቸው የሚጠይቅ ቢሆንም የኪራይ ውልን ግን የሚያጠቃልል አይደለም፡፡ ከሕጉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የተለየ ፎርም እንዲከተሉ የሚፈለጉት ውሎች የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ሁሉም ውሎች ሳይሆኑ በድንጋጌው ውስጥ ተለይተው የተቀመጡ ውሱን የውል ዓይነቶች ናቸው፡፡ አግባብነት ያለው የቁጥር 1723 ድንጋጌ ይዘት የሚከተለው ነው፡፡

1723/1/ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም ባንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በጽሁፍና በማገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል የማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው፡፡

ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ውል በተለየ ፎርም እንዲፈፀም ግድ የሚሆነው ውሉ

1. ባለቤትነትን /ownership/
2. የአላባ ጥቅምን /usufruct/
3. መያዣን /mortgage/ ወይም
4. ሌላ አገልግሎትን (servitude) ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የተደረገ

እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ አንድ ውል የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከትም ቢሆን ከእነዚህ ውሎች በአንዱ ውስጥ የሚካተት እስካልሆነ ድረስ በተለየ ፎርም መከናወን የለበትም፡፡ ከእነዚህ ውሎች በአንዱም ውስጥ ከማይካተቱና በዚህም ምክንያት የተለየ ፎርም ከማያስፈልጋቸው ውሎች መካከል የኪራይ ውል አንዱ ነው፡፡ የኪራይ ውል

የባለቤትነት መተላለፍን የሚመለከት አይደለም፡፡ የአላባ ጥቅምን፣ መያዣን ወይም ሌላ አገልግሎት /servitude/ ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረግም አይደለም፡፡ በመሆኑም የተለየ ፎርም የሚጠይቀው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ የቤት ኪራይን ለሚመለከቱ ውሎች አግባብነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ሕጉ ከሚያስቀመጠው አስገዳጅ ፎርም ውጪ ተዋዋይ ወገኖች የውላቸው አፈፃፀም ልዩ በሆነ አጻጻፍ ሥርዓት ሊወስኑት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1719/3/ ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ተዋዋዮቹ ሕጉ የማያስገድደውን ፎርም ለመፈፀም የተስማሙ እንደሆነ ውሉ ፍጹም የሚሆነው የተስማሙበትን የውላቸውን አፈጻጸም ሞልተው ሲዋዋሉ ብቻ እንደሆነ የሕጉ ቁጥር 1721 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ህግ መሠረት የፎርሙን ዓይነትና ይዘት የሚወስኑት ተዋዋዮቹ ራሳቸው በመሆናቸው ሊከተሉ ስለፈለጉት ፎርም በመካከላቸው ግልጽ የሆነ ስምምነት መኖር ይገባዋል፡፡፡ በቁጥር 1719 እንደተገለፀው በመርህ ደረጃ ውል ለመዋዋል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ በመሆኑ ውሉ እንዲፀና ተዋዋዮቹ እንዲፈፀም የፈለጉት ተጨማሪ ፎርማሊቲ ምን እንደሆነ ማወቅ የሚቻለው ተዋዋዮቹ ባደረጉት ውል ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የፎርሙን አይነት የምስክሮቹን ብዛት፣ ስለመመዝገብ አስፈላጊነት፣ አዋዋይ ፊት ስለመቅረብ ወ.ዘ.ተ ተዋዋዮቹ በፍላጎት የጨመሩት ፎርም ስለመኖሩ በተዋዋዮቹ መካከል ከተደረገው ስምምነት መገንዘብ መቻል አለበት፡፡

ተዋዋዮቹ ውላቸውን በጽሁፍ ካሰፈሩ የጽሁፉን ፎርማሊቲ እንደፈለጉ መገመት ቢቻልም ይህ በጽሁፍ የሰፈረው ስምምነት በምስክሮች እንዲረጋገጥ ወይም እንዲመዘገብ፣ ወይም አዋዋይ ፊት እንዲቀርብ መፈለጋቸውን የሚያሳይ አይሆንም፡፡ በጽሁፍ ከመሆኑ በተጨማሪ ሌሎቹም ፎርማሊቲዎች እንዲሟሉ መፈለጋቸው በጽሁፉ በራሱ ወይም በሌላ መልክ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ ነገር መኖር አለበት፡፡

በመሆኑም ተዋዋዮች በጽሁፍ መዋዋላቸውን ብቻ መሠረት በማድረግ ውሉ በምስክሮች ካልተረጋገጠ አይፀናም ማለት ተዋዋዮቹ ያልፈለጉትንና ያልተስማሙበትን ፎርም ከፍላጎታቸው ውጪ እንዲጫንባቸው ማድረግ ስለሚሆን ትክክለኛና ሕጉን የተከተለ አተረጓጎም አይደለም፡፡ ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ አይፀናም የሚለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1727/2/ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ውሉ በጽሁፍ እንዲሆን ግዴታ የተጣለ እንደሆነ ወይም ተዋዋዮቹ በስምምነት በሁለት



ምስክር ፊት እንዲረጋገጥ ሲፈልጉ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ውጪ ተዋዋዮች የፈረሙትን ሰነድ በመካከላቸው የውል ግንኙነት ለመመሥረት በቂና ብቸኛ ፎርሙ አድርገው ከተቀበሉት ፍርድ ቤቶች ፍላጎታቸውን ከማስፈፀም ውጪ ሌላ ተጨማሪ ፎርም ሊጠይቁ አይገባም፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይን የሚመለከተው የፍትሐብሔር ህጉ ሌላው ክፍልም ቤትም የሚመለከት የኪራይ ውል የተለየ ፎርም እንዲከተል የሚያስገድድ ድንጋጌ የለውም፡፡ /ቁጥር 2896-3018/፡፡ ይልቁንም የዚሁ ክፍል አካል የሆነው አንቀጽ 2898 የሚደነግገው የኪራይ ውልን ለማረጋገጥ ስለሚያስፈልገው የማስረጃ አይነት እንጂ የሚፀና የኪራይ ውል ለመመሥረት መኖር ስለሚገባው ጽሁፍ /ፎርም/ አይደለም፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "ቢሆንም የኪራዩ ውል የመከናወኑን ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይህ ውል መኖሩን ምስክሮች በማቅረብ ወይም በግምት አስተያየት ለማስረዳት ይቻላል" በማለት ስለሚደነግግ የኪራይ ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ምስክሮች ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ያመለክታል፡፡ ይህም ቀድሞውኑ የሚፀና የኪራይ ውል ለመመስረት የተለየ ፎርም መኖር አስፈላጊ አለመሆኑን ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ህጉ የማይጠይቀውን የፎርም መስፈርት መሠረት በማድረግ አመልካች ያቀረበው ሰነድ ረቂቅ እንጂ የሚፀና ውል አይደለም ማለቱ የውል ህጉን በተሣሣተ መንገድ መተርጎሙን የሚያመለክት ነው፡፡ ከላይ እንደተብራራው የኪራይ ውል ልዩ ፎርም የሚጠይቅ ባለመሆኑ በአመልካች በኩል ቀረበ የተባለው ሰነድ በሁለት ምስክር አለመፈረሙ ብቻውን ውል የለም ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ አይደለም፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2898/1/ የኪራይ ውልን ለማስረዳት የጽሁፍ ማስረጃ እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ለማስረጃነት የሚፈለገው ጽሁፍ ለውሉ መጽናት (validity) ከሚፈለገው ጽሁፍ ጋር ተመሳሳይ ፎርማሊቲ እንዲኖረው ሕጉ አይጠይቅም፡፡ በመሆኑም ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰነድ የግድ በሁለት ምስክሮች መፈረም አለበት ሊባል አይችልም፡፡ ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰነድ ያስረዳል የተባለውን ፍሬነገር ለማረጋገጥ የሚያስችል ተአማኒነት እስከአገኘ ድረስ ፍርድ ቤቱ የግድ በምስክሮች ፊት አልተፈረመም ወይም ለውል መጽናት የሚፈለጉትን ሌሎች መስፈርቶች አላሟላም በማለት ዋጋ እንዲያጣ ለማድረግ የሚያስችለው የህግ ድጋፍ የለውም፡፡

ስለዚህ 1ኛ. የኪራይ ውል በጽሁፍ መሆን እንዳለበት የሚያስገድድ ህግ ስለሌለ
2ኛ.ተዋዋዮች በጽሁፍ መዋዋላቸው ብቻውን ምስክርም እንዲኖር መፈለጋቸውን ስለማያሳይ፣

3ኛ.ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰነድ የግድ በምስክር መረጋገጥ ስለሌለበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውንና ማስረጃዬ ነው ያለውን የውል ሰነድ የፍትሐብሔር ሕጉን አንቀጽ 1720/1/ እና 1727/2/ በመጥቀስ ረቂቅ እንጂ አስገዳጅነት ያለው ውል አይደለም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አተረጓጎም በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡

<u>በሕግ ግምትና በይርጋ ድንጋጌዎች መካከል ያለው ግንኙነት በተመለተ</u>

ከዚህ ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ሲመለከት አመልካች ከጠየቀው ክፍያ እስከ 8/2/89 ዓ.ም ድረስ ያለውን በይርጋ ታግዷል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህም ረገድ ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሕግ 2024 የተቀመጠውን የሕግ ግምት (presumption of payment) የተለየ ይዘትና ዓላማ ካለው የይርጋ ሕግ (Period of limitation) ጋር በማምታታት መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል፡፡

የይርጋ ሕግ አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ፍሬ ነገር መመርመር ሳያስፈልገው አንድን ክስ ውድቅ የሚያደርግበት ሥርዓት ሲሆን የሕግ ግምት ግን ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ በተከራካሪዎች መካከል የቀረበው ማስረጃ ሲመዘን ተፈጻሚ የሚሆን ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አልፎ አልፎ የውጤት መመሳሰል የሚያጋጥም ቢሆንም የሕግ ግምትን ተፈጻሚ ለማድረግ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ፍሬ ነገርና አግባብነት ያለውን ሕግ እንዲመረምር የግድ የሚል ሲሆን ይርጋ ግን ጊዜውን በመቁጠር ብቻ ክሱ በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳይሰማ የሚያደርግ ሥርዓት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ ከ2020-2024 ባሉት ድንጋጌዎች የተለያዩ የህግ ግምቶች አስቀምጧል፡፡ እነዚህ የሕግ ግምቶችን እንደብዙዎቹ የህግ ግምቶች አንድ ክስ ለችሎት ቀርቦ በሚታይበት ወቅት የማስረዳት ሸክም ያለበት ማነው? በሕግ የሰፈረውን ግምት ማፍረስ የሚቻለው እንዴት ነው? ወ.ዘ.ተ. የሚሉትን ማስረጃን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንጂ አንድ ጉዳይ በጊዜ ማለፍ ምክንያት ክስ እንዳይቀርብበት የሚከለክሉ የይርጋ ደንቦች አይደሉም፡፡ በመሆኑም ሁለት ዓመት ያለፈው ዕዳ እንደተከፈለ የሚቆጥረው አንቀጽ 2024 ሁለት ዓመት



ካለፈው በጉዳዩ ላይ የሚቀርበውን ክስ በይርጋ የማገድ ውጤት የለውም፡፡ አንድ ክስ በይርጋ ይቋረጣል ወይስ አይቋረጥም የሚለውን በሚመለከት /ተከሣሹ በ2024 በተቀመጠው ድንጋጌ ተጠቃሚ በሆነባቸው ጉዳዮችም ጭምር/ ተፈጻሚ የሚሆነው የውልን ግንኙነት የሚመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ሕግ ነው፡፡ አጠቃላይ የይርጋ ገደብ ደግሞ በ1845 ሥር እንደተደነገገው 10 ዓመት ነው፡፡ በዚህ መሠረት አንድ ክስ በይርጋ የሚታገደው ክሱ ከመቅረቡ ከአስር ዓመት በላይ ሲሆን እንጂ ሁለት ዓመት የሞላው እንደሆነ አይደለም፡፡ ከሁለት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች ባለው ጊዜ ውስጥ የሚገኘውና በክሱ የተጠቃለለው ክፍያ በቁጥር 2024 በተቀመጠው የሕግ ግምት የሚሸፈን በመሆኑ ከሣሹ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት አለመወጣቱን በመመርመር ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገሩ ውሣኔ የሚሰጥበት እንጂ ከወዲሁ በይርጋ ታግዷል በማለት ወደ ሥረ ነገሩ ሳይገባ ከክርክር ውጪ የሚያደርገው አይደለም፡፡

በመሆኑም በዚህም ረገድ ፍርድ ቤቱ ክስ የቀረበበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ እስከ 8/2/89 ዓ.ም ድረስ ያለው ሂሣብ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡ ክሱ የቀረበው በ4/2/91 ዓ.ም በመሆኑ በይርጋ የሚታገደው ከ4/2/81 ዓ.ም በፊት ያለው ሂሣብ ብቻ ነው፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.3993 በ9/10/95 እና ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.23335 የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡
2. ፍ/ቤቱ ፍሬ ነገሩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ወደ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመለስ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 17191

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት መስፍን አቁበ ዮናስ

አመልካች፡- አስቴር አርአያ

መልስ ሰጭ፡- አቶ ግርማ ወዳጆ

*ውል - የውል ጉዳይ አወሳሰን - ስለ ውሎች ውጤት ውለን በመተርጐም ሰበብ ደኞች አንድ ውል ሲፈጥሩ ስላለመቻላቸው - ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ለዩ ለዩ ደንቦች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1711፣1731፣1676/2/፣2635፣2640፣2646*

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካከ ባቀረበችው ክስ በጠየቀችው መሠረት ተጠሪ አመልካች ከከፈለው ብር 35,000/ ሰላሣ አምስት ሺህ/ በተጨማሪ በፍርዱ ከተገኘው ጥቅም 20% ብር 124,188.59 /አንድ መቶ ሃያ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍል ሲወስን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች ለሰጠችው አገለግሎት ካገኘችው መደበኛ ክፍያ በተጨማሪ በፍርድ ከሚገኘው ጥቅም 20% ታስቦ እንዲከፈላት በውል የተደረገው ቃል በፍትህ ሆነ በርትዕ የሚደገፍ አይደለም በሚል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ



ውሳኔ፤- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደፈለጋቸው የመወሰን መብት ያላቸው ሲሆን በዚህ መሰረት የሚደረጉ የውል ስምምነቶች በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደ ህግ ሆነው ይቆጠራሉ፡፡
2. ሆኖም ልዩ የዕውቀት ያላቸውን የስራ ውሎች የሚያደርጉ ተዋዋዮች ስምምነት ላይ የደረሰባቸው የስራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ መሆናቸው ግልፅ በሆነ ጊዜና ለሙያ ስራ ተግባሩም ክብር ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ መጠኑን ዳኞች በመሰላቸው ሊቀንሱት ይችላሉ፡፡

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**
**ሰበር ችሎት**

የመ/ቁ17191
ሐምሌ 29 ቀን 1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበ ዮናስ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስተር አርአያ
ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ወዳጆ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በሰበር ችሎቱ ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ በሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ሥራ የካቲት 3 ቀን 1987 በተደረገው የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ውል መሠረት በማድረግ ተጠሪ ለአመልካች ከከፈለው ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) በተጨማሪ "ከፍርዱ ከሚገኝ ጥቅም 20% ሊከፍል የተስማሙበትን ብር 520,000 (አምስት መቶ ሃያ ሺህ ብር) አመልካች በክሱ ምክንያት ካወጣው ወጭና የጠበቃ አበል ጋር ይከፈል በማለት ክስ መስርቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን አከራክሮ የአሁኑ ተጠሪ "ጥቅም" አላገኘሁም በሚል በሙያ አገልግሎት ውሉ የተስማማበትን ክፍያ አልከፍልም ማለቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጾ፣ የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግምት መሠረት በማድረግ 124,188.59 (አንድ መቶ ሃያ ራት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም) የዳኝነቱንና የጠበቃ አበሉን ጨምሮ ይከፈል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ፣ አንድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ሙያተኛ ለአገልግሎቱ እንዲከፈለው ከተወሰነለት መደበኛ የክፍያ በተጨማሪ "ከፍርድ ከሚገኘው ጥቅም" ታስቦ እንዳከፈለው የሚደረግ የውል ቃል በርትዕም ሆነ በፍትህ የሚደገፍ አይደለም በማለት የሥር ፍቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡



የአሁን አመልካች በሰበር እንዲታይላት ያቀረበችው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሱ ነጥቦች ያሉት መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀር ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ተጠሪ መልሷን አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን እንዲያቀርቡ ተደርጐ ክርክሩ አብቅቷል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ በዋናነት የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጭብጥ የእውቀት ጠባይ ያላቸው የሥራ ውሎችን አስመልክቶ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስምምነት በተደረሰባቸው የክፍያ መጠኖች ላይ አለመግባባቶች ሲነሱ የዳኞች ሚና ምን ይሆናል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ውል በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የማደረግ ስምምነት ነው፡፡ ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ያስገነዝባበናል፡፡ ውሉን ለመዋዋል ሕጉ በሰጠው ነፃነት መሠረት የሚደረገው የውል ስምምነቶች በግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖች መካከል መብትና ግዴታዎች የሚጥሉ በመሆናቸው ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ እንደ ሕግ ሆነው የሚያገለግሉ መሆናቸውን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁኗ አመልካችና ተጠሪ የካቲት 3 ቀን 1987 ዓ.ም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ውል ያደረጉ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በዚህ ውል ስምምነት መሠረት ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ተይዞብኛል የሚለውን ቤት በማስመለስ ረገድ የአሁኗ አመልካች ለምታበረክተው ሙያዊ የጥብቅና አገልግሎት ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) ለመክፈልና ከፍርዱ ከሚገኘው ጥቅም 20% ለመክፈል የተስማሙ መሆኑን ከሥር መዝገቡ ተረድተናል፡፡ በዚህ የውል ስምምነት ቤት የተመለሰለት የአሁኑ ተጠሪ ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ) ለአመልካች የከፈለ ቢሆንም ከፍርድ ከሚገኘው ጥቅም ለመክፈል የተስማሙበትን 20% እንዲከፍል ክስ በቀረበበት ጊዜ «ጥቅም» አላገኘሁም በሚል ሲከራከር የቆየ ቢሆንም ጉዳዩን የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉን መሠት በማድረግ የንብረቱን ግምት አስልቶ ተጠሪ ብር 124,188.59 (አንድ መቶ ሃያ ራት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፍ ሲል የገለጽነውን የውል ሕግ መሠረታዊ መርህ የሆነውን "በፍቃደኝነት ወደ መዋዋልን" መሠረት አድርጐ ውሣኔ የሰጠ ቢሆንም

የዚህ መርህ አፈጻጸም በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ አግባብ ካላቸው ልዩ ድንጋጌቻች ጋር እንዴት መገናዘብ እንደሚገባው ሳይመረምር ከውሣኔ እንደደረሰ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በግራቀኙ መካከል በሕጋዊ መንገድና በፈቃደኛነት የተቋቋመን ግልጽ ውል ትርጉምንና ርትዕን ምክንያት በማድረግ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1711፣1714(2) እና 1733 ከሚደነግጉት ውጭ እና በወቅቱ በሥራ ላይ ያልነበረን ደንብ ዋቢ በማደረግ "ከፍርድ የሚገኘውን ጥቅም" ለሙያዊ አገልግሎት በሚደረግ ስምምነት ውስጥ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ያስቀመጡትን ግልጽ የውል ቃል ያለምንም የዉል ማፍረሻ ምክንያት ውድቅ እንዲሆን ማድረጉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከፍ ብለን ለማሳየት እንደሞከርነው የየትኛውም ሕጋዊ ውል መሠረቱ በፈቃድ መስጠት ላይ የተመሠረተ ስምምነት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ሕጉ በሰጣቸው ነፃነት ተጠቅመው ንብረትነትን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ይህ በጠቅላላ ክፍሉ የተነገረው የውል መሠታዊ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህን ጠቅላላ ደንቦች የሚለውጡ ወይም የሚያሟሉ ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ልዩ የሆኑ ደንቦች ካሉ በፍትሐብሔር ሕግ 5ኛ መጽሐፍ እና በንግድ ሕጉ የሚመለከቱ ስለመሆኑ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1776(2) ያስገነዝባል፡፡

በዚህም መሠረት አሁን ግራቀኙ እየተከራከሩበት ያለው ሙያዊ የዕውቀት ሥራ የሚመለከት ውል በፍትሐብሔር ሕጉ 5ኛ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች መካከል አንደኛ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ልዩ የእውቀት ጠባይ ያላቸው የሥራ ውሎች ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2632 እና በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ በተመለከቱ ድንጋጌዎች የሚመሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የውል አይነቶች ልዩ ዕውቀትን የሚመለከቱ በመሆናቸው የተለየ ስምምንት ከሌለ በቀር የእውቀት ሥራውን የተዋዋለው ሰው ግዴታዎቹን ራሱ መፈፀም እንደሚጠበቅበት ከሕጉ ቁጥር 2636(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡

ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ፈቅዶ የመዋዋል መርህን ተጠቅመው እነዚህን አይነት መሰል ውሎች መዋዋል ቢችሉም በነዚህ ልዩ ውሎች መሠረት ስምምነት ላይ



የተደረሱባቸው የሥራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ መሆናቸው ግልጽ በሆነ ጊዜ እና ለሙያ ሥራ ተግባሩም ክብር ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የሥራ ዋጋ መጠኑን ዳኞች በመሰላቸው ሊቀንሱት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ሕግ አይነተኛ ዓላማ የተለየ እውቀት በሚሻው ጉዳይ ዙሪያ አማራጭ የሌለውን ወይም አማራጩ በእጅጉ ሊጠብበት የሚችለውን ተዋዋይ ወገን የሙያውን ተግባር ከሚያከናውነውና ልዩ እውቀት ካለው ሙያተኛ ተዋዋይ ወገን ጋር ውልን ፈቅዶ በመዋዋል ረገድ የሚኖረውን ቦታ (position) በተቻለ መጠን ለማቀራረብ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በዚህ ረገድ በአብነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ጉዳዮች መካከል ከቀዳጅ ሀኪሞች፣ ከጥርስ ሐኪሞች ወይም ከአእምሮ በሽታ ሐኪሞች እና ሰዎችን ከማከም ኪነጥበብ ጋር ተያይዘው የሙያቸውን ተግባር የሚያከናውኑ ሰዎች ከበሽተኞቻቸው ወይም ከወኪሎቻቹው ጋር ባደረጉዋቸው ውሎች መነሻነት ስምምነት የተደረሰባቸው የሥራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ ሆነው በተገኙ ጊዜ እና ሕይወትን መታደግን ዋንኛ ሙያዊ መርህ አድርጎ ከተነሣው የዋጋውን መጠን ሊያሻሽሉት እንደሚችሉ የፍት.ሕግ ቁጥር 2640 እና 2646 ይደነግጋሉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ ግራቀኙ የልዩ ዕውቀት ፀባይ ያለው አገለግሎት ሥራ ውል ያደረጉ መሆኑ ይታመናል፡፡ ንብረቱ የተወሰደበት የአሁኑ ተጠሪ ለሚሰጠው ሙያዊ አገልግሎት በውሉ የተመለከተውን ብር 35,000 እና በፍርድ ከሚገኘው ጥቅም 20% ለመስጠት ተስመቶ የነበረ መሆኑን ይህ ችሎት በሚገባ ተገንዝቧል፡፡ ይህ ስምምነት ውልን ፈቅዶ በመዋዋል መርህ ላይ ተመስርቶ የተደረገ ውል አይደለም ለማለት እንኳን የሚያስችል ነገር ባይኖርም ከፍ ብለን ከላይ ሕጉ ሊጠብበቃቸው ከተነሳው ዓላማ አኳያ ጉዳዩን በጥልቀት ስንመረምረው የአሁኗ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ለሰጠችው ሙያዊ አገልግሎት 35,000 (ሰላሣ አምስት ሺህ) የተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ ክፍያ ከንብረቱ ግምት አኳያ በመቶኛ ሊሰላ 17% ይሆናል፡፡ አሁን አመልካች በተጨማሪ እንዲከፈላት እየጠየቀች ያለችው 20% ከቀድሞ ክፍያ ጋር ሲደመር የጠቅላላ ቤቱን ግምት 37% መሆኑ ታውቋል፡፡ የተጠየቀው የገንዘብ መጠን ደግሞ ከንብረቱ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በተለምዶ ለአገልግሎቱ ከሚጠየቀው ክፍያ ጋር ሲታይ እጅግ በጣም የተጋነነና ለሙያውም ሥራ ክብር ቢሆን ተቃራኒ የሆነ መሆኑን አምነንበታል፡፡

በመሆኑም ስምምነት የተደረሰበት የሥራ ዋጋ መጠን የበዛ እና ለሙያ ሥራ ክብርም ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ዳኞች መጠኑን እንዲቀንሱ ሕጉ የሰጣቸውን ሥልጣን በመጠቀም የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች የንብረቱን ግምት ማለትም የብር 620,942.98

(ስድስት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠሀን መቶ አርባ ሁለት ብር ከዘጠና ስምንት ሣንቲም) 10% (አሥር በመቶ) የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ቀደም ሲል በውሉ መሠረት የወሰደው ብር 35,000 ከክፍያው ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሊሆን የሚገባ መሆኑን አምነንበታል፡፡

ው ሣ ኔ

- ተጠሪ ብር 27,094.30 (ሃያ ሰባት ሺህ ዘጠና አራት ብር ከሠላሣ ሣንቲም) ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይከፈል፣
- የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፣
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሐምሌ 8 ቀን 1996 ዓ.ም በፍ/ብ/ይ/ቁ 14821 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

# ቅፅ 2

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ህዳር 1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ማውጫ


1. የሰበር መ/ቁ 13223/ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ/ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባቀረቡትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማናቸውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት በመስጠት ስላለበት ትዕዛዝ/ ........................................ 1
2. የሰበር መ/ቁ. 14414/ የጊምቢ አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ/ በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ.42/85 ተፈፃሚ ስላለመሆኑ........................................ 10
3. የሰበር መ/ቁ 15270 /የአስር አለቃ ተሻገር አስታጥቄ እና አቶ አዊስ አው አበዲ/ በከተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት/ ........................................ 19
4. የሰበር መ/ቁ 15410 /አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን/ አጠቃላይ የአሰራን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ሳይሆን የግል ጥቅምን መሠረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክሮች ችሎት ስለመሆኑ/ ........................................ 27
5. /የሰበር መ/ቁ 16273 /የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገንታ ገምአ/ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሠረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ/ ........................................ 33
6. የሰበር መ/ቁ 16624 (ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ እና የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ/ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6/1 መሠረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ) ........................................ 53
7. የሰበር መ/ቁ 16720 ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና የመካከለኛው አዋሽ፣ አበባ፣ ተንዳሆ፣ የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅቶች/ በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈጸምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በያላ በመጀመሪያ ፍርድ ባለዕዳ የሆነበት ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተውን የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ/ ........................................ 60
8. የሰበር መ/ቁ . 16896 ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የኢሉባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ/ የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ከተስማሙ ፍርድ ቤቱ ይህን ስምምነት ማስፈጸም ያለበት ስለመሆኑ/ ........................................ 75
9. የሰበር መ/ቁ 17077 /ዝቋላ ስቱል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ/ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኂላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደርገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ/ ........................................ 83
10. የሰበር መ/ቁ 17189 /የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ ዘለቀ/ በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውል ተቋርጦ ስራ ያልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ/ ........................................ 91
11. የሰበር መ/ቁ. 17429/ ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ/ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ ........................................ 108
12. የሰበር መ/ቁ 17533/የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስስልጣን እና ሙሉ አብርሃ/ የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሠረት የጉምሩክ ስነ ስርአት የልተፈጸመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረግ ወይም ዴክላራሲዮን ባመስጠቱ በዕቃው ባለቤት ላይ በሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ/ ........................................ 116
13. የሰበር መ/ቁ 17712 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች/ - /በተሰረዘ የባለህብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለህብትነት መብት ስላለመኖሩ/ ........................................ 132
14. የሰበር መ/ቁ 18307 /ንብ ትራንስፖርት አ.ማ እና አቶ ተገኑ መሸሻ/ በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ የሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለማመለከቱ ውሎች ክፍል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሲሆን የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ/ ........................................ 141

የሰበር መ.ቁ 13223

ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አስፋው አበበ

ስለ ፍርድና ስለትዕዛዝ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ጉዳይ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ስለሚሰጥበት ሁኔታ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182/2/፣ 342፣345/1/ለ/

መልስ ሰጭ የጎንደር ስጋ ፋብሪካ ገንዘብ የሆነ ብር 486,312.00 የባንኩን አሰራር በመጣስ ለአምጭው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሰላ ቅርንጫፍ በኩል እንዲከፈለው በማድረግ በፈጸመው ድርጊት ከስራ ተሰናብቶ የወንጀል ጉዳዩ በሂደት ላይ የነበረ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ሰጭ ወደ ስራ እንዲመለስ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ እየታየ እያለ መ/ሰጭ በፈጸመው ድርጊት በወንጀል ተጠያቂ ተደርጎ ብር 500.00 የተቀጣ ቢሆንም ይኸው ክርክር የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል መዝገቡን በማስረጃነት አላቀረበም በሚል ክርክሩን ውድቅ ስላደረገው የቀረበ አቤቱታ፡፡



ውሳኔ፡- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሻሻለው ውሳኔዎቹ ተሽረዋል፡፡

1. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡
2. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ከያዘው ጭብጥ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ፍርድ መስጠት ይችላል፡፡

የመ.ቁ. 13223

ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - መንበረ አድማሱ ቀረበች

ተጠሪ፡- አቶ አስፋው አበበ - ቀረበ

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ አቋርጦታልና ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ሲል በአሁን አመልካች ላይ ክስ መስርቷል። አመልካቹም ለሥራ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሆነው ተጠሪው ሐሰተኛ ማሕተምና ፊርማ የያዘ የማዘዣ ደብዳቤ ለባንኩ ቀርቦ ሳለ የበኩሉን ማጣሪያ ባለማድረግ የጎንደር ስጋ ፋብሪካ ገንዘብ የሆነው ብር 486,312.00 ለአምጪው በአሰላ ንግድ ባንክ አማካኝነት እንዲከፈል ማድረጉ መሆኑን በመዘርዘር ባንኩ ኪሣራ ላይ እንዲወድቅ አድርጓልና የሥራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ መቋረጡ ተገቢ ነው ሲል መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል።

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የደብዳቤው ማህተምና ፊርማ ትክክለኛነት የሥራ ድርሻው በሆነ ሌላ ሰው የተረጋገጠ መሆኑን፣ ተጠሪ ይህን የመስራት ኃላፊነትም ሆነ ግዴታ የሌለበት መሆኑን፣ በባንኩ መመሪያም መሰረት ሰነዱን ከተጠራጠረ ገንዘቡን ከመክፈሉ በፊት አውጪውን ማማከር ያለበት ከፋዩ የአሰላ ባንክ እንጂ ተጠሪው የሚገኝበት የባንኩ የመስቀል አደባባይ ቅርንጫፍ አለመሆኑን በመግለጽ የተጠሪው የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነውና የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ውሣኔው እስከተሰጠበት እለት ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካቹ ይግባኝ ተጠሪው ደግሞ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከራከሩ ሲሆን የከፍተኛ ፍ/ቤትም ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ብቻ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ ሲል የስር ፍርዱን አሻሽሎታል።

በመቀጠል አመልካች ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተጠሪም መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት ከቀረበለት ክርክር በመነሳት በጉዳዩ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ተጠሪ ፈጽሞታል በተባለው ተግባር በወንጀል ጥፋተኛ ተሰኝቷል? ወይስ አልተሰኘም? የሥራ ውሉስ መቋረጥ በሕግ የተደገፈ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

#በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና በጥፋቱም ምክንያት ለያዘው ሥራ ብቁ ሆኖ አለመገኘት; የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ምክንያት መሆኑ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/ቀ/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገር ስንመለስ አመልካች ተጠሪው በፈፀመው ጥፋት በመ.ቁ. 4176/88 በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኛነት ውሣኔ ተሰጥቶበት ብር 500.00 ተቀጥቷል ሲል ተከራክሯል፡፡ ይህ ክርክር የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ አመልካቹ በተጠቀሰው አይነት ይከራከር እንጂ የወንጀሉን መዝገብ በማስረጃነት ሊያቀርብ አልቻለም በሚል ክርክሩን ውድቅ ማድረጉን በውሣኔው አመልክቷል፡፡

በመሰረቱ አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በእራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪነት ይቀርብለት ዘንድ ማዘዝ እንዲችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.345 ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ እንዲሁም አንድ ፍ/ቤት ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በእራሱ አነሳሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሰነድ፣ የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሰጠበት መዝገብ እንዲቀርብለት ማዘዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት በአደረገው ምክንያት ሳይገደብ ጉዳዩን እራሱ በተረዳው አይነት ጭብጥ ለውጦ ፍርድ ሊሰጥ እንየማችላ

5

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 እና 182/2/ ላይ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከኍ [illegible] እንደተመለከተው ይህን ጉዳይ በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪው በወንጀል ተከስሶ የተቀጣ ስለመሆኑ ክርክሩ በአመልካች ቀርቦለታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ክርክሩን ከአዋጅ ቁ. 42/85 አኳያ

ሊመረምረው እና ውሣኔውንም ለመስጠት ተጠሪው በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠበትን የጥፋተኛነት ውሣኔ ይዘት አለያም ጉዳዩ ከሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር ያለውን ተያያዥነት እንዲያየው ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በአመልካች ቁጥሩ የተጠቀሰለትን የወንጀል መዝገብ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በእራሱ አነሳሽነት ጭምር ሊያስቀርበው ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ይህንን አላደረገም፡፡ ይልቁንም ተጠሪው በወንጀል ስለመቀጣቱ ክርክሩ ቢቀርብም መዝገቡ በማስረጃነት ሊቀርብ አልቻለም ሲል ነጥቡን አልፎታል፡፡ በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ የሥራ ክርክሩን ጉዳይ ለመወሰን የግድ አስፈላጊ መሆኑ እየታየም ፍ/ቤቱ በወንጀሉ ክስ የተሰጠውን ፍርድ በእራሱ አነሳሽነት አስቀርቦ አለማየቱ የክርክሩን አመራር ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች አለማስደገፉንና በውጤቱም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል ግን ይህ ችሎት ተጠሪው ግብረ አበር በመሆን ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ መጠኑ ከላይ የተጠቀሰው የፋብሪካው ገንዘብ በአሰላ ቅርንጫፍ አማካኝነት ለሌላው ተከሣሽ እንዲከፈል አድርጓል



በሚል ከሌሎች ተከሣሾች ጋር በከባድ አታላይነት ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሶ ፍ/ቤቱ ተጠሪውን በወ/መ/ሕ/ቁ. 412/1/ መሠረት ጥፋተኛ በማድረግ ብር 500.00 የቀጣው መሆኑን እና ይህም ፍርድ በተጠሪው አማካኝነት ይግባኝ በቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3885 መጽናቱን አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቹ በመ.ቁ. 6928 ፍርዱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል ያቀረበውን አቤቱታ በአለመቀበል መዝገቡን የዘጋው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ይህ በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ ተጠሪው ጥፋተኛ መሰኘቱን ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛ የተሰኘው ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ፈጽሞታል በተባለ ወንጀል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የተረጋገጠበት ጥፋትም በስራው ለመቀጠል ብቃት የሌለው መሆኑን ለማሳየት የሚበቃ ነው፡፡ እንደውም የሥራ ውል መቋረጥ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/ቀ/ መደገፉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም አቤቱታው በቀረበበት ውሣኔ ተጠሪው የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራ እንዲመለስ መወሰኑ የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡

ውሣኔ

1ኛ. የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ሕጋዊ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም።

2ኛ. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 21/88፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 6222 ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል።



ሰበር መ/ቁ. 14414

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች:- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች :- የጊምቢ ከተማ አስተዳዳር ጽህፈት ቤት

መልስ ሰጭ:- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ

*ስለ አዋጅ ቁ. 42/85 ተፈጻሚነት - የአሰሪና ሰራተኛ ትርጓሜ - የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 2/1/፣3/2/ /ሠ/*

መ/ሰጭ የአዋጅ ቁ.42/85ን መሠረት በማድረግ አመልካች ይኸንኑ ሕግ ተላልፎ ከስራዬ ያገደኝ በመሆኑ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት በጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበችውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጭ ከስራ ከታገደችከት ቀን ጀምሮ ያለው ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 39፣40 እና 43 የተመለከተው ክፍያ (የስንብትና የካሣ ክፍያ) ተከፍሏት እንድትሰናበት ፍ/ቤቱ በመወሰኑና

ውሣኔውንም የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ችሎት በማጽናታቸው የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ውሣኔ</u>

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት፣ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. አንድ ክርክር በአዋጅ ቁ.42/85 አግባብ የሚዳኘው በአዋጁ እንደተሰጠው ትርጓሜ አንድ ወገን ተከራካሪ አሰሪ ሌላው ወገን ተከራካሪ ደግሞ ሰራተኛ የሚባሉ ከሆነ ነው፡፡
2. በአዋጅ "አሰሪ" ተብሎ ለሚጠራ "ድርጅት" የተሰጠው ትርጓሜ የሕዝብ አስተዳደር ስራ የሚያከናውኑ አካላት "ድርጅት" ሊባሉ እንደማይችሉ በግልጽ ያመለክታል፡፡
3. በአዋጁ ትርጓሜ "አሰሪ" ተብሎ ከማይጠራ "ድርጅት" ጋር የስራ ውል ያለው ሠራተኛ በአዋጁ ትርጓሜ "ሠራተኛ" ሊባል አይችልም፡፡
4. አንድ በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሠራተኛ በመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር አዋጅ አለመሸፈኑ በራሱ በአዋጅ ቁ.42/85 የሚሸፈን አያደርገውም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 14414

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት - አላዛር ኢተፋ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ- አልቀረበችም፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ ጉዳይ የጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የአዋጅ ቁ. 42/85ን መሠረት በማድረግ የአሁኑ አመልካች ይኸን ሕግ ተላልፎ ከስራዬ አግዶኛልና ኪሣራዬን ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ ስትል ባቀረበችው ክስ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሥራ ከታገደችበት እለት ጀምሮ ያለው ደመወዝዋ እንዲከፈላት እና ወደ ሥራዋ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጁ አንቀጽ 39፣40 እና

43 የተመለከተው ክፍያ (የስንብትና የካሣ ክፍያ) እንዲሰጣት እና እንድትሰናበት ወስኗል፡፡

የወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ውሣኔ ያፀናው ሲሆን በመቀጠል ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የመጨረሻ ፍርድ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህም ችሎት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡለትን ክርክር መርምሯል፡፡

ሊፈታ የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ የተከራካሪዎቹ ግንኙነት በአዋጅ ቁ. 42/85 ይሸፈናል? ወይስ አይሸፈንም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2/1/ መሠረት አንድ አካል አሠሪ ለመሰኘት በአዋጁ አግባብ ሰራተኛን ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ድርጅት የሚባለው ደግሞ የንግድ፣



የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን ወይም ሌላ ሕጋዊያን ተግባራትን ለማከናወን የተመሠረተ ተቋም መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2/2/ ላይ ተተርጉሟል፡፡ ይኸ ለጅርጅት የተሰጠው ትርጓሜ የሕዝብ አስተዳደር ሥራ የሚያከናውኑ አካላት ድርጅት ሊባሉ እንደማይችሉ በግልጽ ያመላክታል፡፡ በሌላም በኩል የመንግሥት አስተዳደር ሰራተኞች በልዩ ሕግ ከሚተዳደሩ ሌሎች ሠራተኞች ውስጥ የተመደቡ መሆናቸው እና ከአሰሪያቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ እንደማይሆን በአንቀጽ 3/2/ሠ/ ላይ ተጠቅሷል፡፡

አመልካች የሕዝብ አገልግሎት ሥራ የሚያካሂድ የመንግሥት ተቋም መሆኑን ከስያሜው እንኳ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጠሪ የቀረበውም ክርክር አመልካች ድርጅት ነው በሚል እና ይህንንም በማስረዳት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ክርክሩ ተጠሪ በመንግሥት ሠራተኝነት የታቀፈች አይደለችም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስም ሠራተኞቹ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ የታቀፉ አልነበሩም ተጠሪ ክስ ከመሠረተች በኋላ የወጣው የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ቁ. 61/94ም ወደ ኋላ ሄዶ ስለማይሰራ ግንኙነታችን በአዋጅ ቁ. 42/85 የሚሸፈን ነው የሚል ነው፡፡

በዚህ ችሎት እምነት የአንድ ሙግት ይዘት በአዋጅ ቁ. 42/85 አግባብ የሚዳኝ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በአዋጁ እንደተሰጠው ትርጓሜ አንዱን ወገን ተከራካሪ አሰሪ ሌላው ወገን ተከራካሪ ደግሞ ሰራተኛ ሊሰኙ ይገባል፡፡ ከአዋጁ አግባብ ቀጣሪው አሰሪ ተቀጣሪው ደግሞ ሠራተኛ ሊባሉና ሁለቱም በድንጋጌው የተቀመጠውን የትርጓሜ መስፈርት እንዲያሟሉ ያስፈልጋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አሰሪው አመልካች የሕዝብ አስተዳደር ሥራ የሚያካሂድ የመንግሥት መ/ቤት በመሆኑ ድርጅት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አመልካቹ አሰሪ ድርጅት ባለመሆኑም ተጠሪዋ በአዋጁ አሰሪ ከተባለ አካል ጋር የሥራ ውል ግንኙነት ያላት ሠራተኛ ናት ልትባል የምትችል አይደለችም፡፡ ይህ ደግሞ ሁለቱም በአዋጁ የተቀመጠውን ትርጓሜ አለማሟላታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

በእርግጥ ተጠሪ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ያልታቀፈች ሠራተኛ መሆንዋን በመግለጽ መከራከርዋን ተገንዝበናል፡፡ ይህም አዋጁ ተፈፃሚ የማይሆነው በአዋጁ አንቀጽ 3/2/ሠ/ መሠረት



በልዩ ሕግ ለሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች እንጂ ለእኔ በልዩ አዋጁ ላልታቀፍኩት አይደለም በሚል ዓይነት መሟገቷን ያመላክታል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ እንደምትከራከረው በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጁ የታቀፈች አይደለችም ሊባል የሚችል አይነት ቢሆን እንኳን አለመታቀፏ ብቻውን እርሷን በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ሠራተኛ፣ አመልካቹን ደግሞ ድርጅት ሊያሰኛቸው የሚችል አይደለምና ግንኙነታቸው በተጠቀሰው አዋጅ የሚሸፈን ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርሰን አይሆንም፡፡ አመልካች ድርጅት፣ ተጠሪ ደግሞ የድርጅት ሠራተኛ መሆናቸው በአልተረጋገጠበት ሁኔታ አዋጅ ቁ. 42/85 ለክርክራቸው ተገቢነት ሊኖረው የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አይኖርም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አለኝ የምትለውን የመብት ጥያቄ ለግንኙነታቸው ተፈፃሚ ሊሆን ከሚገባው ሕግ አኳያ አቃንታ ልታቀርብ ከሚገባት በቀር የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ለመብቷ መጠየቂያ ልታደርግ አትችልም፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የተቀጠሰውን አዋጅ ተመስርተው የሰጡትን ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ፍርድ ይህ ችሎት አልተቀበለውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና በመ/ቁ. 01235 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ.42/85 መሠረት አይተው የሰጡት ከፍ ሲል የተመለከተው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

የሰበር መ/ቁ. 15270

ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የ፲ አለቃ ተሻገር አስታጥቄ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አዊስ አው አብዲ

*በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን - ከሣሽ የመሆን ችሎታ - ፍርድ ቤቱ የክስ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ስለሚወስንበት ሁኔታ/በክሱ አቤቱታ ላይ የተገለጸው ነገር የማያስከስስ ሆኖ ሲገኝ/፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33/2/፣ 231/1/ሀ/ - የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67*



በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን ቦታ የከተማው አስተዳደር በ1982 ለአመልካች የሰጠው በ1945 ዓ.ም. ቦታው ለመ/ሰጭ አባት ተሰጥቶት እያለ በመሆኑ ለመ/ሰጭ አባት የተሰጠው የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሳይሰረዝ ሌላ ካርታ ለአመልካች መስጠቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የጅጅጋ ዞን ወረዳ ፍ/ቤት በመወሰኑና ውሣኔውም በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡<u>ውሣኔ</u>

የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት፣የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡

1. የከተማ ቦታ በአዋጅ ቁ. 47/67 መሠረት የመንግስት በመሆኑ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡
2. በከተማ ቦታ ላይ ያለን መብት አስመልክቶ ክስ ማቅረብ የሚቻለው ከአዋጅ ቁጥር 47/67 መውጣት በኋላ የመንግስት አካል በሰጠው የይዞታ ወይም የመጠቀም መብት መሠረት ነው፡፡

የሰበር መ/ቁ. 15270

ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የአስር አለቃ ተሻገር አስታጥቄ

ተጠሪ፡- አቶ አዊል አው አብዲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ነው የተባለን የከተማ ቦታ ለማስመለስ በሚል በሶማሌ ብ/ክ/መ/በጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በጉልበትና በሕገወጥ መንገድ የያዘብኝን ቦታ ይልቀቅልኝ በማለት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የተከሣሽን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የመከላከያ ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ቦታ ለከሣሽ ይልቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ



ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም እንደዚሁ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎአል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ማለትም የሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.05/1/8/96 በ15/5/96 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አቤቱታው በዚህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተገቢውን ሕጋዊ ሥነ-ስርዓት ተከትለው መወሰን አለመወሰናቸውን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጉዳዩን ከስር መሠረቱ አንስተን መርምረናል፡፡ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ማየት እንደቻልነው ተጠሪ ክስ ሊመሰርት የቻለው አባቱ የተወለዥን የአፈር ቤትና የውሃ ጉድጓድ ያለበትን በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን ቦታ ተከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) በጉልበትና በሕገወጥ መንገድ ይዞብኛል በማለት ነው፡፡ መብቱን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበው ማስረጃ በ1945 ዓ.ም ለአባቱ ተሰጥቶ ነበር የሚለው የቦታ ይዞታማረጋገጫ ካርታ ብቻ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ቦታው በላዩ ላይ ምንም ዓይነት ቤትም ሆነ ንብረት ያልነበረበትና በማንም ሰው ያልተያዘ መሆኑ ተረጋግጦ በ1982 ዓ.ም በከተማው አስተዳደር የተሰጠው መሆኑን

፣በሰሙ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው መሆኑን እና በላዩም ላይ ቤት ሰርቶበት ግብርም እየከፈለበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ በዚህ ረገድም ማስረጃዎችን አቅርቦአል፡፡ የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤትም ቦታው ለከሣሽ (ለአሁኑ ተጠሪ) ሊለቀቅ ይገባል በማለት የወሰነው አመልካች (የስር ተከሣሽ) ያቀረባቸው ማስረጃዎች ቦታው በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠው መሆኑን አያረጋግጡም በሚል ሳይሆን፣ በ1945 ዓ.ም ለከሣሽ አባት የተሰጠው የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሣይሰረዝ ሌላ ካርታ ለተከሣሽ መሰጠቱ ሕገወጥ ነው፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ቦታ በከተማ አስተዳደር ክልል የሚገኝ ማለትም የከተማ ቦታ ነው፡፡ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ይዞታ ስር የቆየና በላዩም ላይ አመልካች ቤት የሰራበት እንደሆነም ተረጋግጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቦታው ለአመልካች ከመሰጠቱ በፊት ማለትም ከ1982 ዓ.ም በፊትም ቢሆን በተጠሪው አባትም ሆነ በተጠሪው ይዞታ ስር እንዳልነበረ፤ ይልቁንም የጦር ሰፈር አካል እንደነበረ በተጠሪው የክስ ማመልከቻ ጭምር መገለፁን ነው የተገነዘብነው፡፡



የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67 ከታወጀበት ቀን (1967) ጀምሮ የከተማ ቦታ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡ ግለሰቦች በከተማ ቦታ ላይ የመጠቀም ወይም የይዞታ መብት ሊኖራቸው የሚችለው በሚመለከተው የመንግሥት አካል በሕጋዊ መንገድ ሲሰጣቸው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም አከራካሪው ቦታ ከፍ ሲል በጠቀስነው አዋጅ ቁ.47/67 መሠረት የመንግሥት ንብረት የሆነው ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ነው በመሆኑም ሊያዝበት የሚችለው መንግሥት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ባዶ መሆኑ እና በማንም ሰው አለመያዙ ተረጋግጦ ለአመልካች ተሰጥቶአል፡፡ በ1945 ዓ.ም ለተጠሪ አባት ተሰጥቶ የነበረው ካርታም ከ1967ቱ አዋጅ ወዲህ ለተጠሪው አባትም ሆነ ለተጠሪው የሚሰጠው መብት የለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ቦታው በተጠሪው አባትም ሆነ በተጠሪው ይዞታ ስር የነበረ ለመሆኑ ወይም በእነሱ ይዞታ ስር እያለ ለአመልካች የተሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልቀረበ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚችልበት ምክንያት እንኳን አልነበረውም፡፡ እኛ እንዳየነው ተጠሪ ክሱን የመሠረተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33(2) የግድ በሚለው መሠረት ክስ በመሠረተበት ቦታ ላይ መብት ያለው መሆኑን ከጅምሩ (ከመሠረቱ) ሳያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም የወረዳው ፍ/ቤት ክሱን

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33(2) እና 231(1)(ሀ) መሠረት ከጅምሩ መሠረዝ ነበረበት፡፡ ይህን መሠረታዊ የሥነ - ሥርዓት አካሄድ ባለመከተል ተጠሪን ከሕግ አግባብ ውጪ ባለመብት እንዲሆን በመወሰኑም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሞአል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበባቸው በሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም በጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራን በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 15410

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ጅፋር

መልስ ሰጭ፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

*ስለሥራ ክርክር - የሥራ ክርክር ችሎቶች ስልጣን - የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን - የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 147*

አመልካች የደመወዝ ጭማሪ ክፍያ ይፈጸምልኝ በማለት ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክስ ቢያቀርብም ቦርዱ ጉዳዩ በቦርዱ ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ በአፈጻጸም የሚጠየቅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደመወዝ ጭማሪን አስመልክቶ የተሰጠ ውሣኔ የለም በማለት ሽሮ የደመወዝ ጭማሪውን ጉዳይ የማየት ሥልጣን የቦርዱ ነው ከሚል እምነት በመነሳት ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን ለቦርዱ ሲመልስለት ቦርዱ በበኩሉ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ወሰነ፡፡ በቦርዱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢቀርብም

ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ፍርድ የሰጠሁበት በመሆኑ እንደገና ሳየው የምችልበት ሥርዓት የለም በማለት ውድቅ ስላደረገው የቀረበ አቤቱታ፡፡

## ውሣኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. የአሰሪ አጠቃላይ የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ሥርዓት ሕገ ወጥ ነው በሚል የሚቀርብን ስክ የማየት ሥልጣን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡
2. የግል ጥቅምን መሠረት አድርጎ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የሥራ ክርክር ችሎት ነው፡



ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

የመ.ቁ. 15410

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ጅፋር - ቀረበ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ግርማ ማርቆስ ቀረበ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው የአመልካች እና የተጠሪ ክርክር የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪው የተጠቀሰውን ክፍያ ይክፈለኝ ሲል ከአሰሪ እና ሠራተኛ ቦርድ ዘንድ ክስ ይመሰርታል፡፡ ቦርዱም በሁለቱ መካከል በነበረ ክርክር አስቀድሞ የተሰጠ ፍርድ እንደነበር ጠቁሞ ይህም ጥያቄ አብሮ ፍርድ እንዳገኘ

የሚቆጠር ነውና በአፈፃፀም እንጂ በክስ ሊጠየቅ የሚገባው አይደለም በማለት ይወስናል፡፡

ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የደመወዝ ጭማሪን አስመልክቶ የተሰጠ ፍርድ ስለሌለ ጥያቄው በክስ እንጂ በአፈፃፀም ሊጠየቅ አይገባም በማለት የቦርዱን ውሣኔ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ እንደዚሁም ቦርዱ የደመወዝ ጭማሪውን ክርክር አይቶ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ ጉዳዩን ወደ ቦርድ የመለሰውም ይህን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለው ቦርድ እንጂ ፍ/ቤት አይደለም በሚል እምነት መሆኑን በውሣኔው አመላክቷል፡፡

በመቀጠል ጥያቄው በቀጥታ ክስ አይነት ለአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ቀርቦለታል፡፡ ቦርዱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ አስቀድሜ ፍርድ የሰጠሁበት ጉዳይ ስለሆነ ደግሜ ላየው የምችልበት ሥርዓት የለም በማለት በአሁን አመልካች የቀረበለትን ይግባኝ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ይህም ችሎት በግራ ቀኙ የቀረበለትን ክርክር መርምሯል፡፡



ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥም ቦርድ ይህን የደመወዝ ጭማሪ ክርክር ለመዳኘት ሥልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአመልካች የደመወዝ ጭማሪ ይገባኛል ክርክር ተጠሪው በዚህ ረገድ የወሰደው አጠቃላይ እርምጃ የሠራተኞችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነው የሚል ይዘት ያለው አይደለም፡፡ አለያም የተጠሪው የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ሕገ ወጥ ነውና ሊስተካከል ይገባዋል በሚል አይነት የቀረበ አይደለም፡፡ ይልቁንም ክርክሩ የግል ጥቅምን ወይም መብትን ከማስከበር አኳያ የቀረበ መሆኑን በግልጽ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ይህም ይህ ችሎት በመ.ቁ. 18180 ለግል እና ለወል የሥራ ክርክር አይነቶች ከሰጠው ትርጉም አኳያ ሲታይ የግል እንጂ የወል የሥራ ክርክር የሚሰኝ አይደለም፡፡ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣንም የፍ/ቤት እንጂ የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ አይሆንም፡፡

ስለሆነም ቦርዱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም የሚል ውሣኔ መስጠቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ወደ ቦርድ ሲመልሰው ክርክሩን የመዳኘት ሥልጣን ያለው ቦርድ ነው በሚል እምነት እንጂ ይህን ነጥብ በጭብጥነት ይዞ ፍርድ ያልሰጠበት መሆኑን ከውሣኔው መገንዘብ ስለሚቻል ቦርዱ የሥልጣኑን ጥያቄ በጭብጥነት ይዞ ፍርድ መስጠቱ ጉዳዩን እንዲዳኝ ከመለሰለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ ጋር አይጣጣምም ወይም ይቃረናል ሊያሰኘው የሚችል አይሆንም፡፡ እንዲሁም ለሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዳይ የሚፈቅድልኝ

ሥርዓት የለም ሲል የሰጠው ምክንያት የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ ባይታይም ይግባኙን ውድቅ በማድረጉ ግን የፈፀመው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የለም፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ.ቁ.14/01/93 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 21501 የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡



ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም.

የመ/ቁ.16273

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገንታ ገምአ

*የስራ ክርክር - የክስ ምክንያት መኖር -(በቋሚ ልሁን ጥያቄ ላይ) የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን (የቋሚነት ጥያቄንና የግል የጥቅማጥቅምን አወሳሰን በተመለከተ)- የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 9፣10፣138 142 ፡- ከሳሽ ስለመሆን ችሎታ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 33*

አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ቋሚ ሠራተኛ እንዲሆንና ጥቅማ ጥቅምም እንዲሠጠው በማለት ስለወሰኑ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሳኔ፡- የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጡት ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከሕግ አንጻር ጉደለብኝ የሚለው መብት ካለ ከሚጠይቅ በቀር ቋሚ ልሁን በሚል የሚያቀርበው ጥያቄ የክስ ምክንያት /Cause of action/ የለውም፡፡
2. የጥቅማ ጥቅም ክፍያን በተመለከተ ይህ ጥቅም ቀረብኝ የሚል ሠራተኛ የሚያቀርበው ክስ የዛን ሠራተኛ ጉዳይ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ እንደግል የሥራ ክርክር የሚቆጠር እንጂ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ ስለሆነም የጥቅማጥቅም ይከፈለኝ ጥያቄ የግል ክርክር በመሆኑ ለአሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ቀርቦ የሚስተናገድ አይሆንም፡



የሰበር መ/ቁ. 16273

ጥቅምት 22/98 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገንታ ገምአ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ፍርድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ሚያዚያ 21/96 ዓ.ም. በመ/ቁ. 303/02/94 በሰጠው ውሣኔ እና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን በማፅናት በመ/ቁ. 30835 ሰኔ 16/96 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ነው፡፡

ለአቤቱታው መነሻ ምክንያት የሆነው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ያቀረበው ክስ ሲሆን፣ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በድርጅቱ ውስጥ በጥበቃ ሥራ ተቀጥሬ በመሥራት ላይ የምገኝ ስለሆነና ሥራውም ዘላቂነት ያለው ሆኖ ሣለ የቋሚ ሠራተኛነት መብቴ ሊጠበቅልኝ ባለመቻሉ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ሠራተኛ እንድሆን፣ ለቋሚ ሠራተኞችም የሚሰጠው ጥቅማጥቅም ክሱን ካቀረብኩበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሰጠኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፡- ተጠሪው የሻምበል ባሻ የውትድርና ማዕረግ ያለው በጡረታ ላይ የሚገኝ እንደሆነ ጠቅሶ በወቅቱ ለተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት ችግሩ እስኪወገድ ድረስ ጥበቃውን ለማጠናከር የቀድሞ ወታደሮችን ቀጥሮ ለመመደብ እንዲችል ኰርፖሬሽኑ ለበላይ አካል ጥያቄ አቅርቦ በተፈቀደለት መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ እንጂ በቋሚነት በሥራ ላይ ሊቀጥል የሚችል አለመሆኑን፤ የጥቅማ ጥቅም ጥያቄውም በህብረት ስምምነቱ ለተወሰነ ጊዜ ለተቀጠረ ሠራተኛ ተፈፃሚ የሚሆን አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ቦርዱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 10 መሠረት የተቀጠረ መሆኑን ተከሳሽ በተጨባጭ በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 መሠረት ከሣሽ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ነው፡፡ ጥቅማጥቅምን በተመለከተም በህብረት ስምምነቱ መሠረት ውሣኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት እየታሰበ ሊሰጠው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ይህ አቤቱታ ሊቀርብ ችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት ቦርዱም ሆነ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ነው ሲል ውሣኔው እንዲታረምለት አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪውም ቀርቦ መልሱን በመስጠት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ስህተት ስለሌለበት ውሣኔው ፀንቶ ልሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት ከክርክሩ በመነሳት ጉዳዩ ምን የክስ ምክንያት /cause of action/ ቦርድስ ይህን ጉዳይ ለማየት የሚያስችለው ሕጋዊ ሥልጣን አለው ወይ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ከሥር ውሣኔና አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርመሮታል፡፡

የክስ ምክንያት /cause of action/ አለ ወይም የለም የሚለውን ከማየታችን በፊት የዚህን ቃል ፅንሰ ሃሣብ ማየቱና መረደቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለ ክስ ምክንያት /cause of action/ ፅንስ ሀሳብ በ1958 ዓ.ም. በወጣው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ውስጥ መካተቱን ከሕጉ አንቀጽ 29፣80/2/፣ 224/2/፣ 23/1//ሀ/ … ወዘተ መረዳት የሚቻል ሲሆን ለቃሉ የሰጠው ትርጉም ግን የለም፡፡

በመሠረቱ ማንም ሰው በህግ ችሎታ ኖሮት በሌላ ሰው ላይ ማናቸውንም ክስ ለማቅርብ እንዲችል አስቀድሞ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሠረተበት ነገር ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 ይደነግጋል፡፡ በዚህም ከሣሽ ከተከሣሽ ላይ ሊፈፀም የሚችል መብት አለኝ ብሎ ለማለት አስቀድሞ ለመብቱ መገኘት መነሻ የሆነውን ነገር በማረጋገጥ የተጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ከሣሹ በሕግ መብት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡



ከሕጉ አንቀፅ 80(2) ላይም መረዳት የሚቻለው የክስ ምክንያት ሲባል አንድ ሰው አንድን ነገር ከአንድ ሰው ላይ ለማግኘት ፍ/ቤቱ እንዲወስንለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው የፍሮ ነገር ሁኔታ ሲሆን፣ ይህም ፍሬ ነገር ዳኝነት ለማግኘት የሚያስችል መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ሮበርት አለን ሴድለር "Ethiopian civil procedure" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት መጽሀፍ ላይ "የክስ ምክንያት" አለ ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የቀረበው ነገር ቢረጋገጥ ከሣሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅደሉታል ወይ? ለሚለው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ሲቻል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በግራ ቀኙ መካከል በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ውል ግንኙነት መኖሩ አልተካደም፡፡ ተጠሪው በሥር ያቀረበው ክስ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀፅ 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ልቆጠር ይገባል በማለት ሲሆን፣ ከዚሁ የቋሚ ልሁን ጥያቄው ጋር በተጓዳኝ ያቀረበው ለሌሎች ቋሚ ሠራተኞች የተሰጠው

ጥቅማጥቅም ለእኔም ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለቦርዱ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እነዚህን ጥያቄዎቹን ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ተጠሪው ቋሚ ልሁን ሲል ያቀረበው ዋነኛው ጥያቄ ከአመልካች ጋር አድርጎት የነበረው ውል ባሕርይ እንዲተረጎምለት የጠየቀበት ሲሆን፣ ለሌሎች ሰራተኞች የተጠሰው ጥቅማ ጥቅም ለኔም ይሰጠኝ የሚለው ጥያቄ ደግሞ በውሉ መሠረት ሊያገኝ የሚገባውን ነገር ግን ቀረብኝ ያለውን ጥቅም ለማስከበር የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ የመጀመሪያው የውሉ ባሕርይ እንዲገለጽለት ከመጠየቅ የዘለለ ጥቅም የሌለው ሲሆን ሁለተኛው ግን ውሉ አልተከበረምና ውሉን የጣሰው ወገን የውሉን ቃለ እንዲያከብር እንዲደረግለት የሚጠይቅ ነው፡፡

በመካከላቸው የሥራ ውል የተፈፀመ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተቀበሉበት ጉዳይ ነው፡፡ የሥራ ውል የራሱ ልዩ ባሕሪያት ያሉት ቢሆንም ከአጠቃላይ ውሎች ጋር የሚጋራቸው በርካታ ባሕሪያት እንዳሉትም መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህ አንዱና ዋነኛው ውል ከተፈፀመ በኂላ ይኸው ውል በተዋዋዮች መካከል የአስገዳጅነት ባሕርይ



ያለው መሆኑ ነው፡፡ ተዋዋዮቹ በውሉ የሚገደዱት በመርህ ደረጃ ሁለቱም ስምምነት ላይ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች ከውል የሚመነጭ መብት ለማግኘት የፍርድ ቤት ውሣኔ የግድ አያስፈልጋቸውም፡፡ ውሎች የፍርድ ቤቶች ይሁንታ ሳያስፈልጋቸው በአንዱ ወይም በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ መብትና ግዴታ የሚጥሉ በመሆናቸው ተዋዋዮች ወደ ፍርድ ቤቶች ሊመጡ የሚገባው በውሉ መሠረት አልተፈፀመም የሚሉት ነገር ካለ ብቻ ወይም ውሉ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች እንዲፈርስላቸው የፈለጉ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚሀ ውጪ በተዋዋዮቹ መካከል ያለው የውል ዓይነት እንዲነገር ወይም ውሉ እንዲፀድቅ ለፍርድ ቤቶች ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም፡፡

ይህ አጠቃላይ የውሎች መሠረት ሃሣብ በሥራ ውልም ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 9 የሰፈረው መሠረት ሃሣብ በመርህ ደረጃ አንድ ሰራተኛ ሳልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ የሚገመት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የአዲሱ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9 ድንጋጌም ተመሣሣይ ይዘት ያለው ነው፡፡ ማንኛውም በአዋጁ የሚሸፈን

ሠራተኛ የዚህ የህግ ግምት ተጠቃሚ ነው፡፡ ይህ የሕግ ግምት የሕግ ውጤት እንደመሆኑ የፍርድ ቤት ችሮታ ሳያስፈልገው ውሉ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰራ የሕግ ግምት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከዚህ ሕግ ግምት አንጻር ጎደለብኝ የሚለው ነገር ካለ ከሚጠይቅ በቀር ቋሚ ነህ ልባል የሚል ጥያቄ ሊያቀርብ አይገባውም፡፡ በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የተፈፀመው ውል በሕጉ ግምት የሚሸፈን ሳይሆን አዋጁ በአንቀጽ 10/በአዲሱም አዋጁ አንቀጽ 10/ የሚሸፈን ነው የሚል ክርክር ሊነሳ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ይህም ቢሆን ሊነሣ የሚችለው ሠራተኛው ቀረብኝ የሚለው ጥቅም ወይም በአሰሪው ከሕጉና ከውሉ ውጪ ተፈፀመ የሚለውን በደል ማሳየት ሲችል ነው፡፡ በመሆኑም በኔና በአሰሪዬ መካከል ያለው የሥራ ውል ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚ ነው ተብሎ የተርጎምልኝ የሚለው ክስ የክስ ምክንያት ያለው ባለመሆኑ በቦርድም ይሁን በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቋሚ ልሁን



የሚለው ጥያቄ የአንድን ሠራተኛ የውል ግንኙነት እንጂ አጠቃላይ የሥራ ሁኔታውን የሚመለከት ባለመሆኑ የግል የሥራ ክርክር እንጂ

የወል የሥራ ክርክር አይደለም በመሆኑም ጉዳዩ የክስ ምክንያት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚቀርብም ጉዳይ አይደለም፡፡ ቦርዱ ሥልጣን ያለው የወል የሥራ ክርክሮችን ለመመልከት እንጂ የግል የሥራ ክርክር ለመዳኘት አይደለም፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ተደራራቢ ምክንያቶች ቦርዱ የቀረበለትን ይህን የመጀመሪያ ጥያቄ ማስተናገዱ አግባብ አይደለም፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ሠራተኛው ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠው ጥቅም ለኔም ይጠበቅልኝ የሚል ጥያቄ አያይዞ ያቀረበ በመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ማስተናገዱ የሚያመጣው ለውጥ መኖር አለመኖሩ ቀጥሎ የምንመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ይህ ጥያቄ አስፈሪው የውሉን ወይም የሕጉን ወይም የሁለቱን ድንጋጌ በመፃረር መብቴን ተጋፍቷል የሚል እንደምታ ያለው በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ውሉ የተጣሰበት ወገን

መፍትሄ ፍለጋ ወደሚመለከተው አካል ከሶ መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ ውል ወይም ሕግ ተጥሶ የአንድ ወገን መብት የተጓደለ ከሆነ መብቱን ለማስጠበቅ ክስ ማቅረብ ትክክለኛ አሠራር ነው፡፡ ጥቅም ተጓደለብኝ የሚል ሰራተኛ በሕጉ አንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ነው የሚል የህግ ግምት ተጠቃሚ ስለሆነ ቋሚ መሆኑን ማስረዳት አያስፈልገውም፡፡ ሠራተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስካቀረበ ድረስ ጉዳዩን የሚያየው አካል ቋል እንደሆነ ግምት መውሰድ ይገባዋል፣ ቋሚ እንዳልሆነ ማስረዳት የሌላኛው ወገን ኃላፊነት ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ጥቅም ቀረብኝ የሚል ሠራተኛ የሚያቀርበው ክስ የዛን ሠራተኛ ጉዳይ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በሕጉ አንቀጽ 138 መሠረት እንደግል የሥራ ክርክር የሚቆጠር እንጂ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጥያቄ የሚቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ባይባልም ለቦርዱ ቀርቦ የሚስተናገድ ነጥብ ግን አይደለም፡፡ የወል የሥራ ክርክር ከግል የሥራ ክርክር የሚለየው በምንድነው የሚለው የሕግ ነጥብ ላይ ይህ ፍ/ቤት በመዝግብ ቁ.18180 በሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ አሁን በዝርዝር



መድገሙ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ አንድ ሠራተኛ እሱን ብቻ የሚመለከትና የሌሎችን ሠራተኞች የሥራ ሁኔታ የማይመለከት ክስ ያቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ የግሉ የሥራ ክርክር እንጂ የወል የሥራ ክርክር ሆኖ ሊታይ አይገባውም፡፡ የወል የሥራ ክርክር ካልሆነ ደግሞ ለቦርዱ ቀርቦ ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባ አይሆንም፡፡ በአዋጃ ቁ. 42/85 አንቀጽ 1382 መሠረት በአዲሱም አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 138 የግል ሥራ ክርክርን የማየት ሥልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህም ረገድ ቦርድ የሄደበት አቅጣጫ ሕጉ ካስቀመጠው ሥርዓት ውጪ ነው፡፡ በመሆኑም ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠ ጥቅማ ጥቅም ለኔ አልተጠበቀልኝም የሚለውን አጠቃላይ ክስ ቦርዱ የተመለከተው ከስልጣኑ ውጪ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

ለማጠቃለል ቋሚ ሰራተኛ እንደሆንኩ ይወሰንልኝ የሚለው ክስ የክስ ምክንያት የሌለው በመሆኑና የግል ጉዳይም በመሆኑ፣ የጥቅማ ጥቅም ጥያቄውም የግል ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ቀርበው መታየታቸው የጉዳዩ አመራር የህጉን ሥርዓት

ያልተከተለ በመሆኑ ትክክለኛውን የሕግ ትርጉም ተከትሎ እንዲሄድ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ውሣኔ

1. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሚያዝያ 21/96 ዓ.ም. በቁጥር 303/02/94 የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30835 ሰኔ 16/96 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽረዋል፡፡
2. ውሣኔዎቻቸው የተሻሩ መሆናቸውን እንዲያውቁት የፍርዱና የውሣኔው ቅጂ ይተላለፍላቸው፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



## የሐሳብ ልዩነት

አብዛኛው ድምጽ በተጠሪ የቀረበው አንድም የስራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል መሆኑ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ ሌላም የሚገባኝን ጥቅማ ጥቅም እንዳገኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚለው የክስ ነጥብ የውል የስራ ክርክር ሊሰኝ የሚችል ስለአልሆነ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም ሲል በሰጠው የውሣኔ ክፍል እኔም የምስማማበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥራ ቅጥር ውሌ ላልተወሰነ ጊዜ እንደሆነ ይወሰንልኝ በሚል አይነት የቀረበው የተጠሪ አቤቱታ “ የክስ ምክንያት” የለውምና በፍርድ ቤት ጭምር ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም በሚል ዋነኛ ምክንያት ውድቅ በመደረጉ ባለመስማማት እንደሚከተለው በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

አንድ ከሣሽ ክስ በመሰረተበት ነገር ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን በማሳየት በሕግ አግባብ ዳኝነት ይሰጥለት ዘንድ መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህን ከ ላይ በአብዛኛው ድምፅ በተሰጠው ውሣኔ ውስጥ ከተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ጭምር መረዳት ይቻላል፡፡ ክሱ ጥቅም ወይም መብት የተጠየቀበት መሆኑን ለማሳየት

የቻለ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ጉዳዩ የክስ ምክንያት ያለው ነው ለመሰኘት ይበቃል፡፡

በስራ ክርክር ጉዳይ በሚቀርቡ ክሶች እንዲጠየቅ የሚፈለገው ዳኝነትም ከዚህ አጠቃላይ መርህ በተለየ ሁኔታ እንዲታይ የሚያስገድድ ሕግ የለም፡፡ ስለሆነም አንድ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ክስ ደመወዝ፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሥራ ስንብት ክፍያ ወዘተ… ሊከፈለኝ ይገባል በሚል አይነት የጥቅም ጥያቄን መሠረት አድርጐ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አለዚያም እድገት ይሰጠኝ፣ ዝውውር ላገኝ ይገባል፣ የተወሰደብኝ የዲሲፒሊን እርምጃ ተገቢ አይደለም ወዘተ… የሚሉ የመብት ጥያቄዎችን ብቻ መሠረት አድርጎ ሊቀርብ ይችላል፡፡ እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ የተጠቀሱት የክፍያ ወይም የመብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄዎች ለሥራ ክርክር ጉዳይ በተናጥልም ሆነ በጥምር የክስ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ከአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 138፣142፣162 ወዘተ … መንፈስም መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ ቅጥሩ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንለት በአቀረበው ክስ ጠይቋል፡፡



በተጨማሪም ይገባኛል የሚላቸው ጥቅሞች መኖራቸውን እና አመልካቹ ጥቅሞቹን የከለከለውም ቅጥሩ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑን ስለአልተቀበለለት መሆኑን በክሱ አመላክቷል፡፡ የክሱም አቀራረብ የሥራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ነው ቢሰኝ ያጣቸው ጥቅሞች ያለ ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ እንደሚከበሩለት ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ የተጠሪ የሥራ ውል የተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑን እና ጥቅሞቹ ያለተሰጡትም ቅጥሩ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ባለመሆኑ ምክንያት መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡

ይህ የክርክራቸው ይዘት አመልካች እና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን የሥራ ውል በየራሳቸው እንደሚጠቅማቸው የተረጎሙት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ግራ ቀኙ በተጠሪ የሥራ ውል ሁኔታ ላይ ማለትም የተጠሪ የሥራ ውል የተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ፍሬ ነገር ላይ ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ይህ ልዩነታቸው ሊፈታ የሚችለው በፍርድ እንደመሆኑም ጉዳይ ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሊቀርብ እና የሥራ ውሉ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 ወይም 9 የሚሸፈን መሆኑ

አለመሆኑ ተጣርቶ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል፡፡ በእርግጥ በዚህ አይነት የሚቀርቡና የሥራ ውላችን ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ይረጋገጥልን በሚል መልኩ የሚመሰረቱ ክሶች በቀጥታ የጥቅም ጥያቄን የያዙ ክሶች አለመሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን የሥራ ቅጥር ውሌ በአሰሪው ከሕግ ውጭ የተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል እንደሆነ ተወስዶብኛልና ሊታረምልኝ ይገባል የሚል ይዘት ያላቸው እንደመሆናቸው መሠረታቸው የመብት ጥያቄ መሆኑ አከራካሪ ሊሆን የሚይገባው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ይህን መሰሉ ጥያቄ በአንድ ክስ ውስጥ ለብቻው ቀርቦ ዳኝነት ቢጠየቅበት እንኳን ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚሰኝበት በሕግ የተደገፈ ምክንያት አይኖርም፡፡ ጉዳዩ የእራሱ የሆነ የክስ ምክንያት ያለው በመሆኑም ጭብጥ ሆኖና ከአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 9 እና 10 ጋር ተገናዝቦ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ክሱ ከሳሹ ቀረብኝ የሚባልን ጥቅም በሚጠይቅ መልኩ የቀረበ እንዲሆን አያስፈልግም፡፡ ይልቁንም የቀረበው ክስ ቀረብኝ የሚባልን ጥቅም ብቻ ጠቅሶ የቀረበ ቢሆን እንኳን የጥቅም ይገባኛል ጥያቄው ውሣኔ ከማግኘቱ አስቀድሞ ቅጥሩ የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ



ጊዜ የመሆኑ ነገር ከሕጉ አግባብ ታይቶ ምላሽ ያገኝ ዘንድ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ይህ ሁኔታ ሊያጋጥም እና የሥራ ውሉ የሚሸፈነው በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9 ነው? ወይስ 10? የሚል ክርክር ሊነሳ እንደሚችልም በአብዛኛው ድምፅ ጭምር መታመኑን ከውሣኔው መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ይረጋገጥልኝ በሚል አይነት የሚቀርብ ክስ  የክስ ምክንያት የለውም የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የሚገባ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የክስ ምክንያት ያላቸውም የሚባሉ ክሶች በይዘታቸው ተከሣሹ ክሱ በተመሰረተበት ጉዳይ ላይ የውልም ሆነ የሕግ ኃላፊነት እንደአለበት የሚያመለክቱ አይደሉም፡፡ እንዲህ ያሉ ክሶች ከመሰረቱም ክሱ ተከሣሹ ላይ ሊመሰረት የቻለበትን ሕጋዊ ምክንያት ለማሳየት የሚበቁም አይደሉም፡፡ ጉዳዩ ተከሣሹን የማይመለከተው መሆኑ ግልፅ ከመሆኑ የተነሳም ወደ ክርክሩ ፍሬ ነገር መግባቱ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ተረጋግጣ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ምክንያት ይዘው የሚመሰረቱ ክሶች ግን አሰሪ የሆነው ተከሣሽ ቅጥሩ የተወሰነ ጊዜ

የሥራ ውል መሆኑን እስከአላስረዳ ድረስ የሥራ ውሉን ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ያደረገው ዘንድ የሕግ ኃላፊነት እንዳለበት የሚያመላክቱ ናቸው በተጨማሪም በዚህ መዝገብ የተያዘውን ክርክር ጨምሮ በሌሎች በርካታ መሰል ሙግቶችም ውስጥ ተከታይ ጥቅሞችን ያለክርክር ለማስገኘት የሚበቃን የሙብት ጥያቄ መሰረት አድርገው የሚመሰረቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም የክስ ምክንያት የላቸውም የሚባሉ አይሆኑም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የዚህ መዝገብ ተከራካሪዎች ልዩነት የቅጥሩን የቆይታ ጊዜ ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ በጥቅሞቹ አከፋፈል ጉዳይ ላይ ስምምነት እንጂ ልዩነት እንደሌላቸው ግልፅ ነው፡፡ የተጠሪ የሥራ ውል በሕግ አግባብ ተመዝኖ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ቢረጋገጥ ተጠሪው ጥቅሞቹን ሊያገኛቸው እንደሚችል በአመልካቹ ጭምር የታመነ መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተጠሪ የሥራ ውል የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ ጊዜ ውል መሆኑ በፍርድ ሳይረጋገጥ ተጠሪው ጥቅሞቹን ያገኛል ወይም አያገኝም የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ እንደማይችል የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው የሥራ ቅጥሩ ሁኔታ አስቀድሞ ሳይፈታ



የጥቅም ጥያቄው ጉዳይ ምላሽ ሊያገኝ እንደማይችል እየታወቀም የክሱ ዋና ክፍል የሆነው የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ተረጋገጦ ይወሰንልኝ የሚለው የተጠሪ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም መባሉ ሕጋዊ አሳማኝነት የሌለው ነው፡፡

በእኔ እምነት የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ይወሰንልኝ በሚል አይነት የሚቀርቡ ክሶች ምንም እንኳን የወል የሥራ ክርክር ባለመሆናቸው ምክንያት በአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሊታዩ የማይችሉ ቢሆኑም የግል የሥራ ክርክር አይነቶች በመሆናቸው በፍርድ ቤት ሊዳኙ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ጥያቄዎች የክስ ምክንያት የላቸውምና የትኛውም የዳኝነት አካል ዘንድ ሊቀርቡ አይችሉም በሚል በአብዛኛው ድምፅ በተሰጠው የውሣኔ ምክንያት ባለመስማማት ስሜ በሦስተኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኛ በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የሰበር መ.ቁ. 16624

ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ

መልስ ሰጭ፡- የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ

*ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ለሰጠው ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ አቤቱታ - የፍትሐብሔር ስነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 6/1/*

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ውሳኔውን የሰጠው ሀሰተኛ የኑዛዜ ሰነድን መሰረት አድርጎ በመሆኑ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረበችውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ጥያቄው የቀረበው አመልካች ይግባኝ ካቀረበች በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ።



ውሳኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል።

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት መሆን አለበት።
2. በውሳኔው ላይ ይግባኝ ከቀረበ የይግባኙ መዝገብ ቢዘጋም ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም።

የሰበር መ/ቁ. 16624

ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ ጠበቃው ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ ቀርባለች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

ይህ መዝገብ ተከፍቶ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሐምሌ 19 ቀን 1996 ዓ.ም. ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገችው ማመልከቻ መነሻ ነው፡፡



ከመዝገቡ ለመመልከት እንደተቻለው ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሟቹ ወታደር በቀለ መኩሪያ ሚያዝያ 8 ቀን 1989 ዓ.ም. አድርጓል በተባለው ኑዛዜ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ታህሣስ 17 ቀን 1994 ዓ.ም. ባቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ የተመለከተው ፊርማ ተመርመሮ የተናዛዡ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ውድቅ በማድረግ ወስኖ ከቆየ በኋላ የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የምትለው የአሁኗ አመልካች ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ፍ/ቤቱ ለሰጠው ውሣኔ መሠረት የሆነው ለፖሊስ ቴክኒክ ምርመራ ተልኮ እንዲመረመር የተደረገው የኑዛዜ ሰነድ ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር የተያያዘው ትክክለኛው ሰነድ ሣይሆን በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ ባቀረበችው አቤቱታ ላይ የአሁኗ ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት ካደረገ በኋላ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. በሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው የይግባኝ ቅሬታ ከመቅረቡ በፊት ነው፡፡ በቀረበው ጉዳይ ግን አመልካች ቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ለይግባኝ

ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባለች፡፡ የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ ከቆየች በኋላ ይግባኙን በማቋረጥ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6 መሠረት ዳኝነት ይታይልኝ የሚል ጥያቄ ልታቀርብ አትችልም በሚል ምክንያት ሣይቀበላት ቀርቷል፡፡

አመልካች የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/4/ ዳኝነት እንደገና ሊታይ ይገባል አይገባም በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት አይቻልም ስለሚል ፍ/ቤቱ የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚለውን በቀጥታ ለሰበር ችሎት ልታቀርብ ችላለች፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ እንደገና ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያስፈልገዋል ተብሎ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ማመለከቻውም ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ደርሷት ቀርባ በጽሁፍ መልስ ሰጥታበት ተከራክራለች፡፡

ይህ ችሎት በበኩሉ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባም የተባለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6/1/ ማናቸውም ሰው ፍርዱን ወይም ውሣኔውን



ለሰጠው ፍ/ቤት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በቀረበው ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ፍ/ቤቱ አስቀድሞ በሰጠው ውሣኔ ላይ ለከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በፍ/ቤቱ ለምርመራ እያለ ሲቀጥር መቆየቱ ተረጋግጧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የይግባኙን መዝገብ አስቀርቦ በተመለከተበት ጊዜ ሁሉ ይግባኙ በእንጥልጥል ላይ ነበር፡፡ አመልካች ይግባኙን አዘግቻለሁ የምትለው ፍ/ቤቱ የይግባኙን መዝገብ በማስቀረብ ለምርመራ ተበሎ መቀጠሩን በማረጋገጥ ከመለሰው በኋላ ነው፡፡ አመልካች ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርባለች አላቀረበችም የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ማቅረቧ ከተረጋገጠ በኋላ ይግባኙን ለሚሰማው ፍ/ቤት መዝገቡ እንዲዘጋላት ጠይቃ አዘግታ መቅረቧ የይግባኝ ቅሬታ አላቀረበችም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ አመልካች ይግባኝ ማቅረቧ ከተረጋገጠ ከላይ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት እንደገና ዳኝነት ይታይልኝ በሚል የምታቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት

አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበታል በሚል ምክንያት እንደገና ዳኝነት ሊታይ አይችልም በሚል በሰጠው ብይን ተፈጽሟል የሚባል የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ በፍ/መ/ቁ.3324, ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡



የሰበር መ.ቁ. 16720

ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት አበራሽ ጉቱ

መልስ ሰጭ፡- 1. የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት
2. አቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት
3. ተንዳሆ እርሻ ልማት ድርጅት
4. የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት

*ፍርድ እንዲፈጸም ስለማቀርብ ማመልከቻና ስለ አፈፃፀሙ ስነስርዓት - ለፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት - ጉድለት ያለበት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ*

*ስለማስጥበት ስርዓት፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378፣ 384፣ 385/1/*

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ሰጭዎች ለአመልካች ብር 167,831.94 እንዲከፍሉ፤ አመልካች በበኩላቸው ለመ/ሰጭዎች ብር 17,183.94 እንዲከፍሉ፤ ከሰጠው ውሳኔ አመልካች ለመ/ሰጪ ብር 17,182.50 እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመለወጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ/ብር 17,182.50/ መ/ሰጭዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ በመወሰኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ ቀደም ብሎ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ የተወሰነውን እና በጠቅላይ ፍ/ቤቱ በኋላ የተሻሻለውን ብር 17,182.50 ቀንሰው ቀሪውን ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲስተካከልና በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈል ትዕዛዝ እንዲሰጥ በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ አመልካች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሳኔ ባለማያያዙ በውሳኔው መሠረት ትእዛዝ ሂሳብ ሲሰራ ይችል ስላልነበርና በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፍል የተሰጠ



ውሣኔ ባለመኖሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ ትክክል ነው በሚል ውድቅ በማድረጉና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. በአንድ ውሣኔ ላይ በከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ባለመብት የሆነበት የውሳኔ ክፍል እንዲፈጽም ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡
2. የአፈፃፀም ማመልከቻው የቀረበለት ፍ/ቤትም ውሳኔው ካልታገደ በቀር አፈጻጸሙን ሊቀጥል ይገባዋል፡፡
3. ከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ከፊል ባለመብት የሆነበት የውሳኔ ክፍል እንዲፈጸምለት የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቶ ከፊል ባለዕዳ በሆነበት የውሳኔ ክፍል ይግባኝ ካቀረበና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም ውሳኔ ከሰጠ ባለመብቱ አዲስ የአፈጻጸም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው፤ ሌላ የአፈጻጸም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞው የአፈጻጸም መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እና የተሻሻለው ውሳኔ እንዲፈጸምለት ለማድረግ ይችላል፡፡

4. የመጀመሪያው የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ተፈጽሞ ያለቀ ቢሆንም እንኳን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው በቀድሞው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዳይቀጥል የሚከለክል ምክንያት የለም፡፡

5. የአፈጻጸም መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የቀረበው ጥያቄ ትክክል ያልሆነ ህግ ተጠቅሶ የቀረበ ቢሆንም እንኳን ማመልከቻው እንዲስተካከል ፍ/ቤቱ ያዛል ወይም ፍ/ቤቱ ራሱ አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት አድርጎ ጥያቄውን ይመረምራል እንጅ ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ አይገባም፡፡

6. በአፈጻጸም ደረጃ ወለድ እንዲከፈል ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት የሚችለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ውሳኔ ከተሰጠ ነው፡፡



መ/ቁ. 16720

ጥቅምት 22 ቀን 1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሒሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ ወኪል ሚደቅሳ ጉቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የመካከለኛ አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

2. አቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት አልቀረቡም፡፡

3. ተንዳሆ እርሻ ልማት አልቀረቡም፡፡

4. የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በ7/7/93 ጽፈው ያቀረቡትን የአፈፃፀም ማመልከቻ መሠረት በማድረግ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለሥር ፍ/ቤት በፃፉት አቤቱታ

የአሁኑዎቹ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 167831.94 /አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ሲወስንባቸው በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከሀምሳ ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍሉ የተወሰነውን ገንዘብ በተመለከተ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ውሣኔው የተሻረ በመሆኑ ቀደም ሲል ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ የተወሰነውን ብር 17182.50 ቀንሶ ቀሪውን ገንዘብ ብቻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲያስተካክል እና እንዲሁም በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈል ትእዛዝ እንዲሰጥ አመልክተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ ለአፈፃፀም መሠረት በሆነው በመ/ቁ 639/82 ሐምሌ 30 ቀን 1983 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ አመልካች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ ከመዝገቡ ጋር ስላላያያዙ ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ



የሰጠው በዚሁ ውሣኔ መሠረት ሲሆን ትእዛዝ በተሰጠበት ወቅት ፍ/ቤቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ ሂሣቡን ሊሰራ ስለማይችል የሰጠው ትእዛዝ ትክክለኛ ስለሆነ የሚታረም አይደለም፣ በተፈረደው ገንዘብ ላይም ወለድ እንዲከፈል የተሰጠ ውሣኔ ስለሌለ የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም የጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪዎች ብር 17182.50 እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሣኔ የሥር ፍ/ቤት እንዲፈፀም ትእዛዝ አለመስጠቱ የተሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ወይም የሚሽር ስለሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘብ እንዲከፈለኝ እና በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ቀደም ሲል አመልካች በመ/ቁ 639/82 ሐምሌ 30/1983 በተሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው በውሣኔው መሠረት ተፈጽሞ ጉዳዩ አብቅቷል፡፡ በወቅቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ከአፈፃፀም ማመልከቻው ጋር አያይዘው አላቀረቡም፡፡ ስለዚህ አዲስ አፈፃፀም መዝገብ ከሚከፍቱ በቀር የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ መሠረት አድርገው የቀድሞ አፈፃፀም ትእዛዝ እንዲስተካከል ያቀረቡት ጥያቄ ሥነ-ሥርዓትን ያልተከተለ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን በዚህም ጉዳይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ አንድ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻን የአቀራረብ እና የአፈፃፀም ሥርዓት ነው፡፡

አንድ የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት የሚጀምረው የተፈረደለት ሰው /የፍርድ ባለመብት/ በፍርዱ መሠረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም



ማመልከቻ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ ነው /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/1/ ይመለከቷል/፡፡ በመሆኑም አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከማቅረቡ በፊት የተፈረደ ፍርድ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ እንዲፈፀም በሚቀርበው የፍርድ ውሣኔ ደግሞ ከሳሽ ከጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ውስጥ ከፊሉ ተወስኖለት ከፊሉ ውድቅ የሚደረግበት ወይም በከፊል አንደኛው ተከራካሪ ወገን በከፊል ደግሞ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ባለመብት ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በመሆኑም በከፊል ባለመብት የሆነው ወገን ወይም ከፊል የዳኝነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ወገን በተወሰነበት ጉዳይ ወይም ውድቅ በተደረገበት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ይግባኝ ጠይቆ በተፈረደለት መጠን ብቻ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ሲያገኝ ባለመብቱ አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው አዲስ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅር ብቻ የቀድሞውን የአፈፃፀም መዝገብ ከማንቀሳቀስ የሚከለክለው ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይ የሚለው በዚህ ጉዳይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ነው፡፡

በመሠረቱ የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት ዓላማው በአንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ባለመብት የሆነውን ሰው ውሣኔው ወይም ትእዛዙ ያስገኘለት መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ በመሆኑ አንድ ፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ እስከቀረበለት ድረስ ውሣኔው እንዲፈፀም ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት ይገባዋል፡፡ በመሆኑም በአንድ ውሣኔ ላይ ከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ባለመብት የሆነበት የውሣኔ ክፍል ሊፈፀም የሚችል እስከሆነ ድረስ ይኸው የውሣኔ ክፍል እንዲፈፀም ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ የአፈፃፀም ማመልከቻ የቀረበለት ፍ/ቤትም፣ ውሣኔው ካልታገደ በቀር አፈፃፀሙ ሊያቆም ስለማይችል /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 332 ይመለከቷል/፣ አፈፃፀሙን ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ ይግባኝ የተባለበት ከፊል የውሣኔው ክፍል ግን ሊፈፀም የሚችለው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ የመሻር፣ የመለወጥ፣ ወይም የማሻሻል ስልጣን አለውና ነው፡፡ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም ውሣኔ ከሰጠ ባለመብቱ፣ አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት



ሳያስፈልገው፣ ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞ የአፈፃፀም መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እና ውሣኔው እንዲፈፀምለት ለማድረግ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ተፈጽሞ ያለቀ ቢሆንም እንኳን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በቀድሞው መዝገብ ላይ እንዳይቀጥል የሚከለክል ነገር የለም፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 378/3/ሪ/ እና ቁጥር 384ም አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከቀረበ በኋላ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በተለያየ ጊዜ ሌላ ማመልከቻ እየቀረበ ነገሩን ለማንቀሳቀስ እንደሚቻል ማመልከታቸው ባለመብቱ አዲስ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በቀድሞ መዝገብ እንዲፈፀም ማድረግ የሚቻል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የዚህም አላማ በአንድ ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በአንድ መዝገብ ተጠቃሎ እንዲፈጸም ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም በከፊል የውሣኔው ክፍል ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ያቀረበ ወገን ይግባኝ ያለበት ጉዳይ እስኪወሰን ሳይጠብቅ የፍርድ ባለመብት የሆነበት ጉዳይ ብቻ እንዲፈፀም ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይግባኝ ያለበት ጉዳይ ከተወሰነለት ደግሞ አዲስ

መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞውን መዝገብ አንቀሳቅሶ በይግባኝ የተወሰነለትን ፍርድ ሊያስፈጽም ይችላል፡፡

ከዚህ በመነሳት ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በመ/ቁ. 639/82 በ30/11/83 የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ለአመልካች 163529 ብር እና የዳኝነቱን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲወስን አመልካች ደግሞ ለተጠሪዎች 17182.50 ብር ከነዳኝነቱ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 657/84 በ26/9/84 በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመለወጥ 17182.50 ብር ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በመሆኑም አመልካች በከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲከፈላቸው ከተወሰነላቸው ብር 163529 በተጨማሪ ብር 17182.50 እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡

ነገር ግን አመልካች የመጀመሪያ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡ እንዲፈጸምላቸው የጠየቁት በመ/ቁ. 639/82 የተሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ በወቅቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፈጸም የቀረበ ጥያቄ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት



እንዲፈፀም የሰጠው ትእዛዝ ትክክል ነበር፡፡ ነገር ግን አመልካች ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው አስወስነዋል፡፡ በመሆኑም አዲስ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልጋቸው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጸምላቸው ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው መጠየቃቸው የሥ/ሥ/ሕጉ የሚፈቅድላቸው ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች ማመልከቻውን ሲያቀርቡ የጠየቁት የአፈፃፀም ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 እና 208 መሠረት እንዲያስተካክል በመሆኑ ለጥያቄአቸው መሠረት ያደረጓቸው የሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ቢሆንም አንድ ባለጉዳይ አቤቱታውን ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ ሕግ የመጥቀስ ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ አመልካች የተሳሳተ የሕግ አንቀጽ በመጥቀሳቸው ብቻ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡ የቀረበለትን ማመልከቻ አግባብነት ካለው የሕጉ ድንጋጌ ጋር መመርመር ተገቢውን መፈፀም የፍ/ቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ማመልከቻው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት አልቀረበም የሚልበት ምክንያት ካለው እንኳን አቤቱታው ተስተካክሎ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 385/1/ ይመለከቷል/፡፡

አመልካች በይግባኝ ፍ/ቤት የተሰጣቸውን ፍርድ ለፌ/መ/ደ ፍ/ቤት ስላቀረቡ ፍ/ቤቱ ውሣኔው መሠጠቱን አውቋል፡፡ ስለዚህም በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው ተገቢውን ትእዛዝ ከመስጠት ፋንታ አመልካቹ የተጠቀሱት የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ በመሣሣቱ ብቻ አቤቱታውን ውድቅ በማድረጉ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

ሌላው አመልካች የጠየቁት በተፈረደው ዋና ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ በርግጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/3/ሰ/ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ በፍርዱ መሠረት የሚጠየቀው የገንዘብ ልክ ከነወለዱ እንዲገለጽ ያዛል፡፡ ነገር ግን ይህ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ በዋናው ውሣኔ ላይ ወለድ እንዲከፈል የተሰጠ ውሣኔ ካለ ይኸው ወለድ ተሰልቶ ትክክለኛው አሀዝ በአፈፃፀም በማመልከቻው እንዲገለጽ የሚያዝ እንጂ ውሣኔ ያልተሰጠበትን የወለድ ክፍያ የአፈፃፀም ፍ/ቤቱ እንዲያስከፍል ስልጣን የሚሰጠው አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ የአፈፃፀም ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ከማስፈፀም አልፎ ውሣኔ ያልተሠጠበትን ጉዳይ እንዲፈፀም የማድረግ ስልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ በሰጡት ውሣኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡



**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/90 በመጋቢት 20 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8076 በግንቦት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ እና የዳኝነቱን ብር 671.00 /ስድስት መቶ ሰባ አንድ/ በድምሩ 17853.50 /አስራ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሣ ሦስት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡
3. አመልካች በጠየቁት የገንዘብ መጠን ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ ወለድ ሊከፈላቸው አይገባም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 16896

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡** - ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

**መልስ ሰጪ፡** - የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ

*ውል - የውል ጉዳይ አወሳሰን - የውሎች ውጤት፡ -*

*የፍትሐብሔር ሕግ 1711፣ 1731/1/*

አመልካችና መ/ሰጪ በገቡት ውል አንቀጽ 24 ግራ ቀኙ እርስ በእርሳቸው ካልተስማሙ አንዱ ወገን በሕግ ወይም በሽምግልና መጠየቅ ይችላል በሚለው ድንጋጌ ክርክሩ በሽምግልና ብቻ ይታያል ተብሎ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም በማለት አመልካች ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጐ የኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ውሣኔ በመስጠቱና ውሣኔው በበላይ ፍ/ቤቶች በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡



<u>**ውሣኔ**</u> የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡
2. በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው፡፡
3. የተጠቀሰው የውሉ ድንጋጌ አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኝነት የሚታይ መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ፍ/ቤት ይህንኑ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፡፡

ጥቅምት 16 ቀን 1998

የመ/ቁ. 16896

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ ቀረበ፡፡

መልስ ሰጭ፡- የኢሊባቡር ዞን ትምህርት መምሪያ - ቀረበ

ፍርድ

ለሰበር ችሎቱ ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ መልስ ሰጭ የአሁኑ አመልካችንና ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ በተባለ ድርጅት ላይ ውልን መሠረት አድርጐ በአጠቃላይ 184.559.26/አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሺ አምስት መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፈለው በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጭ በበኩሉ በውሉ መሠረት ጉዳዩ በግልግል ዳኛነት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ፍ/ቤት እንዲቀረብ



የተደረገው አላግባብ መሆኑን ገልጾ በመቃወም መልስ ከመሰጠቱ በተጨማሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15803 ገላጋይ ለመምረጥ እንዲቻል ክስ ያቀረበ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ መልስ ሰጭ ብር 31.111.40/ሰለሣ አንድ ሺ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአርባ ሣንቲም/ እንዲከፍልና ክርክሩ ላስከተለው ወጭና ኪሣራ በቁጥር 300/ሦስት መቶ ብር/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ በበላይ ፍ/ቤቶች ፀንቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰበር እንዲታይለት ባቀረበው አቤቱታ ላይ ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል መሠረት አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት የሚታይ መሆኑ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤት ይሄን አልፎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሣ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ የመ/ሰጭን መልስና የአመልካችን የመልስ መልስ አድምጧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በግራቀኝ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሲነሱ በውላቸው መሠረት በግልግል ዳኝነት ይታያል የተባለው የውል ቃል ታልፎ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲታይ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በዋንኛነት መመርመርና መወሰን ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

ከጉዳዩ አጠቃላይ ሁኔታ እንደተረዳነው በአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጭው መካከል ቀኑ በግልጽ ባልተመለከተ የውል ሰነድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ለማድረግ ውል የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለሥራው ማስጀመሪያ የሚሆን ቅድመ ክፍያ የአሁኑ አመልካች ከመ/ሰጭ ላይ ከተቀበለ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት በስምምነት መጨረስ ባለመቻላቸው የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭ በዞኑ ፍ/ቤት ክስ ከመመስረቱ በፊት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገላጋይ ዳኛ ለማስመረጥ ክስ የመሠረተ መሆኑን ታውቋል፡፡ በተጨማሪ የዞኑ ፍ/ቤት አሁን የቀረበውን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተቃውሞውን በብይን ውድቅ በማድረግ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት «በውሉ አንቀጽ 24 መሠረት ግራቀኙ እርስ በእርሣቸው ካልተስማሙ አንዱ ወገን በሕግ ወይም በሽምግልና መጠየቅ ይችላል፡፡» ይላል እንጂ ጉዳዩ በሽምግልና ብቻ ይታያል ተብሎ የተቀመጠ ግዴታ ስለሌለ ተቃውሞውን አልተቀበልነውም የሚል መሆኑን ፍ/ቤቱ በ9/1/95 ከሰጠው ብይን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል



የተደረገውን የውሉን አንቀጽ 24 እንደመረመረው ተዋዋይ ወገኖች በመካከል አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣ ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኝነት የሚዳኝ ስለመሆኑ በሚገባ ተገንዝቧል፡፡

ይህ ሁኔታ በግልጽ ሰፍሮ እያለና በሌላ ፍ/ቤትም አስቀድሞ ክስ የቀረበለት መሆኑ ለዞኑ ፍ/ቤት የተገለፀለት ቢሆንም ፍ/ቤቱ ለመቀበል ሣይፈቅድ ቀርቷል፡፡ እንደሚታወቀው ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የሕጉን አግባብ ተከትለው የተቋቀሙት ውሎች ደግሞ ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ መብትና ግዴታን ስለሚጥሉ እንደሕግ ሆነው የሚያገለግሉ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1731(1) ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካችና መልስ ሰጭ መካከል የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ለመስራት በተደረገው ውል በአንቀጽ 24 ላይ አለመግባባቶች በግልግል ዳኛነት የሚታዩ ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቶ እያለ ፍ/ቤቱ የውሉን አንቀጽ እርሱ በመሰለው ብቻ ተርጉሞ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.06203 በ10/10/96 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፤

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17077

ጥቅምት 14 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል

መልስ ሰጪ፡ - አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ

ውል፡ - ስለዋስትና - በዋናው ባለዕዳ ግዴታ ላይ ስለሚደረግ መለዋወጥ (ዋሱን ሣያስፈቅድ ባለገንዘቡ ለባለእዳው የመክፈያ ጊዜ የማራዘሙ ውጤት)፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1928(1)

አመልካች የእዳ መክፈያ ጊዜውን ዋስ የሆነውን መልስ ሰጭን ሳያስፈቅድ ያራዘመ በመሆኑ መልስ ሰጪ (ዋሱ) ከገባው ግዴታ ነፃ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1928 (2) ዓላማ ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና በባለእዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ነው፡፡
2. የመፈፀሚያ ጊዜ የተያዘላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜያቸው ሲጠናቀቅ ዋስ ላልተፈፀመው ግዴታ ተጠያቂ እንደሚሆን ሁሉ ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ በኋላ ባለገንዘቡ በራሱ ፈቃድ በችሮታ መልክ የሚያደርገው የክፍያ ጊዜ ማሻሻያ ሆነ ሌሎች እርምጃዎች ዋስትና ከተገባለት ከቀድሞ ግዴታ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ለበሰለው እዳ ከመጠየቅ አይድንም፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17077

ጥቅምት 14 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጐስ ወልዱ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡** - ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል - አቶ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

**መልስ ሰጪ፡** - አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ መኰንን ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁኑ አመልካች የእዳ መክፈያ ጊዜውን ዋስ የሆነውን የአሁኑን ተጠሪ ሳያስፈቅድ ያራዘመ በመሆኑ ዋሱ ከገባው ግዴታ ነጻ ነው ብለው ውሣኔ በማስተላለፋቸው ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፤ ተጠሪ ስለደንበኛው በመሆን አውጥቼው ለበረው የብረት ግዢ ጨረታ የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ አመልካችን ተጠቃሚ በማድረግ የሰጠ ስለሆነ የተጠሪ ደንበኛ የሆነው ድርጅት በጨረታ አሸናፊነቱ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና በ10 ቀናት በማቅረብ ውሉን እንዲፈርም ቢጠየቅ ይህን ባለመፈፀሙ የቢድ ቦንድ ዋጋውን ተጠሪ እንዲከፍለው ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ የተለያዩ ነጥቦች ያካተተ መልስ የሰጠ ሲሆን በዋነኛነት ክሳች የተከሳሽ ደንበኛ ማሸነፉን ገልጾ ደብዳቤ ሲጽፍለት ከጨረታ ቅድመ ሁኔታና ከተከሣሽ ፈቃድ ውጭ የፎርማውን ቀን በ10 ቀናት አራዝሟል፡፡ በዚህም ሳያበቃ ለተጨማሪ 5 የሥራ ቀናት እንዲራዘም አድርጓል፡፡ በመሆኑም ክሳሽ ያለተከሳሽ ፈቃድ የግዴታ ጊዜውን በማራዘሙ ከተጠያቂነት ነጻ ነኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም አመልካች የተጠሪ ደንበኛ ጨረታ ያሸነፈ መሆኑን በመግለጽ ጥር 6 ቀን 1994 ዓ.ም. በቁጥር ዝስሮሚ/200/07/94 በተጻፈ ደብዳቤ ውሉን በመፈረም የመልካም ሥራ አፈጻጸሙን በአሥር ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ፣ ይህ ሳይሆን ቀርቶ



ለማደርስ ጉዳት ተከሣሽ በገባው ግዴታ መሠረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ለተከሣሽ ደንበኛ በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል፡፡ የአሁኑ አመልካች በመቀጠል ጥር 21 ቀን 1994 ዓ.ም ቁጥር 2 ዩኤስኦ ኤም/200/05/94 በሆነ ደብዳቤ የተባለውን ጊዜ በ5 ቀናት ያራዘመ መሆኑን ለተከሣሽ ደንበኛ ገልጸ ጽፏል፡፡ እነዚህ ደብዳቤዎች የተጠሪ ደንበኛ ውል እንዲዋዋልና ዋስትናውን እንዲያቀርብ የተሰጠውን 10 ቀናት ያለ ዋሱ ፈቃድ ማራዘማቸውን የሚያስረዱ በመሆናቸው በሕ.ቁ.1928/2/ መሠረት ዋስ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ከገባው ግዴታ ነጻ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ይግባኙ ውድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

አመልካች በሰበር እንዲታይለት ያቀረበው ማመልከቻ ይህንን ነጥብ የሚመለከት በመሆኑና የሕግ ትርጉም የሚያስነሳ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ መልስና የአመልካች የመልስ መልስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም የማያስፈልገው ነጥብ፣ በዋስትና ውል የተመለተን የአንድ ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜ፣ የመፈፀሚያ ጊዜ ካበቃ በኋላ ባለገንዘቡ የዋሱን ፈቃድ ሳይጠይቅ በራሱ ችሮታ ተጨማሪ የማስፈፀሚያ ጊዜ ለባለዕዳው ሰጥቶ ቢገኝ ድርጊቱ ዋሱን ከተጠያቂነት ነፃ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም? የሚለው ይሆናል፡፡

እንደሚታወቀው ለአንድ ግዴታ አፈጻጸም ዋስ የሚሆን ሰው ባለዕዳ እንዲፈጽም የሚጠየቀውን ግዴታ በተስማማበት ሁኔታ ወይም ጊዜ ያልፈፀመ እንደሆነ ይህንኑ ግዴታ ለባለገንዘቡ ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1920 ላይ ተደንግጓል፡፡ ግዴታውን እንዲፈጽም የሚጠራ ማንኛውም ዋስ ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና ባለዕዳው መካከል የእርሱን ግዴታዎች ያባባሱ አዲስ ስምምነቶችን በማንሳት ግዴታውን ላለመፈፀም መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን ቁጥር 1928/1/ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አንቀጽ በተለይ በንዑስ ቁጥር 2 የዋሱ ፈቃድ ሳይኖር በባለገንዘቡ



የሚደረግ የመክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ተግባር ዋሱን ከነጭራሹ ከተጠያቂነት ነጻ የሚያደርገው መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪ ደንበኛ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትናውን እንዲያቀርብና ውል እንዲዋዋል አመልካች ደብዳቤ መጻፉ ተረጋግጧል፡፡ ዋሱን ጨምሮ ግዴታ የገቡበት የግዴታ መፈፀሚያው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ አመልካች ሌላ ተጨማሪ ቀናት የሰጠ ደብዳቤ መጻፉ ታውቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች በራሱ ፈቃድ ያደረገው የተጨማሪ ጊዜ ችሮታ የእኔን ዋስትና ቀሪ ያደርገዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በዋንኛነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ፣ የአሁኑ አመልካች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜውን ካለዋሱ ፈቃድ አራዝሟል የተባለው መቼ ነው? የሚለው ይሆናል፡፡ ከጉዳዩ በግልጽ መረዳት እንደተቻለው የአሁኑ አመልካች ጥር 6 ቀን 1994 ዓ.ም የተጠሪ ደንበኛ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም እንዲያቀርብና ውል እንዲዋዋል ሲገለጽለት ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርስ ጉዳት የአሁኑ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ገልጿል፡፡ ከሕጉና

ከዚህ ደብዳቤ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ነገር ከተባለው 10ኛ ቀን በኋላ ማለትም ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ማብቂያ በኋላ ባለዕዳው የተመለከቱትን ግዴታዎች ፈጽሞ ካልተገኘ ዋሱ በባለዕዳው እግር ተተክቶ ግዴታውን መፈፀም እንደሚገባው ነው፡፡ በአንጻሩ ከዋሱ ፈቃድ ውጭ ከግዴታ መፈፀሚያ ማብቂያ ጊዜያት በፊት በዋናው ባለዕዳ ግዴታ ላይ የሚደረግ ለውጥ ዋሱን ነጻ የሚያወጣው መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1928/2/ ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓይነተኛ አላማ ከፍ ብለን ለመግለጽ እንደሞከርነው ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና ባለዕዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ጊዜ የተያዘላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች የግዴታ መፈፀማያ ጊዜያቸው ሲጠናቀቅ ዋስ ለግዴታው ተጠያቂ እንደሚሆን ሁሉ ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ በኋላ ባለገንዘቡ በራሱ ፈቃድ በችሮታ መልክ የሚያደርገው የክፍያ ጊዜያት ማሻሻያም ሆነ ሌሎች እርምጃዎች ዋስትና ከተገባለት ከቀድሞ ግዴታ ጋር



የማይገናኝ በመሆኑ ለበሰለው እዳ ከመጠየቅ የሚያድን አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ሕጉ ሊጠብቀው ከተነሳው ዓላማ በመውጣት የአሁኑ አመልካች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜው ያለፈበትን ግዴታ ከዋሱ ፈቃድ ውጪ አራዝሞአል በማለት ዋሱ ከተጠያቂነት ነጻ እንዲሆን የተከተለው አካሄድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ግዴታ የተገባባቸው መፈፀሚያ ጊዜያት ከተጠናቀቁ በኋላ ባለገንዘቡ ለዋናው ባለዕዳ የሚሰጣቸው የችሮታ መፈፀሚያ ጊዜያትም ሆኑ ሌሎች እርምጃዎች ዋሱ ግዴታ የገባበትን የቀድሞውን ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜያት ማራዘሚያ ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም በማለት ይህን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ውሣኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት የቢድ ቦንድ ዋጋ ብር 239,600 (ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይከፈል፡፡

- የዳኝነቱን በታሪፉ መሠረት የጠበቃ አበል 10% ለአመልካች ይክፈል
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ይመለስ።



የሰበር መ/ቁ. 17189

ጥቅምት 17 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡ - የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት**

**መልስ ሰጪ፡ - አቶ ንጉሴ ዘለቀ**

*የስራ ግንኙነትን ስለማቋረጥ - በአሰሪ አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ - ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ስለማቋረጥ - ስለ ደመወዝ - ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ክፍያ ስለሚደረግበት ሁኔታ፡ -*

የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 27/1/በ፣ 53/1/፣54 መልስ ሰጪ የአመልካች ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሆኖ በማሰራበት ወቅት በስሩ የሚገኘውን ገንዘብ ያኘ በተገቢው ሁኔታ ባለመቆጣጠሩ የአሰሪው ድርጅት ገንዘብ እንዲመዘበር ምክንያት በመሆኑ መ/ሰጪ ከስራ የተሰናበተው በአዋጁ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27(1) (በ) መሠረት በአግባቡ ነው በሚል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/ሰጪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለስ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

**ውሣኔ፡** - የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. “ገንዘብ” አንድ ግዙፍነት ያለው ተንቀሣቃሽ “ንብረት” ነው፡፡
2. በአሰሪ “ገንዘብ” ላይ የደረሰ ጉዳት በአሰሪ “ንብረት” ላይ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡
3. የአዋጅ ቁ.42/85 ድንጋጌዎች የስራ ውል በአሰሪው አነሳሽነት በተቋረጠበትና የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው የሚል ውሣኔ በሚሰጥበት ወቅት ሠራተኛው ያልሰራበትን ጊዜ ደመወዝ እንዲያገኝ የሚፈቅዱ አይደሉም፡፡



የመ.ቁ. 17189

ጥቅምት 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብድልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት - አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ንጉሤ ዘለቀ - አልቀረበም

## ፍ ር ድ

ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ ስላቋረጠው ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ እንደመልሰኝ ይወሰንልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ይህ ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙ በጉዳዩ ያቀረቡለትን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ እና የአመልካችን ኦዲተር በምስክርነት ከሰማ በኂላ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው በአመልካቹ ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት

ጉዳት በማድረሱ ምክንያት ስለሆነ ስንብቱ በሕብረት ስምምነቱ እና በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/1//በ/ የተደገፈ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ ይግባኝ በቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሽሮ ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ እንዲሁም ብር 100.00 ወጭና ኪሣራ እንዲከፈለው ተወስኗል፡፡

አመልካች ተጠሪው ወደ ሥራ ሲመለስም ሆነ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተጠሪው ደግሞ በሰጠው መልስ ውዝፍ ደመወዙን የማላገኝበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ወደ ሥራ መመለስን አስመልክቶ ስለቀረበው አቤቱታ የሰጠው መልስ ግን አለመኖሩን ማመልከቻው ያስረዳል፡፡

ይህም ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በክርክሩ ሊፈቱ የሚገባቸው ጭብጦችም የተጠሪ የሥራ ውል መቋረጥ በሕግ የተደገፈ ነው? ወይስ አይደለም? ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው መወሰኑስ የሕግ መሠረት አለው የሚሉት መሆናቸውንም ተገንዝቧል፡፡



ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቹ የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅነቱ የየእለቱ ገቢ ተሰብስቦ ባንክ መግባቱን ማረጋገጥ ሲገባው በጊዜው ገንዘብ ያዥ የነበረው አቶ ስለሺ ታደለ ባዘጋጀው የገንዘብ እና የባንክ መዝገብ ላይ በመፈረም ወይም ሳይፈርም በመተው ጉድለት እንዲፈጽም ረድቶታል በሚል ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ በየቀኑ ከሽያጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ የመቆጣጠር ጉድለት ቢገኝ ገንዘብ ያገኙን መተማመኛ አስፈርሞ በመመሪያው መሠረት እርምጃ የመውሰድ እንዲሁም ገንዘቡ ባንክ ገቢ መደረጉን የማረጋገጥ ጉዳይ በሥራ መዘርዝሩ ላይ የተጠቀሰ የተጠሪ የሥራ ድርሻ መሆኑም በሥር ውሣኔ ተመልክቷል፡፡

ተጠሪ ይህ ኃላፊነት እንዳለበት አልካደም፡፡ የሚከራከረው ገንዘብ ያዡ እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር 1999 ላደረሰው ጉድለት እርሱም ቢሆን ከሥራ አልተሰናበተም ይልቁንም በዚህ ጥፋቱ በተግሳፅ ታልፏል፡፡ ሌሎች ጉድለቶች ተገኝተዋል በተባለበት ጊዜ ደግሞ እኔ እረፍት ላይ የነበርኩ በመሆኑ አይመለከተኝም በሚል አይነት መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመሰረቱ ገንዘብ ያዥው እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር 1999 አጉድሏል የተባለው

ብር 6,221.93 ሲሆን በዚህ ጊዜ ተጠሪው በሥራ ላይ የነበረ መሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲሁም ተጠሪው ገንዘብ ያኘው በዚህ ጥፋቱ በተግሳጽ ብቻ ታልፏል በሚል በቀር እርሱ በዕለቱ ጉድለቱን በማግኘትና በመመሪያው መሠረት ተገቢውን በማድረግ የሥራ ድርሻውን በአግባቡ የተወጣ መሆኑን አላስረዳም፡፡ እንደውም በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪው ያለበትን የሥራ ግዴታ ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ገንዘብ ያገኘ በዚህ ድርጊት በተግሳጽ ታልፏል ማለቱም የእርሱን ኃላፊነትና ግዴታ የሚያስቀርለት አይሆንም፡፡

እንግዲህ ክርክሩን አስቀድሞ የዳኘው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከፍ ሲል ከተጠቀሰው አግባብ በማየት ድርጊቱ ተጠሪው በአመልካች ላይ ጉዳት ማድረሱን ለማረጋገጥ ይበቃል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ሌሎች በተጠሪው ተፈጽመዋል ወደተባሉ ጥፋቶች መሄድ እንደማያስፈልግ በውሣኔው ጠቅሶታል፡፡ በሌላ በኩል ግን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ እንደተፈፀመ የተረጋገጠው ከላይ የተጠቀሰው የገንዘብ ጉድለት ተጠሪውን ከሥራ ለማሰናበት



የሚበቃ መሆን አለመሆኑን አልመዘነም፡፡ በተጠሪ ተፈጽመዋል ወደተባሉ ሌሎች ጥፋቶች ዘልቆ መፈጸም አለመፈጸማቸውንም ለማጣራት አልሞከረም፡፡ ለፍርዱ መሠረት ያደረገው ገንዘብ ያኘው ገንዘብ ባጎደለበት ጊዜ ተጠሪው ሥራ ላይ ስላልነበረ ወደ ሥራ ሲመለስ አልተቆጣጠርክም ተብሎ መሰናበቱ ትክክል አይደለም የሚለውን ምክንያት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፍ/ቤቱ በአመልካች የተነሱትን የክርክር ነጥቦች በሙሉ ቃኝቶ ፍሬ ነገሩን በማጥራት ፍርድ አለመስጠቱን የሚያመላክት ነው፡፡ እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ፍሬ ነገር የደረሰበትን መደምደሚያ አሳማኝ ምክንያት ላይ ሳይመሰረት የለወጠው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመለስ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/1/ ስር ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ሊያቋርጡ የሚችሉ ምክንያቶች የተዘረዘሩ ሲሆን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሚኖረው በአሰሪው ንብረት ወይም ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኛነት ጉዳት ማድረስ የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ እንደሚያቋርጥ የሚደነግገው አንቀጽ 27/1//በ/ መሆኑን

ችሎቱ አምኖበታል፡፡ ችሎቱ እዚህ እምነት ላይ የደረሰው ጉዳዩን ከፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1126 እና 1127 ጋር አገናዝቦ በማየትና # ገንዘብ ; አንዱ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ # ንብረት ; መሆኑን በመቀበል ነው፡፡ በተጨማሪም አንድ ሠራተኛ በአሰሪው የተሰጠውን ኃላፊነት ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት አንድን ነገረ በማድረግም ይሁን ባለማድረግ ሳይወጣው ቢቀርና በዚህ ድርጊቱ ሌላው ሰው በአሰሪው ገንዘብ ላይ በቀጥታ ጉዳት እንደያደርስ ተባብሮ ቢገኝ እራሱ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ሊቆጠር ይገባዋል የሚል ትርጓሜ ለተጠቀሰው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/1//በ/ በመስጠቱ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪው ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ገንዘብ ያዥው ያደረሰውን የገንዘብ ጉድለት መቆጣጠር ሲገባው አልተቆጣጠረም፡፡ ይህ ደግሞ ቢያንስ በከባድ ቸልተኛነት በአመልካች ንብረት ላይ ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ ጉዳት ማድረሱን ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ውሉን መቋረጥ ሕገ ወጥ በማድረግ ተጠሪ ወደ ሥራ እንደመለስ መወሰኑ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ጋር ያልተጣጣመ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



ቀጥሎ ተጠሪ ከሥራ ከተሰናበተ ጊዜ ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ሕጉ ይፈቅዳል ወይስ አይፈቅድም የሚለውን ነጥብ እናያለን፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የሦስት ወር ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ተወስኗል፡፡ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የታዘዘው ሥራ ያልተሠራው በሠራተኛው ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ነው በማለትና የአዋጁን አንቀጽ 54/2/ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም ውሣኔ በአንቀጽ 54/2/ ላይ የሠፈረው ድንጋጌ አባባልና መንፈስ የሚመለከተው የሥራ ውሉ ተቋርጦ የቆየን ሠራተኛ ነው ወይስ ከዚህ የተለየ አኳኋን ያለውን ሠራተኛ ነው የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይህንኑ ለመረዳት ለዚህ አንቀጽ መሠረት የሆኑትን የ53/1/ እና የ54/1/ን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 53/1/ ደመወዝ ማለት # አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉ መሠረት ለሚያከናውነው ሥራ የሚከፍለው መደበኛ ክፍያ ; ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 54/1/ም እንደዚሁ በአዋጁ ወይም አግባብ ባለው ሕግ በተለየ አኳኋን ካልተወሰነ ደመወዝ የሚከፈለው ለተሠራ ሥራ ብቻ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

ከነዚህ ሁለት የተያያዙ የሕግ ድንጋጌዎች የደመወዝን ምንነት እና የአከፋፈል ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአንድ በኩል አንድ ሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈለው ከውል የመነጨ ግዴታውን መፈፀም ሲችል እንደሆነ እናያለን፡፡ የሠራተኛ እና የአሠሪ ግንኙነት የሚመነጨው ሁለቱም ወገን ከሚገቡት ውል ነው፡፡ ይኸው ውል እንደማንኛውም ሌላ ውል ለሁለቱም ወገን መብት ያመነጫል ግዴታንም ይጥላል፡፡ ከነዚህ ተያያዥ መብትና ግዴታዎች አንዱ ሠራተኛው በውል ለማከናወን ቃል የገባውን ሥራ የማከናወን በተሠራው ሥራ መጠን ደግሞ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜና መጠን ደመወዝ የማግኘት መብትና ግዴታ ነው፡፡ በዚህ መሠረት አሠሪው ከሠራተኛው ግልጋሎት ያገኛል፡፡ ባገኘው ግልጋሎት መጠንም በውሉ የተጠቀሰውን ደመወዝ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በመርህ ደረጃ እነዚህ መብትና ግዴታዎች ከውል የሚመነጩ አንዱ ያለሌላው ሊታሰቡ የማይችሉ የአንድ ሕጋዊ ግንኙነት ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሥራ ሳይሠራ ደመወዝ ሊከፈል አይችልም፡፡ ደመወዝ ሳይከፈል ደግሞ ሥራ ሊከናወን አይችልም፡፡ ይህ አጠቃላይ አባባል ከውል ሕግ መሠረተ ሃሳብ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡



ይህ አጠቃላይ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጉ ሠራተኛው ሥራ ባይሠራም ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበትን ሁኔታ በተለየ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 54/2/ ከሁለት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ ሠራተኛው ሥራ ባይሠራም አሠሪው ደመወዝ የመክፈል ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች አንደኛ ሠራተኛው ዝግጁ ሆኖ እያለ አሠሪው ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን መሣሪያና ጥሬ እቃ ሳያቀርብለት የቀረ እንደሆነ ወይም ሁለተኛ ሠራተኛው ሥራ ሳይሠራ የዋለው በራሱ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት እንደሆነ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የተለዩ ሁኔታዎች ከሥራ ውልም ሆነ ከአጠቃላይ የውል መሠረታዊ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጋር ተያይዘው መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጨው ከሥራ ውሉ ነው፡፡ የአሠሪ ደመወዝ የመክፈል ግዴታም የሚመነጨው እንዲሁ ከሥራ ውሉ ነው፡፡ በሌላ በኩል የሥራ ውል ቢኖርም ደመወዝ

የሚከፈለው ለተሠራ ሥራ ብቻ በመሆኑ ሠራተኛው ሥራ ሳይሠራ ደመወዝ እንዲከፈለው ሊጠይቅ አይችልም፡፡ ሠራተኛው በርሱ በኩል ያለውን የመሥራት ግዴታ ሳይወጣ አሠሪው ደመወዝ የመክፈል ግዴታውን እንዲፈጽም ሊጠይቅ የሚችለው ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶቹ አንዱ መኖሩን በማስረዳት ነው፡፡ ስለዚህ በአዋጁ አንቀጽ 54/2/ ያሉት ሁለት መስፈርቶች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በአሠሪና በሠራተኛ መካከል ያለው የሥራ ውል ፀንቶ በሚቆይበትና ሠራተኛው በሥራ ገበታው በሚገኝበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የሥራ ውል በሌለበት ወይም የነበረ የሥራ ውል በተቋረጠበት ሁኔታ የአዋጁ አንቀጽ 54/2/ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

የሥራ ውል በሁለቱም ወገን ሊከበር እንደሚገባና ሊቋረጥ የሚችለውም በሕጉ በሰፈሩ ምክንያቶች ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ አሠራ በአዋጁ አንቀጽ 27 የተጠቀሱ ሁኔታዎች ተሟልተዋል ብሎ ሲያምን ያለማስጠንቀቂያ፣ በአንቀጽ 28 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልቷል ብሎ ሲያምን ደግሞ ሕጉን ተከትሎ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል ሕጉ



ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የሥራ ውልን ለማቋረጥ አሠሪው ክስ መመስረት ሳያስፈልገው የተናጠል እርምጃ የመውሰድ ሕጋዊ መብት አለው፡፡ አሠሪው በዚህ ረገድ የሰጠው ውሣኔ የሥራ ክርክርን መርምሮ የመወሰን ሥልጣን ባለው አካል ታይቶ እስካልተሻረ ድረስ በሁለቱም ወገን የነበረውን የሥራ ግንኙነት ቀሪ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

አሠሪው የሥራ ውሉን ያቋረጠው ሕግ በማይቀበለው ምክንያት የሆነ እንደሆነ ሠራተኛው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ወደአለው አካል ማቅረብ መብት አለው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት አካል አሠሪው የወሰደው ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን በመመርመር ውሣኔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ቀድሞውኑ አሠሪው የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕጉ መሠረት አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ከደረሰ ለሠራተኛው የሚሰጠው መፍትሔ /remedy/ ሕጉ የሥራ ውል አለአግባብ ባቋረጠ አሠሪ ተፈፃሚ እንዲሆን የፈቀደውን መፍትሔ ብቻ ነው፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 43 የሥራውል አለአግባብ ወይም ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ ሲቋረጥ ለሠራተኛው የሚሰጠው መብት በአማራጭ ወደ ሥራ መመለስ ወይም እነደነገሩ ሁኔታ የካሣ ክፍያ

የማግኘት መብት ብቻ ነው፡፡ ሠራተኛ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከማድረግ በተጨማሪ ሠራተኛው ሥራው ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈለው የሚያዝ የሕግ አንቀጽ የለም፡፡ በመሆኑም አለአግባብ ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከማድረግ በተጨማሪ ሥራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ ደመወዙ እንዲከፈለው ማድረግ ሕጉ አይፈቅድም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በመሠረቱ መክፈልም ከተቻለ ደመወዝ የሚከፈለው የሥራ ውል ላለው ሠራተኛ ነው፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ሕገወጥ በሆነ መንገድ ነው ቢባል እንኳ የሥራ ውሉ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እንዲቀጥል ከማድረግ አልፎ ውሣኔው ወደ ኋላ ተመልሶ አሠሪው የሰጠውን ውሣኔ እንዳልተሰጠ መቁጠርና የሥራ ውል እንዳልተቋረጠ በማሰብ ሠራተኛው ሳይሠራ የቀረው በርሱ ጥፋት ባልሆነ ምክንያት ነው ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ሠራተኛው በአሠሪው ውሣኔ ከሥራ እንዲሰናበት ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ሠራተኛው በፍርድ ወደ ሥራ እንዲመለስ በተወሰነበት ጊዜ መካከል የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አለ ሊባል አይችልም፡፡ ለዚህ ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈል ማዘዝም አይቻልም፡፡



በአጠቃላይ ፍርድ ቤቱ አመልካች ውዝፍ ደመወዝ ይከፈል በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት በአላቸው የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎች ትክክለኛ ትርጉም ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ እያንዳንዱ ባለጉዳይ የሚያቀርበውን የሕግ ክርክር መርምሮ ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ተከሣሹ ወገን በሕግ ነጥብ ላይ መልስ ሰጥቶ ባይገኝ ደግሞ የሕግ ጉዳይ የቀረበለት ፍ/ቤት በእራሱ አነሳሽነት በጉዳዩ ጭብጥ ይዞ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ይጠበቅበታል፡፡ ውዝፍ ደመወዝ መከፈል አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ የሕግ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ፍርድ ቤት ከተከሳሹ ወገን የቀረበለት ክርክር ያልነበረ ቢሆን እንኳ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የተጠሪ የሥራ ውል መቋረጥ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27/1//በ/ የተደገፈ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
2. እንዲሁም ይህ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎች በመተርጎም ሕጉ አንድ የሥራ ውል በአሰሪው አነሳሽነት በተቋረጠበትም ሆነ የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በሚል ውሣኔ በሚሰጥበት ሁኔታ ሠራተኛው ያልሰራበትን ጊዜ ደመወዝ እንዲያገኝ የሚፈቅድ አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16329 ሐምሌ 16 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተጠሪ የሦስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡ ይኸው ይፃፍ፡፡

## የሐሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ላይ የተመለከተው ዳኛ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ ለፈፀመው ተግባር የሥራ ውሉ እንዲቋረጥ በማለት በአብላጫው ድምፅ በተሰጠው መደምደሚያ የምስማማ ቢሆንም፣ አብላጫው ድምፅ ተጠሪ ፈፀመ ለተባለው ተግባር ለውሣኔው ዋቢ አድርጐ የጠቀሰው አንቀጽ 27/1/ /በ/ በተጠሪ ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በዚህ የህግ ድንጋጌ ሊሸፈን ባልተገባው ነበር እላለሁ፡፡



የተጠሪ የሥራ ውል በአሰሪው እንዲቋረጥ የተደረገው ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በሚሠራበት ቅርንጫፍ በሥሩ የሚገኘውን ገንዘብ ያዥ በተገቢው ሁኔታ ባለመቆጣጠሩ የአሠሪው ድርጅት ገንዘብ እንዲመዘብር ምክንያት ሆኖአል በሚል ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ይህ አይነቱ ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 27/1/ /በ/ ሥር ይጠቃለላል በማለት መደምደምያ ላይ ደርሷል፡፡ ምንም እንኳን በዚህ አንቀጽ #ንብረት; የሚለው ቃል አገላለጽ #ገንዘብን; የሚያጠቃልል መሆኑን ብስማማበትም በዚህ ጉዳይ ተመዝብሯል ወይም ሌላ ሰው ጥቅም እንዲውለ ተደርጓል የተባለን የአሠሪ ገንዘብ ሆነ ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በአሠሪ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስን በሚመለከተው አንቀጽ ሥር ይጠቃለላል ብሎ ማለት አግባብ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

በአብላጫው ድምፅ የተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የአሰሪውን ንብረቶች በተለይ በማምረት ተግባር ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት

የሚኖራቸውን ንብረቶች ሆነ ተብሎ ወይም በሚያስቀጣ ቸልተኝነት ከሚፈፀሙ የጉዳት ተግባሮች ለመጠበቅ የተደነገገ ድንጋጌ እንጂ የሥራ ተግባርን በመጣስ /Neglect of Duty/ የሚፈፀሙ መሰል የገንዘብ ብክነቶችን የሚሸፍን አይደለም በማለት በመደምደሚያ ሃሣቡ ተስማምቼ በሕጉ አተረጓጐም ላይ በሃሣብ ተለይቻለሁ።



የሰበር መ/ቁ. 17429

ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች: - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

**አመልካች: - ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ**

**መልስ ሰጪ: - አቶ ተስፋዬ ከበደ**

*የኑዛዜዎች ፎርምና ማስረጃ - በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ*

*ፎርም: - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881*

አቶ ከበደ ዳዲ በግልጽ ባደረጉት ኑዛዜ ሰነድ ላይ የኑዛዜ ዝርዝር የአራት ሽማግሌዎች/ምስክሮች/ ስም ከተፃፈ በኋላ እኛ ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው ሽማግሌዎች በትክክለኛ አዕምሮአቸው ሆነው ሲናዘዝ ሰጥተናል ተብሎ የተጠቀሰ ቢሆንም እና ከተናዛዡና ከአራቱ ምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ ይህንኑ ቃል

ለመስማታችን በፊርማችን እናረጋግጣለን የሚል ቢሆንም ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱም ምስክሮች ፊት ስለመነበቡ በግልጽ ያልተፃፈ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመስጠቱና ውሣኔውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

## ውሣኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ሲናዘዙ ሰምተናል፤ አይተናል ተብሎ የተገለጸው የኑዛዜውን መነበብ የሚያመለክት ነው፡፡
2. ኑዛዜው ተነቧል የሚል ቃል በግልጽ አለመስፈሩ ብቻ ኑዛዜውን በምስክሮቹና በተናዛዥ ፊት አልተነበበም በማለት ኑዛዜውን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 17429

ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
ወ/ሮ ሆሣዕና ነጋሽ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ከበደ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁኗ አመልካች በሥር ፍ/ቤት የሟች ባለቤቴ አቶ ከበደ ዳዲ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሠጠኝ ብላ አመልክታ ተጠሪ በተቀዋሚነት ቀርቦ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የአባቴ /የሟች/ አይደለም፣ ኑዛዜው እንዲሻር እኔም ሌላ መዝገብ ያስከፈትሁ ስለሆነ መዝገቦቹ በአንድነት ታይተው ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሁለቱን መዛግብት መርምሮ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበ ይህም ሥርዓት መፈፀሙንና የተፃፈበትን ቀን የማያመለክት ካልሆነ ፈራሽ ነው፣ በኑዛዜው ሠነድ ላይ ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱም ምስክሮች ፊት ስለመነበቡ በግልጽ ያልተፃፈ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ መሠረት ፈራሽ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ አፅንቷል፡፡ አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ሃሣብ የኑዛዜው ፅሁፍ መነበቡን ኑዛዜው የሚያሣይ ሆኖ ሣለ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን፣ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመ የሕግ ስህተት ስለሌለ ፍርዱ ይፅናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ መሠረት የተደረገ አይደለም መባሉ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ጳጉሜ 5 ቀን 1990 ዓ.ም. በተፃፈው የአቶ ከበደ ዳዲ ኑዛዜ ላይ የኑዛዜው ዝርዝርና የአራት ሽማግሌዎች /ምስክሮች/ ስም ከተፃፈ በኋላ



#እኛ ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው ሽማግሌዎች በትክክለኛ አዕምሮዋቸው ሆነው ሲናዘዙ ሰምተናል፤አይተናል; ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ከተናዛዡና ከአራቱ ምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ #ይህንኑ ቃል ለመስማታችን በፊርማችን እናረጋግጣለን ; ይላል፡፡

የፍ/ሕ/ቁ.881/2/ #ኑዛዜው በተናዛዡና አራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸም ሥርዓት /ፎርማሊቲ/ መፈፀሙንና የተፃፈበትንም ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው; በማለት ሲደነግግ የፍ/ሕግ ቁጥር 881/3/ ደግሞ #ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ካላደረጉበት በቀር ፈራሽ ነው; ይላል፡፡

እነዚህ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች አንድ ኑዛዜ አራት ነገሮችን ማለትም ኑዛዜው የተደረገበትን ቀን፣ በአራት ምስክሮች ፊት መደረጉን፣ ኑዛዜው በተናዛቹና በምስክሮች መፈረሙንና መነበቡን ማሣየት እንዳለበት ይደነግጋሉ፤ ከፍ ሲል ከኑዛዜው ፅሁፍ ላይ ወስደን ካሠፈርነው መረዳት የተቻለው ኑዛዜው ጳጉሜ 3 ቀን 1990 በሚል ቀን የተፃፈበት፣ የአራት ምስክሮች ስም ያለበት፣ ምስክሮቹና ተናዛዡ

የፈረሙበት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሌላም በኑዛዜው ላይ #ሲናዘዙ ሠምተናል፣ አይተናል; ተብሎ መገለፁም የኑዛዜውን መነበብ የሚያመለክት ነው፡፡ ሕጉ የኑዛዜውን መነበብ አስፈላጊነት ያስቀመጠው በሚነበብበት ወቅት ሟች/ተናዛዥ የተናገረው በትክክል በፅሁፍ መስፈሩን እንዲረዳና የተናዛዡ ፈቃድ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲቻል ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የኑዛዜው ክፍል #ሲናዘዙ ሠምተናል፣ አይተናል; በሚል የሠፈረው ምስክሮች ያዩትና የሰሙት ኑዛዜው ሲደረግና የተፃፈው ኑዛዜ ሲነበብ ነው ተብሎ መገመት ይኖርበታል፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ኑዛዜውን ለማፍረስ የሚያበቃ የሕግ መሠረት በሌለበት በኑዛዜው ፅሁፍ ላይ ኑዛዜው #ተነቧል; የሚል ቃል ባለመኖሩ ብቻ ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ አልተፃፈም በማለት ፈራሽ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሣ ኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 71/93፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.03644 የሠጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡



ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ. 881 በተደነገገው መሠረት የተከናወነ በመሆኑ የፀና ነው ብለናል፤ ይፃፍ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

## የሃሳብ ልዩነት 184

ስሜ በተራ ቁጥር አራት የተጠቀሰው ዳኛ አብዛኛው ድምፅ የኑዛዜውን ሕጋዊነት በማረጋገጥ በሰጠው ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ የሃሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አሰፍራለሁ፡፡

ከሦስቱ ዓይነት ኑዛዜዎች አንዱ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ነው፡፡ /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 880/ሀ/፡፡ ይህ አይነት ኑዛዜ ለማፅናት በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ይኸም ስርዓት መፈፀምን ማመልከት ይኖርበታል፡፡ /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 881/2/፡፡ ኑዛዜ የሟቹ ጥብቅ የሆነ ራሱ የሚፈፅመው ሥራ ነው፡፡ /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 857/1/ የማንበብ ሥርዓት አስፈላጊ የሆነው በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ሊፅፈው ስለሚችል በሌላ ሰው የተፃፈው ቃል በትክክል የሟች ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ምስክሮቹ ኑዛዜ የተፃፈበትን ቋንቋ ለማወቅና የተፃፈውን ለመስማት ወይም ለማንበብ ራሳቸው ችሎታ ያላቸው መሆንም አለባቸው፡፡ /የፍ/ብ/ሕግቁ.837/

ይህም ድንጋጌ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ የመነበብ ስርዓት አስፈላጊና መነበቡም በትክክል በማያጠራጥር ሁኔታ መፈፀም ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ወደ ጉዳዩ ስንመጣ አብዛኛው ድምፅ ኑዛዜው ተነቧል የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የአቶ ከበደ ኑዛዜ የአራቱን ምስክሮች ስም ከጠቀሰ በኋላ #ሲናዘዝ ሰምተናል አይተናል; እንዲሁም ከተናዛዡና ከምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ ይህንኑ ቃል ለመስማታችን #በፊርማችን እናረጋግጣለን; የሚሉ ቃላቶች በመስፈራቸው ነው፡፡ በእኔ እምነት ምስክሮቹ ሰምተናል አይተናል የሚሉት ሚች ኑዛዜውን በመስጠት ላይ እያለ የተናገረውን ሊሆን ስለሚችል እነዚህ ቃላቶች በርግጠኝነት መነበብን አያመለክቱም ከነዚህ ቃላቶች ሕጉ እንዲፈፀም የሚፈለገውን የማንበብ ሥርዓት መፈፀም አለመፈፀም በትክክል ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ተፈፅሟል ለማለትም ያዳግታል፡፡ ይህ ሕጉ በግልፅ እንዲፈፀም የሚፈልገው ስርዓት መፈፀም ሳይረጋገጥ ደግሞ ኑዛዜው ሊፀና አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሚሽርበት ምክንያት ስለሌለ ሊፀና ይገባል ስል በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17533

ጥቅምት 18 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡ -** የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን

**መልስ ሰጪ፡ -** አቶ ሙሉ አብርሃ

*ስለዲክራሲዮን አሰጣጥ - የመጋዘን ኪራይ ስለሚታሰብበት ጊዜ፡ -*

*የጉምሩክ ባለስልጣን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 60/1989 ዓ.ም.፣ አንቀጽ 2/18/፣ 43/1/ /ሀ/*

አመልካች ከውጭ ያስመጣሁትን እቃ የጉምሩክ ስርአት አልተፈጸመበትም በሚል በመጋዘን በማቆየት ያስከፈለኝን የመጋዘን ኪራይ እና ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ እቃውን ለመሸጥ እንዳይቻል በማድረግ በመጋዘን በማስቀመጥ ለኪራይ እንዳወጣ ያደረገኝን ወጪ እንዲተካልኝ በማለት መ/ሰጪ ያቀረቡትን ክስ በመቀበል መ/ሰጪ በጠየቁት ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሠረት ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ ላደረገው እዳ ያስከፈለውን የመጋዘን ኪራይ የሚመለስበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡
2. የጉምሩክ ባለሥልጣን ዴክላራሲዮን መስጠት የሚችለው በህጉ መሠረት የጉምሩክ ስነ ስርአት ለተፈጸመበት እቃ ብቻ ነው፡፡ የጉምሩክ ስነ ስርአት ላልተፈጸመበት እቃ ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ በእቃው ባለቤት ለሚደርስ ጉዳት የጉምሩክ ባለስልጣን አይጠየቅም፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17533

ጥቅምት 18 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጐስ ወልዱ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ኃ/መለኮት አበበ ቀርቧል፡፡

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ሙሉ አብርሃ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ተከፍቶ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተመሣሣይ መንገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት

መሆኑን በመግለጽ ጥቅምጽ 29 ቀን 1997 ዓ.ም ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገው አቤቱታ መነሻ ነው።

በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት የተጀመረውን ክርክር በመጀመሪያው በፍ/መ/ቁ.34187 ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ ከውጭ አገር በሕጋዊ መንገድ በማስመጣት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሁትን 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት ተከሣሹ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ ይዞ በማቆየት ለመጋዘን ኪራይ ያስከፈለኝ ብር 11.793.10በ ተመላሽ እንዲያደርግልኝ፣ ተከሣሽ በመጨረሻ እቃውን ሲለቅ አብሮ መስጠት የሚገባውን ዲክላራሲዮን ለመስጠት ፈቃደኛ ሣይሆን በመቅረቱና በዚሁ ምክንያት እቃውን በሀገር ውስጥ ለገበያ በማቅረብ ለመሸጥ ባለመቻሌ ለመጋዘን ኪራይ ያወጣሁትን ብር 96.600 እንዲከፍለኝ፣ የእቃውን ዲክላራሲዮንም እንዲሰጠኝ በሚል ባቀረበው ክስ ላይ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን መልስ እንዲሰጥበት አድርጐ ካከራከረ በኂላ ሰኔ 14 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ተከሣሹ ከጉምሩክ ሕግ ጋር በተያያዘ ያነሣቸውን ክርክሮች ውድቅ በማድረግ ክስ የቀረበበትን



ገንዘብ ብር 112.069.95 ከሕጋዊ ወለድ እና ክርክሩ ካስከተላቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች ጭምር ለከሣሹ እንዲከፍል፣ የእቃውን ዲክላራሲዮንም ተከሣሹ እንዲበትን ወስኗል።

የአሁኑ አመልካች ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.32978 የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙን ሠርዞበታል።

ቀጥሎም በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል። አመልካች የአሁን ተጠሪ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት የከፈለው ኪራይ በሕጉ ሊመለስለት አይችልም። የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃው በመጋዘን ለሚቆይበት ጊዜ ኪራይ የማስከፈል ስልጣን አለው። እቃው ተይዞ ሊቆይ የቻለው በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ አንድ ካርቶን የያዘው አንድ ፓኬት የፎቶ ኮፒ ወረቀት ነው ተብሎ ቢገለጽም ሲፈተሽ አንዱ ካርቶን 5 ፓኬት የያዘ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ተጠሪው ከውጭ አገር ያስመጣው 1600 ካርቶን በአጠቃላይ 6400 ተጨማሪ ፓኬቶች የያዘ መሆኑ በተደረገው ፍተሻና ምርመራ ስለተረጋገጠ እቃውን

የመያዝ ሥልጣን አለው፡፡ በእቃው ላይ ተገቢው ቀረጥ ሣይከፈልበት አመልካች ዲክላራሲዮን ለመስጠት አይገደድም፡፡ ተጠሪው እቃውን ከተረከበ በኋላ ለመጋዘን ኪራይ ከፍያለው የሚለውን ገንዘብ የምከፍልበት ምክንያት የለም ባይ መሆኑን በጽሁፍ እንዲቀርብ ያደረገው ማመልከቻ ያስረዳል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለተጠሪው እንዲደርሰው ተደርጐ የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ በተጠሪው በኩል የቀረበው ክርክር፡ -

ተጠሪ የእቃውን መጠንና ብዛት በተመለከተ የሰጠው መግለጫ ትክክለኛ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በአሁኑ አመልካች የተካደ ፍሬ ነገር ስላልሆነ ለሰበር ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪው ስለዕቃው ብዛት አሳስቶ አቅርቧል በሚል የገለፀው ተቀባይነት የለውም፡፡ የቅድመ ጭነት ምርመራ እንዲያደርግ ኃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው ኤስ.ጂ.ኤስ ኩባንያ ሪፖርት ሲያደርግ በዕቃው ብዛትም ሆነ ክብደት ረገድ ስህተት በማድረግ በቀረጥና ታክስ ታሪፍ አመዳደብ ላይ በመንግሥት ገቢና



ጥቅም ላይ ላስከተለው ጉዳትም ሆነ ጥፋት ራሱ ኩባንያው ኃላፊነት ወስዶ ሊከፍል የሚገባው እንጂ እቃ አስመጪው የሚጠየቅበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪው የፈፀመው ጥፋትም ሆነ ስህተት እንደሌለ ታምኗል፡፡ አመልካችም በተጠሪው በኩል የተፈፀመ ጥፋት እንደሌለ እያወቀ እቃው በጉምሩክ መጋዘን እንዲራገፍ በማድረግ ሲጠየቅ ባለማስረከብ በመጋዘን እንዲቆይ ያደረገው ያለአግባብ ነው፡፡ ዲክላራሲዮኑንም የመስጠት ግዴታ አለበት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን አመልካች በበኩሉ በተጠሪው በኩል የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም የሚልባቸውን ምክንየቶች በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ይህ ችሎት በበኩሉ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት በተያዘው ጉዳይ ከሕጉ አኳያ ሊመረመሩ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች፡ -

1ኛ/ እቃ አስመጪው ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው እቃ በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ እንዲከፍል የተደረገው ኪራይ

ይመለስልኝ ብሎ የሚጠይቅበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም? የጉምሩክ ባለሥልጣንስ እቃው በመጋዘን ለቆየበት ጊዜ ያስከፈለውን ኪራይ ሊመልስ ይገባል የሚባልበት ምክንያት ይኖራል?

2ኛ/ የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃ አስመጪው ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው እቃ ብዛት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ ተገልጾ ከቀረበው መጠን በላይ በሚል እና ከቀረጥና ታክስ ጋር በተያያዘ ምክንያት ዲክላራሲዮን አልሰጥም ብሎ መከልከል ይችላል አይችልም?

3ኛ/ የአሁኑ ተጠሪ እቃውን ከተረከብኩ በኂላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቴ የተነሣ ሊሸጥ ባለመቻሉ ሌላ መጋዘን ተከራይቼ ለማቆየት አውጥቻለሁ የሚለውን ገንዘብ የጉምሩክ ባለሥልጣን ለመክፈል ይገደዳል አይገደድም? የሚሉት መሆናቸውን ከመዝገቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በቅድሚያ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ተከፍሏል የተባለው ኪራይ ሊመለስ ይገባል አይገባም የሚለው ክርክር ሲመረመር ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በባለሥልጣኑ እንዲከፍል የተጠየቀውን ኪራይ ብር 11,793.10 ከፍሎ እቃውን በመረከብ ወስዶ ከቆየ በኂላ ይህንኑ ገንዘብ ሊመልስልኝ ይገባል ብሎ ሊከሰው የቻለው እቃው ወደ አገር እንደገባ እንዲያስረክብ ሲጠየቅ የዕቃው ብዛት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ ተገልጾ ከቀረበው በላይ ሆኖ ተገኝቷል በሚል ሣቢያ እቃውን ይዞ በመጋዘን በማራገፍ እንዲቆይ ያደረገው ያለአግባብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የክሱ ፍሬ ነገር ያስረዳል፡፡

በሕጉ በኩል ያለው ሲታይ የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 43/ሀ/ ላይ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ እቃ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተፈጽሞበት እስኪወጣ ድረስ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ የሚከፈልበት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ኪራዩም የሚከፈለው ለባለመጋዘኑ የጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በዚሁ ሕግ መሠረት እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ መክፈል የሚገባው መሆኑን አውቆ የተጠየቀውን ኪራይ ከፍሎ እቃውን አውጥቷል፡፡ ተጠሪው የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃውን በመጋዘን ያቆየው ያለአግባብ ነው በሚል የሚያቀርበውን የክርክር ምክንያት በተመለከተም የጉምሩክ ባለሥልጣን ተጠሪው ወደ አገር ያስመጣው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ እያንዳንዱ ካርቶን በውስጡ አንድ ፓኬት እንደያዘ ተደርጐ የቀረበለት ቢሆንም ሲፈተሽ እያንዳንዱ ካርቶን 5 ፓኬት የያዘ መሆኑን ሊያረጋግጥ በመቻሉ በሕጉ መሠረት ሊከፈልበት



ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በተያያዘ ምክንያት ይዞ ያቆየ ሆኖ የሚታይ እንጂ ከሕጉ ውጪ ፈጽሟል የሚባል ነገር የለም፡፡ የእጥፍ እጥፍ ሆኖ የተገኘው እቃ በህገወጥ መንገድ የገባ ነው ተብሎ ባይታይ እንኳን የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሣይፈጽምበት ከጉምሩክ መጋዘን ሊወጣ አይችልም፡፡ ተጠሪው ይኸው የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሣይፈፀም የጉምሩክ ባለሥልጣን ወዲያው እቃውን እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ማስረከብ ነበረበት፣ በጉምሩክ መጋዘንም ማቆየት አልነበረበትም በማለት የማያቀርበው ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ የከፈለው ኪራይ ይመለስልኝ ብሎ የሚጠይቅበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የተከፈለውን የመጋዘን ኪራይ የሚመልስበት ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለእቃው ብዛት የተሣሣተ መረጃ የሰጠው የቅድመ ጭነት ምርመራ አድራጊው ኤል.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ ስለሆነ አቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ የተከፈለው የኪራይ

ገንዘብ ሊመለስለት ይገባል በሚል የወሰነው የጉምሩክ ሕግን ያገናዘበ አይደለም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ለመስጠት ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ጭብጥ በተመለተም የአሁኑ አመልካች እቃውን የሚመለከት ዲክላራሲዮን ለሰጠው አይገባም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ተሟልቶ ሣይከፈል ዲክላራሲዮን ሊሰጠው አይችልም በሚል ምክንያት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ቀረጡ ተሟልቶ ባይከፈልም የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን አልሰጥም ብሎ ሊከለከል አይችልም፣ በእቃው ብዛት አገላለጽ ላይ ስህተት የፈፀመው የቅድመ ጭነት ምርመራ ያደረገው ኤስ.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ ጉዳይ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት ይኸው ድርጅት ነው ባይ ነው፡፡

በተጠቀሰው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2/18/ ላይ እንደተመለከተው “የጉምሩክ ዲክላራሲዮን” ማለት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ወይም



ተላላፊ እቃዎች ዝርዝር የሚገለጽበትና የጉምሩክ ሥነ ሥርአት የሚፈፀምበት በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅ ቅጽ ሲሆን ከዚህ የሕግ አገላለጽ ዲክላራሲዮን በዋናነት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት የሚፈፀምበት ሰነድ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት መፈፀም የሚለውም ሲታይ በቀረጥና ታክስ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣንም ዲክላራሲዮን አዘጋጅቶ ሊሰጥ የሚችለው በሕጉ መሠረት ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት ተደርጐ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ለፈፀመበት እቃ ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሳልተፈፀመበት እቃ ግን የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን እንዲሰጥ ሕጉ አይፈቅድም፡፡ እቃ አስመጪው በበኩሉ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ የተፈቀደለትን እቃ አይነት፣ ብዛትና ክብደት በትክክል ገልጾ ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በማቅረብ በታሪፍ መሠረት ተወስኖ የማጠየቀውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል የጉምሩክ ሥነ ሥርአት እንዲፈፀምበት ሳላደረገው እቃ ዲክላራሲዮን ይሰጠኝ ብሎ የመጠየቅ መብት ሊኖረው

አይችልም። በቀረበው ጉዳይ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ባስገባው እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ተሟልቶ ያልተከፈለ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው። በቅድመ ጭነት ምርመራው ሪፖርት ላይ የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር የሚያስገባው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት እያንዳንዱ ካርቶን አንድ ፓኬት የፎቶ ኮፒ ወረቀት የያዘ መሆኑ ተገልጾ ለጉምሩክ ባለሥልጣን የተላከ ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኋላ ሲፈተሽ አንዱ ካርቶን አምስት ፓኬት የያዘ ሆኖ መገኘቱም ተረጋግጧል። ተጠሪው ይህንኑ እያመነና በክርክሩም ሂደት በልዩነቱ ላይ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ብር 49.024.78 መኖሩን እየገለጸ ስህተቱን የፈፀመው የቅድመ ጭነት ምርመራ ያደረገው ኤስ.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ ስለሆነ ቀረጥና ታክስ ተሟልቶ ባይከፈልም የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ሊሰጠኝ ይገባል በሚል ያቀረበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የለውም። የአሁኑ አመልካች የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ላልተፈፀመበት እቃ ለተጠሪው ዲክላራሲዮን መስጠት



አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔም ሕጉን መሠረት የደረገ ስላልሆነ የሚሰረዝ ነው።

በመጨረሻም የአሁኑ ተጠሪ እቃውን ከተረከበ በኋላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቱ ምክንያት መጋዘን ተከራይቶ እቃውን ለማቆየት አወጣሁ የሚለውን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ይገደዳል አይገደድም የሚለው ሲመረመር ከላይ እንደተገለጸው የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ለመስጠት የማይገደድ ሆኖ ስለተገኘ አስመጪው እቃውን ካስወጣ በኋላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቱ ምክንያት ለመጋዘን ኪራይ አውጥቻለሁ የሚለውን ብር 96,600 የጉምሩክ ባለሥልጣን የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም።

ሲጠቃለል አንድ እቃ በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በሕጉ መሠረት የተከፈለ ኪራይ አይመለስም።

የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ለመስጠት አይገደድም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በሕግ የሚጠየቀው ኪሣራ የለም፡፡

በዚህ ጉዳይ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በሕጉ መሠረት የተከፈለውን ኪራይ የጉምሩክ ባለሥልጣን ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለስለት፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን እንዲሰጥ ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት የተጠየቀውን ኪሣራ እንዲከፍል በሚል በተሰጠው ውሣኔም የሕግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በፍ/መ/ቁ.3417፣ በ14/10/96 ዓ.ም.



የሰጠው ውሣኔም ሆነ ጉዳዩራ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 32978፣ በ16/2/97 ዓ.ም. ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚል የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 17712

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡** - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት

**መልስ ሰጪ፡** - የወ/ሮ ሳድያ እስማኤል ወራሾች

*ስለባለሀብትነት ማስረጃ - የባለሀብትነት የርስት የምስክር ወረቀት - ተቃራኒ ማስረጃ፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/፣ 1196/1*

መልስ ሰጪ በስር ፍ/ቤት በቀረበባቸው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 5፣ ቀበሌ 09 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 797 እና 798 የሆኑትን የንግድ ቤቶች ለስር ከሣሽ እንዲያስረክቡ ከተወሰነባቸው በኂላ አመልካች በክርክሩ ገብቶ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን እንዲሽር ያቀረበውን ጥያቄ ንብረቶቹ ለመወረሳቸው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ውድቅ በማድረጉና የተሰጠውንም ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡



**ው ሣ ኔ፡** - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ብይን በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡

1. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነትን የምስክር ወረቀት ማስረጃ የተሰጠው ሰው የዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
2. ማስረጃው የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1195 የተመለከተው የሕሊና ግምት ፈራሽ ይሆናል፡፡
3. በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት አይኖርም፡፡

የሰበር መ/ቁ. 17712

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረበ

ተጠሪ፡ - የወ/ሮ ሳድያ እስማኤል ወራሾች እነ ወ/ሮ ሣባህ አብዶ/

ወራሽ አህመድ አብዶ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በሰበር ችሎቱ ለቀረበው ክስ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር በመቃወም አመልካች በመሆን የሥር ፍ/ቤት ታህሣሥ 6 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት



በሰጠው ውሣኔ ላይ የተቃውሞ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ ይዘቱም ተቃውሞ በቀረበበት ፍርድ ተከሣሽ የሆኑት አቶ አማን መሐመድ ከመቃወም አመልካች በውል ተከራይተው የሚነግዱበትን በወ.5 ቀበሌ 9 የቤት ቁ. 797 እና 798 የሆኑትን ንግድ ቤቶች ተቃውሞ በቀረበበት ፍርድ ከሣሽ የሆኑት ወ/ሮ ሳዲያ የግል ንብረቶች ናቸው በሚል ተከሣሽ ቤቶቹን ለቀው ለከሣሽ እንዲያስረክቡ እንዲሁም ከየካቲት 7 ቀን 1994 ጀምሮ ያለውን ኪራይ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ በመስጠቱ ነው፡፡ በመቃወም አመልካች ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሱ ላለፉት 28 አመታት ለአቶ አማን መሐመድ አከራይቶ ሲጠቀም መቆየቱንና ለከሣሽ ተሰጥቶ የነበረው ቁጥር 5127386 የሆነ የባለቤትነት ደብተር በአ/አበባ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤቶች ጉዳይ መምሪያ የተሰረዘ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮ የቆየ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ስለ መወረሳቸው የሚያረጋግጥ የመረካከቢያ ቅጽ አልቀረበም በማለት የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረ ቢሆንም በተመሣሣይ ሁኔታ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁን አመልካች በሰበር አቤቱታው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በተሰረዘና ተቀባይነት በሌለው ማስረጃ ላይ ተንተርሶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብሎ ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሳ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የተጠሪ መልስና የአመልካች የመልስ መልስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት በተሰረዘ ጊዜ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማስረጃ ለተሰጠው ሰው ለዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ እንደሚያስቆጥረው ተመልክቷል፡፡ በአንፃሩ ማስረጃው የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ከፍ ብሎ



በፍትሐብሔር ቁጥር 1195 ላይ የተመለከተው የሕሊና ግምት ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1196/1/ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በሕግ አግባብ ሥልጣን ተሰጥቶት ይህን መሰሉን የባለሀብትነት ማስረጃ የሚሰጠው ክፍል ቁጥር 5127386 የሆነውን የባለቤትነት ደብተር የሰረዘው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት ደግሞ የሚገኝ የባለሀብትነት መብት አይኖርም፡፡ የተጠሪ ወራሾችም አውራሻቸው ያልነበራቸውን መብት ሊወርሱ አይችሉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከፍ ሲል በተጠቀሱት የሕግ ቁጥሮች መሠረት የባለሀብትነት የምስክረ ወረቀቱ የተሰረዘ መሆኑን የተረዳው ቢሆንም የባለቤትነት ደብተሩ መሰረዝ ለአሁኑ አመልካች የሚሰጠው መብት የለም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ይህን ፍርድ በድምጽ ብልጫ ሰጥተዋል፡፡

## ውሣኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም. በመ/ቁ. 15563 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

- ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

<u>**የሐሳብ ልዩነት**</u>

በአንድ ክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ለመግባት የሚችል እና በክርክሩ ሳይካፈልበት የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት መቃወሚያ ሊያቀርብበት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ላይ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አግባብ አንድ አመልካች ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በነበረው ክርክር ተካፋይ ሊደረግ ይገባው ነበር፣ አሊያም ሳይሚገትበት የተሰጠው ፍርድ የእርሱን መብት የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል ይሰኝለት ዘንድ ለአብቱታው የአቀረበው ማስረጃ ይህንኑ የሚያረጋግጠለት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በወረዳ 5 ቀበሌ 19 ውስጥ የሚገኙትን ቁጥር 797 አና 798 የሆኑ የንግድ ቤቶች የተጠሪዎች አውራሽ እንድትረከብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚጎዳው ነውና ገብቼ ተከራክሬ ፍርዱን እንዳሽር



ይፈቀድልኝ ሲል ይህን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 በመጥቀስ አቤቱታው ለተጠቀሰው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ በቤቶቹ ላይ መብት አለኝ የሚለው ደግሞ በመንግሥት የተወረሱ ናቸው በሚል መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ቤቶቹ በመንግሥት የተወረሱ መሆናቸውን የማያሳይለት ማስረጃ አላቀረበም፡፡ የአቀረበው ሙግትም ይህ ማስረጃ አለኝ ወይም ነበረኝ በሚል አይነት ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በሌላም በኩል ንብረቱ ባለቤት የሌለው ጠፍ የሆነ ንብረት ነው የሚል ክርክርና ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1194 አግባብ ሊታይና የቤቶቹ ባለቤት መንግሥት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ለተጠሪዎች አውራሽ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ደብተር ተሰርዟል ማለቱ ብቻውንም ለእርሱ መብት የሚሰጠውና አቤቱታውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አግባብ እንዲስተናገድለት ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡

በኔ እምነት የስር ፍርድ ቤቶች ወደ ዋናው ጉዳይ ተመልሰው ክርክሩን እንደገና መመርመር ሳያስፈልጋቸው አመልካቹን ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚያስችልህ መብት መኖሩን አላስረዳህም በሚል ከወዲሁ

ጥያቄውን ውድቅ በማድረጋቸው የፈፀሙት የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ውሣኔያቸው ሊፀና የሚገባው ነው በማለት ስሜ በሦስተኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኛ አብዛኛው ድምጽ በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 18307

ጥቅምት 25 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

**አመልካች፡** - ንብ ትራንስፖርት አ.ማ

**መልስ ሰጪ፡** - አቶ ተገኑ መሸሻ

*የስራዎች አገልግሎት መስጠትን የሚመለከቱ ውሎች ለሰራተኛው ስለማገባው የደመወዝ መብት ስራ ላልተሰራባቸው ቀናት ደመወዝ ስላለማግኘት - ስለ ስራ አለመኖር /በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ ስለሆነ ሰራተኛ/፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2534፣ 2540፣ 2541/1/*

መልስ ሰጪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቴክኒክ ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኜ ስሰራ ከስራ ከመሰናበቴ በፊት ታግጄ በቆየሁበት ከታህሣሥ 23 ቀን

1994 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ ያለው ደመወዜ እንዲከፈለኝ በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጪ የጠየቀው ገንዘብ እንዲከፈለው ውሣኔ በመስጠቱና ውሣኔውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

**ውሣኔ፡** - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. በድርጅት ሥራ መሪና በድርጅቱ መካከል ያለ የስራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎትን መስጠት ስለማመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታዮቹ በተደነገጉት ህጎች መሠረት ነው፡፡
2. የስራ መሪ ደመወዝ ለተሰራ ስራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሰራ ስራ የሚከፈል አይደለም፡፡
3. የስራ መሪው አንድም የስራ አገልግሎት ባይሰጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሰሪው ስራ ሳይሰጠው በመቅረቱ ወይም እንዳይሰራ



በመከልከሉ የተነሳ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት የለው ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሠራተኛው /የስራ መሪው/ ስራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሰሪው ሥራ ሳይሰጠው ወይም እንዳይሰራ በከለከለው ጊዜ እንጂ ሠራተኛው ከስራና ከደመወዝ ታግዶ የስራ አገልግሎት ላልሰጠባቸው ጊዜያት አይደለም፡፡

የሰበር መ/ቁ. 18307

ጥቅምት 25 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

**አመልካች፡ - ንብ ትራንስፖርት አ.ማ**

**መልስ ሰጪ፡ - አቶ ተገኑ መሸሻ**

ለዚህ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ ሲሆን አመልካቹ ተከሣሽ ነበር፡፡

የተሰጠው የሥራ ክስ በድርጅቱ ውስጥ የቴክኒክ ዋና ክፍል ሀላፊ ሆኜ ስሠራ ከታህሣሥ 23/94 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ ታግጄ ከቆየሁ በኋላ ሰኔ 5/95 የተፃፈ የስንብት ደብዳቤ ተሠጥቶኛል ስለዚህ



ከታገድኩበት ጊዜ አንስቶ እስከተሠናበትኩበት ጊዜ ድረስ ያለው የ17 ወር ከ15 ቀን የተጣራ ደመወዜ 23.500 (ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ወጪና ኪሣራ ተጨምሮ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽ ማለትም ተጠሪው ቀርቦ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ በብይን ውድቅ የተደረገበት ቢሆንም ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበተው ድርጅቱን የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ መሆኑን በመግለጽ ሥራ ላልሠራበት ጊዜ ደመወዜ ሊከፈለው እንደማይገባ ይከፈለው ቢባል እንኳ ከ3 ወር ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከሣሽ የሥራ መሪ እንደመሆኑ በፍ/ህጉ ላይ የሥራ መሪን ከሥራ ስለማገድ የተደነገገ ድንጋጌ የለም፣ በድርጅቱ የውስጥ ደንብ ስለመኖሩና በውስጥ ደንቡ መሠረት ስለማገዱ አላስረዳም በመልስ የዘረዘራቸውን ተግባራት ከሣሽ ፈጽመዋል ቢባል እንኳ ከሥራና ከደመወዝ ለማገድ በቂ ምክንያቶች አይደሉም በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/1 ሠራተኛው አገልግሎት ባይሰጥም ይህ የሆነው በአሠሪው ምክንያት ከሆነ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ አለበት፣ የ3 ወር

ደመወዝ ብቻ ሊከፈላቸው ይገባል የሚለው የተከሣሽ ክርክር በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/2/ የተመለከተው የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት እንጂ የሥራ ውሉ ለታገደበት ጊዜ የሚመለከት አይደለም በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡

አመልካቹ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ይታረምልኝ ሲል በ14/5/97 የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ፍሬ ቃል ተጠሪው በ5/10/95 እና በ5/2/95 ተጽፎ የተሰጣቸው ደብዳቤ የሥራ ስንብት ሣይሆን የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በአግባቡ አልመረመረም፡፡

አመልካች ተጠሪን ከሥራ ለማገድ ምክንያት ያደረገው በድርጅቱ ሥራና ገንዘብ ላይ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳት ማድረሣቸውን የሚያመለክቱ



ናቸው፡፡ ፍ/ቤቱ የፍ/ሕ/ቁጥር 2575 ስለ ሥራ ውል መቋረጥ እንጂ ስለ ሥራ ውል ማገድ የሚመለከት አይደለም ያለው ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪው በእገዳ ላይ ለቆዩበት ጊዜ ሥራ እንዳይሠሩ የከለከላቸው ድርጅቱ ነው ተብሎ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ስህተት ነው ምክንያቱም የፍ/ሕ/ቁጥር 2540 ሥራ ላልተሠራባቸው ቀኖች ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም የሚለውን የሚቃረን ነው፡፡ የፍ/ህግ ቁጥር 2574/2/ ከ3 ወር የማይበልጥ ክፍያ እንዲከፈል የደነገገው የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ ነው ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት ነው በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ ውሣኔዎቹ ተሽረው ወጪና ኪሣራ ተከፍሎን እንሠናበት የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ማመልከቻው ለተጠሪው ደርሶ ሚያዝያ 19/1997 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አይገልጽም፣ የ6 ወር የጊዜ ገደብ የከሣሽን የጥቅም ጥያቄ በይርጋ አያግደውም፣ ተጠሪው በጥፋት ተከስሼ አላውቅም፣ ባልተቀጣሁበት ጉዳይ ጥፋት ነው ተብሎ ለሠበር አቤቱታ መቅረቡ

ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪ በ5/10/95 እና በ5/2/95 የተፃፈው የሥራ የምስክር ወረቀት እንጂ የሥራ ስንብት ደብዳቤ አይደለም ያሉት የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ስህተት መሆኑን አያመለክትም፣ አመልካች መ/ቤት ከሥራና ከደመወዝ ያለበቂ ምክንያት አግደውና አሰናብተው ስለአጉላሉኝ በደሉ ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ሳይሆን የፍሬ ነገር ክርክር ነው፣ በፍ/ሕግ ቁጥር 2540 ሥራ ላልሠራባቸው ቀኖች ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም ለተባለው ተጠቃሹ ህግ ሠራተኛው ሥራውን በራሱ ፍላጐት ሣይሠራ ሲቀር እንጂ አሠሪው ሥራ ሲከለክለው የሚጠቀስ አይደለም፣ የፍ/ሕግ ቁጥር 2574/2/ ለኪሣራ እንጂ ውዝፍ ደመወዝን የሚመለከት አይደለም፣ ከዚህ ጉዳይ ጋርም ግንኙነት የለውም ስለሆነም ጥያቄው ከበቂ ኪሣራ ጋር ተሠርዞ እንድሠናበት በማለት ሲከራከር አመልካቹ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን፣ በኛ በኩል ተጠሪው ከሥራ ታግዶ ለቆየበት ጊዜ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አግባብ ካላቸው



ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ተጠሪው በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ሆኖ ሲሠራ የነበረ በመሆኑ የአመልካችና የተጠሪው የሥራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 16 የሥራ አገልግሎትን መስጠት ስለሚመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታይዎቹ በተደነገጉት ሕጐች መሠረት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሠሪን የሥራ ውል ስለማቋረጥ እንጂ አሠሪን ከሥራ ስለማገድ በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም ካለ በኃላ በፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ መሠረት አመልካቹ ተጠሪውን ከሥራና ከደመወዝ አግዶ ለቆመባቸው ወራቶች ደመወዙን ይክፈለው ሲል ወስኗል፡፡

በመሠረቱ ከፍ/ሕግ ቁጥር 2534 ድንጋጌ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ደመወዝ ለተሠራ ሥራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሠራ ሥራ የሚከፈል አይደለም፡፡

የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2540 ይህንኑ የሕጉን መርህ በመከተል ሥራ ላልተሠራባቸው ጊዜያት ወይም ቀናት ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም በማለት ግልጽ ድንጋጌ አስፍሮ ይገኛል፡፡

ይሁንና የፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ ሠራተኛው አንድም የሥራ አገልግሎት ባይሠጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሠሪው የሥራ ሣይሠጠው በመቅረቡ ወይም እንዳይሠራ በመከልከሉ የተነሣ የሆነ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት አለው ሲል ሠራተኛው የሥራ ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሥራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሠሪው ሥራ ሣይሠጠው ወይም እንዳይሠራ በከለከለው ጊዜ የሚያገለግል እንጂ ሠራተኛው ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የሥራ አገልግሎት ላልሠጣባቸው ጊዜያት ደመወዝ እንዲከፈለው የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ብቻ ብለው በተመለከቱት የፍ/ብሄር ድንጋጌዎች አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል ብለናል፡፡

**ውሣኔ**

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34240 በ5/5/97 የሠጠው ውሣኔ እና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1119 በ1-2-97 የሠጠው ውሣኔ



በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት የተሻሩ ስለሆነ የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረሳቸው መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

# ቅፅ 3

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የካቲት 1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

**ማውጫ**

1. የስራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ የመ/ቁ 15815/ (አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ/ 1
2. የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ - የመ/ቁ. 17483 (የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ) ........................................................... 6
3. ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ የመ/ቁ 16648 (የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ አንለይ ያየህ) ..........................................10
4. ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ - የመ/ቁ 11924 (የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ 30
5. አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ የመ/ቁ. 14057 (የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ) ...................................... 41
6. በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሳ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ - የመ/ቁ 16270 (አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ መታ) .............................. 49
7. በህግ ወጥ መንገድ የስራ ውል የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ የመ/ቁ. 18581 /በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ር ቀቡላ ከድር/ ............................... 55
8. የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ የመ/ቁ 15631 (እነ የሻረግ መንግሥት እና እማሆይ የሻረግ ፈረደ)......................................... 64
9. ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወስነው በውሉ መሠረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ የመ/ቁ. 15551 (ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ) ................. 79
10. ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ የመ/ቁ. 16062

11. ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የመ/ቁ. 14554 (ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ) ........................................................... 81
12. ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ የመ/ቁ. 15672 (አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ) .................................................. 87
13. የመጥሪያ አደራረስ አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ የመ/ቁ 16301 (ተገኝ እንግዳ እና አስናቀች ኪዳኔ) ........................ 90
14. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ የመ/ቁ 10797 (ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም) ........................................................................ 93
15. በጨረታ ለገዛው ንብረት ገዢ ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ ስርአት የመ/ቁ 18199 (ዶ/ር ምናሴ እሸቴ እና እነ ግርማ አያና) ... 98
16. የመንግሥት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ የሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት የመ/ቁ 16378 (የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ጉ/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን) ..................... 101
17. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ የመ/ቁ. 18342 (የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሃኑ ህሩይ) ......................................................... 106
18. ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ የመ/ቁ 14699 (የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ) ..................................... 111

*የመ.ቁ. 15815*

*ታህሣሥ 10 ቀን 1998 ዓ.ም*

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት- ቃሲም ፈጂስ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን አበበ- አልቀረበም

*የስራ ክርክር - ስለ ማኔጅመንት አባል የሆነ ሰው የስራ ስንብት፣ ስለ ስራ ስንብት እና መመለስ፣ የካሳ ክፍያ እና ማስጠንቀቂያ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2570፣ 2573፣ 2574፣ 2571*

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪን አመልካች ከስራ ያባረረው ህጉን ተከትሎ ባለመሆኑ የተቋረጠበት ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎት ወደ ስራ ሊመለስ ይገባል በማለት በአርሲ ዞን ከፍ/ቤት የተሠጠውን ውሳኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>፡- የአርሲ ዞን ከፍ/ቤት የሰጠውና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያጸናዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡

1ኛ. በስራ አመራር ላይ ያሉ አባላት የስራ ውላቸው ቢቋረጥ የሚያገኙት መፍትሔ በአሠሪ ሠራተኛ አዋጅ የሚሸፈኑ ሠራተኞች ከሚያገኙት መፍትሔ የተለየ ነው፡፡

2ኛ. በአመራር ላይ ያለው ሠው ያለበቂ ምክንያት ያለማስጠንቀቂያ ቢባረር የሶስት ወር ደመወዝ ካሳ ይሠጠዋል እንጂ ወደ ስራ ሊመለስ አይችልም፡፡

*ታህሣሥ 10 ቀን 1998 ዓ.ም*

*የመ.ቁ. 15815*

*ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ*

*አቶ ፍስሐ ወርቅነህ*

*አቶ አብዱልቃድር መሐመድ*

*ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ*

*አቶ መስፍን እቁበዮናስ*

*አመልካች፡- አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት- ቃሲም ፈጂስ ቀረበ*

*ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን አበበ- አልቀረበም*

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ክሱን የመሠረተው ተጠሪው ሲሆን አቤቱታውም በአጭሩ አመልካች በ1989 ዓ.ም የወጣውን የማኔጅመንት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37(1) በመተላለፍ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ የቀረብኝ ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀ□ን በጉዳዩ ከአከራከረ በኋላ የተጠሪ የስራ ስንብት ደንቡን ተከትሎ ያልተፈፀመ ስለሆነ የተቋረጠበት ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎት ወደ ስራ ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔም ጉዳዩን በይግባኝ ባየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡

በመቀጠል አቤቱታ የቀረበለት ይህ ችሎትም የግራ ቀፅን ክርክር መርምሯል፡፡

አንድ የማኔጅመንት አባል የሆነ ሰው ከሥራ ቢሰናበት ስንብቱ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ወደ ስራ እንዲመለስ መወሰንን ሕጉ ይፈቅደዋል? ወይስ አይፈቅደውም? የሚለው ነጥብ በጉዳዩ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ መሆኑንም ተገንዝቧል፡፡



ተጠሪ ከአስተዳደሩ ክፍል የሚፈረጅ ሰራተኛ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ከስራ የተሰናበተውም በድርጅቱ የስራ አመራር ቦርድ በተሰጠ ውሣኔ መሆኑ በስር ውሣኔ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም በአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ተጠሪ ፈፅሞታል የተባለው ጥፋት አስቀድሞ በኮሚቴ ከዚያ ደግሞ በይግባኝ በስራ አመራር ቦርድ ታይቶ ውሣኔ ሊያገኝ ሲገባው ተጠሪው በቀጥታ በቦርዱ ከስራ እንዲሰናበት መወሰኑ በደንቡ የተቀመጠውን ሥርዓት የጠበቀ አይደለም በሚል ምክንያት ከፍ ሲል የተጠቀሰው ውሣኔ በስር ፍርድ ቤቶች መስጠቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በመሠረቱ የስር ፍርድ ቤቶች ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት የአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡን መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ ይህ የአስተዳደር መተዳደሪያ አንድ የአመራር አባል ጥፋት ፈጽሟል ቢሰኝ የጥፋቱ መፈፀም አለመፈፀም ተጣርቶ እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት የተቀመጠበት ደንብ መሆኑንም ከውሣኔያቸው መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቶቹ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተበትን ሁኔታ ከደንቡ ጋር በማገናዘብ ስንብቱ በደንቡ የተመለከተውን ሥርዓት ያከበረ አይደለም የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረሣቸውም ከፍ ሲል ተጠቅሷል፡፡ እንግዲህ የተጠሪ የስራ ስንብት ደንቡን የተመሠረተ መሆን አለመሆኑን ለመለየት የክርክሩን ፍሬ ነገር ማጥራት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ የዚህ ችሎት የስራ ድርሻ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ደንቡን የተከተለ አይደለም ሲሉ በፍሬ ነገሩ ረገድ የደረሱበትን መደምደሚያ ይህም ችሎት ተቀብሎታል፡፡

በሌላ በኩል ግን በአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያልተፈፀመ የስራ ስንብት ለሰራተኛው ወደ ስራ የመመለስን መፍትሔ ሊያሰጠው የመቻል አለመቻሉ ጉዳይ የሕግ ጥያቄን የያዘ ነውና በዚህ ችሎት ሊዳኝ ይገባዋል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለስ ይወስኑ እንጂ ይህንኑ እንዲወስኑ ያስቻላቸው የደንቡን አንቀጽ በውሣኔያቸው አልጠቀሱም፡፡ አሊያም ደንቡ በስሩ ከተመለከተው ስርዓት ውጭ ከስራ የተሰናበተን ሰራተኛ ወደ ስራ የመመለስ አላማ ያለው መሆኑን

አላረጋገጡም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ የአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ ከስርዓት ውጭ የተናበተ የአመራር አባል ወደ ስራ ይመለስ ዘንድ የሚፈቅድ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ደግሞ ፍርድ ቤቶቹ ተጠሪ ወደ ስራ ይመለስ ሲሉ ለደረሱበት መደምደሚያ በደንቡ የተፈቀደ መፍትሄን መነሻ አለማድረጋቸውን ለማመላከት ይበቃል፡፡ ፍርድ ቤቶቹ ያስደገፉት ሕግ ሣይኖር የደረሱበት ይህን ይህ ማጠቃለያም አሳማኝነት የሚጎድለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ጉዳዩ ለክርክሩ አግባብነት ከአለው የፍ/ብ/ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ሊመረመር የሚገባው መሆኑን አምነንበታል፡፡ በመሠረቱ ተጠሪ የስራ አመራር አባል በመሆኑ ከአመልካች ጋር የፈፀመው ያልተወሰነ ጊዜ የሰራ ውል ከሁለቱ በአንዳቸው የሁለት ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊቋረጥ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2570 እና 2571 ላይ መረዳት ይቻላል፡፡ አንድ አሰሪ የስራ ውሉን ያቋረጠበት በቂ ምክንያት ከሌለው ደግሞ ለሰራተኛው የሦስት ወር ደመወዙን የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በዚሁ ሕግ አንቀጽ 2573 እና 2574 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች እንደ ተጠሪ ያሉ የስራ አመራር አባላት የፈፀሚቸው የስራ ውሎች ያለበቂ ምክንያት እንኳ ሊቋረጡ እንደሚችሉ የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ የስራ ውሉ መቋረጥ በአሰሪው በኩል በቂ ምክንያት ያልተሰጠበት ከሆነም ሰራተኛውን ወደ ስራ የመመለስ መፍትሄ የሚያስገኙለት ሣይሆን ካሣ ተቀብሎ ይሰናበት ዘንድ የሚፈቅዱለት ናቸው፡፡ ይህም የሚያሣየን በሥራ አመራር ላይ የሚገኙ ሰዎች የሥራ ውላቸው ቢቋረጥ የሚያገኙት ሕጋም መፍትሄ (remedy) ሌሎቹ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚሸፈኑ ሰራተኞች ከሚያገኙት መፍትሄ የተለየ መሆኑን ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ለአንድ መብቴ ተነካ ለሚል ወገን የሚሰጡት መፍትሄ ደግሞ በሕጉ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከተጠቀሱት ሕጎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው የሥራ አመራር ላይ ያለ ሰው ሕጉ በማይፈቅደው ምክንያት እንኳን ከሥራ ቢሰናበት ፍርድ ቤት ወደ ሥራው እንዲመለስ ለማድረግ የሚያስችለው የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ሕጉ የሰጠው መብት ካሳ መቀበል ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በቦርድ ውሣኔ ከስራ መሰናበቱ እንጂ አመልካቹ የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ በመሰጠት የስራ ውሉን ያቋረጠው



መሆኑን አልተረጋገጠም፡፡ እንዲሁም ተጠሪው ለስንብቱ ምክንያት የተደረጉትን መስሪያ ቤቱን በቅንነት ለማገልገል ፈቃደኛ አይደለም፡ የበታች ሰራተኞችን ይንቃል ትእዛዞች አይቀበልም... ወዘተ በሚል በአመልካች የተጠቀሱትን ጥፋቶች መፈፀም አለመፈፀሙም በስር ፍርድ ቤቶች አልተረጋገጠም፡፡ በሌላ በኩል ግን የሥር ፍርድ ቤቶች የተጠሪ የስራ ስንብት የአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡን ተመስርቶ የተፈፀመ አይደለም የሚል ማጠቃለያ ላይ የደረሱ ሲሆን ይህም ችሎት ፍርድ ቤቶቹ በጉዳዩ ፍሬ ነገር የደረሱበትን የተጠቀሰውን ማጠቃለያ ተቀብሎታል፡፡ እነዚህ በጉዳዩ የሚታዩት ፍሬ ነገሮች ተዳምረው ሲመዘኑም አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አልነበረውም ለማለት ያህል የሚበቁ መሆናቸውንም አምኖበታል፡፡ ይህም ተጠሪው ማስጠንቀቂያ ያልተሰጠው በመሆኑ ምክንያት የሁለት ወር ደመወዝ የስራ ስንብቱ በበቂ ምክንያት ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ደግሞ ቢበዛ የሦስት ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲያገኝ የሚያስችለው እንጂ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚያደርገው አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ወደ ስራ እንዲመለስ የሰጡት ውሣኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የፍትሐብሔሩ ድንጋጌዎት ጋር ያልተጣጣመ ነው፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የተጠሪ የስራ ውል መቋረጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2570(1) የተደገፈ ነውና ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም፡፡
2. ይሁን እንጂ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠበት በቂ ምክንያት ስለሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2573 እና 2574 መሠረት የሦስት ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፈለው ተወስኗል፡፡
3. በተጨማሪም ተጠሪው የሁለት ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ያልተሰጠው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2570(2) እና 2571 መሠረት የሁለት ወር ደመወዙ እንዲከፈለው ተወስኗል፡፡
4. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 38/95 የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 2339/95/016 ግንቦት 3 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 17483

ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ገጠር መንገች ባለሥልጣን

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሮማን ደምሴ

*የስራ ክርክር - ይርጋ - አላግባብ ተቋርጧል የተባለን የስራ ውል ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ - የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162(1)*

አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ወይ ስራዋ እንድትመለስ እና ጥቅማ ጥቅሞቹ እንዲጠበቁለት በማለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የሠጡትን ውሳኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u> ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1ኛ. የስራ መደብ ያልተቋረጠ ከሆነ ወደ ስራ ልመለስም ሆነ የውል አበል ክፍያ ይገባኛል የሚል ጥያቄ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162(1) ስር ከተመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ድንጋጌ እንጂ በተለይ ከተደነገጉት ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡

2ኛ. አንድ ሠራተኛ ከስራና ከደመወዝ ከዘጠና ቀን በላይ ከታገደ የስራ መቋረጡ ባይገለፅለትም መብቱን ለመጠየቅ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው የዕገድ ጊዜ ከሚያበቃበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡





ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ገጠር መንገች ባለሥልጣን - ሰላማዊት ኃይሉ ቀረበች

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሮማን ደምሴ - ቀረበች

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ ዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በመሠረተችው ክስ የተጀመረ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች ከሕዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ጥር ወር 1993 ዓ.ም ድረስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንድውል ከአስደረገ በኋላ ኦዲት ይደረግና ትመለሻለሽ በሚል ከስራና ከደመወዝ አግዶኛል፡፡ ይሁን እንጂ ከሚያዝያ 23 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የኦዲቱ ስራ የተከናወነ ቢሆንም ስራዬ ላይ ግን ሊመልሰኝ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም የውሎ አበሌን ከፍሎ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም ክሱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ስለሆነ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162/1/ መሠረት በይርጋ ይታገድልኝ የሚል መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳዩም አለኝ የሚለውን መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የተጠሪ የስራ ውል መቼ እንደተቋረጠ ባይታወቅም ክሱ የተመሠረተው ግን ኦዲት ተደርጎ ትመለሻለሽ ተብያለሁ ከአለችበት እለት ከጥር ወር 1993 ዓ.ም በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ ማለትም ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም ነው እንዲሁም ተጠሪ አመልካቹ መብቴን አውቆልኛል ብትልም ለዚህ ያቀረበችው የጽሁፍ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም ሌላ የቆጠረቻቸው የሰው ማስረጃዎችም ያላስረዱላት በመሆኑ የይርጋው አቆጣጠር ሊቋረጥ የሚችል አልሆነም ስለሆነም ክሱ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አንድ የስራ ውል የሚቋረጠው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27(2) መሠረት አሰሪው ለሰራተኛው በሚሰጠው ጽሁፍ መሆን ሲገባው ይኸ በአመልካቹ አልተደረገም፡፡ ስለሆነም በሁለቱ መካከል የተፈፀመው የስራ ውል ስላልተቋረጠ አመልካቹ ለተጠሪዋ መሰጠቱ ከቆመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ደመወዝዋን ከፍሎ ወደ ስራዋ ሊመልሣት ይገባል በማለት ወስኖ የስር ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሣኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ይህም ችሎት በግራ ቀኑ የቀረበለትን ክርክር መርምሯል፡፡ ምላሽ የሚያስፈልገውም የጉዳዩ ነጥብ በተጠሪ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊተገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ የተያዘውን ጭብጥ ለመፍታት በቅድሚያ ጉዳዩ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162 ስር ከተመለከቱት የይርጋ ደንቦች ውስጥ ከየትኛው ንዑስ አንቀጽ አግባብ ሊታይ እንደሚገባው መለየት ያስፈልጋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቹ ተጠሪዋ በእጅዋ ከገባው ገንዘብ ውስጥ ብር 21.595.00 አጉድላ ለግል ጥቅምዋ ማዋሏ ተረጋግጧል ቢልም ይህን ምክንያት ጠቅሶ የስራ ውሏን አለማቋረጡን አልካደም፡፡ ክርክሩ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ከዋለችበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ የስራ ውሏ ተቋርጧል ሊሰኝ ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሁለቱ መካከል ያለው የስራ ግንኙነት በሕግ መቋረጡን ስለማያመለክት ውሉ አልተቋረጠም ሲል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሊነቀፍ የሚገባው አልሆነም፡፡ የስራ ውሉ ያልተቋረጠ በመሆኑም ተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ ይገባል ስትል ያቀረበችው የክሷ ነጥብም ሆነ የውሎ አበል ክፍያ ይገባኛል ስትል ያነሣቸው ጥያቄ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) ስር ከተመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ደንብ ድንጋጌ አኳያ እንጂ በተለይ ከተደነገጉት ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) አግባብ ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ከስራ እና ከደመወዝ ከኅዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ታግዳ የቆየች መሆኑን አልካደችም፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ግንቦት 14 ቀን



1994 ዓ.ም ድረስ ሒሣብ እያስመረመርኩ ስለሆነ ስራ ላይ እንደነበርኩ ሊቆጠርልኝ ይገባል በሚል አይነት ተከራክራለች፡፡ ተጠሪ በሒሣብ ማስመርመር ተግባር ላይ መቆየቷ ግን መደበኛ ስራዋን ስታከናውን ነበር የሚያሰኛት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረበችው ክርክር አሣማኝነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከስራና ከደመወዝ የታገደችበት እለት ኅዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም መሆኑን ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡

እንግዲህ ከፍ ሲል እንደመለከተው ተጠሪ የስራ ውሏ መቃረጥ በአመልካቹ ባይገለጽላትም ከኅዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ከስራና ከደመወዝ መታገድዋ ግን ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከዘጠና ቀናት በላይ ከስራና ከደመወዝ ሊታገድ እንደማይችል ደግሞ ከአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 21(1) መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ሕጉ ለእግድ የፈቀደው ጊዜ እንደአበቃ ይገባኛል የምትለው ነገር በአመልካቹ ካልተደረገላት መብቷን ክስ መስርታ ትጠይቅ ዘንድ ይገባል፡፡ ክሷን የምትመሰርተውም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) መሠረት ጥያቄዋን ልታቀርብ ከምትችልበት ማለትም የእግዱ ጊዜ ከማያበቃበት ከየካቲት 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ማለትም እስከ የካቲት 14 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ብቻ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

አመልካች ግን ክሷን የመሠረተችው ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የተጠቀሰውን የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ አሳልፎ የቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተችው ክስ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል፡፡

2ኛ. የዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.63/95 ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል ሲል የሰጠው ውሣኔ ፀንቶ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ደኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመ.ቁ. 02006 እና 16113 ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

*የመ/ቁ.16648*

*ታህሣስ 20 ቀን 1998 ዓ.ም.*

**ዳኞች፡-** *1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ*

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

5. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

**መልስ ሰጭዎች፡-** እነ አቶ አንለይ ያየህ /27 ሰዎች/

*ስለ ስራ ክርክር- የይርጋ ጊዜና የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ- የመብት ጥያቄ ስለሚቀርብበት የጊዜ አቆጣጠር - የይርጋ ጊዜ መቋረጥ - የይርጋ መብትን ስለመተው - ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን ስላለው ስልጣን - የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162፣ 163፣ 164፣ 165፣ 166 (በጉዳዩ የተሰጠው የህግ ትርጉም የአዋጅ ቁ.42/85ን በመሻር በወጣው አዋጅ ቁ.377/96 ድንጋጌዎችም ተፈፃሚነት አለው)*

መ/ሰጭዎች በጌዶ፣ነቀምት እና ጊምቢ ባከናወነው የትራንስሚሽን መስመር መዘርጋት ስራ ለተሳተፉት ሌሎች ሰራተኞች አመልካች መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም የሰጠው የሁለት ዕርከን ጭማሪ እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት አመልካች ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቦርድ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

**ውሳኔ፡-** የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዩ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 162 /3/ መሰረት የደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ ሊጠየቅ ይገባው ነበር ከሚሰኝበት ጊዜ ጀምሮ የስራ ውሉ ተቋርጦ ቢሆን እንኳን ይህን ከግምት ሳያስገባ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡
2. የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ጥያቄ በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው በሚቀርብበት ጊዜ በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/3/ በተደረጉ የይርጋ ድንጋጌዎች ይመራል፡፡
3. የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ተተኪዎች ወይም ወራሾች የሰራተኛውን ወይም የአሰሪውን ሳይሆን የራሳቸውን መብት መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ጥያቄ በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/4/ በተደነገጉት ሳይሆን በአንቀጽ 162/1/ በተደነገገው የይርጋ ድንጋጌ ይመራል፡፡
4. በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቋረጠው ክሱ በአዋጅ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን በተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በፍርድ ቤቶች በተቋቋሙ የስራ ክርክር ችሎቶች የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
5. ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባልተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በስራ ክርክር ችሎት የቀረበ ክስ በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜን መቆጠር አያቋርጥም፡፡
6. በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 164/2/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቋረጠው አቤቱታው የቀረበው ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበ እንደሆን ብቻ ነው፡፡
7. ለአሰሪ የቀረበ አቤቱታ በአዋጅ ቁ.42/85 (377/96) አንቀጽ 164(2) መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠርን አያቋርጥም፡፡
8. በአዋጅ ቁ.42/85 (377/96) አንቀጽ 166(1) ከፍትሐ-ብሄር ህግ ቁጥር 1793 ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት፡፡
9. ሰራተኛ ወይም አሰሪ በአዋጅ ቁ.42/85 (377/96) አንቀጽ 166(1) ለመጠቀም በድንጋጌው የተመለከቱት ሁኔታዎች መከሰታቸውን እና ክሱ በይርጋ የሚታገድበት ከመድረሱ በፊት ያልቀረበው በድንጋጌው ከተመለከቱት ሁኔዎች ቢያንስ በአንዱ መከሰት ምክንያት መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ አለበት፡፡

የመ.ቁ. 16648

ታህሣስ 20 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አልቀረበም፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ አንለይ ያየህ /27 ሰዎች/ - ጠበቃ ብዙአለም መርሻ ቀረበ

## ፍ ር ድ

ይህ ክርክር አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ዘንድ የተጀመረ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለቦርዱ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት ክስ ተከሣሽ /አመልካች/ በጌዶ፣ ነቀምት እና ጊምቢ በአከናወነው የትራስሚሽን መስመር መዘርጋት ሥራ ላይ በተለያየ የሥራ መደብ አገልግሎት ሰጥተናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ሥራ ላይ ለተሳተፉት ሠራተኞች በመሉ በመንግስት ትዕዛዝ መሠረት ከመጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ የሁለት እርከን ጭማሪ ሲያደርግ እኛን ግን ከልክሎናልና ለእኛም ይህን ጭማሪ ከሞራል ካሣ እና ከወጭና ኪሣራችን ጋር ሊከፍለን ይገባል ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ የተጠየቀው የእርከን ጭማሪ ክፍያ ለሌሎች ሠራተኞች ከተፈፀመበት ከመጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት እስከ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ከአስራ ሰባት ወር በላይ በመሆኑ ክሱ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/1-3/ መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል ሲል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በአማራጭም መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡



ክርክሩ የቀረበለት ቦርድም " …. የከሣሽና የተከሣሽ የሥራ ግንኙነት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ …." በክሱ የቀረበው ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር በመግባትም ከከሣሾቹ ውስጥ ከፊሎቹ ብቻ የአንድ እርከን ጭማሪ እንዲሰጣቸው እና ይኸውም ከመጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ተስተካክሎ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፍርዱ ጉድለት የለበትም በማለት የይግባኙን መዝገብ ዘግቶታል፡፡

በመቀጠል አመልካች ከአስራ ሰባት ወራት በኋላ የቀረበው የተጠሪዎች ክስ በይርጋ አይታገድም በሚል በመወሰኑ ሕግ ተጥሷል፤ እንዲሁም በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ የተሳሳተ ፍሬ ነገርን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ሊሻርልን ይገባል ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎችም በጠበቃቸው አማካኝነት በአቀረቡት መልስ መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. የእርከኑ ጭማሪ እንደሚሰጥ ውሣኔው ለሠራተኞቹ ይፋ የሆነበት ቀን እንጂ ክፍያው የተፈፀመበት ቀን አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ሌሎቹ ሠራተኞች የካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም. የእርከኑ ጭማሪ ተጠቃሚዎች መሆናቸው ሲገለጽላቸው ይህ ለተጠሪዎቹ ሳይደረግ በመቅረቱ ተጠሪዎቹ ይህን እንደአወቁ የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም. አቤቱታቸውን ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቅርበዋል፡፡ ለዚህ አቤቱታ በፅሁፍ ምላሽ ያላገኙ ስለሆነም የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል የሚልና በጥቅሉም ፍርዱ እንዲፀና የሚጠይቅ መልስ አቅርበዋል፡፡

ችሎቱም በዚህ ጉዳይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ በተጠሪዎች የቀረበው ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ሕግ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው አግባብነት ላለው አካል ቀርበው የሚታዩበትን የተለያየ የጊዜ ገደብ አስቀምጦ ይገኛል፡፡ በዚህም

ምክንያት አንድን ጉዳይ ለአንድ አካል አቅርቦ እንዲታይ ለማድረግ ጉዳዩ በሕግ የተፈቀደለትን የጊዜ ገደብ ጠብቆ የቀረበ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ በሕግ የተወሰነለትን ጊዜ አሳልፎ የቀረበ ጉዳይ ወደ ፍሬ ነገሩ ተገብቶ የመታየትን እድል ሳያገኝ ከወዲሁ ውድቅ ሊደረግ ወይም በይርጋ ሊታገድ ይችላል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በግራ ቀኙ የቀረበው ሙግት የሥራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ሕግም የአዋጅ ቁጥር 42/85 ነው፡፡ ይህ የአዋጅ ቁ. 42/85 በክፍል አስር ምዕራፍ አንድ ከአንቀጽ 162 — 166 በሚገኙት ሕጎች ስር ስለ ይርጋ ደንብ ደንግጓል፡፡ የአዋጅ ቁ. 42/85ን የሻረው የአዋጅ ቁ. 377/1996ም በተመሳሳይ የሕጉ ክፍል፣ በተመሳሳይ የሕጉ ምዕራፍ እና በይዘታቸው ጭምር አንድ አይነት በሆኑ አንቀጾች ስር የይርጋ ደንብን አስቀምጧል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የአዋጅ ቁ. 42/85 ነውና ለጭብጣችን ምላሽ ለመስጠት እንድንችል በዚህ ውሣኔያችን ውስጥ እንደአግባብነታቸው ይህ አዋጅ ያስቀመጣቸው የይርጋ ደንቦች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለት ሕጎች አንድ አይነት አንቀጾች የያዙ በመሆናቸው በዚህ ውሣኔ ውስጥ ለአዋጅ ቁ. 42/85 የይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የሚሰጠው ትርጓሜ በአዋጅ ቁ. 377/1996 ለሚገኙትም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

የአዋጅ ቁ. 42/85 የመብት ጥያቄዎች ስለሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በአንቀጽ 162 ላይ ደንግጓል፡፡ ከመነሻው የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በዚህም ሆነ በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ከአልተወሰነ በስተቀር ጉዳዩን ማቅረብ ከሚቻልበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ከአልቀረበ የመብቱ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ አመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የጉዳዩ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጉዳዩን ለማቅረብ ከሚቻልበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ እንዲሁም በሕግ የተለየ የጊዜ ገደብ ያልተደረለት ጉዳይ ሁሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ እንደሚገባው



በመደንገግ አጠቃላይ የሆነ የጊዜ ወሰን አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ይኸው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 በንዑስ አንቀጽ /2/፣ /3/ እና /4/ ላይ ሕጉ የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነላቸውን የአቤቱታ አይነቶች ለይቶ አመላክቷል፡፡

የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 የተለየ የይርጋ ጊዜ ከወሰነላቸው የመብት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያው የሆነው አንቀጽ 162/2/ "ሠራተኛው የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ሥራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል" በማለት ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩልም የሥራ ውልን መቋረጥ ምክንያት አድርጎ ሠራተኛው በአሰሪው ላይ አሊያም አሰሪው በሠራተኛው ላይ የሚያነሳው የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በስድስት ወር ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በዚሁ አንቀጽ 162/4/ ላይ ተደንግጓል፡፡ በግልጽ እንደሚታየው የመጀመሪያው ድንጋጌ የሥራ ውሉን መቋረጥ ሕጋዊነት በመቃወም ወደ ሥራዬ ልመለስ ይገባል የሚል ሠራተኛ ይህን ጥያቄውን ለማቅረብ የሦስት ወር ጊዜ ብቻ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ ሁለተኛው ድንጋጌ ደግሞ የሥራ ውልን መቋረጥ መነሻ አድርገው የሚቀርቡ ማናቸውም አይነት የክፊያ ጥያቄዎች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተገደቡ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ከእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በመብቱ መጠቀም የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው ወደ ሥራ ልመለስ ይገባል የሚል ክስ በሠራተኛው በእራሱ እንጂ በተተኪዎቹ ወይም በወራሾቹ ሊመሰረት የሚችል አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ከሥራ ውል መቋረጥ በኋላ ሠራተኛውም ሆነ አሰሪው አንዱ ከሌላው ወገን ሊጠይቋቸው የሚችሏቸው የክፍያ አይነቶች በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የሚታመን ነው፡፡

እንዲህ በሚሆን ጊዜ ተተኪዎቹ ወይም ወራሾቹ መሰረት አድርገው የሚቀርቡት የእራሳቸውን ሳይሆን የአውራሻቸውን ሠራተኛ ወይም አሰሪ መብት ነውና በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ ስለሆነም የሠራተኛውን ወይም የአሰሪውን መብት ተክተው በወራሾቻቸው ወይም በተተኪዎቻቸው የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎች የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ሊታገዱ ይገባል፡፡

ሌላው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነለት የአቤቱታ አይነት በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም " ሠራተኛው የሚያቀርበው የደመወዝ የትርፍ ሰዓትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ..." መቅረብ እንደሚገባውና ይኸ ካልሆነ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ይህን አንቀጽ ተመስርቶ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአሰሪውና በሠራተኛው መካከል የተፈፀመው የሥራ ውል ፀንቶ በአለበት ሁኔታ ሠራተኛው ከአሰሪው የሚጠይቀውን ክፍያ የሚመለከት እንጂ የግድ የሥራ ውሉን መቋረጥ ተከትሎ የሚነሳ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የስድስት ወሩ የይርጋ ጊዜ እንደሁኔታው ክፍያው ሊጠየቅ ይገባ ነበር የሚሰኝበትን እለት ተመስርቶ መቆጠር የሚጀምር እንጂ ውስን የመነሻ ጊዜ የተቀመጠለት አይደለም፡፡

ይኸ አንቀጽ 162/3/ ሠራተኛው አሰሪውን ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና ሌሎችም ክፍያዎችን ሊጠይቅ የሚችልበትን ውስን ጊዜ ያስቀመጠ ቢሆንም የሥራ ውልን መቋረጥ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደመነሻ ባለመውሰዱ ከአንቀጽ/2/ እና /4/ ይለያል፡፡ ይርጋውም ሠራተኛው የተጠቀሱትን ክፍያዎች ሊጠይቅ ይገባው ነበር ከሚሰኝበት ጊዜ ይነሳና ምናልባትም የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንኳ ቢሆን ይኸን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ እስከ ስድስት ወር ድረስ መቆጠሩ ይቀጥላል፡፡ እንዲሁም



እነዚህ ክፍያዎች በሠራተኛው ሳይሆን በተተኪዎቹ ወይም በወራሾቹ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ እንዲህ በሚሆን ጊዜም ጥያቄው የሠራተኛውን መብት ተመስርቶ የሚቀርብ ነውና ልክ እንደቀድሞው ሁሉ በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ ስለሆነም ተተኪዎች ወይም ወራሾች የተጠቀሱትን ክፍያዎች ሠራተኛው ሊጠይቅ ይገባው ነበር ከሚባልበት ጊዜ አንስቶ እስከ ስድስት ወር ድረስ ካልጠየቁ በቀር ክሳቸው በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡

እንግዲህ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ የተለየ የይርጋ ጊዜ የተቀመጠላቸውን የመብት ጥያቄዎች የሚመለከት ከሆነ ከንዑስ አንቀጽ/2/ እስከ /4/ የተጠቀሱትን የሦስት ወይም የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ አክብሮ የቀረበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር የማይሸፈን ከሆነ ደግሞ በንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተውና በአንፃሩም ሰፊ በሆነው የአንድ ዓመት የጊዜ ወሰን ውስጥ እንዲቀርብ ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የይርጋ ጊዜ የተወሰነበት የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 ሠራተኛውና አሰሪው አንዱ ከሌላቸው የመብት ጥያቄዎችን የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ብቻ በመጥቀስ የተደነገገ መሆኑን ከአንቀጾቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የሠራተኛው ወይም የአሰሪው ጥያቄ በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው በሚቀርብበት ጊዜም የይርጋው አቆጣጠር ሊለወጥ እንደማይገባ ከላይ ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ የሠራተኛውም ሆነ የአሰሪው ተተኪዎች ወይም ወራሾች የሠራተኛውን ወይም የአሰሪውን ሳይሆን የእራሳቸውን መብት መሠረት አድርገው አንዳቸው ከሌላቸው ክፍያ ሊጠይቁ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ እንዲህ በሚሆን ጊዜ ግን የይርጋው አቆጣጠር ከአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ ወይም /4/ አኳያ ሳይሆን አጠቃላይ የይርጋ ደንብ ድንጋጌ ከሆነው ከአንቀጽ 162/1/ አግባብ መታየት ይገባዋል፡፡ ስለሆነም የተጠቀሱት ሰዎች

በእራሳቸው መብት ላይ ተመስርተው የሚያቀርቡት ክስ በሌላ ሕግ ላይ በሌላ የይርጋ ደንብ ካልተሸፈነ በቀር በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/1/ መሠረት የመብታቸውን ጥያቄ ሊያቀርቡ ከሚችሉበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ አመት ድረስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ ሊቀርብ የሚችልበትን የጊዜ ወሰን አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ጉዳይ በሕግ የተወሰነለትን የጊዜ ወሰን ጠብቆ ባይቀርብም እንኳን ሊታይ የሚችልባቸው ሦስት ሁኔታዎች እንዳሉ ደንግጓል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ከአንቀጽ 164 እስከ አንቀጽ 166 ባሉት ድንጋጌዎች ላይ ተጠቅሰው የሚገኙ ሲሆን እነርሱም፡- የይርጋ ጊዜ መቋረጥ፣ የይርጋ መብትን መተው እና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጊዜው ያለፈበትን ክስ መቀበል መሆናቸው በእነዚሁ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡

## ስለ ይርጋ ጊዜ መቋረጥ

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የመጀመሪያው ሁኔታ የይርጋ ጌዜ መቋረጥን ይመለከታል፡፡ ይህ ሁኔታ የተደነገገበት የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164 የይርጋ ጊዜ፡

1. የሥራ ክርክርን ለሚወሰን ባለስልጣን ክስ ቀርቦ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ፣
2. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈጸም ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሣኔ በጽሁፍ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ፣
3. በይርጋው ጊዜ ተጠያቂ የሆነው ወገን የሌላውን መብት በጽሁፍ ሲያውቅለት ወይም በከፊል ሲፈጽምለት ሊቋረጥ እንደሚችል ደንግጓል፡፡



በመሰረቱ አንድ ወገን ተከራካሪ በሌላው ላይ ክስ መስርቶ የመገኘቱ ጉዳይ ተጀምሮ የነበረን የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር እንደሚያቋርጠው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1851/ለ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ለሥራ ክርክር ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የአዋጅ ቁ. 42/85ም ከዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ጋር በተስማማ ሁኔታ ክስ አቅርቦ የመገኘት ነገር የይርጋን ጊዜ አቆጣጠር እንደሚያቋርጥ በአንቀጽ 164/1/ ላይ ጠቅሶታል፡፡ የይርጋውን አቆጣጠር የሚያቋርጠው ክስ የተመሰረተውም የሥራ ክርክርን ከሚወስን ባለስልጣን ዘንድ ሊሆን እንደሚገባ በንዑስ አንቀጹ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ የሥራ ክርክርን እንዲወስን ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን ሲል ማንን ለማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ስለማይሰጥ ይህን ነጥብ ለመፍታት ይተረጎም ዘንድ ያስፈልጋል፡፡ ከአዋጅ ቁ. 42/85 አግባብ የሥራ ክርክር የሚወሰን ባለሥልጣን ሊሰኝ የሚችለው የትኛው አካል ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ " ውሣኔ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማየቱ ይጠቅማል፡፡ ይህ "ውሣኔ" የሚለው ቃል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 3 ላይ አንድን ክርክር የያዘ ፍርድ ቤት "... ተከራካሪዎቹ ወገኖች ያቀረቡትን ክስና መልስ እንዲሁም ማስረጃዎቹን መርምሮ ...." የሚሰጠው ውሣኔ ማለት እንደሆነ ተተርጉሟል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ ከዚህ ትርጓሜ አኳያ ሲታይ አንድን አካል የሥራ ክርክርን የሚወስን ባለስልጣን ነው በሚል ለመፈረጅ ተቋሙ በሥራ ክርክር ጉዳይ ላይ ግራ ቀኝ ወገንን አከራክሮ ውሣኔ ለመስጠት በአዋጁ ስልጣን የአገኘ ሊሆን ይገባዋል፡፡ እንደሚታወቀው በአዋጁ መሰረት አንድም ፍርድ ቤቶች በስራቸው በተቋቋሙ የሥራ ክርክር ችሎቶች አማካኝነት፤ ሌላም በየክልላዊ መስተዳድሩ የተቋቋመ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሥራ ክርክር ጉዳይ ላይ ውሣኔ ይሰጡ ዘንድ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይኸንንም ከአዋጁ አንቀጽ 137-140 እንዲሁም ከ147-156 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ላይ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ሁለት ዳኝነት

ሰጭ አካላት የሥራ ክርክርን ለመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው ልንላቸው እና የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/1/ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ሲል አንድም ፍርድ ቤትን ሌላም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን ማለቱ ነው። በሚል ልንተረጉመው ይገባል።

በተጨማሪም የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/1/ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ክስ ማቅረብ የይርጋን ጊዜ እንደሚያቋርጥ ከሚደነግግ በቅር ክሱ ክርክሩን ለመዳኘት ስልጣን ለሌለው አካል ቢቀርብ የይርጋው አቆጣጠር ምን ሊሆን እንደሚገባ አላመለከተም። ለምሳሌ ፍርድ ቤት እና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሁለቱም የሥራ ክርክርን ለመዳኘት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ቢሆኑም ፍርድ ቤት የወል የሥራ ክርክርን፤ ቦርድ ደግሞ የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከቱ ክሶች ይዳኙ ዘንድ በአዋጁ ስልጣን አልተሰጣቸውም። ስለሆነም እነዚህ አካላት ዘንድ የቀረበው ክስ በስልጣናቸው ሊሸፈን የማይችል የሥራ ክርክር ሆኖ ቢገኝ የይርጋው አቆጣጠር ይቋረጣል? ለሚለው ጥያቄ ድንጋጌው ግልጽ ምላሽ ስለማይሰጥ ነጥቡን ለማጥራት ይቻል ዘንድ ድንጋጌው ከሌላ ተዛማጅነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ እንዲተረጎም ያስፈልጋል። በዚህ ችሎት እምነትም ለዚህ ጉዳይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278/3/ አግባብነት ይኖረዋል።

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278/3/ በፍርድ ቤት ፈቃድ እንደገና ስለሚቀርቡ ክሶች የይርጋ አቆጣጠር የሚደነግግ ነው። ይኸውም አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ በከፊልም ሆነ በሙሉ አንስቶ ከሣሹ ክሱን እንደገና እንዲያቀርብ ሲፈቅድ የይርጋው ዘመን የመጀመሪያው ክስ እንዳልቀረበ ተቆጥሮ በአዲሱ ክስ መሰረት እንደሚታሰብ ይጠቅሳል ይኸም ሁለተኛው ክስ የቀረበው የፍርድ ቤትን ፈቃድ ተመስርቶ ቢሆንም እንኳ የቀደመው ክስ የኋለኛውን ክስ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር እንደማያቋርጠው ያስረዳናል። ሕጉ ይህን ከአልፈቀደ ደግሞ ከሣሽ ክርክሩን ለመዳኘት ከስልጣኑ ውጭ ለሆነ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በሁለተኛ ደረጃ የመሰረተውን ክስ የይርጋ አቆጣጠር ያቋርጠዋል ማለቱ አሳማኝነት የሌለው



ይሆናል። የያዝነው ጉዳይ ከዚህ ሕግ አግባብ ሲታይ ደግሞ አንድ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ክስ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ቀርቦ መገኘቱ ብቻውን የይርጋውን ዘመን አቆጣጠር የሚያቋርጠው አይሆንም። ክሱ የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር ያቋርጠዋል ይሰኝ ዘነድ ለፍርድ ቤት ወይም ለቦርድ መቅረቡ ብቻ ሳይሆን የቀረበው የሥራ ክርክሩን ጉዳይ ለመዳኘት በሕጉ ስልጣን ላለው አካል እንዲሆን ያስፈልጋል።

ሌላው የይርጋን ዘመን አቆጣጠር የሚያቀርጠው የአዋጅ ቁ. 42/85ን እንዲያስፈፅም ስልጣን ለተሰጠው አካል አቤቱታ አቅርቦ መገኘት መሆኑ በአንቀጽ 164/2/ ላይ ተመልክቷል። ይህ አካል የመጨረሻ ውሣኔ በጽሁፍ እስከሚሰጥ ድረስ ይርጋው ሊቋረጥ እንደሚገባም በድንጋጌው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ አዋጁን እንዲያስፈጽም ስልጣን የተሰጠው አካል ማን ነው? በዚህ አካል የሚተላለፈው ውሣኔስ በሕጉ አግባብ ውሣኔ ሊሰኝ ይገባዋል? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለማግኘት ድንጋጌውን መተርጎም ይገባናል።

በቅድሚያ ሁለተኛውን ጥያቄ እናያለን። በመሰረቱ ከሕግ አግባብ "ውሣኔ" ሊባል የሚገባው ምን ዓይነት ውሣኔ እንደሆነ ከፍ ሲል ተገልጿል። "ውሣኔ" ሊሰጡ የሚችሉት የሥራ ክርክርን ለመዳኘት ስልጣን ያላቸው አካላት ብቻ መሆናቸውንም በችሎት ከተሰጠው ትርጓሜ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አዋጁን ለማስፈፀም ስልጣን በአለው አካል የሚሰጥ ውሣኔ የአስተዳደር ውሣኔ ሊባል ከሚችል በቀር በሕጉ አግባብ በዳኝነቱ አካል እንደተሰጠ ውሣኔ የሚቆጠር አይደለም።

ወደ መጀመሪያው ጥያቄ ስንመለስ ጉዳዩን የሠራተኛና የማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም የክልሎች የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን አኳያ መመርመሩ ተገቢነት ይኖረዋል። ይህ ሚኒስቴር በርካታ ተግባሮችን እንዲያከናውን በአዋጅ ቁ. 42/85 ስልጣን የተሰጠው ሲሆን ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። ከአዋጁ አንቀጽ 119 ብንጀምር ይህ ሚኒስቴር በዚህ ድንጋጌ መሠረት

የማሕበራትን ምዝገባ ሊከለክል ይችላል፤ በአንቀጽ 120 እና 122 መሠረት የማሕበራትን የመመዝገቢያ የምስክር ወረቀት በመሰረዝ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሣኔ ሊያሳልፍ ይችላል፤ በአንቀጽ 20 መሰረት ሠራተኛን ከሥራ ለማገድ የተሰጠ ምክንያት በቂ በመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤ ከዚህ የሚኒስቴሩ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደሚችል ደግሞ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 20/3/ ላይ ተመልክቷል፤ በተጨማሪም ሚኒስቴሩ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 137/2/ መሠረት ፍርድ ቤት ዘንድ ተገቢ ብዛት ያላቸው የሥራ ክርክር ችሎቶች ይቋቋሙ ዘንድ ለተገቢው አካል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል፤ በአሰሪውና በሠራተኛው መካከል የወል የሥራ ክርክር ሲነሳ በንቀጽ 141 መሠረት ጉዳዩን በማስማማት ለመጨረስ አስማሚ ይመድባል፤ እንደዚሁም በአንቀጽ 178 መሠረት ስለ ሥራ ሁኔታ ቁጥጥር የሚያደርጉ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡ እነዚህ ከሞላ ጎደል የተጠቀሱት በሕጉ የተፈቀዱት የሚኒስቴሩ ተግባራት ሚኒስቴሩ በአሰሪና ሠራተኛው ግንኙነት ላይ ከፍተኛ የሆነ የአፈፃፀም ኃላፊነት እንዳለበት ያረጋግጡልናል፡፡ ሌላ ከሚኒስቴሩ የተስተካከለ የአስፈፃሚነት ኃላፊነት የተሰጠው አካል አለመኖሩንም ከአዋጁ መረዳት ይቻላል፡፡ ይልቁንም ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ 170/1/ ላይ ሕጉን ለማስፈፀም ይችል ዘንድ በበርካታ ጉዳዮች ላይ መመሪያ የማውጣት ስልጣን እንደተሰጠው ተመልክቷል፡፡ ይህም ሚኒስቴሩ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግን በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈጸም በአዋጁ ስልጣን የተሰጠው ብቸኛ አካል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ለዚህ አካል /በስሩ እንዲመድባቸው ስልጣን ለተሰጠው ተቋማት ጭምር/ በአዋጁ እንዲያከናውናቸው ስልጣን በአገኘበት ተግባራት ረገድ አቤቱታ አቅርቦ መገኘትም በአንቀጽ 164/2/ መሠረት የይርጋውን ዘመን አቆጣጠር የሚያቋርጠው ይሆናል፡፡



የመጨረሻው ለይርጋ ጊዜ መቋረጥ ምክንያት የሚሆነው በአንቀጽ 164/3/ ላይ እንደተመለከተው በይርጋው ጊዜ ማለፍ ተጠቃሚ የሆነው ወገን ያልሆነውን ወገን መብት በቃል ሳይሆን በጽሁፍ ሲያውቅለት አሊያም መብቱን በከፊል ፈጽሞለት ሲገኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ምክንያት የይርጋውን አቆጣጠር ከሦስት ጊዜ በላይ ሊያቋርጠው እንደማይችል በዚሁ ድንጋጌ ላይ የተመለከተ ነው፡፡

በእርግጥ የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164 ሦስት አይነት የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች ያስቀመጠ ቢሆንም የይርጋው መቋረጥ በይርጋ ዘመኑ አቆጣጠር ላይ ያለውን ውጤት ግን አላመለከተም፡፡ በመሆኑም የይርጋ ጊዜ መቋረጥ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ለማወቅ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1852/1/ን ከጉዳዩ ጋር አገናዝቦ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ይህ አንቀጽ አንድ የይርጋ ዘመን ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ "... እንደገና አዲስ የይርጋ ዘመን ..." ሊቆጠር እንደሚገባ ደንግጓል፡፡ ይህም ይርጋው ከመቋረጡ በፊት ተቆጥረው የነበሩት ቀናት እንዳለ ቀሪ እንደሚሆኑና የይርጋው ጊዜ እንደገና እንደ አዲስ ተብሎ ሊቆጠር እንደሚገባ ያስገነዝበናል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164 በተመለከቱት ሁኔታዎች ሳቢያ አንድ የይርጋ ጊዜ መቋረጡ ቢረጋገጥ ቀጣዩ የይርጋ ዘመን ይኸን ከፍ ሲል የተጠቀሰውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1852/1/ የተመለከተውን አቆጣጠር ይከተል ዘንድ ያስፈልጋል፡፡

በመሰረቱ አንድ የሥራ ክርክር ክስ የቀረበበት ወገን ክሱ የይርጋ ጊዜው ያለፈበት ነው ሲል ቢቃወም በእርግጥ ክሱ ጊዜው ያለፈበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ የጉዳዩ ጭብጥ ሆኖ እንደሚያዝ ይታመናል፡፡ ለዚህ ጭብጥ መመስረት ምክንያት የሆነው ክርክር የቀረበው በተከሣሹ በመሆኑም የይርጋውን ጊዜ ማለፍ ያስረዳ ዘንድ ይገባዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱን ያቀረበው ወገን የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል የሚል

ክርክር የሚያነሳ ቢሆን ይህን ሙግቱን በቅድሚያ ያስረዳ ዘንድ ይጠበቅበታል፡፡

በተጨማሪም የሥራ ክርክር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሣሹ አስቀድሞ በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤት ወይም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ማቅረቡን ከአረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ 164/1/ መሠረት የይርጋውን ዘመን መቋረጥ ሊቀበለው ይገባል፡፡ ከተጠቀሰው የሕጉ መስፈርት ውጭ የሆኑ ምክንያቶችን ለውሣኔው መሠረት ሊያደርግ አይችልም፡፡ ለምሳሌ ያህል ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ለሥራ ክርክር ችሎቱ ነበር በሚልና በመሳሰለ ምክንያት የይርጋውን አቆጣጠር መቋረጥ አልቀበልም ሊል አይችልም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ሚኒስቴሩ ብቻ መሆኑ ከላይ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሣሹ ለዚህ ሚኒስቴር /በስሩ ለሚመድባቸው ተቋማት ጨምሮ/በስልጣኑ ክልል አቤቱታ አቅርቦ እንደነበር ከአረጋገጠ የይርጋውን ዘመን በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/2/ መሠረት ሊያቋርጠው ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ለሆነ አካል አቤቱታ መቅረቡ መረጋገጡ ግን የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጠው አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ከሣሽ ሠራተኛ ለአሰሪው መ/ቤት አቤቱታ አቅርቤ ውጤቱን ስጠባበቅ ነበር ሲል መከራከሩንና ይህንንም ማረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ለይርጋው ዘመን አቆጣጠር ማቋረጫ አድርጎ ሊወስድለት አይችልም፡፡

## የይርጋ መብትን ስለመተው

እንደሚታወቀው በአዋጅ ቁ. 42/85 ውስጥ የተመለከተው የይርጋ ሕግ በፍሬ ነገር ሕግ /Substantive law/ ላይ እንጂ በሥነ ሥርዓት ሕግ /Procedural law/ ላይ የተቀመጠ የይርጋ ደንብ አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ሕግ /Substantive law/ ላይ የሚገኝ የይርጋ ደንብ ደግሞ በተከሣሹ ወገን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ሊቀርብ የሚገባው ነው፡፡



ተከሣሹ በመቃወሚያነት አንስቶ ከአልተከራከረበት በቀር ፍርድ ቤት በእራሱ አነሳሽነት ጉዳዩ የይርጋ ጊዜ ያለፈበት መሆን አለመሆኑን አጣርቶ እና ሕጉን ጠቅሶ ፍርድ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ስለሆነም አንድ የሥራ ክርክር ክስ የተመሰረተበት ተከሣሽ የይርጋውን ክርክር በመቀወሚያነት ካላነሳው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 165 አግባብ በዚህ ረገድ የመከራከር መብቱን እንደተወው ይቆጠራል፡፡ በውጤቱም በሕግ የተወሰነለትን ጊዜ አሳልፎ የቀረበው ክስ በይርጋ ምክንያት ውድቅ ሳይደረግ ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር ተገብቶ የመዳኘት እድልን ያገኛል፡፡

## ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

አንድ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ክስ የይርጋ ጊዜውን አሳልፎ ቢቀርብ እና ይህ የሆነው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በውሣኔ ሰጭው አካል ቢረጋገጥ ምንም እንኳን ክሱ ጊዜው ያለፈበት ቢሆንም ሊታይ እንደሚገባ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 166 ላይ ተደንግጓል፡፡ የተጠቀሰው ምክንያት በተወገደ በአስር ቀን ውስጥ ያልቀረበ ክስ ግን ተቀባይነት እንደማያገኝ በዚሁ ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል፡፡

በግልጽ እንደሚታየው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ አልተተረጎመም፡፡ ስለዚህም ጉዳዩን ይህን ሐሳብ ከሚተረጉመው የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1792 ጋር አገናዝቦ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792 እንደተደነገገው

> ከዓቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው አንድ ባለዕዳ ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍጹም መሰናክል በሆነ ዓይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመው ጊዜ ነው፡፡

ጉዳዩ ከዚህ ትርጉም አኳያ ሲታይ አንድን የሥራ ክርክር ክስ ጊዜው ሊያልፍበት የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል

ለመፈረጅ ክሱ ቀድሞ ሊታሰብ በማይችል እና ከሣሹም ፍጽም የሆነ መሰናክል የገጠመው በመሆኑ ምክንያት ብቻ በጊዜው ሳይመሰረት መቅረቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ትርጓሜ እነዚህ ምክንያቶች ምን አይነት ምክንያቶችን ይመለከታል? የሚለውን ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ይሆናል፡፡ የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 166 ከአቅም በላይ ሊሰኙ የሚችሉ ምክንያቶችን ያላመላከተን በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ እንደገና ወደ ፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መመለስ ያስፈልገናል፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ በቁጥር 1793 ላይ ከአቅም በላይ ሊሰኙ የሚችሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር አስቀምጧል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ/ ባለዕዳው አላፊ የማይሆንበት ያልታሰቡና በሌላ ሰው ላይ የሚመጡ ድንገት ደራሽ ነገሮች፣

ለ/ ውሉ እንዳይፈጸም በመንግሥት የሚደረግ ክልከላ፣

ሐ/ እንደ መሬት መናወጽ፣ መብረቅ፣ ማዕበል ይህን የመሳሰለ ፍጥረታዊ መቅሠፍት፣

መ/ የጠላት የውጭ አገር ጦርነትና የአገር ውስጥ ጦርነት፣

ሠ/ የባለዕዳው መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ሕመም /መሆናቸው ተመልክቷል/፡፡

እንግዲህ ከሣሽ ክሱን በጊዜው ያልመሰረተበት ምክንያት ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ በተመከቱት ምክንያቶች ስር የሚሸፈን ከሆነ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ገጥሞታል የሚሰኝ ይሆናል፡፡ ዳኝነት ሰጭው አካልም ይህንን ከአረጋገጠ ጊዜው ያለፈበትን ክስ ተቀብሎ ወደ ፍሬ ጉዳዩ በመግባት ፍርድ ይሰጥበት ዘንድ ይገደዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 166 " ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት "ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተረጎመም፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ምን አይነት ሊሆኑ እንደሚገባም አላመለከተም፡፡ ነገር ግን



በይርጋ የታገደን ክስ ለመቀበል" በቂ ምክንያት" ተደርገው የሚወሰዱ ምክንያቶችን አመላክቷል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ የሠራተኛ መታመም፣

ለ/ የሠራተኛው በትዕዛዝ ከመደበኛ የመኖሪያ ሥፍራ ውጭ መዛወር

ሐ/ የሠራተኛው ከብሔራዊ ጥሪ ላይ መገኘት

እነዚህ በድንጋጌው የተመለከቱት ውስን ምክንያቶች በሠራተኛው የቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ መሆኑ ቢታይም ተቀባይነት ያገኝለት ዘንድ የሚፈቅዱ ናቸው፡፡ እንዲሁም እነዚህ እክሎች የገጠሙት ሠራተኛ ጉዳይ በዳኝነት አካል ሳይታይለት እንዳይቀር ልዩ የሆነ ጥበቃ የማድረግን ነገር አላማ ማድረጋቸውን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል ነው፡፡ በእርግጥ እነዚህ ምክንያቶች በሠራተኛው ክስ ተጠቅሰው መገኘታቸው ብቻውን ጊዜው ያለፈበትን ጉዳይ ለመቀበል የሚበቃ አይሆንም፡፡ ይህን ማድረግም ከድንጋጌው አላማ ጋር የተጣጣመ መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ አይረዳንም፡፡ ስለሆነም ሠራተኛው ጊዜው ያልፈበትን ክስ ቢያቀርብ እና ጉዳዩ ከዚህ ድንጋጌ አግባብ እንዲታይለት ቢጠይቅ መታመሙን ወይም በትዕዛዝ ከመኖሪያ ሥፍራው መዛወሩን ወይም በብሔራዊ ጥሪ ላይ የነበረ መሆኑን የሚያሳይለትን ማስረጃ በማቅረብ በቅድሚያ ክርክሩን ያስረዳ ዘንድ ያስፈልጋል፡፡ ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የምክንያቱን ተገቢነት በግራ ቀኙ ከቀረበለትም ሆነ በእራሱ አነሳሽነት ከአስመጣው ማስረጃ አኳያ ሊመረምረው ይገባል ፍርድ ቤቱ ይህን ሲያደርግም እነዚህ ምክንያቶች ሠራተኛው ክሱን እንዳይመሰርት መሰናክል የሆኑበትን መጠን ጭምር ከግምት እንዲያስገባ ያስፈልጋል፡፡ በውጤቱም ፍርድ ቤቱ እነዚህ ምክንያቶች ከሣሹ ክሱን ሊመሰርት በማይችልበት ደረጃ ላይ አድርሰውት ነበር ሲል የሚያምንበት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ፍርድ ቤቱ በይርጋ የታገደውን ክስ ከወዲሁ ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

አሁን በዚህ መዝገብ ወደተያዘው ክርክር እንመለሳለን፡፡ በዚህ ውሣኔ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ለቦርድ አቅርበውት የነበረው ክስ ለሌሎች ሠራተኞች የተደረገው የሁለት እርከን ጭማሪ ለእኛም ሊሰጠን ይገባል የሚል ሲሆን አመልካችም ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ተቃውሞውን አቅርቦ የተከራከረበት ነው፡፡

በመሠረቱ ይህ የተጠሪዎቹ ጥያቄ የክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ እንዲሁም የክፍያ ጥያቄው በመካከላቸው ያለው የሥራ ውል ፀንቶ በአለበት ጊዜ የተነሳ እንጂ የሥራ ውል መቋረጥን ተከትሎ የቀረበ አይደለም፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የይርጋው አቆጣጠር ጉዳይ በተለይ ከተደነገገው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ አግባብ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በዚህ የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ መሠረት የተጠቀሰው የክፍያ ጥያቄ ሊጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ድረስ ካልተጠየቀ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ የሁለት እርከን ጭማሪ ለሌሎች ሠራተኞች ተደርጓል የሚሉት መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. እንደነበር ከስር ውሣኔ ላይ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ክሳቸውን ለቦርድ ያቀረቡት ደግሞ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም. መሆኑ በስር ውሣኔ የተመለከተ ነው፡፡ በዚህ ችሎት እምነት አመልካች ለሌሎቹ ሠራተኞች ጭማሪውን አድርጓል መባሉ በስር ክርክር በተጠሪዎች ጭምር የታመነበት መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ክፍያው በተጠሪዎች ሊጠየቅ የሚገባበት ጊዜ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡ የተጠሪዎቹ ክስ የቀረበው ከዚህ ጊዜ በኋላ ከአንድ ዓመት በላይ ቆይቶ በመሆኑም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት በስድስት ወሩ ይርጋ ሊታገድ የሚገባው መሆኑ የማያከራክር ነው፡፡

በእርግጥ ተጠሪዎች የእርከን ጭማሪው ለሌሎቹ ሠራተኞች የተደረገው መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. አይደለም፡፡ ይኸ ቀን ጭማሪ መደረጉ ለሠራተኞች ይፋ የተደረገበት ቀን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም. ለሌሎቹ



ሠራተኞች ተጠቃሚ መሆናቸው ሲገፍላቸው ለተጠሪዎች ግን ይኸ ባለመደረጉ የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም. ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቤቱታ በማቅረባችን የይርጋው አቆጣጠር ተቋርጧል በማለት በስር ፍርድ ቤቶች ያላነሱትን ክርክር ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ በመሰረቱ ይኸ የተጠሪዎቹ ክርክር በዚህ ችሎት የቀረበ አዲስ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባ አልነበረም፡፡ ይኸ ቢታለፍ ደግሞ አሁንም ተጠሪዎቹ ሌሎቹ ሠራተኞች የእርከን ጭማሪው ተጠቃሚ መሆናቸው ሲገፍላቸው ለእኛ ይህ ሳይደረግ ቀርቷል ከሚሉበት ከየካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም. ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ማለትም እስከ ነሐሴ 8 ቀን 1993 ዓ.ም. ክሱን ሊመሰርቱ ሲገባ ይህን አድርገው ባለመገኘታቸው ይህም ክርክራቸው የይርጋውን ጊዜ ማለፍ የሚያረጋግጥባቸው ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ችሎት ለአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/2/ ከሰጠው ትርጓሜ አግባብ የአመልካች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቤቱታ ማቅረብ አዋጁን እንዲያስፈጽም ስልጣን ለተሰጠው አካል አቤቱታ እንደማቅረብ ስለማይቆጠር ይኸ ተጠሪዎቹ ፈጽመነዋል ያሉት ድርጊትም የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ/ ተጠሪዎች በአመልካቹ ላይ የመሰረቱት ክስ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ መሰረት በይርጋ ሊታገድ ይገባል፡፡

2ኛ/ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደቅደም ተከተላቸው በመ.ቁ. 171/02/93 እና በመ.ቁ.28793 የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ አድርገው የአንድ እርከን ጭማሪ ለተጠሪዎች እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መ/ቁ.11924

ሕዳር 15 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ትዕግስት ወርቁ

*የሥራ ውል ስለሚቆይበት ጊዜ - ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል እና ለተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል - ስለ ስራ ውል መቋረጥ እና ውዝፍ ዕዳ ክፍያን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9፣ አንቀጽ 10 እና 24*

ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ወደ ስራ እንድትመለስ እና የአንድ አመት ደመወዝ እና የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት በማለት ስለወሰኑ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u> ፡-የአመት ፈቃድን በተመለከተ ሳይጨምር በቀረቹ ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔች ተሽረዋል፡፡

1ኛ. በአንድ አሠሪ እና ሠራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ያልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል፡፡ እንዲሁም ማናቸውም የስራ ውል ጊዜ እንዲልተወሰነለት የስራ ውል ሊወሰድ ይገባል፡፡

2ኛ. ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ አንድ የሥራ ውል ውሉ መስፈርቶችን በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 10 መሠረት ያሟላ ከሆነ ሊቆይ የሚችለው ጊዜው እስከሚያልቅ ወይም ስራው እስከሚያልቅ ድረስ ነው፡፡



የሰበር መ/ቁ.11924

ሕዳር 15 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን - ግርማ ማርቆስ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ትዕግስት ወርቁ - ቀረበች

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 24/1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 22/1997 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላ አገልግሎት ውስጥ በሚገኝ የስራ መደብ በተላላኪነት ሳገለግል ቆይቼ አለአግባብ የስራ ውሌን ስላቋረጠው ጥቅሜን ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሰኝ፤ አሊያም የስራ ስንብት ክፍሎ ያሰናብተኝ ስትል በአሁን አመልካች ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመሰረተችው ክስ ነው፡፡ ይህም ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በጉዳዩ አከራክሮ ተጠሪ ወደ ስራ እንድትመለስ፤ የአንድ ዓመት ደመወዝ እና የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፍርዱ ጉድለት ያለበትም በማለት የይግባኙን መዝገብ ዘግቶታል፡፡

ይህም ችሎት ግራ ቀኙ በጉዳዩ ያቀረቡለትን ክርክር መርምሯል፡፡

በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተደረገው የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የተደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በጉዳዩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ጭብጡን አሳማኝ በሆነ መልኩ ለመፍታት ይቻል ዘንድም በቅድሚያ የሥራ ውል ስለሚቆይበት ጊዜ የሚደነግጉትን የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9 እና 10ን በመመስረት ነጥቡን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ አንቀጽ 9ን እንመልከት፡፡ ይህ አንቀጽ … በአንቀጽ 10 ከተመለከቱት በቀር ማንኛውም የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የስራ ውል ቆይታን

የሚመለከት አንድ መሰረት አስቀምጧል፡፡ ይኸውም በአንድ አሰሪ እና ሰራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ተደርጎ ሊቆጠር እንደሚገባ አመልክቷል፡፡ እንዲሁም ማናቸውም የስራ ውል ጊዜ እንደአልተወሰነለት የስራ ውል ሊወሰድ ይገባው ዘንድ ሕጉ ግምት የወሰደበት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንደ አንቀጽ 9 አገላለጽ አንድ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያስቀምጠረውን የሕግ ግምት ቀሪ አድርጎ ውሉን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነው የሚል ለመፈረጅ የስራ ውሉ ከአዋጅ አንቀጽ 10 አኳያ የተደረገ መሆኑ እንዲረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ወደ ተከታዩ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 ስንመለስ ይህ አንቀጽ ለተወሰነ ስራ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የስራ ውል ሊደረግባቸው የሚችልባቸውን ሁኔታዎች በመዘርዘር አስቀምጧል፡፡ ይህም በድንጋጌው የተወለከቱት መስፈርቶች የመማላታቸው ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲቆይ በማድረግ፤ አሊያም የተወሰነ ስራ ለመስራትም ሆነ ለማሰራት ብቻ ሲባል ማድረግ በሕግ የተፈቀደ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንደዚሁም ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የስራ ውል የሚደረገው በአንቀጹ በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ መሆኑን በመጠቆም አንድን የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል ማድረግ እንደ ልዩ ሁኔታ ሊቆጠር የሚገባው ተግባር መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህ የሕጉ መንፈስም በዚህ ድንጋጌ /በአንቀጽ 10/ ሊሸፈኑ የማይችሉ የስራ ውል አይነቶች ሁሉ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረጉ ይቆጠራሉ በሚል በተደነገገው የአዋጁ አንቀጽ 9 ይደግፋል፡፡

እንግዲህ አንድ የሰራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ በመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ላይ ሙግት ሲነሳ በቅድሚያ በአሰሪው እና በሰራተኛው መካከል በጽሑፍም ሆነ በቃል የተደረገውን የስራ ውል ይዘት ሰፊ ዝርዝር ከያዘው የአዋጁ አንቀጽ 10 ጋር እያገናዘቡ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም አንድ አሳማኝነት ያለው መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ሕጉ እንደዚህ ያሉ የስራ ውሎች እንዲደረጉ የፈቀደባቸውን የስራ ሁኔታዎች መለየት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ እንዲሆም የስራ ውሉ ከተጠቀሰው ድንጋጌ አግባብ የተደረገ መሆኑን የማስረዳት ሸክሙ የአሰሪው ነው? ወይስ የሰራተኛው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠትን ይጠይቃል፡፡ በአጠቃላይ ይህን የአዋጁን አንቀጽ 10 የመተረጎምን ጉዳይ የግድ ያደርገዋል፡፡

በግልጽ እንደሚነበበው የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10፡-

1. *የተወሰነ ሥራ ለመሥራት* /the performance of specified piece work/
2. *ለጊዜው በሥራው ቀሪ የሆነን ሠራተኛ ለመተካት* /the replacement a worker who is temporally absent/:
3. *የሥራ ብዛትን ለማቃለል*/ in the event of abnormal pressure of work/:
4. በህይወት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚያስችል አጣዳፊ ስራን ለመስራት እንዲሁም በሥራ ወይም በንብረት ላይ የደረሰን ጉዳትና ብልሽት ለማደስ /urgent work, to prevent damage or disaster to life or property, to repair defects of breakdowns in works, materials, buildings or plants of the works of the undertaking/:
5. *እየተቃረጠ የሚሰራን ቋሚ የአሠሪ ሥራ ለመሥራት* /an irregular but permanent part of the employer/:
6. *ወቅት ጠብቆ የሚሠራን ቋሚ የአሠሪ ሥራ* /seasonal but permanent part of the works of the employer/:
7. *ቋሚ ያልሆነ እና አንዳንዴ በሚያስፈልግ ጊዜ በቻ የሚሠራን ሥራ ለመሥራት* /an occasional and not part of the permanent activity of the employer/ የተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ *ሥራ* ውል ማድረግ እንዲቻል ደንግጓል፡፡

በዚህ ችሎት እምነት ይህ ድንጋጌ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል የሚደረግባቸውን ሶስት አይነት የሥራ ሁኔታዎች ያመላክታል፡፡ የእነዚህን የሰራ ሁኔታዎች አይነት ለመለየት ድንጋጌው ቋሚ እና ቋሚ ያልሆኑ የአሠሪ ስራዎች ሲል ለይቶ ከአስቀመጣቸው ንዑስ አንቀፆች መነሳቱ ነገሩን ግልፅ ያደርገዋል፡፡

ቋሚ በሆነ የአሰሪ ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ለማድረግ የሚቻል መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩን የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ

/5/ እና /6/ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ድንጋጌዎች የስራ ውሉ የሚደረግባቸው ቋሚ የአሰሪው ስራዎች እየተቃረጡ ወይም ወቅት ጠብቀው የሚሰሩ ሊሆኑ እንደሚገባቸው በማመልከት ተጨማሪ መስፈርቶችን አስቀምጠዋል፡፡ ይህም የድንጋጌዎቹ ይዘት ቀጣይነት በሌላቸው /በተከታታይነት በማይሰሩ/ የአሰሪው ቋሚ ስራዎች ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ሊደረግ የሚችል መሆኑን እና እነዚህም እንደ አንድ የሥራ ሁኔታ ልንወስዳቸው እንደሚገባ ያስገነዝቡናል፡፡

ይሁን እንጂ የቀጠቀሰው የድንጋጌዎቹ መንፈስ ቋሚ በሆነና ያለማቋረጥ በተከታታይ በሚሰራ የአሰሪው ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ለማድረግ አይቻልም? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚቻል የታመናል፡፡ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 ከአስቀመጣቸው ከፍ ሲል ከተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች ውስጥ ቀጣይነት በአለው የአሰሪው ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ውል ማድረግ እንደሚቻል በግልጽ የሚፈቀድ ድንጋጌ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አንቀጹ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /4/ ባሉት ንዑስ አንቀጾች የስራው አይነት ቋሚ የአሰሪው ስራ የመሆን አለመሆኑን ጉዳይ ሳያነሳ ሌሎች የተጠቀሰውን አይነት ውል ሊደረግ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች አስቀምጦ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም እነዚህ ንዑስ አንቀጾች ትርጓሜ አግኝተው በአሰሪው ቋሚ ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል እንዲደረግ የሚፈቅዱ አይደለም እስከአልተባለ ድረስ ሕጉ በተጠቀሰው አይነት ሥራ ላይ የተጠቀሰውን አይነት ውል ማድረግ አይፈቅድም የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡ ወደ ትርጓሜያቸው ስንመለስ ደግሞ ቢያንስ የተወሰነ ስራ ለመስራት ወይም ለማሰራት፤ ቀሪ የሆነን ሰራተኛ ለመተካት እና የስራ ብዛትን ለማቃለል ሲባል የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ማድረግ እንደሚቻል የሚጠቅሱት ከንዑስ ቁ./1/ እስከ /3/ ያሉት ድንጋጌዎች የአሰሪውን ቋሚ ስራ በሚያገል መልኩ የተደነገገ ናቸው ለማለት የሚያበቁ አይደሉም፡፡ ይልቁንም ከፍ ሲል በተመለከቱት ምክንያቶች መነሻ የሚደረግ የስራ ውል በቀጣይነት ከሚሰሩ እንጂ በቀጣይነት ከማይሰሩት ስራዎች ጋር ያለው ተያያዥነት እምብዛም የሚታይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የቅጥሩ ምክንያት በእነዚህ ንዑስ አንቀጾች የተመለከቱትን ውስን ምክንያትቶች እስከያዘ ድረስ ውሉ የተደረገበት ስራ ቀጣይነት ያለው ነውና የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ሊደረግ



አይችልም የሚል በሕግ የተደገፈ ማጠቃለያ ላይ ሊደረስ አይቻልም፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ድጋጌዎች አግባብ በአሰሪው ቋሚ ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ማድረግ የሚቻል ሲሆን ይህም እንደ ሁለተኛው አይነት የስራ ሁኔታ ሊቆጠር ይገባዋል፡፡

ቋሚ ባልሆነ የአሰሪው ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ሊደረግ እንደሚችል በግልጽ የሚያሳየን ደግሞ ንዑስ አንቀጽ/7/ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ውሉ የሚደረግበት ስራ ቋሚ የአሰሪ ስራ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት የሌለው ጭምር መሆኑን ከድንጋጌው በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደ ንዑስ /7/ ግልጽ ባይሆንም በንዑስ /4/ ላይ የተመለከተው ይኸው የስራ ውል የሚደረግበት ሌላ ሁኔታም ከዚሁ ቋሚ ከአልሆነው እና ቀጣይነት ከሌለው ስራ ሊመደብ የሚገባው መሆኑን ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ቋሚ ያልሆነ እና በቀጣይነት የማይከናወን የአሰሪው ስራም ውሉ እንዲደረግ ሕግ የፈቀደበት ሶስተኛው  አይነት የስራ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባዋል፡፡

እንግዲህ አንድ የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የስራ ውል ነው ለመሰኘት ጊዜ የተወሰነበት የመሆኑ ጉዳይ ብቻ የሚበቃ አይደለም፡፡ ውሉ በጊዜ ከመገደቡ ባሻገር በአንቀጽ 10 በተመለከቱት እና ከላይ በዝርዝር ሊታዩ ከተሞከሩት የስራ ሁኔታዎች አግባብ የተደረገ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

እንዲሁም አንድ የስራ ውል የተወሰነ ስራ ለመስራት ወይም ለማሰራት ሲባል የተደረገ ነው ለመሰኘት ለተወሰነ ስራ መደረጉን የሚያሳይ ጥቅል ሐሳብ ማስቀመጡ ብቻ የሚበቃ አይሆንም፡፡ ለተወሰነ ስራ መደረጉን ከማመልከት በተጨማሪ በአንቀጽ 10 ስር በተዘረዘሩት እና ከላይ ከተጠቀሱት የስራ ሁኔታዎች አግባብ የተደረገ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል የተደረገ አንድ የስራ ውል በአንቀጽ 10 የተመለከቱትን መስፈርቶች በአሟላ ወይም በአላሟላ ጊዜ ሁለት የተለያዩ ሕጋዊ ውጤቶችን ያስከትላል፡፡ ይኸውም አንደኛ ውሉ መስፈርቶቹን አሟልቶ ከተገኘና ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ከሆነ ጊዜው እስከሚያልቅ ብቻ የሚቆይ ሲሆን ለተወሰነ ስራ

የተደረገ ከሆነ ደግሞ ስራው እስከሚያልቅ ድረስ ብቻ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ከዚያም ውሉ በአዋጁ አንቀጽ 24 መሰረት በሕግ ይቋረጣል፡፡ ሁለተኛ ውሉ መስፈርቶቹን አሟልቶ ካልተገኘ በአዋጁ አንቀጽ 9 መሰረት በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

አንድ አከራካሪ የስራ ውል በአንቀጽ 10 የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ የሚለየው ተከራካሪዎቹ ከሚያቀርቡት ማስረጃ አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ለማስረዳት የሚቀርቡት ማስረጃ ምን አይነት ሊሆን እንደሚገባ በሕጉ ተለይቶ የተወሰነ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሙግቱን ለማስረዳት የፅሁፍም ሆነ የቃል ማስረጃ ማቅረብ እንደሚቻል የሚታመን ነው፡፡ ይልቁንም የሚያከራክረው ቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ያለበት ማን ነው? አሰሪው ነው? ወይስ ሰራተኛው? የሚለው ጉዳይ ሲሆን ይህም አወዛጋቢ ነጥብ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቶበታል፡-

1ኛ- ከፍ ሲል እንደተመለከተው አንድ ከአሰሪ ጋር የስራ ውል ያለው ሰራተኛ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሊቆጠር እንደሚገባ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9 ግምት ወስዶለታል፡፡ በዚህ የሕግ ግምት የስራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው ሲል የሚከራከረው ሰራተኛ ተጠቃሚ በመሆኑ ይህን ክርክሩን የሚደግፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ አይጠበቅበትም፡፡ ይልቁንም በሕግ የተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳቱ ግዴታ የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነውና በአንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው ሲል በሚከራከረው በአሰሪው ላይ ይወድቃል፡፡

2ኛ- እንደሚታወቀው አንድ የስራ ውል በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው? ወይም አይደለም? የሚለው አከራካሪ ጭብጥ በአንድ ጉዳይ ሊመሰረት የሚችለው አንዱ ወገን ተከራካሪ የስራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው ሲል ሌላው ደግሞ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነው በማለት በሚሟገቱበት ሁኔታ ነው፡፡ በአብዛኛ የመጀመሪያው አይነት ክርክር የሚቀርበው በሰራተኛው ሲሆን ሁለተኛው አይነት ክርክር ደግሞ በአሰሪው የሚቀርብ ነው፡፡ ይህም የሙግታቸው አቀራረብ ለተጠቀሰው ጭብጥ መመስረት ምክንያት የሆነው



ክርክር በአሰሪው በኩል መቅረቡን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የጉዳዩ ጭብጥ እንዲሆን ያስቻለውን ክርክር ያቀረበው አሰሪው ከሆነ ደግሞ ይህን ክርክሩን በቅድሚያ ያስረዳ ዘንድ የግድ ይሆንበታል፡፡ ይህም the one who alleges in the affirmative shall prove it ከሚለው አገላለጽ ጋር የተስማማ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ይህን ጉዳይ ስለ ማስረጃ ማቅረብ ግዴታ እና ስለአቀባበሉ ከተደነገገበት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ክፍል ጋር ማገናዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል ስር የሚገኘው አንቀጽ 2001 አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የሚያሳይለት ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባው፤ ግዴታው ፈርሷል ወይም ተቀይሯል ወይም ቀርቷል የሚል ወገን ደግሞ ይህ ተግባር መፈፀሙን የሚያሳይለትን ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት ደንግጓል፡፡ በያዝነው አይነት የስራ ክርክር ጉዳይ የገባውን ግዴታ ሊፈጽምልኝ ይገባል የሚል ክርክር የሚቀርበው በአሰሪው ሳይሆን በሰራተኛው ነው፡፡ ስለሆነም ከተጠቀሰው ድንጋጌ አግባብ ሰራተኛው የግዴታውን መኖር ለማስረዳት በመካከላቸው የስራ ውል ያለ መሆኑን ብቻ ማሳየቱ የሚበቃው ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን የስራ ውሉ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው በሚል የሚከራከረው አሰሪ ይህን የስራ ውሉ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የሚወድቅ መሆኑን ያረጋገጥልኛል የሚለውን ተግባር ያስረዳ ዘንድ ይጠበቅበታል፡፡

እንግዲህ አንድ የስራ ውሉ በአንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው ሲል አሰሪው በተከራከረ ጊዜ ሁሉ ይህንን ክርክሩን የሚደግፍለት የጽሁፍም ሆነ የሰው ማስረጃ በቅድሚያ እንዲያቀርብ ያስፈልጋል፡፡ በአሰሪው የቀረበው ማስረጃ ከተመዘነ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ሰራተኛው ቅጥሩ በአሰሪው እንደተባለው ሳይሆን በሌላ በአንቀጽ 10 ሊሸፈን በማይችል የተለየ ሁኔታ መፈፀሙን በማስረዳት በአሰሪው የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ያስተባብል ዘንድ ይገባዋል፡፡

እንዲሁም አንድ ፍ/ቤት የተከራካሪዎች የጽሁፍም ሆነ የቃል የስራ ውል ከአንቀጽ 10 አግባብ መደረግ አለመደረጉን ሲፈትሽ አለነ የሚሉትን ማስረጃ ከፍ ሲል በተመለከተው ስርዓት ሊያስተናግድ ይገባዋል፡፡ እርሱም ይጠቅመኛል የሚለውን ሌላ

ተመሳሳይ አይነት ወይም አግባብነት ያለው የአካባቢ ማስረጃ ለውሳኔው መሰረት ሊያደርግ ይችላል።

በሌላም በኩል አንድ የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ መሆን አለመሆኑን የማጣራቱ ጉዳይ በአሰሪው እና በሰራተኛው መካከል የተደረገውን የስራ ውል የመተርጎምን ተግባር ይሠምራል። አከራካሪ ሆኖ የተገኘውን የስራ ውል ለመተርጎም ደግሞ ተዋዋዮቹ ውሉን ሲያደርጉ የነበራቸውን ፈቃድ መለየት ያስፈልጋል። ስለሆነም ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የያዘውን ጭብጥ ሲፈታ የስራ ውሉ በተደረገበት ጊዜ አሰሪውና ሰራተኛው የነበራቸው የሐሳብ አንድነት ምን እንደነበር ሊያረጋግጥ ይገባል። ፍ/ቤቱ በአደረገው ማጣራት የስራ ውሉ የተደረገበት የተዋዋዮቹ ፈቃድ ውሉ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 10 በተመለከቱት ሁኔታዎች ላይ መፈጸሙን አረጋግጦልኛል የሚል ከሆነ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ይደርሳል። የስራ ውሉ የተደረገበት የተዋዋዮቹ ፈቃድ በተጠቀሰው አንቀጽ 10 ስር የሚወድቅ አይደለም ካለ ደግሞ ውሉን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የስራ ውል ይቆጥረዋል።

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ ማለትም ለስድስት ወራት መቀጠሯን የሚያሳይ የፅሁፍ የስራ ውል በማስረጃነት ቀርቦለታል። ቅጥሩም ወቅታዊ ስራን ለማከናወን በሚል መፈፀሙን ውሉ በግልጽ ያመለክታል። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ውሉ ጊዜ የተወሰነለት መሆኑ ብቻውን የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል የሚያሰኘው አይሆንም። ስለሆነም ውሉ በአዋጅ 42/85 አንቀጽ 10 አግባብ የተደረገ መሆን አለመሆኑ ጭምር መታየት ይኖርበታል።

ሁለቱ ወገኖች የፈፀሙት ውል ተጠሪ የተቀጠረችው ወቅታዊ ስራን ለማከናወን መሆኑን የሚጠቅስ ሲሆን አመልካቹ ደግሞ ተጠሪ የተቀጠረችው በንድ ወቅት ተከስቶ የነበረን የስራ ብዛት ለማቃለል ነው ሲል ከስር ጀምሮ መከራከሩን መዝገቡ ያስረዳል። ይህም የአመልካቹ ክርክር /ምንም እንኳን ውሉ የቅጥሩ ምክንያት ወቅታዊ ስራን ለመስራት የተደረገ መሆኑን የሚያመላክት ቢሆንም/ ተጠሪ የተቀጠረችበት የጠቅላላ አገልገሎት ክፍል የተላላኪነት ስራ ወቅት ጠብቆ የሚሰራ ቋሚ የአሰሪው ስራ በሚል ሊፈረጅ እንደማይችል በአመልካቹ ጭምር የታመነበት መሆኑን ያረጋግጣል። እንዲሁም የክርክሩ አቀራረብ ጉዳዩን ከንዑስ አንቀጽ /6/ ጋር ሳይሆን ከንዑስ /3/ ጋር አገናዝበን እንድናየው እና አመልካቹም በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ማስረዳት አለማስረዳቱን እንድንለይ ይጠይቀናል።

ከጉዳዩ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ የተቀጠረችው በቀጣይነት በሚከናወን የአሰሪው ቋሚ ስራ ላይ ነው። ተጠሪም ብትሆን የምትከራከረው ስራው ወቅት ጠብቆ የሚሰራ ነው በሚል ሳይሆን ያለማቋረጥ የሚሰራ የስራ አይነት ነው በሚል ነው። በቀጣይነት የሚሰራ የአሰሪ ቋሚ ስራ ላይ የስራ ብዛትን ለማቃለል በሚል የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ማድረግ በንዑስ ቁ./3/ የተፈቀደ ነው። በእርግጥ የቀረበው የስራ ውል አመልካቹ እንደሚከራከረው ውሉ የተደረገው በአንድ ወቅት የተከሰተን የስራ ብዛት ለማቃለል መሆኑን በግልፅ የሚጠቅስ አይደለም። ይህ ማለት ግን ውሉ የአመልካቹን ክርክር አያስረዳለትም በሚል ከወዲሁ እንድንደመድም የሚያስችለን አይደለም። ይልቁንም በውሉ ላይ የተወለከተው የቅጥሩ ምክንያት ከዚህ ንዑስ አንቀፅ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን የማየቱን ጉዳይ አስፈላጊ የሚያደርገው ነው። ተጠሪ የተቀጠረችበት የተላላኪነት ስራ የወቅት ስራ አይደለምና በዚህ ችሎት እምነት በውሉ ላይ ወቅታዊ ስራን ለማከናወን መቀጠሯ መገለፁ በጊዜው የነበረውን የሥራ ብዛት ለማቃለል ሲባል መቀጠሯን ለማረጋገጥ ያህል የሚበቃ ነው። ስለሆነም አመልካቹ ላቀረበው ክርክር ውሉ እንደ በቂ የፅሁፍ ማስረጃ ሊቆጠርለት የሚገባ ነው።

በሌላ በኩል ተጠሪ በቦታው ሌላ ቀጥሮ እኔን አለአግባብ አሰናበተኝ የሚል አጠቃላይ ይዘት ያለው ክርክር ከማቅረቧ ውጭ ስራ ለማቃለል ቀጠርኳት ማለቱ ሐሰት መሆኑን አስረዳለሁ በሚል አይነት አልተከራከረችም። በዚህ አይነት ከልሟገች እና ሙግቷንም ካላስረዳች ደግሞ የአመልካቹን ክርክር አስተባብላለች የሚያስብላት አይደለም። ተጠሪ እንደምትከራከረው በቦታው ሌላ መቀጠሩን በስር ፍ/ቤት በቆጠረቻቸው ምስክሮች እንደአስረዳች ቢወስድላት እንኳ የተቀጠረችው የስራ ብዛት ለማቃለል አለመሆኑን በማስረዳት የአመልካቹን ክርክር አስተባብላለች የሚያሰኛት አይሆንም። ምክንያቱም በእርሷ ቦታ ሌላ የመቀጠሩ ጉዳይ እርሷ የተቀጠረችው ስራ ለማቃለል ሲባል አይደለም የሚል አሳማኝነት ያለው መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የሚችል አይደለም።

በጥቅሉም በሁለቱ መካከል የተደረገው የስራ ውል በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10/3/ የሚሸፈን የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል መሆኑን ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡ በውሉ የተወሰነ ጊዜ ሲያልቅ ውሉ መቋረጡም በአዋጁ አንቀጽ 24/1/ የተደገፈ ነውና የስር ፍ/ቤቶች የውሉን መቋረጥ ሕገወጥ አድርገው ወደስራ እንድትመለስ መወሰናቸው ከሕጉ ያልተጣጣመ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ- በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል የተቋረጠበት ምክንያት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ባለመሆኑ አመልካች ወደ ስራ ልትመለስ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

2ኛ- ይህ ችሎት በመ.ቁ.17189 ለጉዳዩ አግባብነት ላላቸው የአዋጅ ቁ.42/85 ድንጋጌዎች ትርጓሜ በመስጠት ሕጉ ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የሚፈቅድ አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ተጠሪ ያልሰራችበት ጊዜ ደመወዝ ሊከፈላት አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

3ኛ- በመሆኑም ተጠሪ የአመት ፈቃድ እንዲሰጣት የተወሰነውን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሳይጨምር ቀሪዎቹ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.224/90፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ.857/93 የተሰጡት የውሳኔ ክፍሎች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡



የሰበር መ/ቁ 14057

ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
አቶ አሰግድ ጋሻው

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
**ተጠሪ**፡- አቶ ጌታሁን ኃይሉ

*ስራ ክርክር - የዓመት እረፍት ክፍያ - የአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79/2/ እና /5/፣ 77/5/፣ 77/3/*

የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ መስርተው የ128 ቀናት የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጣቸው የጠየቁበመጀመሪያ ያየው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የተላለፈ የዓመት እረፍት ፈቃድ ከሁለት አመት በላይ መራዘም ስለሌለበት 128 የእረፍት ቀናት ተቀንሶ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ጀምሮ ተጠሪ እስከተሰናበቱበት ድረስ የአንድ አመት ከአሥራ ሦስት ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ ብቻ ይከፈል በማለት ሊወሰን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ የተጠሪ ገንዘብ (የጠየቀው የአመት እረፍት) ሳይቀነስ ሊከፈል ይገባል በማለት በመወሰኑ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሻሻለው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

1. ከሁለት አመት በላይ የተራዘሙ ፈቃዶች በገንዘብ የሚተኩ አይደሉም፡፡
2. አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የዓመት ፈቃድ ክፍያ ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለው አይችልም፡፡

የሰበር መ/ቁ 14057

ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍሰሀ ወርቅነህ

ስንዱ አለሙ

ሆሳዕና ነጋሽ

አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጌታሁን ኃይሉ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

አመልካች ለሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 15313 ህዳር 25 ቀን 1996 ዓ.ም የዓመት ዕረፍት ክፍያን በተመለከተ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ከሌሎች ክፍያዎች ጋር የተጠራቀመ የ128 ቀናት የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው ነው፡፡ አመልካች የዓመት ዕረፍት ክፍያን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79 2 እና 5 መሠረት የተላለፈው የዓመት ፈቃድ የሚቀጥለው ሁለት ዓመት በላይ ሊራዘም አይችልም ተጠሪ የጠየቀው ክፍያ በሕጉ ከተሰጠው በላይ ስለሆነ ሊከፈለው አይገባም በማለት መከራከሩን የፍ/ቤቱ ውሣኔ ያሳያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ /... የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 192/1/ሠ አዋጅ ቁጥር 64/68 የሆነውን በግልጽ የሻረው በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ አዋጅ ቁጥር 42/85 ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም የሚለው የተከሣሽ ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ ስለሆነም በአዋጅ ቁ.42/85 በአንቀጽ 79/5/ ሥር በአንቀጽ 79/1 እና /2/ የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ከሁለት ዓመት በላይ መራዘም እንደሌለበት የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የከሣሽ 128 የእረፍት ቀናት ተቀንሶ አዋጁ በስራ ላይ ከዋለበት



ከጥር 12/85 ጀምሮ እስከተሰናበቱበት ጊዜ እስከ ጥር 28/86 ዓ.ም ያለው ጊዜ አንድ ዓመት ከአስራ ሶስት ቀናት የአመት ዕረፍት ክፍያ ብቻ በአንቀጽ 77/3/ መሠረት እንዲከፈል የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79/5/ የዓመት ዕረፍት ከሁለት ዓመት በላይ ሊተላለፍ አይችልም ሲል ሠራተኛው ከሁለት ዓመት በላይ ያጠራቀመው የዓመት ዕረፍት ካለ አይገባውም ማለቱ አይደለም፡፡ ይልቁንም በአዋጁ በቁጥር 77/5/ ላይ ያልወሰደው የዓመት ፈቃድ በጠቅላላ ታስቦ እንዲከፈለው ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የጠየቀው የዓመት ዕረፍት ክፍያ ሳይቀነስ እንዲከፈለው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔውን በመሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች የከፍተኛ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት ፈጽሟል ሲል አቤቱታ ያቀረበው በዚህ ውሣኔ ነው፡፡ ታህሣሥ 19 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ በውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተሰርቷል ሲል የሚያቀርባቸው ክርክሮችም፣

- የተጠሪ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለኝ ጥያቄ ከሥራ ከመሰናበታቸው ጥር 30/86 ዓ.ም በፊት የነበረና በተለይም አዋጅ በአንቀጽ 34/4/ ከሀ-ሠ መሠረት ያልተላለፈ በመሆኑ ሊጠየቅ አይገባም፡፡
- በአዋጅ አንቀጽ 79/2-3/ መሠረት ሠራተኛው ጠይቆ ወይም አሠሪው የሥራ ሁኔታ አስገድዶት የተላለፈ ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በዚሁ አንቀጽ 79/5/ በግልጽ እንደተቀመጠው በሁለቱ ስምምነት የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ቢኖር እንኳን ከሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ተጠሪ በአዋጁ መሰረት የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ያላቸው ለመሆኑ ያልገለጹ ከመሆኑም በላይ አንቀጽ 79/5/ ከሁለት አመት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል በግልጽ የደነገገውን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመቀበል በአዋጅ አንቀጽ 77/5/ በሙሉ በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉ ናቸው፡፡

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ታዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት ሚያዚያ 28 ቀን 1996 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልሱም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት እንደሌለበት በመግለጽ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በዚህ ጉዳይ ተመርምሮ ሊወሰን የሚገባው ዋናው የክርክር ጭብጥ አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ቀናት ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው ይገባል ወይ? የሚለው ጭብጥም ይታያል፡፡

በቅድሚያ ግን አመልካች የተጠሪ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለኝ ጥያቄ አዋጅ ቁ. 42/85 ከመውጣቱ በፊት የነበረ መብት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 64/68 መሠረት መታየት ይገባዋል ሲል የሚያቀርበውን ክርክር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ግንቦት 14 ቀን 1990 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 42/85 በሥራ ላይ እያለ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 64/68 በአንቀጽ 192/ሠ/ እንደተሻረ ተገልጿል፡፡ አዋጅ ቁጥር 64/68 በኂላኛው አዋጅ በስራ ላይ ከዋለ በኂላ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጅ ቁጥር 42/85 በቁጥር 191 እንደተደነገገው አዋጅ ቁጥር 64/68 በሥራ ላይ እያለ ክሱ መታየት ጀምሮ ቢሆን ነበር፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተሻረውን አዋጅ ቁጥር 64/68 ተፈፃሚ ለማድረግ መታየት ያለበት የኂላኛው አዋጅ ሲተካ ሥራ ላይ ሲውል ጉዳዩ በቀድሞው አዋጅ መታየት የጀመረ መሆን አለመሆኑን እንጂ መብቱ የተገኘበትን ጊዜ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው አዋጅ ቁጠር 42/85 በሥራ ላይ እያለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይኸው አዋጅ ቁ.42/85 ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የአዋጁን ተፈፃሚነት በተመለከተ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመቀጠልም አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ሁሉ ያለጊዜ ገደብ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይችላል ወይ? የሚለውን ዋና ጭብጥ እንመለከታለን፡፡



ይህን ጭብጥ ለመመርመር በቅድሚያ የዓመት ፍቃድን ምንነትና አስፈላጊነት መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 42/85 ከአንቀጽ 76-78 ካሉት ድንጋጌዎች የአመት ፈቃድ ለሠራተኛ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የስራ ቀናት የዕረፍት ጊዜ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዋጁ ቁጥር 13/4/ መሠረት ሠራተኛው ለሥራ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ በስራ ላይ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ የአመት ዕረፍት ከሚሰጥባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሠራተኛው ይህን የሚጠበቅበትን ግዴታ ማሟላት እንዲችል ነው፡፡ በአዋጁ ስለ ዓመት ፈቃድ የሚናገረው ጠቅላላ ድንጋጌ /አንቀጽ 76/2/ በዓመት ፈቃድ ፋንታ በገንዘብ መክፈል የተከለከለ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃድ ለማግኘት ያለውን መብት በማናቸውም ሁኔታ ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ተቀባይነት እንደሌለውም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ /1/ ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች ገንዘብ የአመት ፈቃድን መተካት እንደማይችል ሠራተኛው የአመት ፈቃዱን ባልተጠቀመ ቁጥር ፍቃዱ ወደ ገንዘብ ተለውጦ መከፈል እንደሌለበትም ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል በዋናነት የአመት ዕረፍት ለሠራተኛ የሚሰጠው ሳይከፋፈል ሲሆን መሰጠት ያለበትም ከእያንዳንዱ አመት የአገልግሎት ዘመን በኂላ ሳይጠራቀም ነው፡፡ /ቁጥር 77/1/ እና 78 ፡፡ ሆኖም ሠራተኛው ተከፋፍሎ እንዲሰጠው ሲጠይቅና አሠሪውም ሲስማማ ለሁለት ተከፍሎ ሊሰጠው ይችላል፡፡ /79/1/ እንዲሁም ሠራተኛው ሲጠይቅና አሰሪውም ሲስማማ በአሠሪውም በኩል የሥራ ሁኔታ ሲያስገድደው የሠራተኛውን የፈቃድ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ /አንቀጽ 79/1/ እና /3/ የአመት ዕረፍትን ከላይ እንደተገለፀው በአሠሪና በሠራተኛው ስምምነት ማራዘም ቢቻልም ሊራዘም የሚችልበት ጊዜ ግን በሕጉ ወሰን ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም አይችልም፡፡ ይህ ድንጋጌ ከሁለት አመት መራዘም በኂላ ሠራተኛው ፍቃዱን የግድ መጠቀም ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በመቀጠልም ሠራተኛው በዚህ ሁኔታ ተራዝሞ ያልተጠቀመበትን ፍቃድ ሁሉ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይችላል ወይ? ወደሚለው ጭብጥ እንመለሳለን፡፡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈልባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች በአዋጁ በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም 1ኛው የሥራ ውሉ ለተቋረጠ ሠራተኛ ሲሆን 2ኛው ደግሞ በአንቀጽ 80 እንደተገለፀው አሠሪው በፍቃድ ላይ ያለ ሠራተኛን ጠርቶ ፈቃዱን ሳይጨርስ ስራውን እንዲቀጥል ካደረገ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በአንቀጽ 80/2/ ሠራተኛው ያልተጠቀመበትን ማለትም የቀረውን የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተተምኖ ሊከፈለው እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ለያዝነው ጭብጥ አግባብነት ያለው የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛን በማስመልከት ስለሚፈፀመው የአመት ዕረፍት ክፍያ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 77/5/ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ያልወሰደው የአመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ እንደሚከፈለው ይደነግጋል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የአመት ዕረፍት መሠረት ሃሣብ ክፍያ የሚፈፀምበት የዕረፍት ቀናት ማግኘት ቢሆንም የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ግን እደደአላማው በዕረፍቱ ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ በዋናነት የአመት ዕረፍት በገንዘብ እንዲተካ ሕጉ ባይፈቅድም በስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ግን በዕረፍቱ ፋንታ ገንዘብ እንዲከፈለው በህጉ ተፈቅዷል፡፡ ይህም የሆነው ከላይ እንደተገለፀው የስራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት ሠራተኛው በዕረፍቱ ሊጠቀምበት የማይችል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ክፍያ የሚፈፀምባቸው የትኞቹ ፍቃዶች ናቸው የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የአመት ፍቃድ ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በአንቀጽ 79/5/ ተደንግጓል፡፡ በአንቀጽ 76/1/ እና /2/ አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃዱን ለመተው ስምምነት ማድረግ እንደማይችል በአመት ፈቃድ ፈንታ ገንዘብ መክፈል የተከለከለ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩ የአዋጅ አንቀጽ 77/5/ የሥራ ውሉ ለተቋረጠ ሠራተኛ እንዲከፈል የፈቀደው የአመት ዕረፍት ክፍያ ሠራተኛው ስራ ላይ ቢሆን ኖሮ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ፍቃዶችን እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ይኸውም በህጉ መሠረት ሁለት አመት የተራዘሙ ወይም ሊራዘሙ



የሚችሉና የደረሱ ፍቃዶችን ይጨምራል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ከሁለት አመት በላይ የተራዘሙ ፍቃዶች በገንዘብ የሚተኩ አይደሉም የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት አንድ ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመት የአመት ፍቃድ ክፍያ ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለው አይችልም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሠራተኛው የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት ዕረፍት ሁሉ ያለምንም የጊዜ ወሰን ወደ ገንዘብ ተቀፋሮ9 ሊከፈለው እንደሚችል በመቁጠር የአዋጁ ቁር 42/85 አንቀጽ 77/5/ን መተርጎሙ የአመት ፈቃድ አላማንና መሠረተ ሃሣብን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ሊታረም ይገባል፡፡

በመቀጠልም የአመት ዕረፍት ሠራተኛው በግልጽ በጽሁፍ ወይም በቃል ካልጠየቀ አሰሪውም በግልጽ እንዲተላለፍ ካልፈቀደ ፍቃዱ እንደተላለፈ አይቆጠርም ወይ? የሚለውን ጭብጥ እንመለከታለን፡፡ የአዋጁን አንቀጽ 79/2/ የአመት ፈቃድ ሠራተኛው ሲጠይቅና አሰሪውም ሲስማማ ሊተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የአመት ፍቃድን ለማስተላለፍ የአሰሪውና የሠራተኛው ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስምምነት በግልጽ ወይም ግልጽ ባልሆነ መንገድ ሊደረግ ይችላል፡፡ ስምምነት ከአሠራርም ሊታይ ይችላል፡፡ ሠራተኛው በስምምነት እንኳን ሊተወው የማይችል የአመት ዕረፍት በሕግ ተሰጥቶታል፡፡ ፍቃዱን መጠቀሙ መብቱም ግዴታውም ነው፡፡ አሠሪው ኘሮግራም አውጥቶ ለሠራተኛው ፍቃድ መስጠት እንዳለበት የአዋጁ ቁጥር 78/2/ ይደነግጋል፡፡ የአመት ዕረፍትን ለተወሰነ ጊዜ ማራዘም እንደሚቻል ከላይ በ1ኛው ጭብጥ ተመልክተናል፡፡ እንግዲህ ሠራተኛው ፍቃድ መውሰድ ባለበት ጊዜ ሳይወስድ ቢቀር አሰሪውም ሳይሰጠው ስራውን እንዲቀጥል ቢያደርግ ከአሠራራቸው ፍቃዱን ለማራዘም የተስማሙ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስምምነቱም ፍቃዱ በሕግ እንዲራዘም እስከተፈቀደ ጊዜ ድረስ ብቻ እንደተደረገ ሊቆጠር ይገባል፡፡

ሲጠቃለል ፍቃድን ለማስተላለፍ የሚደነግገው አዋጁ ድንጋጌ /አንቀጽ 79/ ፍቃድን ለማስተላለፍ አሰሪውና ሠራተኛው መስማማት ያለባቸው መሆኑን

ቢያስገነዝብም ስምምነታቸው ግን ግዴታ በግልጽ መሆን እንደሚገባው የግልጽነት ፎርማሊቲን እንዲያሟላ አያስገድድም፡፡ ስምምነት መኖሩን ደግሞ ከአሠራር መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍቃድ ተላልፏል ለማለት አሰሪውና ሠራተኛው የግድ በግልጽ መስማማት አለባቸው የሚለው ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. ተጠሪ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው የጠየቀው የአመት ዕረፍት ቀናት ክፍያ ሁሉም ሊከፈለው አይገባም፡፡
2. ተጠሪ የ1984፣ የ1985 እና የ1996 ከስራ አስከተሰናበተበት እስከ ጥር 30 ድረስ ያለው የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈለው፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በስራ ክርክር መዝገብ ቁጥር 1438 ነሐሴ 16 ቀን 1994 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15313 ህዳር 25 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡



የመ/ቁ. 16270

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ሐጐስ ወልዱ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች .... አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት

ተጠሪ..... አቶ መሐሪ ማታ

*ከውል ውጪ ያለ ኃላፊነትን በተመለከተ ስለ ካሳ መካስን አወሳሰን*

*የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2)፣ 2086(2)፣ 2081፣ 2090፣ 2091 2102(1) እና 2092*

የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የሆነው የአሁን አመልካች መኪናው አድርሷል በተባለው የግጭት አደጋ ለተጎጂው የጉዳት እና መራል ካሳ እንዲሁም የህክምና ወጪ በድምሩ ብር 30.198 እንዲከፍለው በመወሠኑ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ፡ -</u> የደቡብ ብሐር ብሐረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀድቋል፡፡

1ኛ. ከውል ውጪ ኃላፊነት በሆነ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ የደረሰው በተከሳሹ መኪና መሆኑን ከማስረዳት ውጪ በባለሀብቱ በኩል ጥፋት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡

2ኛ ጥፋት ባይኖርም በኃላፊነት ተጠያቂ የሆነ ሰው ከኃላፊነት ነፃ ለመሆን ጉዳት የደረሰበትን ሠው ሌላ የወንጀል ድርጊት ለመጥቀስ አይችልም፡፡

3ኛ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ ከተላከ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያው ውሳኔ ሳይገደብ የካሳውን መጠን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

የመ/ቁ. 16270

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች ...አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት ነገረፈጅ አቶ ጀማል አህመድ ቀረበ

ተጠሪ..... አቶ መሐሪ ማታ ጠበቃ አቶ ተሰማ አበበ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ተከሣሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች መኪናው አድርሷል በተባለው የግጭት አደጋ ምክንያት ለተጐጂው ለአሁኑ ተጠሪ የጉዳት ካሣ ብር 28,800፣ የሞራል ካሣ ብር 1000 እና የህክምና ወጪ ብር 308 በጠቅላላው ብር 30,198 እንዲከፍለው መወሰኑ ነው፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 15 ቀን 1987 ዓ.ም በሞተር ሣይክል በመጓዝ ላይ እያለ ንብረትነቱ የአዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-00217 መኪና ተገጭቶ አንድ እግሩ በመጐዳቱ ወይም በመቆረጡ ምክንያት ከአደጋው በፊት እየሰራ ያገኝ የነበረው ገቢ መቋረጡን በመግለጽ የመኪናው ባለቤት በሕግ ባለበት ኃላፊነት መሠረት የጉዳት ካሣ ብር 58,600 እንዲከፍለው የሚጠይቅ ክስ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ በኃላፊነቱ ጉዳይም ሆነ በካሣው መጠን ላይ ካከራከረና ማሥረጃም ከሰማ በኋላ ጉዳቱን ያደረሰው የተከሣሹ የአዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት መኪና መሆኑ ስለተረጋገጠ ለደረሰው ጉዳት በሕግ ኃላፊነት አለበት፣ ተጐጂው በተከሣሹ መኪና ባይገጭ ኖሮ እግሩ ሊቆረጥ አይችልም ነበር፣ እግሩ ከተቆረጠ ደግሞ ቀደም ሲል ሲሰራ የነበረውን ሥራ ተመልሶ ለመሥራት እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ በአካሉ ላይ የደረሰው ጉዳትም 50% እንደሆነ ስለተገለፀ ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በክሱ የጠየቀውን



የጉዳት ካሣ በከፊል በመቀነስ ለደረሰበት ጉዳት ብር 28,800 የሞራል ካሣ ብር 1000 እና ለህክምና ያወጣውን ወጪ ብር 308 በጠቅላላው ብር 30,198 ሊከፍለው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኃላፊነቱ ጉዳይም ሆነ የካሣውን መጠን በማስመልከት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.3144 የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የአሁኑ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት አድርጐ የይግባኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በመጨረሻ ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ የሚታይበት ጉድለት የለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 348(1) መሠረት አጽንቶታል፡፡

አመልካች የክልሉ ሁለት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ በተመሣሣይ መንገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ምክንያት በዚህ መዝገብ ለሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ አመልካች በ30/10/96 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ማመልከቻ ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 5 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተጠሪው ጠበቃ በኩል በጽሑፍ የተሰጠውን መልስ ከተመለከተ በኋላ የመልስ መልስ ጽፎ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ አድርጓል፡፡

ችሎቱም የኃላፊነቱን ጉዳይም ሆነ የካሣውን መጠን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በቅድሚያ የአሁኑ አመልካች በተጠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሕግ ኃላፊነት አለበት የለበትም? ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂው(ተበዳዩ) በገዛ ራሱ ጥፋት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለው ሲመረመር በፍሬ ነገር ረገድ የአሁኑ ተጠሪ ሞተር ሣይክል እየነዳ በመጓዝ ላይ እያለ ሁለተኛው ተከሣሽ ሲያሽከረክረው በነበረው ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3.00217 መኪና ገጭቶ ከነሞተር ሣይክሉ በመውደቁ ምክንያት በአንድ እግሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት የተቆረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ካሣ የተጠየቀበት ጉዳት መነሻው የአሁኑ አመልካች መኪና ያደረሰው የግጭት አደጋ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) የአንድ መኪና ወይም የአንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው አደጋውን ያደረሰው መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ወይም ለማንቀሣቀስ ባልተፈቀደለት ሰው ቢሆንም እንኳን መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆነው ባለሀብቱ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት አጥፊ ሣይሆን ጉዳት ያደረሰው መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ለደረሰው ጉዳት በሕግ አላፊ ይሆናል፡፡ ተጐጂው ወይም ተበዳዩ ጉዳቱ የደረሰው በተከሣሹ መኪና መሆኑን ከማሥረዳት ውጭ በባለሀብቱ በኩል ጥፋት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡

በሌላም በኩል ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለሀብት ከአላፊነት የሚድንባቸው የሕግ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂው ወይም በተበዳዩ ጥፋት ምክንያት እንደሆነ አላፊነት አያመጣም በሚል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2066(2) ላይ የተመለከተው ነው፡፡ ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለሃብት ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂው ጥፋት ምክንያት ነው የሚል መከላከያ ካለው የማስረዳት ሸክም የራሱ ይሆናል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2086(2) ላይ እንደተመለከተው የአንድ መኪና ባለሀብት ጉዳቱ የደረሰው በከፊል ወይም በሙሉ ከተበዳዩ ጥፋት የተነሣ መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር በከፊልም ሆነ በሙሉ ከአላፊነቱ ሊድን አይችልም፡፡

በቀረበው ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ለደረሰው ጉዳት በተበዳዩ በኩል ጥፋት አለ በማለት የሚከራከረው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን አንደኛው ተጠሪው የሌላ ድርጅት ሞተር ሣይክል ሰርቆ እየነዳ ሲሄድ ነው የተገጨው በሚል የቀረበ ነው፡፡ የተሰረቀን ሞተር ሣይክል ወይም ሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ በሚነዳ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ በአላፊነት አያስጠይቅም የሚል ሕግ የለም፡፡ የጉዳቱም መንስኤ ተበዳዩ የተሰረቀ ሞተር ሣይክል ይዞ መገኘቱ ወይም መንዳቱ ሣይሆን የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር መንገዱን በማጥበብ ተጠሪው የሚነዳውን ሞተር ሣይክል ሊገጨው መቻሉ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው የተሰረቀ ሞተር ሣይክል እየነዳ ሲጓዝ ነው የተገጨው በሚል ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መከላከያ ሊሆን አይችልም፡፡ ሁለተኛው ሞተር ሣይክል ለመንዳት የሚያስችል መንጃ ፈቃድ የለውም የሚለው ነው፡፡ መንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑ ብቻ ጉዳቱ የደረሰው በእርሱ ጥፋት ነው ለማለት አያስችልም፡፡ መታየት የሚገባው ሞተር ሣይክሉን እየነዳ ሲጓዝ የፈፀመው ጥፋት ምንድነው የሚለው ነው፡፡



የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተጠሪው መንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ከሚገልጽ በቀር በሥር ክርክሩ ወቅት ተጠሪው የፈፀመው ጥፋት መኖሩን አላስረዳም፡፡ መንጃ ፈቃድ ሣይኖረው የሚያሽከረክርን ሰው በመኪና መግጨት በሕግ በአላፊነት ከመጠየቅ ሊያድን ስለማይችል አመልካች በዚህም ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ የአሁኑ አመልካች መኪናው ላደረሰው ጉዳት አላፊ ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

የካሣውን መጠን በተመለከተም ተጐጂው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መኪና በተፈፀመው ግጭት የተነሣ አንድ እግሩ የተቆረጠ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በእግሩ መቆረጥ ምክንያት ቀደም ሲል የተሰማራበትን ሥራ ለመቀጠል አልቻለም፡፡ ከአደጋው በፊት በወር ብር 120 ደመወዝ እየተከፈለው ሲሰራ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማሥረጃ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረቡን ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይህንን የሚያፈርስ ሌላ ተቃራኒ ማሥረጃ አላቀረበም፡፡ ፍ/ቤቱም በተጠሪው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ገቢው ሊቋረጥ መቻሉንና ጉዳቱም ዘለቄታ ያለው መሆኑን በመገንዘብና ከአደጋው በፊት በየወሩ ሲያገኝ ነበር የተባለውን ደመወዝ በመነሻነት በመጠቀም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2102(1) መሠረት የጉዳት ካሣውን ልክ በርትዕ በማመዛዘን ወስኗል፡፡ የካሣ አከፋፈልና ልክ የሚወሰነው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2090 ጀምሮ በተከታታይ በተፃፉ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ የመጀመሪያው ቁጥር 2090(1) በመደቡ በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሠው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ በመክፈል እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን ቁጥር 2091 ደግሞ ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ አላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋራ እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ ቀጥሎ ያለው ቁጥር 2092 ሲታይ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ እስኪፈፀም ድረስ ሣይጠበቅ ካሣ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚህ ሌላ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2102(1) ላይ የሠፈረውን ድንጋጌም ስንመለከት ስለጉዳቱ ምን ያህል ኪሣራ እንደሚከፈል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞች የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጐጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሣራውን ልክ በርትዕ እንዲወስኑ የሚፈቅድ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሣው መጠን ስለመብዛት አለመብዛቱ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲመረመር በተጐጂው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመኪና

ግጭት በደረሰው አደጋ ምክንያት አንድ እግሩ ሊቆረጥ መቻሉ ከአደጋው በፊት እየሰራ ሲያገኝ የነበረውን ገቢ ያስቀረበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚኖረውን የኢኮኖሚ እድገት እንደሚጐዳው ይገመታል፡፡ በነበረው ሥራ በመቀጠል ወይም በሌላ ሙያ በመሰማራት የራሱን የገቢ ምንጭ ሊያሻሽልና ሊያሣድግ ይችላል፡፡ በደረሰበት አደጋ የአንድ እግሩ መቆረጥ ደግሞ በዚህ የወደፊት እድሉ ላይ ሁሉ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡

ይህ ሁሉ ሲታይ በወቅቱ የ23 ዓመት እድሜ ነበረው የተባለው የአሁኑ ተጠሪ በዋናው መንቀሣቀሻ በእግሩ ላይ የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት እና ይኼው ባለው የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ ያስከተለው ጉዳት ተመዛዝኖ በርትዕ ብር 28,800 ካሣ እንዲከፈለው መወሰኑ በሕጉ እይታ በዝቷል ለማለት አይቻልም፡፡ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ቀርቦለት በነበረው ክሥ መነሻ ጉዳዩን መርምሮ የጉዳት ካሣ ብር 16.000 እንዲከፈለው ከወሰነ በኋላ በይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች መከላከያ መልስ እና ማሥረጃ አቅርቦ ክርክርና ማሥረጃው ከተጠናቀቀ በኋላ መወሰን አለበት ብሎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን ከመለሰለት በኋላ ከሣሹ የአሁኑ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91(1) መሠረት ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ ተፈቅለት በአዲስ መልክ ክርክሩ ተካሂ በመጨረሻ በሰጠው ውሣኔ የካሣውን መጠን ከፍ አድርጐ በመወሰኑ ተፈጽሟል የምንለው የሕግ ስህተት የለም፡፡ ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶ ከተላከ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ውሣኔ ሣይገደብ የካሣውን መጠን ዝቅ ወይም ከፍ አድርጐ ከመወሰን የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ በኃላፊነቱ ጉዳዩም ሆነ በካሣው መጠን አወሳሰን ረገድ ተፈጽሟል የሚባል የሕግ ስህተት አልተገኘም፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በይ/መ/ቁ.3144, ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ 18581

ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- በአ/አ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጣቢያ

ተጠሪ፡- ሲ/ር ቀቡላ ከድር

*የስራ ውል መቋረጥ፣ የካሣ፣ አከፋፈል እና የስንብት ክፍያ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 23/1/፣ 43/3/፣ 40/1/2፣44*

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ብተተጠሪ እስከ 6 ወር የሚደርስ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ስራ ትመለስ በማለት ውሳኔ በመስጠቱና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በማፅናት ሆኖም የ3 ወር ውዝፍ ደመወዝ ብቻ ይከፈላት ሲል ውሳኔ መስጠቱን ተከትሎ የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. በአዋጁ የሥራ መልቀቂያ አለማቅረብ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት አይደለም፡፡
2. የሠራተኛው የስራ ውል ቀጥሎ ወደ ስራ ቢመለስ በአሰሪው ድርጅት ህልውና ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ሠራተኛው ህጋዊው ካሣ ተከፍሎት ከስራ ይሠናበታል፡፡

የሰበር መ/ቁ.18581

ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሚዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- በአ/አ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጣቢያ ጠበቃ መሐመድ ሲራጅ

ተጠሪ፡- ሲ/ር ቀቡላ ከድር ቀረቡ።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 30985 ጥር 24 ቀን 1997 ዓ.ም ተጠሪ የሶስት ወር ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ ትመለስ ሲል በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተሰርቷል በማለት ነው።

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው በአመልካች ድርጅት በነርስነት በማገልገል ላይ እያለሁ መልቀቂያ አላመጣሽም በሚል ያለአንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ የሥራ ውሌን ስላቋረጠ ደመወዜ ተከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ፣ የማልመለስ ከሆነ በአንቀጽ 42(4)(ሀ)፣ በ39፣ በ38 እና በ35(1) መሠረት ሙሉ ካሣ የስንብት ክፍያ ክፍያው ለዘገየበት የ1 ወር የማስጠንቀቂያ ሁለት ወር ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ነው።

የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርቦ የበኩሉን ክርክር አድርጓል። በመልሱም ተጠሪዋን ያሰናበተው መልቀቂያ ልታመጣ ባለመቻሏ እንመልቀቂያ የሌላቸውን ባለሙያዎች እንዳይቀጠሩ ደግሞ የክልሉ ጤና ቢሮ መመሪያ እንዳወጣ፣ መልቀቂያ እንድታሟላ ማስጠንቀቂያ እንደሰጣት፣ የተጠሪ ሥራ ላይ መቆየት ደግሞ የጤና ጣቢያ የሙያ ፈቃድ ሊያስነጥቅና ድርጅቱንም ሊያዘጋ በሚችል ደረጃ ላይ በመድረሱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 26(1) መሠረት ውሉ የሚቋረጥበት ሁኔታ በመፈጠሩ ስለሆነ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል።

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም መመሪያው በአዋጅ ቁጥር 42/85 በተደነገጉት የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ውስጥ ሊሸፈን የማይችል የሥራ ማሰናበቻ ምክንያት አይደለም። በአዋጁም ወደፊት ሚ/ር መ/ቤት በመመሪያ የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ሊደነግግ ይችላል አልተባለም። መመሪያው ከአዋጁ ያነሰ ሲሆን ከአዋጁ ይጋጫል። ከአዋጁ ሣይጋጭ ሊተገበር የሚችለው መልቀቂያ ያላገኘ ሠራተኛ መልቀቂያውን እንዲያገኝና እንዲሠራ አሠሪው ትጋትና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ መልቀቂያ ያላቸውን እንዲቀጥር ለማሳሰብ እንጂ የተቀጠሩትን ማሰናበቻ አይሆንም። ስለዚህ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ብሎ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ ወስኗል።

የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል። ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ወደ ሥራ መመለሱን ጥያቄ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት የወሰነ ሲሆን ደመወዙን ግን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል የ3 ወር ደሞዝ እንዲከፈላት ወስኗል።

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች የሕግ ስህተት ተሰርቷል ሲል የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በመፃፍ ባቀረበው ማመልከቻ የሚያቀርባቸው ክርክሮች፤

- ተጠሪ የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ሣይኖራቸው በጤና ጣቢያችን መሥራታቸው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመሪያ ተደነገገውን ክልከላ የሚቃረን በመሆኑ በድርጅታችን ላይ የተደቀነውን የመዘጋት አደጋ ለመከላከል፣ የሥራ ውላችንን ለማቋረጥ መሠረት ያደረግነውን ከአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 26(1) የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግለጽ ባልሆነ ምክንያት በዝምታ በማለፍ፣ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ በዝምታ መታለፉን ካለማረሙም በላይ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን መመሪያ የክልከላ ሕግ ድፍን ባለ ሁኔታ ተጠሪን አይመለከትም በማለት መመሪያውን በመጣስ ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት ስለሆነ፣ ሰበር ሰሚው ችሎት፣

- አንቀጽ 26(1) በዝምታ መታለፍ የሌለበት መሆኑን፣
- የክልከላው ድንጋጌ ከአዋጅ 42/85 ጋር የማይቃረን መሆኑንና መጣስ ሌለበት መሆኑን፣ በሰበር አርሞልን የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ እንዲሽርልን
  - በአዋጅ ቁጥር 42/85 ስለ ውዝፍ ደመወዝ የተወሰነ ነገር የለም እንጂ ቢኖር ኖሮ ትክክለኛ ቦታው በሕገወጥ መንገድ ውሉ ስለተቋረጠበት ሠራተኛ ልዩ ልዩ ክፍያዎች የተደነገገበት አንቀጽ 43 ሆኖ ሳለ ስለመደበኛ ደመወዝ አከፋፈል የሚደነግገውን ከውዝፍ ደመወዝ ጋር ግንኙነት የሌለውን አንቀጽ (54)ን በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤቶች ያስተላለፉት የውዝፍ ደመወዝ ውሣኔ የሕግ ትርጉም ስህተት ስላለበት ስህተቱ ታርሞ ውሣኔውን ውድቅ እንዲያደርግልን፡፡ የሚሉ ናቸው፡፡

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ታዞ ተጠሪዋ መልስ እንድትሰጥ በታዘዘው መሠረት ሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡ ዋና ዋና ክርክሮቹም፣

- መመሪያው በይግባኝ ባይ ላይ ግዴታ የሚጥለው መልቀቂያ የሌለው የጤና ባለሙያ እንዳይቀጠር ነው፡፡ ይግባኝ ባይ መመሪያውን በመጣስ ከተጠሪ ጋር የቋሚነት የሥራ ውል ከመሠረተ በኋላ ግን የሚገዛው በመመሪያ ሣይሆን በአሠሪና ሠራተኛ በአዋጅ ቁጥር 42/85 ነው፡፡ አዋጁ የሚቃረን ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች አዋጁን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንደማይሆን በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 192(2) ስር ተደንግገዋል፡፡

- ይግባኝ ባይ የአዋጁን አንቀጽ 26(1) መሠረት አድርጎ ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱን ጠቅሶ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህንን ክርክርን በዝምታ እንዳለፉት በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ይህ አንቀጽ በውስጡ የሥራ ውል ከሠራተኛው በሆነ ምክንያቶች ወይንም ከድርጅቱ ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች የሥራ ውል ሊቋረጥ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሁንና እነዚህ ሁኔታዎች ምን ማለት እንደሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 27 እና 28 በግልጽ ተደንግገዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በአንቀጽ 26(1) ከድርጅቱ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሥራ ውል መሠረት



ካሣ ተከፍሎ የማሠናበቱ አማራጭ የሚወሰደው ከሥራ ግንኙነቱ ጠባይ የተነሣ የሥራ ግንኙነታቸው ቢቀነስ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ሲሆን ነው፡፡ አመልካች የጤና ጥበቃ ሚ/ር መመሪያን ባለማክበር መልቀቂያ የሌላት ባለሙያ በመቅጠሩ ከክልሉ ጤና ቢሮ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል ተነግሮታል፡፡ እርምጃውም ፍቃዱን ሰርዞ ክሊኒኩን እስከማዘጋት ሊደርስ እንደሚችል ተገልጾለታል፡፡ ይህም የተጠሪ የሥራ ውል ቢቀጥል ለድርጅቱ ህልውና አስጊ ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል፡፡ በሌላም በኩል ለድርጅቱ መዘጋት ምክንያት ልትሆን ትችላለች ከሚላት ተጠሪ ጋር የሥራ ውል እንዲቀጥል ቢደረግ ግንኙነታቸው ጤናማ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ሕጉ የሰጠውን አማራጭ በመከተል የሥራ ውሉ ተቋርጦ ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የስንብት ክፍያን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 39(1) የሙከራ ጊዜውን የጨረሰና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ከአሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ የማግዕት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም የሥራ ውሉ ከሕግ ወጪ ተቋርጦ ሆኖም ለአዋጁ ቁጥር 43/1/2/3/ መሠረት ወደ ሥራው የማይመለስ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚገባው በአዋጁ ቁጥር 43(4) ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካቹም የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብኝም የሚል ክርክር የለውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከላይ በተገለፀው ሕግ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ልታገኝ ይገባል፡፡

የማስጠንቀቂያ ክፍያን በተመለከተ የአዋጁ ቁጥር 43/4/ሀ/ እና 44 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ አሠሪው በአንቀጽ 35 ስለማስጠንቀቂያ የተጠቀሱት ሳያሟላ ሠራተኛውን ከሥራ ካስወጣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጣት ለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዋ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠኝም ስትል ያቀረበችውም ማስተባበያ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሕግ የተጣለበትን ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታውን የተወጣ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፍል አይገባም፡፡

የማዘግየት ክፍያ ጥያቄ ስንመለከት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሠራተኛው ደመወዝ ከደመወዙ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል እንዳለባቸው የአዋጁ ቁጥር 36 ይደነግጋል፡፡ ሠራተኛው ከአሠሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸውም ሂሣብ በማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ ግን ክፍያው ሊራዘም እንደሚችል ይኸው አንቀጽ ይናገራል፡፡ በቁጥር 36 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሠራተኛው መከፈል የሚገባውን ሂሣብ ያልከፈለ አሠሪ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ለሠራተኛው ደመወዝ እንደሚከፍለው በቁጥር 38 ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ይገባታል የሚለውን ክፍያ ለመክፈል ዝግጁ እንደነበር ተጠሪ ግን ተጨማሪ ክፍያ በመፈለግ ክፍያውን ለመቀበል ፍቃደኛ እንዳልሆነች በስር ክርክሩ ገልጿል፡፡ ይህ ክርክር በተጠሪ በኩል የተስተባበለ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት አልተዘገበም፡፡ በሌላም በኩል የተጠሪ ዋና ክርክር ወደ ሥራ መመለስ ነው፡፡ የልዩ ልዩ ክፍያዎች አማራጭ በ2ኛ ደረጃ የቀረበ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ተጠሪ ክፍያው ተቀብሎ ለመሰናበት ፍቃደኛ እንዳልነበረች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በነዚህ ምክንያቶች ክፍያው የዘገየው በአሠሪው ጥፋት ነው ለማለት ስለማይቻል አመልካች የመዘግየት ክፍያ መክፈል የለበትም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ላልተሠራበት ጊዜ ደሞዝ ሊከፈል እንደማይገባ የሰበር ችሎት በመዝ/ቁጥር 17/89 አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን አንቀጾች የተረጎመ ስለሆነ ተጠሪ ያቀረበችው የውዝፍ ደሞዝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ ይህም ችሎት ተስማምቶበታል፡፡
2. የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ በአመልካቹ ህልውና ላይ ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ይህም የግራ ቀኙን ግንኙነት ጤናማ ስለማያደርገው ተጠሪዋ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 43(3) መሠረት ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ተወስኗል፡፡ እንዲሁም የስንብት ክፍያ እንዲከፈላት ተወስኗል:
3. የካሣውን መጠን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 43(4)(ሀ) መሠረት ተሰልቶ እንዲከፈላት ተወስኗል፡፡ የሥራ ስንብት ክፍያም በአዋጁ ቁጥር 40/1/እና /2/ መሠረት ተሠልቶ እንዲከፈላት ተወስኗል፡፡
4. የፌዴራል መጀመሪያና የከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 5984 እና 30985 ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንድትመለስ የሰጡት ውሣኔ ወደ ሥራ መመለሷ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔዎቹን



በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር.348(1) መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የውሣኔዎቹን ግልባጭ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የሐሣብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ የተመለከተው ዳኛ ከላይ በተመለከተው በአብዛኛው ድምጽ ፍርድ ስለአልተስማማሁ የሚከተለውን የሐሣብ ልዩነት አስፍሬያለሁ፡፡

ሠራተኛዋ ከአሰሪዋ ጋር ባላት የሥራ ግንኙነት የተፈጠረ ችግር አለ አልተባለም፤ ችግር አለ የተባለው አሰሪዋ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ባለው ግንኙነት ነው፤ ችግሩም አሰሪው ሠራተኛዋን ካላሰናበተ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እርምጃ ይወስድባታል የሚል ነው፤ እንደተባለው ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአሰሪው ላይ እርምጃ ሊወስድበት እርምጃውን በሕጉ መሠረት መከላከል እንጂ፣ ሚኒስቴሩ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል ተብሎ፣ የአዋጅ አንቀጽ 43/3/ ከሚለው ውጭ ሠራተኛዋ ወደ ሥራዋ እንዳትመለስ በመወሰኑ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መ.ቁ. 15631

ታህሣስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ሐጐስ ወልዱ
3. አቶ ዳኜ መላኩ
4. አቶ አሰግድ ጋሻው
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካቾች፡- 1ኛ. የሻረግ መንግሥቱ
2ኛ. ሰገዴ መንግሥቱ

ተጠሪ፡- እማሆይ የሻረግ ፈረደ

***ስለ ይርጋ - የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነው ጊዜ - የይርጋ ጥያቄ በፍርድ ቤት ተቀባይነት የማይኖርበት ሁኔታ - የፍ/ብ/ህ/ቁ 10001/2/፣ 1168፣ 1845፣ 1853***

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ተጠሪዋ የሚች አባታችን የአቶ መንግሥቱ ዘወልዴን ቤት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክስ መርምሮ የሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የጎንደር ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ያፀናውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ዉሳኔ</u>፡- በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

1. *ውሎች ንብረትን በተመለተ በ1675 መሠረት የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ በዚሁ መሠረት ትርጉም የሚሰጠው የውል ሰነድ ሳይኖር በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845ን በተመለከተ የሚሰጥ ውሳኔ የለም፡፡*
2. *የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለዕጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት ከከፈለ ሌላ ይገባኛል የሚል ሰው እንዲሰጠው ሊጠይቀው አይችልም፡፡*



የሰበር መ.ቁ. 15631

ታህሣስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ሐጐስ ወልዱ
3. ዳኜ መላኩ
4. አሰግድ ጋሻው
5. ሂሩት መለሰ

አመልካቾች፡- 1ኛ. የሻረግ መንግሥቱ
2ኛ. ሰገዴ መንግሥቱ

ተጠሪ፡- እማሆይ የሻረግ ፈረደ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 364 በይግባኝ ደረጃ ቀርቦለት በነበረው ጉዳይ ሲያከራክር ቆይቶ የካቲት 16 ቀን 1996 ዓ/ም መረምሮ የሰሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የአሁኑ አመልካቾች ተጠሪዋ የሚች አባታችን የአቶ መንግሥቱ ዘወልዴን ቤት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔው ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጐንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /1/2/ እና 1845 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የወሰነው በሕጉ አግባብ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

አመልካቾች አባታችን አቶ መንግሥቱ ዘወልዴ ከሞቱ በኋላ በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባውን ቤት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት ተረክበን ተጠሪዋ ባይወልዱንም እናታችን ናቸው ብለን በማሰብ እንዲቀመጡበት ያደረግነውንና በአክብሮት ሣንጠይቃቸው የቆይነውን ንብረት እንዲያስረክቡን በማለት ያቀረብነው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል

በሚል ለሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ንብረቱን ሣንጠይቅ የቆየነው በቤተዘመድ ግንኙነት ምክንያት ተጠሪዋን በመፍራትና በማክበር ስለሆነ ፍ/ቤቱ የይርጋውን ክርክር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853/1/ መሠረት ሊቀበለው አይገባም ባዮች ናቸው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በአመልካቾች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለአሁኗ ተጠሪ እንዲደርሳቸው ተደርጐ ሐምሌ 18 ቀን 1996 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የመልስ መልስ ሰጥተውበት ተከራክረዋል፡፡

በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ክርክር ሲታይ አመለካቾች እኤን የእንጀራ እናታቸውን በማክበርም ሆነ በመፍራት መብታቸውን ሣይጠይቁ ቆይተዋል ሊባል ስለማይችል ፍ/ቤት ይርጋ አልቀበልም የሚልበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ችሎቱም የአሁኑ አመልካቾች ከ1962 ዓ/ም በፊት የሞቱትን የአባታችንን ቤት ይዘው የሚገኙት የአሁኗ ተጠሪ ሊያስረክቡን ይገባል በሚል ያቀረቡት ክሥ በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልሆነም፣ ፍ/ቤት ይርጋ አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለውን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጐንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከአባታችን በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባውን ቤት የአሁኗ ተጠሪ ምንም አይነት መብት ሣይኖራቸው ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆን ይዘው ስለሚገኙ ሊያስረክቡን ይገባል በሚል ያቀረቡትን ክስ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በአሥር አመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሊወሰኑ የቻሉት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም ተደርጓል የተባለውን ውል መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ከሰነዱ እንደሚታየው ግን ቤቱን የአሁኗ ተጠሪ ለቀው ለሟቹ ለአቶ መንግሥቱ ዘውልዴ ወራሾች ማሥረከባቸው እና ሌሎችን ንብረቶችም ስለመክፋፈላቸው



ከመገለጹ በቀር የሟቹ የአባታቸው ሚስት በቤቱ እየተጠቀሙበት ይቆዩ ወይም ይኑሩበት የሚል ነገር የለውም፡፡ ከዚህ ሌላ ቤቱ በሟች ሚስት ይዞታ ሥር ቆይቶ ወደፊት በዚህ ጊዜ ለወራሾች ያስረክባሉ የሚል የውል ቃል የለውም፡፡ በሰነዱ ላይ የሰፈረው በሕግ የውል ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ ውል ማለት ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1675 ላይ እንደተመለከተው ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታቸውን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ሥምምነት ስለሆነ በዚሁ መሠረት የውል ትርጉም የሚሰጠው ነገር ሣይኖር ውል አለ የሚል መነሻ በመያዝ ይርጋን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ስለውሎች በጠቅላላው በሚለው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ተጽፎ የሚገኘው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 ላይ የተመለከተው የአሥር አመት ጊዜ ነው ብሎ መወሰን ትክክል አይደለም፡፡ በአሁኑ አመልካቾች በኩል የቀረበው የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም የተፃፈው ሰነድ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ጋራ በተያያዘ የሚያስነሣው የይርጋ ጥያቄ ስለሌለ በዚህ ጉዳይ የተጠቀሰው የይርጋ ሕግ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላም በኩል የአሁኗ ተጠሪ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሲከራከሩ የነበሩት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም ተፃፈ የተባለውን ሰነድ መነሽ በማድረግ ብቻ ሣይሆን ቤቱ ከ1943 ዓ/ም ጀምሮ ባለማቋረጥ ግብር እየከፈልኩበት ንብረቴ ሆኗል፣ ከሃያ ሰባት አመት በላይ በስሜ ስገብርበት ቆይቼ የቤቱ የቦታ ይዞታም ሆነ የቤቱ ባለቤትነት ሥም በሥሜ ሊሆን ችሏል በሚል ምክንያት ጭምር ሲሆን እነዚህ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን ከመዝገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ፍሬ ነገሮች በመነሣት በሕጉ በኩል ያለው ሲታይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት በሥሙ ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል በሚል ደንግጐ ይገኛል፡፡ ሕጉ

ይርጋ አዘል ስለሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ /ባለይዞታ/ የሆነው ሰው የዚህን ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ለ15 ዓመት በሥሙ ከከፈለ ሌላ ይገባኛል የሚል ሰው እንዲሰጠው ሊጠይቀው አይችልም፡፡ በሕጉ ለባለይዞታው መብቱ ይረጋለታል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ባለይዞታ በመሆን የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ከ15 ዓመት በላይ በሥማቸው ሲከፍሉ ስለቆዩ በሕጉ የዚሁ ሀብት ባለቤት ሆነዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች አባት ከ1962 ዓ/ም በፊት የሞቱ ስለሆነ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተጠሪዋ ይዞታ ሥር የቆየውን ቤት ከሃያ ስምንት አመት በኋላ እንዲያስረክቧቸው ያቀረቡት ክሥ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

አመልካቾች ክስ ሣናቀርብ የቆየነው ተጠሪዋ የሟቹ አባታችን ሚስት በመሆናቸው በመፍራትና በማክበር በመሆኑ ፍ/ቤት ይርጋውን ሊቀበለው አይገባም በሚል ያነሱትን ክርክር በተመለከተም በእርግጥ ፍ/ቤት ይርጋን አልቀበልም የሚልባቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 የተዘረዘሩት ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ባለገንዘቡ የሚፈልገውን ያልጠየቀበት ምክንያት ባለዕዳውን የመፍራትና የማክበር ስሜት መኖር አንዱ ነው፡፡ አመልከቾች ከሃያ ስምንት አመት በላይ ተጠሪዋ ቤቱን እንዲያስረክቡን ሣንጠይቅ የቆየነው የአማታችን ሚስት ስለሆኑ እንደ እናት ስለምናያቸው የመፍራትና የማክበር ስሜት አድሮብን ነው ይበሉ እንጅ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመለካቾች አባታቸው ከሞቱ በኋላ የአባታችንን ንብረት አካፍይን ወይም አስረክቢን የሚል ጥያቄ አንስተው ሽማግሌዎች ሰብስበው የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተፃፈ ሰነድ በተደረገ እርቅ ንብረት መከፋፈላቸው መገለጹና በዚሁ ሰነድ አማካኝነት ቤቱን ተረክበን ነበር ማለታቸው ሲታይ ከዚህ በኋላ ሣይጠይቁ የቆዩት ተጠሪዋን በመፍራትና በማክበር ምክንያት ነው ለማለት አይቻልም በሚል ሣይቀበላቸው ቀርቷል፡፡ በአመልካቾች በኩል ተጠሪዋን የመፍራትና የማክበር ስሜት ነበረ አልነበረም ለሚለው ፍ/ቤት መፍራትም ሆነ ማክበር አልነበረም የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ ወደ ፍሬ ነገር ጥያቄ ስለሚያመዝን በሰበር ደረጃ ሊመረመር አይችልም፡፡ በሰበር ደረጃ ሊታይ የሚችለው የሥር ፍ/ቤት የመፍራትና የማክበር ስሜት መኖሩን አረጋግጦ ይርጋን አልቀበልም ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት



አይደለም በሚል ወስኖ ቢገኝ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ሕግ ቀሪ መሆኑ ቢረጋገጥም ፍ/ቤት ይርጋውን አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት አለ በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተፃፈው ሰነድ በአመልካቾችና በአሁኗ ተጠሪ መካከል ቤቱን በሚመለከት የተደረገ የውል ስምምነት እንዳለ አድርጐ በመመልከት ይህንኑ መነሻ በመድረግ ለተነሣው የይርጋ ጥያቄ የሚመለከተው የይርጋ ሕግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የአሥር አመት ጊዜ ነው ማለቱ የተሣሣተ ሆኖ ቢታይም ክሱ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 አንፃር ሲመረመር በይርጋ ቀሪ ከመሆን የሚድን ሆኖ ስላልተገኘ በውጤቱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ መወሰኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ነዉ፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአሁኑ አመልካቾች በኩል የቀረበው ክሥ በይርጋ ቀሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 15551

ቀን 29/2/98 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ደስታ ገብሩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ

ስለ ውል መፍረስ - ህጋዊ ደንብን ያልተከተለ ውል ስለሚፈርስበት ሁኔታ እና የውል መፍረስ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የሚያወጣው ውጤት - የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716(1)፣ 1815፣ 1816 እና 1817

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ከፈረሠ በኋላ ገንዘቡ ለአመልካች ተመልሶ በመንግስት የተወረሰችዉ መኪና ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የወሰነውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ።

**<u>ው ሳ ኔ</u>** ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል።

-ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በሓላ ተዋዋዮች ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ ምክንያት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ነው፡፡፡



የሰ/መ/ቁ. 15551

ቀን 29/2/98 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ደስታ ገብሩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፐመንት ኩባንያ

ተጠሪ፡- የኢዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪው ላይ ባቀረበው ክሥ መነሻ ነው።

የክሱ ፍሬ ነገር ከሣሽ ላንድክሩዘር መኪና ለመግዛት ፈልጎ ተከሣሽን የመሸጫ ዋጋ ጠይቆ ጥያቄው በተከሣሽ ተቀባይነት በማግኘቱ ተከሣሹ ባቀረበው የመኪና መሸጫ ዋጋ ተስማምተው ከሣሽ ገንዘቡን የከፈለ መሆኑን፤ ነገር ግን መኪናዋ በተከሣሽ ላይሰንስ ጉምሩክ መጋዘን ከገባች በኋላ መኪናዋ በሕገወጥ መንገድ ስለገባች ማውጣት አትችሉም ሲል ጉምሩክ ስለከለከለ ውሉ ውድቅ ሆኖ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

የሥር ተከሣሽ የአሁን ተጠሪም ቀርቦ ከተከራከረ በኋላ ፍ/ቤቱ ውሉ የተደረገው ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡት ዕቃዎች ሐምሌ 12/1988 ከወጣው ደንብ በኋላ የተደረገ ስለሆነ፤ ውሉም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1716/1/ መሠረት ፈራሽ ነው።

ውሉ ፈራሽ ነው ከተባለ ደግሞ ውጤቱ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁጥር 1815/1/ ስለሚደነግግ በክሥ አቤቱታው ላይ የተመለከተውን ብር 177,184.23 /አንድ መቶ ሰባ ሠባት ሺህ አንድ መቶ ሠማንያ አራት ብር ከሃያ ሦስት ሣንቲም/ የኢትዮጵያ ብር ወይም 26037.36 /ሃያ ስድስት ሺህ

ሠላሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስድስት ሣንቲም/ የአሜሪካን ዶላር ተከሣሽ ለከሣሽ ይክፈል፣ ዳኝነት በታሪፉ ልክ፣ የጠበቃ አበል 15% ልዩ ልዩ ወጪ 100 /አንድ መቶ ብር/ ጨምሮ ለከሣሽ እንዲከፍል ሲል ወስኗል።

የአሁን ተጠሪም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ የይግባኙን ክርክር መርምሮ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል በማጽናት ነገር ግን ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ይመለሱ ሲባል ከሣሽ ለመኪናው የከፈለው ገንዘብ ይመለስለት ማለት ሲሆን፤ ተከሣሹም ከውሉ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ የሚመለሰው በውሉ ምክንያት ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው መኪና ወደ ጅቡቲ ሲመለስለት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት አንዱን ወገን ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ አድርጎ ሌላውን ወገን ባለበት ሁኔታ በመተው የሰጠውን ውሣኔ አሻሽለን ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ወደነበረበት ይመለሱ ሲል ውሣኔ ሠጥቷል።

በዚህ ውሣኔ የሥር ከሣሽ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ሲያቀርብ ተከሣሹም መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቧል።

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዋናውን ይግባኝ በተመለከተ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት የለውም በማለት፤ መስቀለኛ ይግባኙም በሥር ፍ/ቤቶች ተመሣሣይ ውሣኔ የተሰጠበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 መሠረት በይግባኝ ደረጃ ሊታይ አይችልም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መልሶለታል።

እንግዲህ የሥር ከሣሹ ማለትም የአሁን አመልካች በ25/8/96 ጽፎ ያቀረበው የሠበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ የሚለው ተጨማሪ የውሣኔ ክፍል አፈፃፀሙን የተወሣሠበ ስላደረገውና የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ማለፉ ሥነ ሥርዓትን የሚቃረን በመሆኑ ይህ ተሻሽሎ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ይፀናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል።

የማመልከቻ ግልባጭ ለተጠሪው ደረሶ ጥር 19/1997 ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካቹ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ለከፍተኛ ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸው በውሣኔው እንደተስማሙበት የሚቆጠር ነው ለዚህ ችሎት



ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን አላሣዩም፣ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል ሲባል ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሁኔታ ይመለሱ መባሉም ትክክል ነው አመልካች መኪናውን አልተረከቡም ለሚሉት አስቀድሞ ያለቀለት ክርክር ስለሆነ አሁን ሊነሣ አይገባውምና አቤቱታው ተሠርዞ ተገቢው ኪሣራ ተቋርጦልን እንሠናበት በማለት የተከራከረ ሲሆን አመልካችም አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ ሰጥቷል።

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ጭብጥ፤ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው የመኪና ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደነበሩበት ይመለሱ ሲባል ለአመልካቹ ገንዘቡ እንዲመለስለት ብቻ ሣይሆን ከጅቡቲ ወደብ መጥታ ጉምሩክ መጋዘን ገብታለች የተባለችውም መኪና ወደ ጅቡቲ መመለስ አለባት ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው? አይደለም? የሚለው ነው።

በመሠረቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የመኪና ሽያጭ ውል እንዲፈርስ በሥር ፍ/ቤቶች በተሠጠው ውሣኔ ላይ አቤቱታ ያልቀረበበት ስለሆነ ይህን ነጥብ መመርመሩ አስፈላጊ አይደለም። የተጠሪው ክርክር ውሉ ይፍረስ ከተባለ ውጤቱ በፍ/ሕግ ቁጥር 1815/1/ መሠረት ተዋዋዮች ወደነበሩበት ይመለሣሉ ስለሚል በዚህ ሁኔታ መመላለስ ስለአለብን የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሹ ገንዘቡን እንዲያገኝ ከተወሰነ መኪናዋም ወደጅቡቲ እንድትመለስ መወሰኑ ተገቢ ነው ሲል አመልካች በበኩሉ መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ ከተባለ ውሣኔው ሊፈፀም የማይችል ይሆናል ባይ ነው።

አከራካሪዋ መኪና ከጅቡቲ ወደብ መጥታ ጉምሩክ መጋዘን ከገባች በኋላ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ገብታለች ተብሎ ጉምሩክ ለከሣሽ ሊሰጥ አለመቻሉንና በዚሁ ምክንያት በመንግሥት ስለመወረሷ ራሱ የሥር ተከሣሽ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ካቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል።

እንግዲህ ምንም እንኳን የፍ/ሕ/ቁጥር 1815/1/ አንድ ውለታ ሲሠረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮችን በተቻለ መጠን ውለታው ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚደነግግ ቢሆንም መኪናዋ ለመንግሥት በውርስ የገባች መሆኑ እየተረጋገጠ ወደ

ጅቡቲ ትመለስ ተብሎ መወሰኑ የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ደግሞ የፍ/ሕግ ቁጥር 1816 እና 1817 የፍ/ሕ/ቀጥር 1815 ልዩ ሁኔታ (exceptions) ሆነው መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡

ይኸውም በተለይ ለዚህ ጉዳይ ተጠቃሽነት ያለው የፍ/ሕ/ቁጥር 1817/1/ … የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሠናክል የሚያመጣ ሲሆን የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ ይቀራሉ ይላል፡፡

ይሁንና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ድንጋጌ በሚቃረን ሁኔታ መኪናዋ በመንግሥት መወረሱን እየተረዳ ወደ ጅቡቲ ትመለስ ሲል የሰጠው የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህን ሥህተት እንዲያርም የቀረበለትን ይግባኝ ያለመቀበሉ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 11936 ጥር 26/96 በዋለው ችሎት ዋናውን ይግባኝ በተመለከተ የሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ተሽሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 216/94 በ24/7/95 በዋለው ችሎት መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የሰጠውን የውሣኔ ክፍል ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ ተሽሯል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁጥር 492/90 በ4/11/93 በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስነናል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረሰው መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡



የመ/ቁ.16062

ህዳር 19 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጎስ ወልዱ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

**መልስ ሰጭዎች፡-** ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ

*ከውል ውጭ ስለሚደርስ አላፊነት- ካሣ ስለሚጠየቅበት ክስ- ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ - የፍትሐ-ብሄር ህግ ቁጥር 2143/1/፣ 2143/2/*

መልስ ሰጭ በአቶ ከበደ ኃይሉ ይሽከረከር የነበረና ንብረትነቱ የአቶ አሊ መሃመድ የሆነ ተሽከርካሪ ሰኔ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ባለቤቴን ገጭቶ ገድሏል በማለት እርሷና ሁለት ህፃናት ልጆቿ ተቋርጦብናል የምትለውን ገንዘብ በማስላት ብር 222,000 እንዲከፈላት መስከረም 4 1992ዓ.ም ባቀረበችው ክስ አመልካች ለተሽከርካሪው በሰጠው መድን በጣልቃ ገብነት በመግባት ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143/2/ መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረበውን ክርክር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

**ውሳኔ፡-** የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብህ/ቁ.2143 ከውል በሚደርስ አላፊነት የቀለብ ገንዘብ በመጠየቅ በሚቀርብ ክስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ሚስት ከውል ውጭ በባሏ ላይ በሚደርስ የሞት ጉዳት የቀለብ ጥያቄ ለማቅረብ ስትል ሚስትነቷን ለማረጋገጥ በፍርድ ቤት የምታቀርበው ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ አያቋርጥም፡፡

የሰ/መ/ቁ.16062

ህዳር 19 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረፈጁ አቶ አብርሃም ፀጋዬ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ አልቀረበችም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ሊሆን የቻለው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡

ይኼው ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ.304/92 በቀረበለት ካሳ ጉዳይ ላይ የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን አድርጐ ጣልቃ ገቡ በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2143/1/ መሠረት ያቀረበውን የይርጋ ክርክር በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በከሣሽ በኩል የቀረበውን ክሥና በግራ ቀኙ መካከል የተደረጉትን የፍሬ ነገር ክርክሮች መርምሮ ከሣሽዋ ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ ባለቤቷ አቶ ሀ/ሚካኤል መርጊያ ንብረትነቱ የአንደኛ ተከሣሽ በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3-17155 መኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት በሚስቱና በሁለቱ ህፃናት ልጆቹ ላይ በቀለብ ረገድ ለደረሰው ጉዳት የመኪናው ባለቤት አንደኛው ተከሣሽ እና መኪናውን ሲያሽከረክር አደጋውን ያደረሰው ሁለተኛው ተከሣሽ በሕግ ኃላፊ ስለሚሆኑ ካሣ ብር 60,000 ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ጣልቃ ገብ የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበኩሉ ግጭቱን ላደረሰው መኪና በገባው የመድን ዋስትና መጠን ካሣውን መክፈል አለበት የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተደረገው የአሁኑ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማትና ክሱም በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል ምክንያት በፍ/ይ/መ/ቁ.03564 ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ መጋቢት 14 ቀን 1996 ዓ.ም መርምሮ በሰጠው ትዕዛዝ ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም



በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙን በመሠረዝ አሰናብቶታል፡፡

በዚህ መዝገብ ለሰበር አቤቱታ የቀረበውም ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ጉዳዩን ተመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ሲሆን አመልካች በተነሣው የይርጋ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት ሰኔ 11 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አብራርቶ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ ተመርምሮ የይርጋው ጥያቄ ከሕጉ አኳያ ተጣርቶ መወሰን የሚያስፈልገው ሆኖ በመታየቱ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻም ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀርባ መልስ እንድትሰጥበት ታዞ በ15/4/97 ዓ.ም የተፃፈ መለስ አቅርባለች፡፡ በጽሑፍ ያቀረበችው መልስ ሲታይ ተጠሪ ባለቤቱ በመኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት በክሱ የተጠየቀው የጉዳት ካሣ እንዲከፈል ሣይሆን በቀለብና መተዳደሪያ ረገድ ታስቦ ሊከፈለን የሚገባ ገንዘብ ነው፡፡ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ ደግሞ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ ሌላ በሚስትነት ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በክርክር ላይ ቆይቼ የመጨረሻ ውሤኔ የተሰጠው በ07/07/90 ስለሆነ ክሥ የማቅረብ መብት ያገኘሁት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ደግሞ በ4/1/92 ያቀረብኩት ክሥ ከይርጋ ነፃ ነው የሚሉትን ክርክሮች ያቀፈ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ ክሥ ያቀረበችው አደጋው ወይም ጉዳቱ ከደረሰ ከሰባት አመት ቆይታ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143/2/ መሠረት ለወንጀሉ ጉዳይ የተወሰነው የይርጋ ዘመን ልክ ይሆናል ከተባለም አደጋውን ያደረሰው ሹፌር የወ/መ/ሕ/ቁ.526/1/ ተጠቅሶ ክሥ ቀርቦበት በብር 1000 የተቀጣ መሆኑ በማሥረጃ ስለተረጋገጠ ለዚህ ወንጀል የተወሰነው የይርጋ ጊዜ ሶስት አመት ብቻ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

ችሎቱም በቀረበው ጉዳይ በዋናነት ሊመረመር የሚገባው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል አይሆንም? ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ የይርጋው ዘመን ልክ ምን ያህል ነው የሚለው የይርጋ ጥያቄ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት እንደተቻለው ከሣሽ የሆነችው የአሁኗ ተጠሪ ሁለተኛ ተከሣሽ የሆነው ከበደ ኃይሉ ንብረትነቱ የአንደኛው ተከሣሽ አሊ መሐመድ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-17155 መኪና እያሽከረከረ ሲጓዝ ሰኔ 5 ቀን 1984

ዓ.ም ባለቤቴ አቶ ሀ/ሚካኤል መርጊያን ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ገጭቶ ገድሎታል በማለት በባለቤቷ መሞት ምክንያት እርሷ እና ሁለት ህፃናት ልጆቹ ቀርቶብናል ወይም አጥተናል የምትለውን ገንዘብ በመግለጽ አስልታ በጠቅላላው ብር 222,000 ተከሣሾች በአንድነት በነጠላ እንዲከፍሏት በ4/1/92 ዓ.ም ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገችው ክሥ ጠይቃለች፡፡ የአሁኑ አመልካች የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቀጥታ የቀረበበት ክሥ ባይኖርም አደጋውን ላደረሰው መኪና የመድን ዋስትና ሰጥቷል በመባሉ ምክንያት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43/1/ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን አመልካችም አደጋውን ላደረሰው መኪና የመድን ዋስትና በተገባለት መጠን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት አምኖ ክሱን በማስመልከት የበኩሉን መልስ ሲሰጥ የይርጋ ክርክር አንስቷል፡፡ በኢንሹራንስ ምክንያት ካሣ እንዲከፍል የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ከተደረገ ኢንሹራንስ ገቢው ጉዳት ደርሳብኛል ብሎ በከሰሰው ሰው ላይ ሊያቀርብ የሚችላቸውን የሕግ ክርክሮች ማቅረብ ይችላል፡፡ አመልካች ሦስተኛ ወገን ሆኖ የክርክር ተካፋይ በሆነበት ጉዳይ ክሱን በመቃወም የይርጋ ክርክር ሊያቀርብ የቻለው በዚሁ ሁኔታ በመጠቀም ነው፡፡

የቀረበውን የይርጋ ክርክር በተመለከተም ጉዳዩ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚመለከት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆን አለመሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143 አኳያ የሚመረመር ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለይርጋው ክርክር መነሻ ያደረገው ይኼው ከውል ከውል ውጭ ስለሚመለከት ካሣ ጉዳይ ክሥ የይርጋ ዘመን የሚወሰነውን ድንጋጌ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገር ጉዳዩ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነት የሚመለከት መሆኑን እያረጋገጠ ተጠሪዋ በአመልካች በኩል ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መልስ ስትሰጥ ጉዳዩ ሟች በመኪና ተገጭቶ ከመሞቱ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ክሱ የተመሠረተው በቀለብ ጥያቄ ላይ እንጅ በጉዳት ካሣ ላይ ስላልሆነ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143 ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም በሚል ያቀረችው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጐጂው በመሞቱ ምክንያት ሚስት ወይም ልጆች በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2095 መሠረት በቀለብ መተዳደሪያ ረገድ የሚያቀርቡት የካሣ ጥያቄም ቢሆን ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚመለከት እንጂ በሌላ የተለየ ግንኙነት ላይ ወይም በሌላ የሕግ ምክንያት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡

በዚሁ በተጠቀሰው የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143 ላይ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ሲታይ የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር «1» ተበዳዩ ክሥ ማቅረብ



የሚችለው ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት አመት ድረስ መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት የበለጠ እንደሆነ የካሣው ጉዳይ ክሥ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት እንደሚሆን ይገልፃል፡፡

የቀረበው ጉዳይ ከዚሁ የይርጋ ድንጋጌ አንፃር ሲመረመር የአሁኗ ተጠሪ ካሣ የተጠየቀበት ጉዳት ሰኔ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ደርሶ የካሣውን ጉዳይ ክሥ ያቀረበችው መስከረም 4 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑ ስለተረጋገጠ በሕጉ የመጀመሪያ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ሁለት አመት የይርጋ ዘመን ያለፈው የመሆኑን ጉዳይ አከራካሪ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚቀረው ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ በወቅቱ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ምን ያህል ይሆናል? በዚህ ሕግ መሠረት ቢታይ የይርጋው ዘመን አላለፈም ሊባል ይችላል አይችልም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ አደጋ ያደረሰውን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር ሁለተኛው ተከሣሽ በዚህ ጉዳይ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት በመኪና ሰው ገጭቶ ገድሏል ተብሎ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526/1/ ተጠቅሶ በቀረበበት የወንጀል ክሥ ፍ/ቤት ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ በገንዘብ መቀጫ ብር 1000 እንዲቀጣ መወሰኑ ተገልጿል፡፡ ሾፌሩ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት የሕግ አንቀጽ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526/1/ መሆኑ ከታወቀ የወንጀሉ ጉዳይ የክሥ አቀራረብ የይርጋ ዘመን ምን ያህል ጊዜ ነው የሚለውን በተመለከተ ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 226 በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ነው ለማለት የተቻለው የይርጋ ዘመን በዚሁ በተጠቀሰው ሕግ ፊደል ሠ ላይ የተመለከተው አምሥት አመት ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ ክሱን ያቀረበችው ጉዳቱ በደረሰ በአምሥት አመት ጊዜ ሣይሆን ከሰባት አመት ቆይታ በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ሚስትነቴን እስካስወሰን ድረስ በክርክር ላይ የቆየሁት ጊዜ መታሰብ የለበትም፣ ክሥ የማቅረብ መብት ያገኘሁት ሚስትነቴን ካስወሰንኩ በኋላ ስለሆነ የይርጋው ጊዜ መታሰብ ያለበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው በሚል ያቀረችው ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ ላይ እንደተመለከተው የይርጋው ጊዜ የሚቆጠረው ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ መዘግየት የጠቀሰችው ምክንያት በሕጉ ይርጋውን የሚያቋርጥ ወይም የሚያረዝም አይደለም፡፡

ክሱ የቀረበው በወንጀሉም ጉዳይ የተወሰነው የይርጋ ዘመን ካለፈ በኂላ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል። አንድ ተከራካሪ ወገን በሕግ ይገባኛል የሚለውን መብት በሕጉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ በሕግ ከሶ የመጠየቅ መብቱ ቀሪ ይሆናል። የአሁኗ ተጠሪም በባለቤቷ መሞት ምክንያት በሕግ ይገባኛል የምትለውን ካሣ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ክሥ አቅርባ ስላልተጠየቀች ካሣ የመጠየቅ መብቷ ቀርቷል።

በዚህ ምክንያት በቀረበው ጉዳይ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

## ው ሣ ኔ

1. ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በ21/9/1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔም ሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ በመ/ቁ.03564 - በ14/7/96 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



የሰበር መ/ቁ.14554

ታህሣስ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
4. ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ፅጌ አጥናፌ

**መልስ ሰጭ**፡- ባለምባራስ ውቤ ሺበሺ

ተዋዋይ ወገን ሳይሆን ውል እንዲሠረዝ ስለመጠየቅ በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ፍ/ቤት የመሠረዝ ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1808/2/፣ 1198/2/

ካለ አመልካች ፈቃድ የጋራቸው የሆነውን ቤት ስም ለማዛወር አመልካች ባለቤት ተከጠሪ ጋር የፈፀመው ውል ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መወሰኑና የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሉ እንዲፈርስ አመልካች የጠየቁት ያለአግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻሩ በመጨረሻም የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡-

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሠሰው ትዕዛዝ ተሽሯል።

1. ተዋዋይ ወገን ሳይሆን በተፈፀመ ውል ምክንያት መብቱ ተነክቷል በማለት ውሉ እንዲሰረዝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጭ ከሆነ፣ ለህሊና ተቃራኒ ወይም ለውል አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም በሚል ምክንያት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የሚቀርብ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም።
2. የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የመሠረዝ ሥልጣን ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጅ የፍ/ቤት አይደለም።
3. በአስተዳደር ክፍሉም እስካልተሰረዘ ድረስ የደብተሩ ባለቤት የቤቱ ባለንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።

የሰበር ችሎት መ/ቁ. 14554

ቀን ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ - ቀረበች

መልስ ሰጭ፡- ባላምባራስ ውቤ ሺበሺ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል በዚህ መዝገብ የሌሉበት የስር 2ኛ ተከሣሽ በሆነው ባለቤቱ በአቶ ተስፋዬ ውቤ የተመዘገበውን እና የጋራ ንብረታችን የሆነውን በወረዳ 20፣ ቀበሌ 44፣ የቤ.ቁ. 399 የሆነውን መኖሪያ ቤት የስር 2ኛ ተከሣሽ ባለቤቱ ከአሁን መ/ሰጭ ጋር በመመሳጠር ለአሁን መ/ሰጭ (የስር 1ኛ ተከሣሽ) ለማስተላለፍ የስምምነት ውል አድርገዋል፤ ስምምነቱ መብቴን የሚነካ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ የሚል ነው፡፡ የስር 2ኛ ተከሣሽ ለክሱ ተቃውሞ እንደሌለው የገለፀ ሲሆን የአሁን መ/ሰጭ በበኩላቸው ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1810 መሠረት በይርጋ ይታገዳል፤ እኔ በሕይወት ያለሁ በመሆኑ ቤቱ ለስር 2ኛ ተከሣሽ በውርስ ተላልፎአል ሊባል አይችልም፤ የቤቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በስር 2ኛ ተከሣሽ ስም ይገኛል ለተባለው ደብተሩ የተገኘው በሀሰተኛ መንገድ



መሆኑን ደብተሩ በስሜ እንዲዛወር የእርቅ ስምምነት ፈርሟል፤ በመሆኑም ቤቱ የራሴ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ቤቱን የአሁን አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሣሽ የጋራ ንብረት ነው፤ የስር 2ኛ ተከሣሽም የጋራ ንብረቱን ያለአሁን አመልካች ፈቃድ የማስተላለፍ አይችሉም በማለት የእርቅ ስምምነቱን ውል ፍ/ቤቱ አፍርሶታል በማለት ወሰነ፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ የአሁን መ/ሰጭ ከስር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ያደረጉት ስምምነት መብቴን ስለሚነካ ስምምነቱ ይፍረስልኝ ያሉት ያለአግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ በምክንያቱ ባይስማማም በውጤቱ በመስማማት አጽንቶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩት የእርቅ ስምምነት ይፍረስልኝ የሚል ጥያቄ ሲሆን የእርቅ ስምምነቱም ውል እንጂ ውሣኔ አይደለም፤ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በውሣኔው የጠቀሣቸው ድንጋጌዎች ከጉዳዩ ጋር የሚገናኙ አይደለም፤ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ እንዲሻር የሚል ነው፡፡ መ/ሰጭ በበኩላቸው አመልካች ያቀረቡት ክርክር የፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይ አይደለም፤ በተደረገው የእርቅ ስምምነት አመልካች የሌለችበት መሆኑ ክስ መመሥረት አትችልም በማለት አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ክርክሩን እና አቤቱታ የቀረበበትን ትእዛዝ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሮታል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች የእርቅ ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላት የክስ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? እና ፍ/ቤት ስልጣን ባለው አካል የተሰጠን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተርን ሐሰተኛ በሆነ መንገድ የተገኘ ነው በሚል የመሠረዝ ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚሉትን ነጥቦች በጉዳዩ መመለስ ያለባቸው ሆኖ አግኝቷቸዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት አቤቱታ ለቀረበበት ውሣኔ መሠረት የሆነውነ ውሣኔ የሰጠው አመልካች ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት በአሁን መ/ሰጭና በስር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገው የእርቅ ስምምነት ውል መብቴን የሚነካ በመሆኑ እንዲሻር የሚል ነው፡፡ ይሄም ለክሣቸው መሠረት ያደረጉት እሣቸው የሌሉበትንና በአሁን መ/ሰጭ እና በስር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገውን የእርቅ ስምምነት ውል መሆኑን በግልጽ ያሣያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1676(1)መሠረት ስለ ውሎች በጠቅላላ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808(2) መሠረት ከተዋዋይ ወገኖች ውጭ የሆነ ማነኛውም ጥቅም አለኝ የሚል ሰው ውሉ እንዲሠረዝ የሚጠይቀው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጭ ከሆነ፤ ወይም ለሕሊና ተቃራኒ ወይም ለውል አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልተጠበቀም በሚል ምክንያት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የእርቅ ስምምነት ውል ተብሎ የተገለፀው የተደረገበት ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የወጣበትን ስም ማዛወር ሲሆን ይህም ከሕግ ውጭ ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው የሚባል አይደለም፡፡ የእርቅ ስምምነት ውል ነው የተባለው ለውሉ የተደነገገው ፎርም አልተጠበቀም የሚል ክርክር ደግሞ አመልካች አላቀረቡም፡፡ እነዚህ ባልተሟሉበት ሁኔታ አመልካች የሌሉበት (ያልገቡት) ውል ይሰረዝ የሚል ክስ የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት መጀመሪያውኑ የክስ ምክንያት የሌለ በመሆኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.33 መሠረት አመልካች ክስ ለማቅረብ የማይችሉ ናቸው በማለት ክሱን መዝጋት ነበረበት፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ



ፍ/ቤትም ይሄንን ስህተት ሣያስተካክል ያለፈው በአግባቡ አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይሄን ስህተት በተመሣሣይ ሁኔታ ማስተካከል ሲገባው አመልካች ባቀረበችው ክስ እንዲሰረዝ የጠየቀችው የእርቅ ስምምነት ውል ሣይሆን ውሣኔ ነው በሚል ይግባኙን ውድቅ ማድረጉን ከትእዛዙ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሠረቱ እንዲሰርዝ የተጠየቀው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ እንዳለው ውሣኔ ነው ቢባል እንኳን በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን በአፈፃፀም ሆነ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ቤቱን በሚመለከት ክስ ሲያቀርብ አመልካች ቀርበው ከሚከላከሉበት ሁኔታ በቀር ክስ ሣይቀርብባቸው በራሣቸው ክስ በማቅረብ ውሣኔው ይሰረዝልኝ የሚል ጥያቄ የሚያቀርቡበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይሄም አመልካች የእርቅ ስምምነት ውል ነው ያሉት አንዱ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድምዳሜ ውሣኔ ነው ቢባል እንኳን አመልካች ይሰረዝልኝ የሚል ክስ ሊያቀርቡ እንደማይችሉ የሚያመለክት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፍ ብሎ በተብራራው ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻር ሲገባው ጉዳዩን መርምሮ የስር 2ኛ ተከሣሽ ያገኘው የባለቤትነት ማሰረጃ ደብተር በሐሰተኛ መንገድ የተገኘ ነው፤ በዚህም ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195(1) የተደነገገው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የያዘ ሰው የቤቱ ባለሀብት እንደሆነ ይቆጠራል የሚለው የህሊና ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196(ለ) መሠረት ፈራሽ ሆኗል፤ በመሆኑም የስር 2ኛ ተከሣሽ የቤቱ ባለንብረት ያልሆነ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ የአመልካችን መብት አይነካም በማለት ነው የስር ፍ/ቤት ውሣኔን የሻረው፡፡ ይሄም ፍ/ቤቱ የአስተዳደር አካል (ክፍል) የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር መሠረዙን ያሣያል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 መሠረት የአስተዳደር ክፍል የሰጠውን የባለበትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ስልጣን እንዳለውና እንደሌለው መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196 የሚመለከተው አንድ የአስተዳደር ክፍል (አካል) የሰጠው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር በድንጋጌው በተመለከቱት ሁኔታዎች መሆኑን ባረጋገጠ ጊዜ የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የሚሰርዝበትን አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር የመሠረዝ ስልጣን ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጅ የፍ/ቤት አለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ ቁ.1198(2) አግባብ

ጭምር መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአስተዳደር ክፍሉ የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር በአስተዳደር ክፍሉ እስካልተሠረዘ ድረስ የባለቤትነት ደብተር ያለው ሰው በፍ/ብ/ ሕ/ቁ.1195(1) በተደነገገው መሠረት የቤቱ ባለንብረት እንደሆነ መቆጠሩ የሚቀርበት የሕግ አግባብ አይታይም፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ የተቸው ክርክሩ ሣይቀርብለት ትንታኔ የሰጠው በአግባቡ አይደለም በሚል እንጅ ፍ/ቤቱ የአስተዳደር አካል የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ስልጣን የለውም በሚል አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንንም በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የሚታየውን ስህተት ሣያስተባብል የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት የሰረዘው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ/ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ተወስኗል፡፡

2ኛ/ እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196 መሠረት ለአከራካሪው ቤት ከአስተዳደር አካል የሰጠውን የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ሥልጣን ያለው ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጂ ፍ/ቤት አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡

3ኛ/ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13999 ጥር 14/1996 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የቀረበ እንዳልሆነ ጠቅሶ የሰጠውን ትችት የሚቀበለው ቢሆንም በመጨረሻ በደረሰበት መደብደሚያ ግን ባለመስማማት ትእዛዙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ/ቁ. 348(1) መሠረት ሽሮታል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



የሰበር መ/ቁ.15672

ታህሣስ 27 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
4. አቶ አሰግድ ጋሻው
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ታደለ ገለቻ

ተጠሪ፡- ውድመጣስ ኑሮ

*ስለ ንብረት ሽያጭ - ንብረት እንደገና በሐራጅ ስለሚሸጥበት ሁኔታ፡-*

*ስለ ሐራጅ አሸናፊ ክፍያ መፈፀሚያ ወቅት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 442*

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ባለቤት የሆነ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ዕዳ እንዲከፈል በማድረግ ሁለት ተጫራቶች በተለያየ ጊዜ አሸንፈው በህጉ መሠረት በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ስላላደረጉ ድርጅትን ባለመብቱ በንብረቱ ግምት ይረከቡት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 ላይ ንብረተ ለምን ያህል ጊዜ በድጋሚ እንዲሸጥ በፍ/ቤቱ እንደሚታዘዝ ሳይደነግግም ንብረቱ ገዢ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም፡፡
2. ሁለት ጊዜ ሐራጅ ሽያጭ ወጥቶ አሸናፊዎች ካልከፈሉ ለ3ኛ ጊዜ ሐራጅ ወጥቶ ቤቱ ሊሸጥ ይገባል፡፡

የሰ/መ/ቁ. 15672

27/04 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

**አመልካች፡-** አቶ ታደለ ገለቻ - ታዬ ባንጃው ጠበቃ ቀርቧል፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ውድመጣስ ኑሮ - አልቀረበም፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

ይህ የአፈፃፀም ክርክር ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት መጋቢት 29 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሠኘታቸው ነው፡፡

ለጉዳዩም መነሻ በሆነው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ተጠሪ (የፍርድ ባለመብት) የነበሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነበሩ አመልካች የሚሉትም የእኔ ባለቤት ከወ/ሮ ይችዓለም ለገሠ ገዝታው ስሙ ያልተዛወረ «ሠላም የህፃናት ልብስ መደብር» የተባለው ድርጅት ተሸጦ ለዕዳዬ መክፈያ እንዲውል የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ሠጥቶ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ድርጅቱን አስገምቶ ፍ/ቤቱም ድርጅቱን ለሐራጅ ጨረታ እንዲቀርብ አድርጓል ሆኖም ግን ሁለት ተጫራቾች በተለያየ ጊዜ ተጫርተው ያሸነፉ ቢሆንም ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ሊያደርጉ አልቻሉም በዚህም መሠረት የከ/ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 መሠረት ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሚሠጠው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የተገለፀ ነገር የለም፣ ነገር ግን አፈፃፀሙ ተግባራዊ መሆን ስላለበት ላልተወሠነ ጊዜ ትዕዛዝ ሲሰጥ መቆየት የለበትም፣ በመሆኑም ንብረቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት የባለዕዳውን ንብረት ባለገንዘቡ እንደሚረከበው ሁሉ ድርጅቱን ባለመብቱ በንብረቱ ግምት መሠረት ይረከቡት የሚል ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡



አመልካችም በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ የከ/ፍ/ቤት የሠጠው ትዕዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበዋል፡፡፡ የይግባኛቸውም መሠረታዊ ነጥብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 ፍ/ቤቱ ንብረቱ እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል ይባል እንጅ በመነሻው ግምት የፍርድ ባለመብቱ (ተጠሪ) ይረከበዋል አይልም የሚል ሲሆን ተጠሪም በዚሁ መሠረት መልሱን ይዞ የቀረበ ሲሆን አመልካችም የበኩሉን የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይህ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ከተገቢው የሕግ ድንጋጌ ጋር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ክርክሩ የቀረበበትን ድርጅት ለመሸጥ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ፣ በሁለቱም ሐራጅ የሐራጁ አሸናፊዎች ሐራጁ በተደረገ በ15 ቀኖች ውስጥ የንብረቱን ዋጋ በሙሉ አልከፈሉም ተብሎ የፍርድ ባለመብቱ ማለትም ተጠሪ ንብረቱን በግምቱ እንዲረከብ መባሉ አግባብ መሆን አለመሆኑን አይቷል፡፡ በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 ላይ እንደተመለከተው የጨረታ አሸናፊ የሆነው ሰው በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ የንብርቱን ዋጋ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ንብረቱን እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል የሚል ተመልክቷል፡፡ ምንም እንኳን እዚህ ላይ በሕጉ ውስጥ ይህ አይነት ሁኔታ የተከሠተበት ንብረት ለምን ያህል ጊዜ በድጋሚ እንዲሸጥ በፍ/ቤቱ እንደሚታዘዝ ያልተመለከተ ቢሆንም ንብረቱ ከነአካቴው ገዥ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ የሚያስደርስ አይሆንም፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ላይ የጨረታው አሸናፊዎች ገንዘቡን አልከፈሉም ማለት ሌላ ገዥ የለም ማለት አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት የከ/ፍ/ቤት ክርክር የተነሣበትን ድርጅት ባለመብቱ በንብረቱ ግምት መሠረት እንዲረከቡት በማለት የሠጠው ትዕዛዝና የጠ/ፍ/ቤቱም የሠጠው ይህንኑ የሚያፀና ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት ሽረን ክርክር የተነሣበት ድርጀት በሐራጅ ይሸጥ ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ወስኗል፡፡ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ስላለቀ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

*የሰበር መ/ቁ. 16301*

*ኀዳር 2 ቀን 1998 ዓ.ም*

*ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ*

*አቶ ሐጐስ ወልዱ*

*አቶ ተገኔ ጌታነህ*

*አቶ ዳኜ መላኩ*

*ወ/ሮ ደስታ ገብሩ*

*አመልካች፦ ተገኝ እንግዳ*

*ተጠሪ፦ አስናቀች ኪዳኔ*

*የመጥሪያን አደራረስ አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት ሁኔታ - በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ተከሳሽ በሌለበት ክስ እንዲታይ የሚደረግበት ሁኔታ - የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 103፣ 105(1)*

አመልካች እሱ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲታገድለትና እሱም ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በደነገገው መሠረት ተጣርቶ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት መታየቱ ባግባቡ ነው ሲል በመወሠን ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተመሣሣይ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**፡- የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያፀናው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 103 እንደተመለከተው መጥሪያ አድራሻ (ሰጪው) መጥሪያውን ለማድረስ ያልቻለበትን ምክንያት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መጥሪያውን ለፍርድ ቤቱ ይመልሳል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት እንደየሁኔታው በመመዘን ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ መጥሪያው እንደተመለሠለት በሕጉ በተመለከተው መሠረት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ስርአት ማስተላለፉ ሕጋዊ ውጤት ያለው ይሆናል፡፡





ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ዳኜ መላኩ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፦ ተገኝ እንግዳ - ቀረበ

ተጠሪ፦ አስናቀች ኪዳኔ - አልቀረበችም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው የመጥሪያን አደራረስ በተመለከተ የተነሣውን ቅሬታ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁኗዋ ተጠሪ ናት፡፡ አመልካቹ በተደረገለት ጥሪ መሠረት አልቀረበም ስለተባለ ክርክሩ እሱ በሌለበት ታይቶ መወሰኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኋላ መዝገቡ የተንቀሣቀሰው አመልካች እሱ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ እንዲታገድለትና እሱም ወደክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት በመጠየቁ ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ፣ ተከሣሽ የስነ - ሥርዓት ሕጉ በደነገገው መሠረት ተጣርቶ ባለመቅረቡ ነው ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲታይ የተደረገው፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት ሣይቀበለው ቀርቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሣሣይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ማለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 859 ሚያዝያ 5 ቀን 96 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡

ክሱ አመለካች በሌለበት እንዲታይ የተደረገው መጀመሪያ በቀጥታ በአድራሻው በመቀጠልም በጋዜጣ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ሊቀርብ አልቻለም በሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ መጀመሪያ በቀጥታ በአድራሻው የተላከለትን መጥሪያ ሊገኝ ባለመቻሉ መስጠት እንዳልተቻለና ወኪሉም መጥሪያውን አልቀበልም ስለማለቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 103 መሠረት በመሐላ ተረጋግጦ ለፍ/ቤቱ በመቅረቡ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 105(1) መሠረት የጋዜጣ ጥሪ እንዲተላለፍ ማዘዙንም ተመልክተናል፡፡ አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ትእዛዝ ተሰጡብኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው እነዚህን የሥነ - ሥርዓት ደንቦች በመከተል የተከናወነው ሂደት ትክክል አይደለም፡፡ መጥሪያው በደንብ እንዲደርሰኝ ሣይደረግ ነው ክርክሩ በሌለሁበት እንዲታይ የተደረገው፡፡ መጥሪያው መጥቶልኝ አልቀበልም አላልኩም፡፡ ስራዬ ሾፌርነት በመሆኑም ጋዜጣውን ማየት ይችላል ተብሎ መገመት የለበትም በማለት ነው፡፡

ከፍ ሲል ከተመለከቱት ሁኔታዎች ማየት እንደሚቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.94(1) በተደነገገው መሠረት መጥሪያውን ለአመልካቹ ልኮአል፡፡ ሆኖም አመልካቹ በአድራሻው ተፈልጎ ባለመገኘቱ እና ሌላም መጥሪያውን መቀበል የሚችል ሰው ሊገኝ ባለመቻሉ በታቀደው ሁኔታ መጥሪያውን ማድረስ ሣይቻል ቀርቶአል፡፡ ይህን መሰል ችግር ሲያጋጥም የሥነ ሥርዓት ሕጉ መፍትሄ አስቀምጦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 103 እንደተመለከተው መጥሪያ አድራሹ (ሰጭው) መጥሪያውን ለማድረስ ያልቻለበትን ምክንያት በመሐላ ቃል አረጋግጦ መጥሪያውን ለፍ/ቤቱ ይመልሳል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት እንደየሁኔታው በመመዘን ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ይህም ማለት ተከሣሽ መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ ያለመሆኑ ወይም ደረሰኝ ለመስጠት እምቢተኛነቱ በመሐላ በተሰጠ ቃል ከተረጋገጠለት መጥሪያው በትክክል እንደደረሰ በመቁጠር ክርክሩ ተከሣሹ በሌለበት እንዲታይ ያደርጋል፡፡ መጥሪያው በትክክል እንደደረሰ ለመቁጠር የሚያስችል ምክንያት ካላገኘ፤ ነገር ግን የመጀመሪያው ሙከራ ተደርጎ ተቀባይ ባለመገኘቱ ምክንያት መጥሪያው መመለሱን ካመነ ደግሞ ቀጥሎ ያለውን ሌላው የመጥሪያ አሰጣጥ ሥርዓት (አማራጭ) ይጠቀማል፡፡ ይህ አማራጭም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.105 ከተመለከቱት አንዱ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጥሪያው እንደተመለሰለት ወዲያውኑ አመልካች በሌለበት ክርክሩ እንዲታይ አላዘዘም፡፡ ተገቢ ሆኖ ያገኘው አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 105(1) ከተመለከቱት ከምትክ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓቶች አንዱን ማለትም የጋዜጣ ጥሪ ማስተላለፍ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተገቢ ነው ያለውን አማራጭ የመወሰን ሥልጣንም የፍ/ቤቱ ነው፡፡ በጋዜጣ የሚደረግ ጥሪ በሕጉ ከተፈቀዱት ምትክ የመጥሪያ አሰጣጥ ሥርዓቶች አንዱ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በመጨረሻ ያቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበሉትም በዚህ ምክንያት እና ጥሪው የተላለፈው ተገቢውን የሥርዓት ደንብ ተከትሎ መሆኑን በማረጋገጣቸው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የፈፀሙት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የሥር ፍ/ቤቶች ትእዛዞች ፀንተዋል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



*የመ/ቁ. 10797*

*ታህሣሥ 27 ቀን 1998 ዓ.ም*

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ አሰግድ ጋሻው
4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ

**መልስ ሰጭዎች፡-** 1. ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም
2. አቶ ሁሴን አብደላ
3. አቶ ንጉሴ ኃይሉ

*ስለ ወንጀል የተወሰነ ቅጣት-የገንዘብ ቅጣቶች - ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 99 - ስለፍርድ አፈፃፀም - የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 1/89 መ/ሰጭዎች ለአመልካች 16,000,000 /አሥራ ስድስት ሚሊዮን/ የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሣኔ ለማስፈጸም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 መሠረት ያቀረበውን ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 መሠረት ሊፈጸም የሚችል ፍርድ የለም ለማለት ፍ/ቤቱ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ በማድረጉ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ው ሣ ኔ፡-የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ እንጅ ባለሀብቱ የፍትሐብሔር ክስ አላቀረበም ወይም ፍርድ ያገኘበት ውሣኔ ለአፈፃፀም የሚያበቃ የፍትሐብሔር ፍርድ አይደለም ተብሎ ሊከለከል የሚችል አይደለም፡፡
2. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ የተወሰነውን ገንዘብ የውሣኔው ባለመብት ሌላ ቀጥታ የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ ሊፈጽም የሚችል ፍርድ ነው፡፡

ታህሣሥ 27 ቀን 1998 ዓ.ም

የሰበር መ/ቁ. 10797

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ አሰግድ ጋሻው
4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ - ጠበቃ ተሾመ ገ/ማርያም ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም - ቀርበዋል
2. አቶ ሁሴን አብደላ - አልቀረበም
3. አቶ ንጉሴ ኃይሉ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት በማለት ሥህተቱ በዚህ ችሎት ታይቶ እንዲታረም ባመለከቱት መሠረት ነው፡፡

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ቁጥር 1/89 በሆነ የወንጀል መዝገብ መጋቢት 5 ቀን 1992 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪዎቹ ለአመልካች በጠቅላላው 16,000.000 /አስራ ስድስት ሚሊዮን/ የአሜሪካን ላር እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የአመልካች ጠበቃ ይህንኑ ውሣኔ መሠረት በማድረግ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ የተባለውን ብር ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲታዘዝለት አመልክቷል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በሁለቱም ወገኖች በኩል ያሉትን ባለጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች በጉዳዩ ያገባናል የሚሉትን ወገኖች አከራክሮ ካበቃ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት አፈፃፀም የሚጠየቅበት ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የበኩሉን ውሣኔ አሳልፏል፡፡ ለውሣኔውም መሠረት ካደረጋቸው ምክንያቶች መካከል፤ በአጠቃላይ ክሱ የሚያተኩረው ተፈፀመ በተባለ የወንጀል ጉዳይ ላይ እንጂ የፍትሐብሔር ይዘት እንደሌለው፣ የክሱ አቅራቢና ባለቤት ዐቃቤ ሕግ ሲሆን ጠሪዎቹ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሣሽ ሆነው የተወሰነባቸው ከመሆኑ ውጪ ከአመልካቹ ጋር በገንዘብ ክርክር እንዳልነበራቸው እና ሌሎች ነጥቦችንም በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ስለ ገንዘቡ ጉዳይ ሊነሣ የቻለው ከመወረስ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የግል ተበዳዩን መብት ለመጠበቅ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት የሚፈፀም አይነት ፍርድ ለመስጠት እንዳልሆነ መረዳት እንደሚቻል ገልጾ የቀረበው የአፈፃፀም ጥያቄ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

አቤቱታው ለሠበር ችሎት የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው አመልካችም በአቤቱታው፣ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከመሠረታዊ ፍርዱ ዓላማ እና ግብ የራቀ፣ የሕግ ግድፈት የሚታይበት እንዲሁም የአመልካችን ሕጋዊ መብት ገፍፎ በፍርድ የተወሰነለትን መብት እንዲያጣ ያደረገ መሆኑን ገልጾ ውሣኔው ውድቅ እንዲደረግለት፤ በአንፃሩ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ.ቁ.1/89 የአሁኖቹ ተጠሪዎች ለአመልካች የተጠቀሰውን 16,000.000 የአሜሪካን ላር እንዲመለስ በወንጀሉ ጉዳይ



አጣምሮ የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 መሠረት እንዲፈፀምለት አመልክቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረባቸው መልስ በአጭሩ፣ አመልካቹ በወ.መ.ሕ.ቁ. 100 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 154 መሠረት በተጠሪዎቹ ላይ በግል ተበዳይነት የፍትሐብሔር ክስ አለማቅረባቸውን፣ የፍ/ብሔር ክስ በጣምራ እንዲታይ አቤቱታ ባልቀረበበት የወንጀል ክስ የሚሰጥ ውሣኔ ደግሞ ቅጣት እንጂ የካሣ ውሣኔ ሊሆን እንደማይችል እንዲሁም አመልካቹ መብት አጉናፅፎኛል የሚሉት ፍርድ ከአፈፃፀም አቤቱታው ጋር ተያይዞ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲደርስ አለመደረጉን ገልፃ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግላት አመልክታለች፡፡

2ኛ ተጠሪ ሁሴን አብደላ የጠ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት በሌለበት የወሰነበት ስለሆነ በዚህም ችሎት አልተገኘም፡፡ 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከ1ኛ ተጠሪ መልስ በተለየ ሁኔታ፣ የወንጀል ችሎቱ ስለ አመልካቹ ገንዘብ ሊያነሣ የቻለው ገንዘቡ በመንግሥት እንዳይወረስ ከማሰብ ጋር አያይዞ መሆኑን የፍትሐብሔር ይግባኙን የመረመረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁ. 1/89 ላይ የተሰጠው ውሣኔ መንግሥት በተጠሪዎች ላይ የሚጠይቀውን የፍ/ብሔር ጉዳይ እንደማያጠቃልል ተገልጾ እያለ በዚህ ተመሣሣይ የወንጀል መዝገብ ውሣኔ በጉዳዩ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያላነሣን ወገን የፍ/ብሔር ጉዳይ ጭምር ያካተተ ነው ለማለት እንማያስደፍር፤ በሌላ በኩል የሰበሩ አቤቱታ ከቀረበበት አፈፃፀም ክርክርና ትእዛዝ በኋላ አመልካች በስዊዘርላንድ የፌዴራል ፍ/ቤት አስወስነው ገንዘባቸውን ወስደው ሳለ በድጋሚ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው አግባብ እንዳልሆነ ገልጾ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ጠበቃ በመልስ መልሱ አቤቱታውን አጠናክሮ የተጠሪዎችን መልስ ተችቷል፡፡ በበኩላችን መዝገቡን መርምረናል፡፡ ምላሽ ማግዕት የሚገባው ሆኖ ያገኘነው ነጥብ፣ በዚህ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት አፈፃፀም ሊጠየቅበት የሚችል ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

ለዚህ ጉዳይ መነሻ በሆነው የወንጀል መዝገብ ቁ.1/89 የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት መጋቢት 5 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ለአመልካች መመለስ የሚገባቸውን 16,000.000 (አስራ ስድስት ሚሊዮን) የአሜሪካን ላር እንዲከፍሉ ፈርዷል፡፡

ክሱ የሚያተኩረው ተፈፀመ በተባለ የወንጀል ጉዳይ ላይ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የወንጀል ክሱን የመረመረውና የወሰነው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ክፍሎ መሆኑን፣ ከእነዚህ አንዱ ወንጀሉን ፈጽመዋል በተባሉት ሠዎች ላይ የእሥራትና የገንዘብ መቀጮ መወሰን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተጠሪዎች ከአመልካችና ከመንግሥት ወሰዱ የተባለውን ገንዘብ ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ መፍረድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አሁን የተጠየቀው ገንዘብ የአመልካች ገንዘብ ስለመሆኑ መረጋገጡን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

እንደሚታወቀው ማናቸውም ሕግ ተላላፊ በወንጀል ሥራው ያገኛቸው ገንዘብና እቃዎች ሕጋዊ ባለንብረቱ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ሊመለሱለት እንደሚገባ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ.99(2)ዬ ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶችጦ በሚለው ክፍል የደነገገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ/ቁ. 1/89 አሁን የተጠየቀውን ገንዘብ ለባለቤቱ ሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እንዲመለስ ውሣኔ የሰጠውም ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጐ እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ባለንበረቱ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን ለመረከብ አዲስ ክስና ክርክር መመስረት ሳያስፈልገው በቀጥታ መረከብ እንደሚችል ነው፡፡ አሁን የተነሳው የአፈፃፀም ጥያቄም ይህንኑ ውሣኔ መሠረት አድርጐ ተጠሪዎቹ ከላይ ተጠቀሰውን ገንዘብ እያንዳንዳቸው በየድርሻቸው መመለስ የሚገባቸውን ያህል እንዲከፍሉ እንዲታዘዝ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ የአፈፃፀም ጥያቄ ክፍ ሲል በጠቀስነው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ አኳያ የገንዘቡ ወይም የንብረቱ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ከመሆኑ ውጭ ባለሀብቱ የፍትሐብሔር ክስ አላቀረበም ወይም ፍርድ ያገኘበት ውሣኔ ለአፈፃፀም የሚያበቃ የፍትሐብሔር ፍርድ አይደለም ተብሎ ሊከለከል የሚችል አይደለም፡፡



ለማጠቃለል ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በፍርድ የተወሰነውን ገንዘብ የውሣኔው ባለመብት ሌላ ቀጥታ የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ሣያስፈልገው በቀጥታ ሊፈፅም የሚቻል ፍርድ ነው በማለት ይህን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ/ቁ. 1/89 ስለገንዘቡ አመላለስ አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ የአሁኑ አመልካች በፍርዱ ውሣኔ በተሰጠው ምርጫ መሠረት ገንዘቡን ለማስመለስ በበኩሉ ያቀረበውን ጥያቄ መርምረን በሚከተለው መልኩ እንዲፈፀም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. 1ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ ወ/ሮ ሸዲያ ናዲም የአሜሪካ ላር 9,000.000 (ዘጠኝ ሚሊዮን ላር)፤
2. 2ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለዕዳ አቶ ሁሴን አብደላ የአሜሪካን ላር 6,443.447.95 (ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሦስት ሺ አራት መቶ አርባ ሰባት ላር ከዘጠና አምስት ሣንቲም)
3. 3ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ አቶ ንጉሤ ኃይሉ የአሜሪካን ላር 556,324.05 (አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺ ሦስት መቶ ሃያ አራት ላር ከዜሮ አምስት ሣንቲም) በጠቅላላ 16,000.000 (አሥራ ስድስት ሚሊዮን የአሜሪካን ላር) ለፍርድ ባለመብቱ ለአሁኑ አመልካች ለሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እንዲመልሱ ታዟል፡፡

- በወ.መ.ቁ. 1/89 ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት መንግሥት ከ1ኛ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ ከወ/ሮ ሻዲያ ናዲም ላይ የሚፈልገውን ገንዘብ ከሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ አስቀድሞ እንዲወስድ ታዟል፡፡
- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ.5915 ህዳር 12 ቀን 1995 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 18199
ህዳር 7 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ሐጐስ ወልዱ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ር ምናሴ እሸቱ
ተጠሪዎች፡- እነ ግርማ አያና (7 ሰዎች)

*በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈፅም የቀረ ገዢ ባጋጠመ ጊዜ ጓርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ሊከተሰው ስለሚገባው ሥርዓት - የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 429*

የአሁኑ አመልካች ፍርድ በማስፈፀም ላይ የነበረ ፍርድ ቤት ባወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት የገዛ፣ ቢሆንም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በዚሁ መሠረት የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ይከፈል በማለት ትዕዛዝ ሊሰጥ በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡ -

**ውሣኔ** ፡-የአማራ ብሐራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

1. በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚቻል በሕጉ አልተመለከተም፡፡
2. የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 እንደሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረከ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡





የሰበር መ/ቁ
ህዳር 7 ቀን 19

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ሐጐስ ወልዱ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ር ምናሴ እሸቱ ጠበቃ አፀደወይን ተክሌ ቀረቡ፡፡
ተጠሪዎች፡- እነ ግርማ አያና (7 ሰዎች) - የ1ኛ ተጠሪ ወኪል ቀረቡ፡፡
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በቀረበው የሰበር አቤቱታ የተነሣው የሕግ ጥያቄ በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሣይፈጽም የቀረ ገዥ ባጋጠመ ጊዜ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ ፍ/ቤት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በማፅናት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ 192/97 ታህሣሥ 7 ቀን 97 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየው የአሁኑ አመልካች ፍርዱን በማስፈፀም ላይ በነበረው ፍ/ቤት በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት (ሆስፒታል) ገዝቶአል፡፡ ሆኖም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የሰጠው ምክንያትም ንብረቱን ተረክብ የተባልኩት ስወዳደር ካሰብኩት እና በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ ከተመለከተው ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ (ተቃውሞ) አልተቀበለም፡፡ ይልቁንም አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ

በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ይክፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የለበትምትክክል ነው ብሎአል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ በፍትሐብሔር ረገድ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ስለፍርድ አፈፃፀም በተመለከተ የፍትሐብሔር ሥነ - ሥርዓት ሕጉ በሰባተኛው መጽሐፍ ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጦአል፡፡ በፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ሥነ - ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ደግሞ ከቁ.422 እስከ 431 በተለይ ተቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አሁን ለያዝነው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ቁ.429 ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ እንደሚደረግ ነው፡፡ በእርግጥ ንብረቱ እንደገና በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛውና ዋጋውን ያልከፈለው ተጫራች ልዩነቱንና ኪሣራውን እንዲከፍል እንደሚገደድም ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚችል በሕጉ አልተመለከተም፡፡ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት በጥብቅ መከተል ያለበትም ሕጉን ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሕጉ ከሚለው ውጪ አመልካች የጨረታውን ዋጋ እንዲከፍል እና ንብረቱንም በግድ እንዲረከብ ነው የታዘዘው፡፡ ስለዚህም ትእዛዙ (አቤቱታ የቀረበበት) መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ ፣</u>

አቤቱታ የቀረበባቸው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/ መ/ቁ. 192/97 የሰጠው ትእዛዝ እና በዚህ ትእዛዝ ፀንቶ የነበረው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡

ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው በየራሣቸው ይቻሉ፡፡



የሰ/መ/ቁ.16378

ታህሣስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የ10 ዓለቃ ጌታቸው ባዩ

**ተጠሪ፡-** በቤ/ዝ/ክ/መ/ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ቅ/መ/ቤት

*ስለ ጡረታ መብት - የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ስለመስራት - ድንጋጌ ቁጥር 46/53 እና አዋጅ ቁጥር 209/55 አንቀጽ 30(2)*

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በመንግስት መስሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ ከወሠደ የጡረታ አበሉን መመለስ አለበት በማለት የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሳኔ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. አንድ የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ተገሎ አበሉን እየተከፈለው ከሆነ በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደሞዝ እና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል አይቻልም፡፡

2. አንድ የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ተገልሎ አበሉ እየተከፈለው በሌላ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጠሮ ደመወዝ ከወሰደ ከጡረታ አበሉ ወይም ከወሰደዉ ደመወዝ በመጠን የሚያነሰዉን ይመልሳል፡፡

የመ/ቁ.16378

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ ቀረበ

ተጠሪ፡- በቤ/ዝ/ክ/መ/ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ቅ/መ/ቤት ነገረፈጅ አቶ ፈርተውሃል ኃይለጊዮርጊስ ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ መውሰድ ይችላል አይችልም፣ ሁለቱን በጣምራ ወስ ከተገኘ የጡረታ አበሉን ለመመለስ ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ ሲወስድ የቆየ መሆኑ ቢረጋገጥም ደመወዙንም ሆነ የጡረታ አበሉን የሚመልስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የወሰነውን የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.348(1) መሠረት



በመሻር ቀደም ሲል በሥራ ላይ በቆየው የጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/55 አንቀጽ 30/2/ መሠረትም ሆነ በኋላ ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 46/1/ መሠረት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝ ማግኘት ከጀመረ የጡረታ አበል እና ደመወዝ በጣምራ ሊወሰድ አይችልም፣ በሕጉ የጡረታ አበሉ ተቋርጦ ይቆያል፣ ስለዚህ 10 አለቃ ጌታቸው ባዩ ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል መመለስ ይገባዋል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ያለአግባብ ሲቀበል ቆይቷል የተባለው የጡረታ አበል በአጠቃላይ ብር 9000 ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም እንዲመልስ የወሰነው ይህንኑ ገንዘብ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡ አመልካች ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል መመለስ አለበት በሚል በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ነው ለሰበር አቤቱታ ያቀረበው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለአሁኑ ተጠሪ እንዲደርሰው ተደርጉ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በጽሑፍ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡ በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በኩል የቀረበው ክርክር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ አንድ የጡረታ መብቱ የተከበረለት ሠራተኛ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ከተቀጠረ የጡረታ ሕጉ የጡረታ አበሉ ወዲያውኑ የሚቋረጥ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ እንደተቀጠረ ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በማሣወቅ የጡረታ አበሉ እንዲቋረጥ ማድረግ ሲገባው ደብቆ ደመወዝና የጡረታ አበል ያለአግባብ በጣምራ ሲቀበል ቆይቷል፡፡ መሥሪያ ቤቱ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መ/ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መቀጠሩን የሚያውቅበት መንገድ ስሌለ የጡረታ አበሉን እንዲያቋርጥ ለማድረግ አይችልም፡፡ የጡረታ አበሉን ሲከፍለው የቆየው ደመወዝ ማግኘቱን እያወቀ አይደለም፡፡ አመልካች በሕግ የጡረታ አበል ስለመቋረጡ አላውቅም የሚለው መከላከያ

መልስ ሊሆነው አይችልም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/በት በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሣኔም የተፈፀመ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ችሎቱም አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ሊቀጠር ከቻለ ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሊቀበል ይችላል አይችልም፤ የአሁኑ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ ከደመወዝ ጐን ለጐን ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል ለመመለስ ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች ቀደም ሲል ሲሰራ ከቆየበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከታህሣሥ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እንዲገለል ተደርጐ የተወሰነለትን የጡረታ አበል ማግኘት ከጀመረ በኋላ ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዝ በሚያስገኝ ሌላ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ በመሥራት ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ተከሣሹ የአሁኑ አመልካች ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየው ያለአግባብ ስለሆነ የጡረታ አበሉን ሊመልስ ይገባል በሚል የከሰሰው በታህሣሥ ወር 1994 ዓ.ም ነው፡፡ ይኼው ከተረጋገጠ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ የሚሆነው በኋላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 345/95 ሣይሆን በወቅቱ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ በሥራ ላይ የነበረው ድንጋጌ ቁጥር 46/53 እና ይህንኑ ድንጋጌ በከፊል በማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 209/55 ነው የተጠቀሰው ድንጋጌ አንቀጽ 30/2/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደመወዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ አለበት ይላል፡፡ ከዚህ ሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ከሁለቱ አንዱን የመምረጥ መብት የተሰጠው ለሠራተኛው ነው፡፡ በሕግ ከተፈቀደለት የጡረታ አበል እና ተመልሶ ከተቀጠረበት የመንግሥት ሥራ ከሚያገኘው ደመወዝ የበለጠ ይጠቅመኛል የሚለውን የመምረጥ እድል በሕጉ ስለተሰጠው ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ እንደተቀጠረ በአካባቢው ላለው የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በማሣወቅ ምርጫው ምን እንደሆነ መግለጽ ይኖርበታል፡፡ የበለጠ የሚጠቅመኝ አዲሱ ደመወዝ ነው ካለ የጡረታ አበሉ እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ በሚቀጠርበት ጊዜ ራሱ ወይም ቀጣሪው መሥሪያ ቤት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ካላሣወቀ በቀር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚያውቅበት



መንገድ ስለሌለ ተከታትሎ የጡረታ አበሉን ማቋረጥ ነበረበት የሚለው ከጡረታ ሕጉ አኳያ ሲታይ ተቀባይነት የለውም፡፡

ጡረታ የወጣው ሰው ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ አዲስ ደመወዝ እና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕጉ ምን ይደረጋል? የሚለው ሲመረመር ሕጉ ደመወዙን ወይም የጡረታ አበሉን ይመልሣል የሚል ግልጽ ድንጋጌ ባይኖረውም በሕጉ ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል አይቻልም ከተባለ አጣምሮ ሲቀበል የቆየውን በሕግ ያልተፈቀደለትን ገንዘብ የማይመልስበት ምክንያት የለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች ከደመወዝ ጎን ለጐን ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል እንዲመልስ ጠይቋል፡፡ ሆኖም አመልካች በወቅቱ በሕጉ በተሰጠው ከአዲሱ ደመወዝ እና የጡረታ አበል አንዱን የመምረጥ መብት ስላልተጠቀመ ሊመልስ የሚገባው ሲቀበል ከቆየው ደመወዝና የጡረታ አበል አነስተኛ ሆኖ የተገኘውን ገንዘብ ነው፡፡ በሕጉ ላይ በተገለፀው መሠረት ሊመርጥ ቢችል ኖሮ ከሁለቱ ከፍ ያለውን ገንዘብ ይመርጣል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከተቀጠረበት ሥራ የሚያገኘው ደመወዝ ዝቅተኛ ሆኖ የጡረታ አበሉ ከፍተኛ ከሆነ የጡረታ አበሉን ትቶ ዝቅተኛ የሆነውን ደመወዝ ይመርጣል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ፍትሐዊም የሚሆነው አጣምሮ ሲቀበል ከቆየው ደመወዝና የጡረታ አበል መካከል ዝቅተኛ የሆነውን እንዲመልስ ማድረግ ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሎ የአሁኑ አመልካች ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ አጣምሮ ሲቀበል ከቆየው ደመወዝ እና የጡረታ አበል መካከል አነስተኛ ሆኖ የተገኘውን እንዲመልስ ወይም ለተጠሪው እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የመ/ቁ.18342

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን

መልስ ሰጭዎች፡- 1ኛ- አቶ ብርሃኑ ህሩይ
2ኛ- አቶ ከበደ ገ/ማርያም

*ስለማኀበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ - የማኀበራዊ ዋስትና ባልስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/1988 አንቀጽ 11/1/ ፡- ስለፍርድ ቤቶች ስልጣን -የፍትሐ ብሄር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 4*

የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማኀበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የማኀበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኂላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ስለሰጠና ውሳኔውንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስላደናው የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. በህግ ተለይተው በአስተዳራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፡፡
2. የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማኀበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስራ ነገር ስልጣን የላቸውም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 18342

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ነገረፈጅ አቶ ፈርተውሃል ኃ/ጊዮርጊስ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ አቶ ብርሃኑ ሕሩይ ቀረበ
2ኛ/ አቶ ከበደ ገ/ማርያም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የሆኑት የአሁኑ ተጠሪዎች በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረን ስናገለግል በቆየንባቸው ዓመታት ለጡረታ አበል እየተባለ ከደመወዛችን ከመቶ አራት፣ ከአሠሪው መሥሪያ ቤት ደግሞ በመቶ ስድስት እየተቀነሰ ለማህበራዊ ዋብትና ባለሥልጣን ገቢ ተደርጓል ያሉትን ገንዘብ የሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ወደነበረበት እንዲመልስ፣ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በበኩሉ ያለአግባብ ከከሣሾች ሂሣብ ወጪ በማድረግ ለትምህርት ቤቱ የሰጠውን ገንዘብ ወደነበረበት ሂሣብ ተመላሽ እንዲያደርግ በሚል የሰጠውን ውሣኔ ከፍተኛው ፍ/ቤት ትክክል ነው ብሎ በማጽናቱ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በዚህ ጉዳይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸው ምክንያቶች የአሁኑ ተጠሪዎች ይህንኑ ከጡረታ አበል ጋር የተያያዘውን ገንዘብ ጉዳይ በሚመለከት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ጥያቄ አቅርበው መሥሪያ ቤቱ በሕጉ መሠረት አይቶ ከወሰነ በኋላ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አመልክተው የመጨረሻ ውሣኔ ሰጥቶበታል ጉባዔው በአዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 11(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ስለሆነ ከዚህ በኋላ በዚሁ ጉዳይ ለፍ/ቤት ክሥ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሠረት ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሎ መወሰን ነበረበት፡፡ ከጡረታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተነሣውን ጥያቄ መደበኛ ፍ/ቤት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም፡፡ የህንን ጉዳይ በየደረጃው የተመለከቱት ፍ/ቤቶች ሕጉን በአግባቡ ሣይተረጉሙ ቀርተዋል በሚል የቀረቡ ናቸው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ የሚጣሩ የሕግ ነጥቦች ያሉት ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻም ለአሁኑ ተጠሪዎች ተልኮ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የመልስ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡

በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ አመልካች ያለአግባብ ከእኛ ሂሣብ አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ በሚመለከት የጡረታ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ክሥ አቅርበን በሥማችን ውሣኔ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ ማሥረጃ አላቀረበም፡፡ የአገልግሎት ዘመናችን ተቀንሶብናል ወይም ያለአግባብ ዕድሜአችን ለጡረታ ሣይደርስ በጡረታ እንድንገለል ተደርጓል በሚል ያቀረብነው ክስ ስለሌለ በጡረታ ሕጉ መሠረት የሚታይ ጉዳይ የለም፡፡ አመልካች አላገባብ ከሂሣባችን አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ ተቀብሎ ወደነበረበት ሂሣብ እንዲያስገባ በሚል የቀረበውን ክሥ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት አመልካቹ መሥሪያ ቤትን ጠይቆ የወሰደው ገንዘብ አላገባብ መሆኑን አምኖ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት መልሶ ገቢ ስላደረገ አመልካች አልፈጽምም የሚልበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ችሎቱም የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ይፈፀምልን ያሉትን ጉዳይ ፍርድ ቤት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡ በአዲስ መልክ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5 ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚፈጽማቸውን ተግባሮች እና የተሰጠውን ሥልጣን የሚዘረዝር ሲሆን በዚህ አንቀጽ ሥር ከታቀፉት ንዑስ አንቀጾች መካከል በንዑስ አንቀጽ 8 ላይ የተመለከተው ሲታይ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት በሚቀርቡ የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን በግልጽ ያረጋግጣል፡፡ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በዚሁ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም በሚመለከት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው በአዋጁ አንቀጽ 11 ላይ ሥልጣን ለተሰጠው ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርቡትን ይግባኞች መርምሮ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ነው፡፡ በሕጉ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በአንድ የማህበራዊ



ዋስትና ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ነው ከተባለ ከዚህ በኋላ በይግባኝ ደረጃም ሆነ በክሥ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የሚሄድበት መንገድ የለም ማለት ነው፡፡ በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍ/ቤት ሊያስተናግድም ሆነ አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግሥት አስተዳደር አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጐች መጠበቅና መከበር ይኖርባቸዋል፡፡ የዳኝነት አካሉ ሥልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጐም ሥራው በሕግ ማቀፍ የሚመራ ነው፡፡ ስለዚህ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ሁሉ ፍርድ ቤት አይቶ ከመወሰን ሊገደብ አይችልም የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4 ላይ በፍርድ ቤቶች እንደተገለፀው በሌላ ሕግ በግልጽ ከታገዱ በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን የላቸውም፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካችን ሊከሱ የቻሉበት ምክንያት እና ባቀረቡት ክስ ይፈፀምልን በሚል ያነሱት ጥያቄ ከማህበራዊ ዋስትና ጉዳይ ጋራ ተያያዥነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ሲመረመር በመጀመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ ቢቆዩባቸው አመታት ለጡረታ መዋጮ እየተባለ ከእያንዳንዳቸው ደመወዝ በወር በመቶ አራት፣ከአሠሪው መሥሪያ ቤት ደግሞ በመቶ ስድስት እየተዋጣ በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በየሥማቸው በተከፈተ ሂሣብ ገቢ ሲደረግ የቆየው ገንዘብ በኋላ ወደተዛወሩበት የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት መተላለፉን ገልፀዋል፡፡

ተጠሪዎች የአሁኑ አመልካች የጡረታ መዋጮውን ወደሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ያስተላለፈው አላገባብ ነው ይበሉ እንጅ በክሣቸው ላይ ከገለፁት ፍሬ ነገር እንደሚታየው ከጥር ወር 1989 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እንዲገለሉ ተደርጓል፡፡ ወደ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት እንዲተላለፍ ተደርጓል የሚሉት ትምህርት ሚኒስቴር ሲሰሩ በነበረበት ወቅት የተዋጣው የጡረታ መዋጮ ወደ ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እንዲመለስ የሚጠይቁትም ተመልሶ በእነርሱ ሥም በተከፈተ ሂሣብ እንዲቀመጥ ለማድረግ ብቻ ሣይሆን ይኸው ታስቦ በጡረታ አበላቸው ላይ እንዲጨመር ለማድረግ ወይም በሕጉ መሠረት ይገባናል የሚሉትን መብት ለማስከበር እንጅ ለሌላ ጉዳይ ለማመቻቸት አይደለም፡፡ የምናነሣው የማህበራዊ ዋስትና መብትም ሆነ ጥቅም የለም የሚሉ ከሆነ ደግሞ የጡረታ መዋጮው ቀደም ሲል በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሥማቸው ተከፍቶ ወደነበረው ሂሣብ እንዲመለስ የሚጠይቁበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የጡረታ መዋጮም በቀጥታ ከማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጋራ ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ተጠሪዎች ወደሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ተላልፏል የሚሉት የጡረታ መዋጮ ወደ ማህበራዊ ዋስትና

ባለሥልጣን እንዲመለስ ተደርጐ በሕጉ መሠረት የሚገባን የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም አለ ካሉ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5(8) መሠረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ጥያቄአቸውን አቅርበው ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ አለባቸው። ተጠሪዎች ትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ በቆዩባቸው አመታት ተዋጥቷል የሚሉት የጡረታ መዋጮ እንዲተላለፍ ከተደረገበት የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ወደማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ካዝና እንዲመለስ መጠየቁ ብቻ በሕጉ ትርጉም የለውም። ወደ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ተላልፋል የተባለው የጡረታ መዋጮ እንዴት ይሆናል? በጡረታ አበል ሊታሰብላቸው ይገባል አይገባም የሚለውን ጥያቄ በሕጉ የመወሰን ሥልጣን ያለው ራሱ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና በይግባኝ ደረጃ የሚያየው ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ እንጅ ፍርድ ቤት አይደለም።

በሌላም በኩል የአሁኑ አመልካች በክርክሩ ላይ እንደገለፀው ይኼው ጉዳይ ቀደም ሲል ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ቀርቦ እስከ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ ደርሶ ታይቶ ውሣኔ ከተሰጠበት እንደገና የሚታይበት የሕግ አግባብ የለም። በሕጉ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ በመሆኑ ያበቃለት ጉዳይ ይሆናል።

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤት በሥረ ነገሩ ላይ የመዳኘት ሥልጣን የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል። በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

## ው ሣ ኔ

1. ይህንን ጉዳይ በማስመልከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 2384ታህሣሥ 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔም ሆነ ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. በክርክሩ ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።
3. የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ



መ/ቁ.14699

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** የኢንጂነር ወርቁ መኮንን የአመልካች ወራሾች

**ተጠሪ፡-** የቦሌ ክ/ከተማ ገቢዎች መምሪያ

*ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሕጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ - የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29*

አመልካች ገቢ ለመፍጠር ወጪ ያደረጉት ገንዘብ በወጪነት ሳይያዝ ግብር እንዲከፍሉበት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ በወጪነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም ወጪ ለመውጣቱ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ በወጪነት ሊያዝላቸው ይገባል በማለት ሲወስን ጉዳዮን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔ ያፀናው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን የቀረቡት ማስረጃች በግብር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ ሰነዶች ስላልሆኑ በወጭነት ሊያዙ ስለማይገባ ግብር ይከፈልባቸው በማለት ውሳኔ በመሥጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

**ዉሳኔ፡-** **የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡**

1. **የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29 «ትክክለኛ» ሰነዶች እንዲቀርቡ የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ወጪች በቀጥታ ገቢን ለመፈጠር ስለመውጣታቸው በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ እና ግብር ከፋዩ ሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ የግብር ግዴታውን እንዳይሸሽ ለመቆጣጠር እንጂ የሰነዶችን አዘገጃጀት ሥነ-ሥርዓት መሟላት አለመሟላት ለመቆጣጠር አይደለም፡፡**
2. **ሰነዶቹ መ/ቤቱ እንዲሟሉ የሚፈልጋቸው ሥርዓቶች ባያማሉ እንኳ ወጪ ለመውጣቱ ሊያረጋግጡ የሚችሉ በቂ ሁኔታችን እስካሳዩ ድረስ ተቀባይነት የማያገኙ ‑ብት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡**

ህዳር 7 ቀን 1998

መ/ቁ.14699

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢንጂነር ወርቁ መኮንን የአመልካች ወራሾች ሞግዚት ወ/ሮ ገነት ኤርሲዶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቦሌ ክ/ከተማ ገቢዎች መምሪያ - ነ/ፈጅ ገዛኸኝ ኢርኮ ቀረበ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሲሆን አመልካች በይግባኝ አቤቱታቸው ገቢ ለመፍጠር ወጪ ያደረጉት ገንዘብ በወጪነት ሳይያዝ ግብር እንዲከፍሉበት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ በወጪነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ጉባኤውም ወጪ ለመውጣቱ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ በወጪነት ሊያዝላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ ያፀናው ቢሆንም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ግን ለድርጅቱ ወጥተዋል የተባሉት ወጪዎችን ለማረጋገጥ የቀረቡት ማስረጃዎች በግብር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ የሆኑ ሰነዶች ስላልሆኑ በወጪነት ሊያዙ ስለማይገባ ግብር ይከፈልባቸው በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም የቀረቡት ሰነዶች ወጪዎቹ ገቢን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ለመሆናቸው ለማረጋገጥ ብቃት ያላቸው ሰነዶች በመሆናቸው በወጪዎቹ ላይ ግብር እንዲከፈል መደረጉ የህግ ስህተት ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደረሰኞቹ በግብር ሕጉ መሠረት የተሰሩ ትክክለኛ ሰነዶች ስላልሆኑ ተቀባይነት ሊያገኙ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከላይ ከተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይህ ችሎት አመልካች ግብር እንዲከፈሉ የተሰጠው ውሣኔ የገቢ ግብርን ለማስከፈል የወጣውን አዋጅ መሠረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በገቢ ግብር አዋጁ መሠረት ግብር የተጣለበትን ገቢ የሚሰበስብ ማንኛውም ሰው በአዋጁ በተመለከተው መሠረት ከጠቅላላው ገቢ ላይ ገቢውን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ በሚገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ግብር የመክፈል ሃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ግብር ከፋይ ገቢን ለመፍጠር ያወጣውን ወጪ ትክክለኛነት ተቀባይነት ሊያገኙ የሚገባቸው ሰነዶች በማቅረብ ወጪዎቹን የማስረዳት



ሸክም አለበት፡፡ የግብር ሰብሳቢው ባለስልጣንም የሚቀርቡለትን ሰነዶች ወጪዎች በትክክል ገቢን ለመፍጠር የወጡ ለመሆናቸው የሚያስረዱ ትክክለኛ ሰነዶች ስለመሆናቸው የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ የቀረቡለት ሰነዶች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሃላፊነት የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን መ/ቤቱ የሰነዶቹን ትክክለኛነት ሊያረጋግጥ የሚገባው እንዴት ነው የሚለው በቀጣይነት መታየት ይኖርበታል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ የወጣው ግብር ከፋዩ ግብር በተጣለበት ገቢ ላይ የሚፈለገውን ትክክለኛ ግብር እንዲከፍል ለማድረግ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀውም ግብር የሚከፈልበት ገቢ ገቢውን ለመፍጠር የወጣው ወጪ ከጠቅላላ ገቢው ላይ ከተቀነሰ በኋላ በሚገኘው ትርፍ ላይ ብቻ በመሆኑ ገቢን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ሳይቀነሱ በጠቅላላው ገቢ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረጉ የአዋጁን አላማ የሚንድ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የቀረቡትን ሰነዶች በሙሉ መቀበሉም ግብር ሊከፈልበት የሚገባው ገቢ እንዲቀንስ የሚረዳ ስለሚሆን የሚቀርቡ ሰነዶች ትክክለኛነት በጥንቃቄ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29 ለባለስልጣኑ የሚቀርቡ የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች ውስጥ የሚሰፍሩ ሂሳቦች ትክክለኛ በሆኑ ሰነዶች /ቫውቸሮች/ መደገፍ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ ትክክለኛ ሰነዶች እንዲቀርቡ የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ወጪዎቹ በቀጥታ ገቢን ለመፍጠር ስለመውጣታቸው በበቂ ሁናቴ ለማረጋገጥ እና ግብር ከፋዩ ሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ የግብር ግዴታውን እንዳይሸሽ ለመቆጣጠር እንጂ የሰነዶቹን አዘገጃጀት ሥነ - ሥርዓት መሟላት አለመሟላቱን ለመቆጣጠር ባለመሆኑ የሰነዶቹ ይዘት ሊታይ የሚገባው ከዚሁ የአዋጁ አላማ አንፃር ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ለመ/ቤቱ የቀረቡት ሰነዶች ወጪ ለመውጣቱ የሚያሳዩ በቂ ሁኔታዎችን እስከያዙ ድረስ መ/ቤቱ ሰነዶቹ ሲዘጋጁ ሊሟሉ ያስፈልጋል የሚላቸው ስርዓቶች /ፎርማሊቲዎች/ በሙሉ ባለመሟላታቸው ብቻ ሰነዶቹን ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ በእርግጥ የሥርዓቶቹ መሟላት ወጪው መውጣቱን ለማረጋገጥ የተሻሉ ማስረጃዎች ሊያደርጋቸው ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ሰነዶቹ መ/ቤቱ እንዲሟሉ የሚፈልጋቸው ሥርዓቶች ባያሟሉ እንኳን ወጪ ለመውጣቱ ሊያረጋግጡ የሚችሉ በቂ ሁኔታዎችን እስካሳዩ ድረስ ተቀባይነት ሊያገኙ የማይችሉበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ወደ ተያዘውም ጉዳይ ስንመለስ አመልካቹ የህንፃ ተቋራጭ ሲሆኑ ግብር የተጠየቁትም ለሚሰሩት የግንባታ ሥራ እንደሆነ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ግብር

የተጣለባቸው ይህንኑ ሥራ አከናውነው ገቢ አግኝተዋል በማለት ከሆነ አመልካች ግንባታውን ማከናወናቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን የሥራ ዘርፍ ለማከናወን ደግሞ አሸዋ፣ ድንጋይ የመሳሰሉት ጥሬ እቃዎች መጠቀማቸው እንደማይቀር አከራካሪ አይሆንም፡፡ አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ግብር የተጣለበትን የግንባታ ሥራ ለመስራት እነዚህ ጥሬ እቃዎች መገዛት አለመገዛታቸው ሳይሆን ግንባታውን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉት ጥሬ እቃዎች መጠን እና ዋጋቸው ነው፡፡ አመልካች ሥራቸውን ለማከናወን ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጥሬ እቃዎች የገዙት ከገጠር የአገሪቱ ክፍል ለመሆኑ የገለፁትን እውነታ ተጠሪ ክርክር እንዳላቀረበበት ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በገጠር የሃገሪቱ ክፍል ለሚደረግ ሽያጭ ደግሞ ማህተም ያለው ደረሰኝ ማግኘት ከባድ በመሆኑ የወጣውን ወጪ ለማረጋገጥ የቀረበው ሰነድ ነጭ ወረቀት መሆኑን አመልካቹ ገልፀዋል፡፡ ግብር ሰብሳቢው መ/ቤትም የቀረበለትን ሰነድ ውድቅ ያደረገውም ሰነዱ ማህተም ያልተደረገበት ነው በሚል ብቻ እንጂ ግብር የተጣለበትን ገቢ ለመፍጠር እነዚህ ጥሬ እቃዎች አልተገዙም ወይም ወጪው የተጋነነ ነው በማለት አለመሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በዚህ በኩል ያቀረበው ክርክር ቢኖር ኖሮ ከፍ ሲል እንደተባለው ጉዳዩ አከራካሪ ሊሆን ይችል ነበር፡፡ በተጠሪ በኩል ግን እንደዚህ አይነት ክርክር አልቀረበም፡፡ በእቃዎቹ ዋጋና መጠን ላይ ክርክር ሳይቀርብ ወጪ መውጣቱ በተረጋገጠ ጉዳይ ላይ ሰነዱ ማህተም የለውም በሚል ብቻ ሰነዱን ውድቅ ማድረጉ ደግሞ በወጣ ወጪ ላይ ግብር እንዲከፈል የማድረግ ውጤት ስለሚኖረው አዋጁን የሚቃረን አፈፃፀም ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ ለመኪና የሰሌዳ ቁጥር ከመስጠቱ በፊት የሻንሲ ቁጥር እየተመዘገበ ጥገና ሲደረግ የነበረ በመሆኑ የቀረበው የታርጋ ቁጥሩ ያልተመዘገበበት ደረሰኝ መሆኑን መዝገብ ያመለክታል፡፡ በዚህ ደረሰኝ ላይ የሰፈረው የሻንሲ ቁጥር የአመልካች መኪና ለመሆኑ ማረጋገጡን ግብር ሰብሳቢው መ/ቤትም አይከራከርም፡፡ መታየት ያለበት ደግሞ የቀረበው ሰነድ ለአመልካች መኪና ጥገና የተደረገ መሆኑን ማረጋገጡ እንጂ የግድ የመኪናው ሰሌዳ ቁጥር መፃፉ ሊሆን አይገባም፡፡ የሻንሲ ቁጥሩም ቢሆን ከታርጋ ቁጥሩ የበለጠ መኪናው የአመልካች መኪና ለመሆኑ የማረጋገጥ ብቃት አለው፡፡ በመሆኑም ደረሰኙ ጥገና የተደረገለት መኪና የትኛው መኪና ለመሆኑ ማረጋገጥ እየቻለ የታርጋ ቁጥሩ ባለመግለጹ ብቻ ገቢን ለመፍጠር የወጣው ወጪ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ለነዳጁ



የወጣውን ወጪ በተመለከተም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ነዳጅ ለመቀዳቱ በተሰጠው ደረሰኝ ላይ የተመዘገበው የመኪናው ታርጋ ቁጥር የአመልካች መኪና ታርጋ ቁጥር ላለመሆኑ የቀረበ ክርክር ሳይኖር የባለቤቱ ስም ባለመፃፉ ብቻ ሰነዱ ወድቅ ሊደረግ የሚገባባት ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሕጉ የሚያዘው ግብር ከፋዩ የተጣለበትን ግብር የመክፈል ግዴታውን ሳይወጣ እንዳይቀር ለመቆጣጠር በመሆኑ ሰነዶቹ በበቂ ሁኔታ ወጪ መውጣቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ነገሮች ከያዙ በሰነድ አዘጋጃጀት ላይ የተለያዩ ፎርማሊቲዎች ባለመሟላታቸው ብቻ ሰነዱን ውድቅ ማድረጉ፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ውጤቱ ከግብር ሕጉ በመውጣት ግብር እንዲከፈልበት ባልተጠየቀ ገንዘብ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረግ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ሰነዶች የተለያዩ ስርዓቶች /ፎርማሊቲዎች/ ባለማሟላታቸው ብቻ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13065 በጥር 26 ቀን 1996 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.7813 በሐምሌ 16 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በግ/ይ/መ/ቁ. ወ-17 በየካቲት 8 ቀን 1992 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡